
# ሚተራሊዮን



ዓለማየሁ ዋሴ እሸቴ

Scanned with CamScanner



# ሚተራሊዮን

ዓለማየሁ ዋሴ እሸቴ

ጥር 2014 ዓ.ም.

Scanned with CamScanner

© ዓለማየሁ ዋሴ እሸቴ 2014 ዓ.ም.
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡
ALL RIGHTS RESERVED

አድራሻ
ዓለማየሁ ዋሴ እሸቴ (ዶ/ር)


E-mail:- Emegua2015@gmail.com

ባሕር ዳር

ኢትዮጵያ

**ዋና አከፋፋይ፡-**
ዝጎራ መጻሕፍት መደብር
0920187906/0920038480






# የጸሐፊው ማስታወሻ

ይህ መጽሐፍ ራሱን ችሎ የሚነበብ ወጥ ታሪክ ያለው ቢሆንም ከዚህ ቀደም ያሳተምኩትን ‹ዝጎራ› የተባለውን መጽሐፌን በቅደሚያ ማንበብ ግን አንዳንድ ጉዳዮችን የበለጠ ለመረዳት ያግዛል፡፡ በተረፈ እንደምትወዱት ተስፋ አደርጋለሁ፡፡


**መልካም ንባብ!**



# መታሰቢያነቱ

ትምህርቱን አቋርጦ ሳስተማረኝ ህልሙን ሰጥቶ ባለህልም ሳደረገኝ፣ አጎትም፣ ወንድምም፣ አባትም ሆኖ በሁሉ ነገር ላሳደገኝ ለአቶ ብርሃኔ ዋሴና ለባለቤቱ ፀሐይ ይስማው ይሁንልኝ።





# ምዕራፍ - ፩

አዲስ አበባ ከሚገኘው የእስራኤል ኢምባሲ ቪዛ ማግኘት በጣም ውስብስብ እንደሆነ ጉዞዬን ለማመቻቸት ከሰበሰብኩት መረጃ ተረዳሁ።ቀላሉ መንገድ ለፋሲካ ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም ምዕመናንን ከሚያጓጉዙ አስጎብኝ ድርጅቶች በመሄድ የቡድን ቪዛ ማግኘት ነው። ቢያንስ 10 ቀናትን በእስራኤል መቆየት ስለሚያስችል ቀላል መንገድ ሆኖ አገኘሁት። ምንም እኳን ሁለት ወራት ያክል የሚያዘገየኝ ቢሆንም አማራጭ የሌለው መልካም ዕቅድ ነበር። ከሁሉም በላይ ያስደሰተኝ ግን በዚህ ጉዞ ባለቤቴን ማካተት መቻሌ ሲሆን እርሷም እጅግ የምትደሰትበት ውብ ስጦታ እንደሆነ ስለገባኝ ነበር።

ለባለቤቴ ከአልማዝ የተሠራ የእጅ አንባር፣ በአንቱ ያጌጠ የአንገት ድሪ ገዝቼ ከምሠጣት ይልቅ ወደ ሆነ ገዳም እንሂድ ብላት እንደምትደሰት አውቃለሁ። ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም እንሂድ ስላት ደግሞ የበለጠ የሚሰማት ደስታ ጥልቅ እንደሚሆን አምናለሁ። ባለቤቴ ለገዳምና ለገዳማዊን አባቶችና እናቶች ያላት ፍቅር ሁልጊዜ ይገርመኛል። የሆነ ገዳም ከሄደች እንደወረደ በሁሉም ነገር ትደሰታለች። የምታየው ሰው ሁሉ ቅዱስ፣ ሥርዓቱ ትክክል፣ ዳቤው ንፍሮው በረከት፣ ጸበሉ ፈዋሽ ነው ብላ ታምናለች። እኔ ደግሞ የመጠራጠር አባዜ አለብኝ። አንዳንዴ በስሕተት እንኳን ገነት ብገባ መጠየቁና መጠራጠሬ የሚቀር አይመስለኝም። ‹ይሄ እኮ ይሄኔ ለስውር ዓላማ የመጣ ይሆናል፤ ያ ደግሞ ሙዳዩ ምጽዋት ገልባጭ ይሆናል፣ ሥርዓቱን የበለጠ ሳቢ ማድረግ አይችልም ነበር፣ ለምን ድብቅ ይሆናሉ የሚሉት ፈተናዎች ገና ከመግቢያው ይጀምሩኛል። በእርሷ እምነት እቀናለሁ። አንዳንዴ እሷን ለማስደሰት አብሬ አደንቃለሁ  እንጂ ውስጤ ግን የለመደውን ምዘና አይተውም። በእኔ ያለው ምሰሶ ሳይሆን በሌሎች ያለው ጉድፍ ለምን ጎልቶ እንደሚታየኝ አይገባኝም። ለነገሩ እኔን ማን ደረጃ መዳቢ አድርጎ እንደሾመኝ አላውቅም።

ሁልጊዜ እርሷ ከሙሉ ሰላሟ ጋር ከገዳም ስትመለስ የእኔ ዝብርቅርቅ እንዳለ ነው። በመዞርም፣ በመስማትም፣ በማንበብም፣ በየቦታው የቃረምኩትን እይዝና ‹እንደዚህ እኮ መደረግ ነበረበት› ስል ‹ስማ ሲሳይ! እነዚህ ሰዎች ትናንት አድርገውት ይሆናል ወይም ነገ ያደርጉት ይሆናል። እኛ እኮ ገና ዛሬ ነው የመጣን› ትላለች። በሌላ በኩል ወጣ ያለና ጉልህ ስሕተት የመሰላትን ካየች በቀጥታና በግልጽ ትናገራለች እንጂ አታጉረመርምም ወይም አታማም። ባልና ሚስት ከአንድ ባሕር ይቀዳሉ ይባላል። እኔና ባለቤቴ ከአንድ ባሕር የተቀዳን አይመስለኝም። ‹ተቀድተንም ከሆነ እርሷ በንጹሕህ ብርጭቆ ስትቀዳ





እኔ በጠማማ ጣሳ ተቀድቼ ይሆናል› እላለሁ።

ለማንኛውም በአንደኛው የጉዞ ወኪል በኩል የባለቤቴንና የእኔን ስምና ፎቶግራፍ ሁጥቼ የሚከፈለውን ከፍዬ ወደ ባሕር ዳር ተመለስኩ።

ማታ እራት ላይ ግዳይ ጥሎ እንደመጣ አባዎራ ጀነን ብዬ፡-

“የዘንድሮ ትንሣኤን የሆነ ቦታ ሂደን ነው የምናሳልፍ” አልኩ።

“ደግሞ ያንተ አንሶ እኔንም ታዞረኝ? እኔ ትንሣኤውን በቤቴ ከልጆቼና ከቤተሰቤ ጋር ነው የማሳልፍ” አለች።

“የሆነ ትልቅ ገዳም እኮ ነው” አልኩ።

“እርሱ መልካም ሐሳብ ነው” አለች እና “ለመሆኑ የት ነው?” አለች።

“አይ ሰርፕራይዝ ነው” አልኳት።

“ይህንን ከየትም የለቃቀምከውን አጉል ጉራ ተምውና ይልቁንስ እንድዘጋጅ ንገረኝ” አለች።

እንደዚህ ያለ ነገር አይመቻትም። ሰርፕራይዝ፣ በርዝ ዴይ፣ ጧት ማታ አይላቭ ዩ የሚባል ነገር አትወድም። ሁሉን ነገር በምክክርና በመተጋገዝ እንዲሆን ትፈልጋለች እንጂ።

“ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ነው” አልኳት።

“እውነትክን ነው? እስኪ ማርያምን በል” አለች ገጿ እንደ መስከረም አደይ እየፈካ።



Scanned with CamScanner

"ጨርሼ ነው የመጣሁት ይኸው የከፈልኩበት" አልኩና ደረሰኙን አውጥቼ አሳየኋት፡፡

"ገና ዛሬ ቁም ነገር ሠራህ! እንዲያው ይህን ሁሉ ሀገር ስትዞር ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምን አለማሰብህ በጣም ይገርመኝ ነበር፡፡ ቢዘገይም ደግ አደረክ ተባረክ" አለችኝና "ለእኔም ከዚህ በላይ የምትሠጠኝ ስጦታ የለም" አለች፡፡

ወደ እስራኤል ለመሄድ ያሰብኩት ለሌላ ጥብቅ ጉዳይ እንጂ ሲጀመር መካናትን ለመሳለም ወይም ባለቤቴን ለማስደሰት አስቤ አልነበርም፡፡ ከልቤ አንቅቼና አስቤ እርሷን ለማስደሰት ብዬ ሐሳቡን አለማመንጨቴን ሳስብ ያታለልኳት መሰለኝ፡፡ ቢሆንም ያም ሰበጉ ሥራ ነውና ከበጉ ሥራ ላይ ሌላ በጎ ዓላማ ቢጨምርበት አያጉሳቁለውም ብዬ ተጽናናሁ፡፡

በወርሃ ሚያዝያ በዕለተ ረቡዕ ከቀኑ በ10 ሰዓት በኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን ከቦሌ ተነሥተን ወደ ቴላቪብ አመራን፡፡ አውሮፕላኑ ምድርን ለቆ አየር ላይ እስኪሆን ድረስ ባለቤቴ ያመነች አትመስልም ነበር፡፡ አውሮፕላኑ የተፈቀደለትን ከፍታ ከያዘና አቅጣጫውን ካስተካከለ በኋላ ካፒቴኑ በተለመደው በበረራ መግለጫው አውሮፕላኑ ከአዲስ አበባ ቦሌ ተነሥቶ ወደ እስራኤል ዋና ከተማ ቴላቪብ የሚያመራ መሆኑን ሲገልፅ ባለቤቴ ደስታዋ ወሰን አጣ፡፡

"ስንቶቹ አባቶችና እናቶች በየብስና በባሕር፣ በሸንተረርና በበረሓ፣ በጥምና በረኃብ የጌታዬን የገቢረ ተኣምራት ስፍራ ለማየት ተንከራተቱ፡፡ እኔ ግን በምቹ አውሮፕላን ቦታውን ልረግጥ ነው" እያለች በምስጋና ከአየሩ ላይ ሌላ አየር ፈጥራ ትንሳፈፋለች፡፡





እኔ በተቃራኒው ‹አሁን ማንን ነው የማገኘው? ምንስ ብዬ ነው የምጠይቀው?› ከሱቅ ገዝቶ ወይም ከታወቀ ሰው ተቀብሎ እንደሚመጣ ብድግ ብዬ መምጣቴ ምን ይባላል?› እያልኩ እብሰለሰላለሁ፡፡

‹ባይሳካስ? እና ባይሳካስ? ቢያንስ ቅዱሳት መካናትን መሣለም ቀላል ነገር ነው? ብቻውን እኮ ትልቅ እድልና በረከት ነው› እያልኩ ለመጽናናት እሞክራለሁ፡፡

በዚያ ላይ ደግሞ ‹የዚች ሴት አምላክ ያመላክትሃል" ብሎ አባ መዐዛ የነገረኝ ትዝ አለኝና ‹አዎን አምላኳ ይገልጥልኝ ይሆናል› እላለሁ፡፡

አመሻሹ ላይ በመጀመሪያው የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስተር በነበሩት ሰው በተሰየመው ‹ቤን ጉርዮን አውሮፕላን ማረፊያ› አርፈን ወዲያው ወደ ቅድስቲቷ ከተማ ኢየሩሳሌም በአውቶቡስ ተጉዘን እኩለ ሌሊት ገደማ ‹ሻሉም› ከተባለው ሆቴል ገባን፡፡



Scanned with CamScanner



# ምዕራፍ - ፪

በጠዋት ተነሥቼ የክፍሉን መስኮት መጋረጃ ገልጬ አሻግሬ ሳይ ኢየሩሳሌም ጸዐዳ ልብስ የለበሰች ሙሽራ መስላ ታየችኝ። ሁሉም ሕንፃ ማለት ይቻላል ነጭ ወይ ቤዥ ቀለም የተቀባ በአረንጓዴ ዕጽዋትና አበቦች የተከበበ ጸዐዳ ነው። ‹ሙሽራው ክርስቶስን ለመቀበል የተሰናዳች ሰማያዊት ሙሽራ አምሳለ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት አልኩ›። ባለቤቴን ቀሰቀስኩና የጠዋቷ ፀሐይ ሳታልፍ ጸዐዳውን ትዕይንት አሻግራ እንድታይ ወደ መስኮቱ አስጠጋኋት።





"የጌታዬ የመከራውና የትንሣኤው ሕያው ምስክር" አለችና ዐይኗ በእምባ ተሞላ።

ወዲያው ተጣጠብንና ለባብሰን ማታ በተነጋገርነው መሠረት ወደ አስጎብኛቻችን ሂደን በአውቶብስ ተሣፈርን። የመጀመሪያው ቀን ጉብኝት ቅድስት ድንግል ማርያም ከዮሐንስ ዘንድ 14 ዓመት የተቀመጠችበት ኋላም በአረፈች ጊዜ በሐዋርያት የተገነዘችበት፣ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉበት ሥፍራ ጽርሐ ጽዮን፣ ቀጥሎ የዳዊት መቃብር፣ እንዲሁም ከሰዓት በዴር ሱልጣን የሚገኘውን የኢትዮጵያ ገዳምና ንግሥት ዕሌኒ መስቀሉን ቆፍራ ያገኘችበትን ሥፍራ ጎበኘን። በጉብኝቱ ወቅት አስጎብኝዎቹ የሚያደርጉትን ገለፃ እያደመጥኩ ከመመዝገብና የሕሊና ጸሎት ከማድረስ በተጨማሪ ድንገት የተለየ ምልክት ባገኝ ብዬ ማማተሬ አልቀረም። ምን አይነት ምልክት እንደምፈልግ ግን ምንም ፍንጭ አልነበረኝም።

ጉብኝታችን አልቆ ራት በልተን ክፍላችን ከገባን በኋላ በጥሞና ለማሠላሠል ሞከርኩ። ‹ነበ እስራኤል ውሉደ ኢትዮጵያ› ማለት ማንን ያመለክታል ብዬ ሳስብ ቤተ እስራኤላውያንን ሊሆን እንደሚችል ከግምት ወደ እርግጠኝነት ተጠጋሁ። ‹ከእነርሱ ውጭ ማን ሊሆን ይችላል?› እያልኩ ሳስብ ከዚህ በፊት ለሆነ ጉዳይ ያጠናሁት የቤተ-እስራኤላውያን ታሪክ በአዕምሮዬ አንድ በአንድ እንደፊልም ይመጣብኝ ጀመር።

እስራኤላውያን አመንዝራው ልባቸው ከቅዱሱ ኪዳን ቢሸፍት የአብርሃም አምላክ ፊቱን ቢያዞርባቸው፣ መከራ ቸነፈር ወርዶባቸው፣ ጠላቶቻቸው ገፍተዋቸው እንደ ጨው ዘር ቢሰደዱ ‹ስዱዳን ፈላሻያ› ሲባሉ ይገባል። ተመልሰውም የተስፋይቱን ምድር ቢናፍቁ እውነትነት አላቸው። ከአሜሪካ፣ ሩሲያ፣ ጀርመን፣ ፖላንድ ወደ ፓለስታይን

ቢተሙ አይገርምም፡፡ ምንም እንኳን ከክርስቶስ ልደት በኋላ የተወሰኑ ፊልሰው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ እንዳሉ ቢታመንም ከክርስቶስ ልደት በፊት ወደ ኢትዮጵያ የተጓዙት ከየነገዱ የተመረጡ እስራኤላውያን ግን መከራ ገፍቷቸው ጦር አሸንፏቸው የኃጢያት መርገምት ሆኖባቸው አልነበረም፡፡

የታላቁ ንጉሣቸውን አደራ ተቀብለው የጥበብ አድናቂዋን ንግሥት ልጅና ወራሽ ቀዳማዊ ምንሊክን ‹ሞዐ አንበሳ› ብለው አንጋሽ ቀዳሽ ሆነው ሲያከብሩ ወደ ሌላዋ የተስፋ ምድር ኢትዮጵያ የተጓዙ አይደሉምን?

የንጉሥ ሰሎሞንን ዝና ሰምታ ከጥበቡ ጥበብ፣ ከአምልኮው አምልኮ ልትቀስም ንንግሥተ አዜብ ማክዳ ጥበብን ናፈቀች፡፡ በዙሪያዋ ለነበሩ አማካሪዎቿና ሹማምንቶቿም አለች፡-

*"እኔ ጥበብን እሻለሁ፤ ልቤ ዕውቀትን ትቃትታለች፤ በጥበብ ፍቅር ተነድፌያለሁ፤ በጥበብ ገመዶችም ታስሬያለሁ፡፡ጥበብ ከብዙ ወርቅና ብር ይልቅ ትልቃለችና፡፡ ጥበብ በምድር ከተፈጠሩት ሁሉ ትበልጣለች፡፡ ጥበብን ከሰማይ በታች በምን ይመስሏታል? ከማር ትጣፍጣለች፣ ከወይን ታስደስታለች፤ ከፀሐይ ይበልጥ ታበራለች፣ ከጣፈጡ ምግቦች ይልቅ ታጠግባለች፡፡ ጥበብ ለልብ አስደሳች፣ ለዐይኖች መብራት፣ ለእግር ቅልጥፍና ለደረት ጥሩር፣ ለራስ አክሊል፣ ለአንገት የወርቅ ማርዳ፣ ለወገብ መታጠቂያ፣ ለጆሮ ማዳመጫ፣ ለልብ ብልሃት ነች፡፡ ጥበብ ለአዋቂዎች መምህራቸው፣ ለልበኞች መፅናኛና መካሪያቸው ናት፡፡ መንግሥት ያለጥበብ አትቆምም፣ ሃብትም ያለጥበብ አይጠበቅም፣ እግርም ያለ ጥበብ በቆመበት አይጸናም፣ ልሳንም ያለ ጥበብ*





*የተናገረው አይወደድም! ጥበብ ልዕልት ናት፤ እንደ እናት አወዳታለሁ፤ እርሷም ታቅፈኛለች፡፡ እኔ ጥበብን ፍለጋ እከታተላለሁ፤ጥበብን ዱካ ልንከተል ሸኮናችን በበሮቿ ደረጃ ሊቸነከር ይገባል፡፡ እንፈልጋታለን፣ እናገኛታለን፣ እንወዳታለን!"*

የመንገዱን ርዝመትና አስቸጋሪነት በአግባቡ የተረዳችው ቢሆንም ለንግሥት ማክዳ ከድካም በላይ ጥበብ በለጠችባት፡፡

አማካሪዎቿም:

*"እመቤታችን ሆይ! ጥበብ እኮ ካንቺም አልታጣም! ጥበብን አጥብቀሽ የምትወጂ በጥበብሽ ነው፡፡ ጥበብ ትጠራሻለችና፡፡እኛ ግን አንቺ ብትሄጂ ከአንቺ ጋር እንሄዳለን፡፡ ሞትም ቢሆን ሞታችን ካንቺ ጋር ይሆናል፡፡ ሕይወትም ቢሆን ሕይወታችን ካንቺ ጋር ይሆናል" አሏት፡፡*

ንግሥተ አዜብ ማክዳ የንግሥትነት ክብርዋ ሳይከልላት፣ የሴ ጉልበቷ ሳያግዳት፣ ጥበብን ፍለጋ ተራራ ወጥታ፣ ቁልቁለት ወ ጋራ ሸንተረር አልፋ፣ ባሕር በረኃ አቋርጣ ተሻግራ ወደ ኢየሩ ረጅሙን ጉዞ ተጓዘች፡፡ 797 ግመል፣ ቁጥሩ በማይታወቅ በቅሎ አጋሰሶች፣ ብዙ ወርቅ፣ ብር፣ የዝሆን ጥርስ፣ ሽቱ፣ የከበሩ ድ ለስጦታ ተጭኖ ትልቅ ቅፍለት ይዘው ወደ ቀይ ባሕር ዳርቻ በብዙ መርከቦች ተሻግራ የዐረቢያን በረኃ አቋርጣ ኢየሩሳሌም

የጠንካራዋ ሴት ልጆች ነን፡፡ የዚች ባለ ብሩህ አእምሮ ንግሥ ከጥበብ ማዶ ሆነን ከዓለም ስልጣኔ ጭራ ሁነን መገኘታ

ተነሥታ ብታይ ምን ትለን ይሆን? ጥበብን ፍለጋ ሳይሆን ሳንቲም ፍለጋ በአለም ሁሉ እንደ ጨው ዘር የምንበተን ምስኪን ሕዝቦች መሆናችንን ብታይ እንዴት ታዝንብን ይሆን?

የንግሥት ማክዳ ልጆች ነን፤ የጥበበ ፈላጊዋ የጥበብ አሳሿ። መቼ ይሆን ወደ ጥንት ክብራችን እንመለስ ብለን ሆ ብለን የምንነሣው፤ የጦራልና የደግነት፣ የአብሮነትና የታታሪነት፣ የጀግንነትና የነጻነት ልዕልና፣ የአልፋ ኦሜጋ ጥበብ ባለቤት ለመሆን በቁጭት የምንነሣው?!

ንግሥተ አዜብ ማክዳ ኢየሩሳሌም እንደደረሰች ንጉሥ ሰሎሞን በክብር ተቀበላት። ጥበቡን ሁሉ አካፈላት። ያቀረበችለትን እንቆቅልሾች ሁሉ ፈትቶ ጥበበኛነቱን አረጋገጠላት። የአባቶቹን የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብን አምላክ ሥርዓተ አምልኮና የታቦተ ጽዮንን ቃል ኪዳን ሁሉ አስረዳት። የቤተ መንግሥቱን ባለሟሎች ስንዱነት ሁሉ አሳያት። ለጉብኝቷ ማስታዎሻ፣ ለሀገሯ ስም መጠሪያ ይሆን ዘንድ በኢየሩሳሌምና ባቅራቢዋ ርስት ጉልት ሰጣት። ለውበቷ፣ ለንጽሕናዋ፣ ለብሩህ አእምሮዋ አድናቆት ልብ አልቀረለትም ነበርና በፍቅሯ ወደቀ። ከማሕፀኗ ዘርን ያስቀር ዘንድ ተጋ። እናም ሆነ! ለእርሱም ለእርሷም በኩር የሚሆነውን ልጁን ከሀገሯ ተመልሳ ቀዳማዊ ምኒልክን (እብነ ሀኪም) ወለደች።

ከጉዞዋ መልስም የተመኘችውን ጥበብ፣ የሰሎሞንን ማስተዋል በጥልቅ እንደቀሰመች ተናገረች።

> *"ወደ ጥበብ በር ዘልቄ ገባሁ። ወደ ጥልቁ መረዳት ሰመጥሁ።ወደ ዕውቀት ጮራ አቀናሁ በእኔም ላይ ጥበብ ብርሃኗን አበራች። ጥበብን ጋሻ አደረኳት በራስ መተማመኔን ጠበቅሁ። ደግሞም ለእኔ ብቻ አይደለም ጥበብን ፍለጋ*





> *ለተጓዙ ሁሉ፣ ለሀገሬ ወንዶችና ሴቶች ሁሉ፤ ለሀገሬ ኢትዮጵያ፣ ለጉረቤቶቿ ሁሉ እንጅ።"*

*ደግሞም አለች፡*

> "ከእንግዲህ ወገኖቼ! እውነትን ውደዱ ሐሰትን ጥሉ። አዎን! ሸፍጥንና ጭቆናን በእናንተ ዘንድ አስወግዱ እግዚአብሔር በመካከላችሁ ነውና። ጸጋውና ክብሩ በመካከላችሁ ነውና እናንተም በአንድ አምላክ ሥር ቤተሰብ ሁናችኋልና!"

ቀዳማዊ ምኒልክ በጥበብና በሞገስ አደገ። እናቱ ንግሥት ማክዳ አባቱን እንዲጎበኝ ወደ ኢየሩሳሌም ላከችው። በጉብኝቱም በአባቱ በንጉሥ ሰሎሞን ፊት ሞገስን አገኘ። አባቱ በእጅጉ ወደደው። በመንበሩ ሊያስቀምጠው በመንግሥቱ ሊሰይመው በልቡ ፈቀደ። ይህንንም ነገረው፣ አለውም፡-

> "እግዚአብሔር ከወደደ እስከ አባቱ ዕድሜ ድረስ ያድርሰኝ። ወደ አባቴና ወደ አባቶቼ ከተወሰድኩ አንተ በዙፋኔ ላይ ትቀመጣለህ። በእኔ ፋንታም ትነግሣለህ። የእስራኤል ሊቃውንት ፈጽሞ ይወዱሃል። እኔን ደካማውን በአባቶቼ ዙፋን ታየኛለህ። ከእኔም በኋላ አንተ እንደ እኔ ትሆናለህ።"

አባቱ ጥበበኛው ንጉሥ ሰሎሞን በእስራኤል ሀገር ከእርሱ ዘንድ ቢቀር መንግሥትን እንደሚያወርሰው፣ ዙፋኑን እንደሚሰጠው ነገረው። የከበረችውን ታቦተ ጽዮን መማፀኛው ትሆን ዘንድ ባቅራቢዋ እንደሚሆን፣ ጥበቡንና ሀብቱን ሁሉ እንደሚሰጠው ቃል ገባለት። እንደ ወጣትነቱም ውብ ልዕልት ወዕቁባት እንደሚድርለት ነግሮ አባበለው።

ቀዳማዊ ምኒልክ ግን ከዚህ ሁሉ ሥልጣንና ተድላ ይልቅ እናቱና የእናቱ ሀገር ኢትዮጵያ በለጡበት፡፡

እናም፡-

"ጌታዬና አባቴ ሆይ! እናቴንና ሀገሬን እተው ዘንድ አይቻለኝም፡፡ እናቴ በቶሎ ወደ እሷ እንድመለስ እንጂ እዚህ እንዳልቀር በጡቶቿ አምላኛለችና! የእስራኤል አምላክ ታቦትም ባለሁበት ትባርከኝ፡፡ ፊትህን ላይ፣ ቃልህን ልሰማ፣ በረከትህንም ልቀበል፣ ወደ እናቴም በደኅና እሄድ ዘንድ ሽቻለሁና ጸሎትህ በሄድኩበት ትከተለኝ" አለው ቁርጥ አድርጎ፡፡

ሃይማኖትህን ያለ ሀገር ሆነህ የትም ልታከብረው ትችል ይሆናል፤ ሀገር ስታጣ ግን ሁሉን ታጣለህ፡፡ ኦርቶዶክስን ግብፅ፣ እስልምናን መካ መዲና፣ ካቶሊክን ቫቲካን፣ ፕሮቴስታንትን ጀርመን ታገኝ ይሆናል፡፡ ኢትዮጵያ ግን የትም የለችም፡፡ ሃይማኖታችን የምንወደው ኢትዮጵያን ቀድሶ ስለሰጠን ነው፤ ኢትዮጵያን የምንወዳት ሃይማኖታችንን እጅግ መንፈሳዊና ከፈጣሪ ጋር የሚያገናኝን ንጹሕ መንገድ ስላደረገችልን ነው፡፡

‹እኛም የንግሥት ማክዳ ልጆች ነን፤ የጥበብ ፈላጊዋ፣ የጥበብ አሳሿ! አዎን የቀዳማዊ ምኒልክ ልጆች ነን፤ እናት ሀገራችንን ፍጹም ወዳጅ፣ ሥልጣን ምቾት የማይለውጠን ታማኝ!› ለማለት መቼ ይሆን የምንደፍረው!

የልጁን ቁርጥ ቃል የሰማው ንጉሥ ሰሎሞን ልቡ ታወከ፡፡ ልቡ የወደደው የበኩር ልጁ በእርሱ ዘንድ እንደማይቆይ ተረዳ፡፡ እናም





መንገዱን ሊያሰናክልበት አልፈቀደም፡፡ ሹማምንቱንና ሽማግሌዎቹን በየነገዳቸው ጠርቶ፡

"የአብራኬ ክፋይ የበኩር ልጄ ተመልሶ ወደ እናቱና ሀገሩ ሊሄድ ነው፡፡ እናም ብቻውን ይሄድ ዘንድ አይገባምና የእስራኤል በኩር ሁሉ አብሮት ይሂድ!" አለ፡፡

‹ክብረ ነገሥት› የተባለው ጥንታዊ መጽሐፍ እንደሚተርክልን በዚህ ውሳኔ መሠረት ቀዳማዊ ምኒሊክ በብዙ እስራኤላውያን በኩራት ታጅቦ፣ ታቦተ ጽዮንን በምሥጢር ይዘው ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ፡፡

ቤተ እስራኤላውያን በዚህ መልክ ወደ ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ መጥተው ክብረ ነገሥትን ጽፈው፣ ሥርዓተ ወሥርወ መንግሥትን መሥርተው፣ ታሪክ ሠርተው፣ ወግ ባህል ሰንደው፣ ብሉይ ከሐዲስ አስተዛዝለው፣ ወልደው ተዋልደው የኖሩ ናቸው፡፡ አፈር ፈጭተው፣ ጭቃ አቡክተው ሸክላ የሠሩ፤ እንጨት ቆርጠው፣ አለዝበው ሞፈር ቀንበር ያበጁ፤ ቆዳ ፍቀው፣ አልፍተው ጠፍር ምናር ሠርተው ሞፈር ከቀንበር ያዋደዱ፤ አቀማዳ ስልቻ ከመጫኛ ጋር ሰርተው ነጋድራሶችን ሩቅ ያስጓዙ፤ አፈር እንጥረው፣ ብረት አቅልጠው ማረሻ ወገል ሠርተው ከእርሻ እስከ ጉርሻ ያስተሳሰሩ፤ ጦር ጉራዴ አበጅተው አርበኞችን ያስታጠቁ፤ ጠይባን ተብለው የተጠበቡ እኛን የሆኑ ናቸው፡፡ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ የበኩላቸውን ያዋጡ አገር ገንቢዎች ነበሩ፡፡

ዘመን የኋሊት ተጉዞ ድህነት ቢንሰራፋ፣ ኑሯቸው ቢጎሳቆል፣ የደከሙለት ሥረወ-መንግሥት ቢቋረጥ፣ ወግ ባህሉ ሁሉ የጨረባ ተዝካር ቢሆን ወደ ኋላ ተመልሰው ጥንተ ሀገራቸውን ከነዓንን ቢናፍቁ ፍርድ የለባቸውም፡፡



Scanned with CamScanner

ይሁን እንጅ ምትሐታዊቷ ኢትዮጵያ ሥጋቸውን ባታደልብም፣ በዚላ በአፓርትመንት ባታኖራቸውም ወግ ባህል፣ ሞራልና ፍቅር፣ መንፈሳዊ ጸጋ አልነፈገቻቸውምና እንደ ዋዛ ጥለዋት ቢሄዱም የምትረሳ አይደለችም። ኑሮ ሲደላ ደረት ሲቀላ በትዝታ የምትንጠው ደጋማዋ ኢትዮጵያ ከቋራ እስከ በለሳ፣ ከደንቢያ እስከ አድዋ፣ ከዋግ እስከ ወልቃይት ደርባባው መልከዓ ምድር መናፈቁ ግድ ነው።

'ትመጣለህ ብዬ ዙሬ ዙሬ ባይ

ወይ ኩራት ወይ ጥጋብ ጎንደር ቀረህ ወይ'

ይላሉ ናፍቆታቸውን በስንኝ ሲገልፁ።

ቤተ እስራኤላውያን አሁንም ድረስ እስራኤል ዘሥጋን ከእስራኤል ዘነፍስ ኢትዮጵያን በማይበጠስ እትብት ያስተሳሰሩ የሁለቱ ባለቃል ኪዳን ሀገሮች ምሥጢራዊ ድልድይ ናቸው።

ዛሬ ምሥጢራዊ ነው የተባለውና ፈልጌ እንዳመጣው የታዘዝኩት ‹ቅርስ› ከእነርሱ ዘንድ ይገኛል ቢባል እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ጎርፍ ፈሳሽ ድንገቴ ሐሳብ ሊሆን አይችልም። በርግጥም ቤተ እስራኤላውያን በኢትዮጵያ በኖሩበት ዘመን ለብዙ ምሥጢር ቅርብ ነበሩና። ወደ ኢትዮጵያ የከበረችውንና ምሥጢራዊቷን ታቦተ ጽዮንን ይዘው መጥተው እንዳከበሩን ሁሉ ይህንን ክቡር ቅርስ ባላደራ ሆነው ጠብቀውትም ይሆናል። ዋናው ጉዳይ ቤተ እስራኤላውያን ሲባሉ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ናቸው። ‹ለዚህ ምሥጢር የቀረበው ማን ነው?› የሚለውን ፈልጎ ማግኘቱ ሲሆን ቢታወቅም ‹ፈቃደኝነቱ ይኖራል ወይ?› የሚለው ሌላው ፈተና ነው።





እንዲሁ በዚህ የሺ ዘመን ትርክትና የመጣሁበትን ጉዳይ ለማስተሳሰርና ውል ለመፈለግ ራሴን ሳዳክርና ሳንገላታ አድሬ እንቅልፍ ባይኔ ሳይዞር ነጋ።

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)
የቴሌግራም ቻናል
ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)



# ምዕራፍ - ፲

የሁለተኛው ቀን ጉብኝታችን ዐርብ የስቅለት ዕለተ ስለነበር ከነገረ መስቀሉ ጋር የተያያዘ ነበር። በጠዋት በቤተ ሳይዳ መፃጉዕ 38 ዓመት የተኛበትን ሥፍራ አይተን የመስቀል ጉዞ ምዕራፎችን ለመጉብኘት ወደ ጲላጦስ የፍርድ አደባባይ አመራን።

ክርስቶስ በመከራ ታስሮ ካደረበትና የግፍ ፍርድ ከተቀበለበት ሊጦስጥራ ጀምሮ እስከ ተቀበረበት ጎልጎታ ድረስ 14 ምዕራፎች ተለይተው ስፍራዎቹ ጉልህ ምልክት ተደርጎባቸዋል። በእያንዳንዱ ምዕራፍ





የተከናወኑ ድርጊቶችና ታሪኮች ተመዝግበዋል። አንዳንዶቹ ላይም ቤተ መቅደስ ተገንብቶባቸዋል። ምዕመናን መስቀለ-ክርስቶስን ተሸክመው በጥልቅ ስሜት እየዘመሩ ክርስቶስ መስቀል ተሸክሞ የተጓዘበትን መስመር ተከትለው ይጓዛሉ። በየምዕራፉ ቆም ተብሎ በእያንዳንዱ ምዕራፍ ምን እንደተደረገ ይተረካል። እግኝ በታላቅ መንፈሳዊ ስሜት እንባውን እያዘራ፣ የክርስቶስን ውለታ እየቆጠረ፣ ንስሐውን እያወረደ ወደፊት ይጓዛል።

በዘመን አቆጣጠራቸው በዚያው ዕለት ስቅለትን የሚያከብሩት የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናትና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን በዕለቱ መስቀል በመሸከም ክርስቶስ በተጓዘበት መንገድ እየተጓዙ በየምዕራፉ የደረሰበትን መከራ እያሳቡ በፍፁም መንፈሳዊ ሥነ-ስርዓት የሚከበርበት ነው። የእኛም የዕለተ ዐርብ መርሐ ግብር የክርስቶስን የመስቀል ጉዞ መዘከር ነበር።

የኢየሩሳሌም ከተማ አስተዳዳሪዎች በዕለቱ ስቅለትን ለሚያከብሩት ለሁሉም የምሥራቅ የክርስትና ቤተ እምነቶች ማለትም ግሪኮች፣ ሩሲያዎች፣ አርመኖች፣ ግብጾች እና ኢትዮጵያውያን የሰዓት ድልድል አድርገዋል። በየዓመቱ መርሐ ግብር ሲወጣ የኢትዮጵያ ምዕመናን ሁልጊዜም ቅድሚያ ይሠጣቸዋል። ቀጥሎ የሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ምዕመናን ይከተላሉ። ቅድሚያውን ማግኘታችን በአሁኑ ሳይሆን በቀደመው ገናና ታሪካችን ይመስላል።

እኔና ባለቤቴም ከሌሎች ኢትዮጵያውን ምዕመናን ጋር ተደባልቀን የመጀመሪያውን ምዕራፍ የግፍ ፍርድ ከተሠጠበት የጲላጦስ አደባባይ ጀመርን። ሁለተኛው ምዕራፍ ሲገረፍና ሲዘበትበት ካደረ በኋላ የሚሰቀልበትን መስቀል የተሸከመበት ስፍራ ነው።

ሕግ የሮማ ዜግነት ያለው በስቅላት አይቀጣም ነበር። በሮማውያን ሕግ የሮማ ዜግነት ያለው በስቅላት አይቀጣም ነበር። ሮማውያን በራሳቸው ዜጋ የማይፈርዱትን ቅጣት በንጹህ ክርስቶስ ላይ በየኑ። አይሁድም ቢሆኑ ተደራራቢ ቅጣት የማይፈቅደውን ሕጋቸውን ተላለፉ። በአይሁድም ሆነ በሮማውያን የዚያ ዘመን ሕግ ሰው ወንጀለኛ ተብሎ ከተበየነበትና የሚሰቀል ከሆነ አይገረፍም፤ ክርስቶስ በሐሰት ተከሰ ከተገረፈ ደግሞ አይሰቀልም ነበር። ክርስቶስ በሐሰት ተከሰ ያላግባብ ስቅላት የተፈረደበት ሳያንስ በሕጎቻቸው የተጻፈውን ከላይ የተጠቀሰውን ድርብርብ ፍርድ የሚከለክለውን ሕጋቸውን ጥሰው እንዲገረፍ ማዘዛቸው በሕግም በሞራልም እጅግ ስህተት እንደነበር ግልፅ ነው። ተደራራቢ ጥፋትና በደል የፈጸመውን የሰው ልጅ ለመታደግ ይህን ተደራራቢ ቅጣት ንጹሑ ክርስቶስ መቀበሉን እያሰቡ መንዝ ልብ ይነካል።

የስቅላት ሞት ቅጣት የሚፈጸመው እጅግ ጨካኝና ከባድ ወንጀሎች ባሉበት ሰው ላይ ብቻ ነበር። ምክንያቱም ከሞት በፊት በፍርደኛው ላይ ከፍተኛ ስቃይ ስለሚያስከትል፣ ራቁቱን ሲሰቀል ከፍ ያለ ውርደት፣ በመጨረሻም ሞት ያለው በመሆኑ ነው። የመስቀል ቅጣት በጥቅሉ ስቃይን፣ ውርደትንና ሞትን በአንድ ላይ የያዘ ቅጣት ነበር።

አይሁድ ግርፋትን በወንጀለኞች ላይ ሲፈርዱ ከፍተኛው 40 ጊዜ ብቻ ነበር። የግርፋቱ ሰንበር በፍርደኛው ላይ ቢበዛ 40 ላይ ብቻ ያርፍ ነበር። በ41ኛው ግርፋት ፍርደኛው ቢሞት ወንጀል እንደተፈፀመበትና ግድያ እንደተካሄደበት ተቆጥሮ ፍርድ አስፈፃሚዎችን ያስጠይቅ ነበር። በዚህ የተነሣ አይሁድ ከ39 ጊዜ በላይ አይገርፉም ነበር። ክርስቶስ ላይ የሆነው ግን እጅግ የከፋ ነበር። መግረፊያው ባለ ብዙ መንታ በመሆኑ በአንድ ግርፋት በርካታ ሰንበሮች ገላው ላይ ያርፉ ነበር። እናም ከአይሁድ ሕግ ውጭ ለቁጥር የሚያታክት ሰንበር ገላው ላይ አረፈ። ሥጋው ተከታትፎ አጥንቱ ታዬ። ይህ ሁሉ ሲሆን





አልታገለም፣ አላንገራገረም፣ አልተከራከረም፤ በፈቃዱ ራሱን ለዚህ መከራ አሳልፎ ሰጠ እንጂ። እናም ክብር በትሕትና፣ ደስታ በሐዘን፣ ሕይወት በሞት፣ ድል በመሸነፍ እንደሚገኝ አስተማረን። በተለምዶ ድል ትርፍ፣ መሸነፍ ጉዳት ይኖረዋል። የክርስቶስ መንገድ ግን በመሸነፍ ማትረፍ ነበር።

ሦስተኛው ምዕራፍ ክርስቶስ መከራው ሆኖበት መስቀል ሸክሙ ከብዶት ለመጀመሪያ ጊዜ የወደቀበት ስፍራ ነው። ቀጥተኛው መንገድ ወደ ግራ እንደታጠፈ የሚገኘው አራተኛው ምዕራፍ ነው።

ይህ ስፍራ ከእናቱ ከድንግል ማርያም ጋር ፊት ለፊት የተገናኘበት አሳዛኝ ትዕይንት ነበር። ለማስተማር ከናዝሬት ገሊላ እንደመጣ በዚያው የፋሲካ በዓልን ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም መውጣቱን ሰምታ ልታየው ስትመጣ በግርፋት ሥጋው ተተልትሎ፣ አጥንቱ ገጦ፣ ልብሱ ተቀዳዶ፣ አካሉ በላብና በደም ተነክሮ፣ ከባድ የእንጨት መስቀል ተሸክሞ፣ ወታደሮች እየገፈታተሩ ሲያንገላቱት ፊት ለፊት የተገናኙበትና ያየችበት ስፍራ ነበር። ክስተቱን በምናብ ለሚስለው ሰው እጅግ ልብ ይነካል። ንጹሑና አንድያ ልጇ ያለበደሉና ጥፋቱ እጅግ ተጎሳቁሎ ከዚያ በላይ ከባድ የእንጨት መስቀል ተሸክሞ ጨካኝ ወታደሮች እየገፈተሩት ስታይ የልቧ ስብራት ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል ማሰብ በራሱ ልብ ይሰብራል።

ባለቤቱ በአስጎብኝዎች የሚነገረውን ይህንን አሳዛኝ ታሪክ እየሰማች በእንባ እየታጠበች ከጎኔ ትራመዳለች። እኔም ብዘመድ ቁስ እየፈታ ያለቅሳል ሆኖብኝ፣ በአንድ በኩል ልቤ በሐዘን እየተወጋ በሌላ በኩል ደግሞ አዕምሮዬ ምልክት እየፈለገ ይናውዛል።

አምስተኛው ምዕራፍ መንገዱ እንደገና ወደ ቀኝ ታጥፎ ዳገት የሚጀምርበት ማዕዘናዊ ስፍራ ነው። ክርስቶስ ከመከራው ብዛት የተነሳ መስቀሉን ተሸክሞ ወደፊት መጓዝ አቅቶት ለሁለተኛ ጊዜ የወደቀበት ሥፍራ ነው። ወታደሮቹ በአቅራቢያው ያገኙትን ‹ስምዖን› የሚባል እንግዳ የሆነ የቀሬና ሰው ጠርተው መስቀሉን ለትንሽ ጊዜም ቢሆን ተሸክሞ እንዲያግዘው ያደረጉበት ስፍራ ነው። ቀሬናዊው ስምዖንም የክርስቶስን መስቀል በመሸከም ያገዘ በታሪክ ብቸኛ ሰው ነበር። ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ሸሽተው ስለነበር ሊያግዘው የሞከረ ሰው አልነበረም። የጥንቷ ቄሬና በአሁኑ ዘመን በሊቢያ ውስጥ የምትገኝ የጥንት አፍሪካዊ ስፈራ ናት። ይህ የታሪክ ክስተት በፓን አፍሪካ ምጡቅ ምሁራን ዘንድ ትልቅ ዋጋ የሚሠጠው ነው። በተለይ በፀረ ኮሎኒያሊዝም ትግል ውስጥ የአውሮፓ ሚሲዮናውያን የአፍሪካ ሕዝብን ወንጌል እንሰብካችሁ፣ ክርስትናን እናስተምራችሁ በሚል ሽፋን የሚያደርጉትን ድብቅ የቅኝ ግዛት ተልዕኮ ሲሞግቱ፦

> "ለመሆኑ እኛ አፍሪካውያን መስቀሉን ተሸክመን ከክርስቶስ ጐን ስንቆም እናንተ የት ነበራችሁ? እናንተ እኮ ስቅለቱን ፈርማችሁ ያስፈፀማችሁ ግፈኞች ናችሁ። እናንተ ለአፍሪካ ክርስትናን ልታስተምሩ የሞራል ታሪክ የላችሁም" ይላሉ።

ከአምስተኛው ምዕራፍ ጀምሮ እስከ አሥረኛው ድረስ ዳገቱ እየጨመረ የሚሄድ አቀበት ነው።

ስድስተኛው ምዕራፍ ኢየሱስ ክርስቶስ ከፊቱ የሚወርደውን ደም የተቀላቀለ ላብ ተመልክታ አንገቷ ላይ የነበረውን ነጭ ሻሽ ፊቱን እንዲጠርግበት አንዲት ደግ ሴት የሰጠችበት ስፍራ ነው። በመስቀል ጉዞ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ እገዛ ለማድረግ ጥረት ያደረገች ብቸኛዋ ሴት ናት። ክርስቶስም በዚያ የጭንቅ ሰዓት ያደረገችውን በጎ ተግባሯን





አስቦ በሰጠችው ሻሽ ፊቱን ጠርጎ መልሶ ሰጣት። ሴቲቱም ሻሹን ተቀብላ ስታይ መለኮታዊ በሆነ ጥበቡ ብርሃናዊ መልኩ ሻሹ ላይ እንደ ፎቶግራፍ ሆኖ ተስሎ አገኘችው። በላቲኖች ዘንድ ይህ ምስል ‹ቬሮኒካ› በመባል ይታወቃል። አንዳንድ ታሪክ አጥኚዎችም ሻሹን የሰጠቻውንና የተቀበለችውንና ደግ ሴት ‹ቅድስት ቬሮኒካ› ብለው ይጠቅሷታል። በሌላ በኩል በአንዳንድ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ዘንድ የህች ደግ ሴት የጲላጦስ ሚስት እንደነበረችና ስሟም ‹አብሮቅላ› እንደሆነ ይነገራል። ለማኘኛውም ይህች ሴት በታላቅ ሐሤትና ደስታ ብርሃናዊ መልኩ የታተመበትን ያንን ሻሽ ይዛ ወደቤቷ በመሄድ ዘመኗን በጸሎትና በምስጋና እንዳሳለፈች ይነገራል።

ሰባተኛው ምዕራፍ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመከራውና ከድካሙ የተነሳ ለሦስተኛ ጊዜ የወደቀበት ስፍራ ነው። ይህ ሲታሰብ ሕሊናም ልቦናም ከፊቃድ ውጪ መሬት ላይ ይወድቃሉ።

ስምንተኛው ምዕራፍ የኢየሩሳሌም እናቶችና ሴቶች መከራውንና እንግልቱን አይተው ልባቸው ስለተነካ ‹ዋይ ዋይ› እያሉ ሲያለቅሱለት አይቶ፦

> "እናንተ የኢየሩሳሌም ሴቶች ሆይ ለእኔ አታልቅሱ! ይልቅስ ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ አልቅሱ! በእርጥቡ ላይ እንዲህ ከጨከኑ በደረቀው ላይ እንዴት ይበረቱ ይሆን?" ያለበት ስፍራ ነው።

የክርስቶስ ትንቢት አይቀርምና ከአርባ ዓመታት በኋላ አይሁዶች በጠላቶቻቸው ተመትተው፣ ከተማቸው ፈርሳ እነርሱም በእንባና በዋይታ በዓለም ሁሉ እንደ ጨው ዘር ተበተኑ። የኋላ ኋላ ትንቢቱ ለእኛ መድረሱ አይቀርምና ዛሬ ሁላችን ስለ በደላችን፣ ስለ ግል

ኃጢአ‹ታችን፣ ስለ ኑሮአችን እሱን እያሰብን በዚህ ስፍራ እናለቅሳለን። ይህንን ማሰብ በራሱ የእምባ ጎርፍ እንዲፈስ ያደርጋል።

የሰው መዓት ጐርፍ ሆኖ በልዩ ትንግርት ሽቅብ ወደ ቀራንዮ ይፈሳ። ከሚጎርፈው ሰው መኻል አንዲት ወጣት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ፡

'መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ

ይገርፉት ነበር ሁሉም በየተራ' ስትል ሁሉም እጅግ ጥልቅ በሆነ ስሜት አብሯት መዘመር ጀመረ።

እኔና ባለቤቴ እጅ ለእጅ እንደተያያዝን ከኋላችን የሰው ጎርፍ ማዕበል እየገፋን ከወጣቷ ዘማሪ አቅራቢያ አደረሰን። ወጣቷ ግጥሙ የጠፋት ይመስል አንዱን ስንኝ ስትደጋግም እኔና ባለቤቴ ተጠቃቀስንና የሚቀጥለውን ስንኝ ጮክ ብለን መዘመር ጀመርን፡-

'በአምላክነቱ ሳይፈርድባቸው

እንዲህ ሲል ጸለዩ አባት ማራቸው'

ፈገግ ብላ ጎንበስ አለችና በአንገቷ የምስጋና ምልክት አሳየችን።

'ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ

እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ'

ብላ ትዝ ስላላት ቀጠለች። ስትዘምር አንድ እጇን ወደ ላይ ዘርግታ እያወዛወዘች ነበር። የጣቶቿ አንጓ ቆሳስለዋል። ‹ነገረ መስቀሉን እያሰበች የምትሰግድበት መሆን አለበት› አልኩ በልቤ።





ዘጠነኛው ምዕራፍ እንዲሁ መስቀሉን ተሸክሞ የወደቀበት ነው። ከዚህ በኋላ መንገዱ እየጠበበ ወደ ግራ ታጥፎ ይሄዳል። ወደ አሥረኛው ምዕራፍ ስንጠጋ መንገዱ በጣም እየጠበበ ይሄድና ዳገቱ አልቆ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይዞታ ወደሆነው ዴርሱልጣን ባለው የመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ያደርሳል። ይህ ምዕራፍ ልብሱን ቀደው ዕጣ ተጣጥለው የተካፈሉበት ቦታ ነው። በመድኃኔዓለም ቤተ ክርስትያን በስተቀኝ ባለች ቀጭን መንገድ ለማለፍ ምዕመኑ የበለጠ ይጨናነቃል።

ከወጣቷ ጋር የበለጠ የመቀራረብ ዕድል ፈጠረልንና ባለቤቴ፡-

"ስለ ዝማሬው ቃለ ሕይወት ያሰማልን" አለቻት።

"አሜን! እናንተም የረሳሁትን ግጥም ስላስታወሳችሁኝ እግዚአብሔር ይባርካችሁ" አለች። ንግግሯ ፍጹም የታረመ ርጋታ የተሞላበት የበሰለች ክርስቲያን ለመሆኗ ምስክር ነበር።

በዚሁ እንደተቀራረብን ከፊትና ከኋላ ሁነን ከምዕራፍ 11 እስከ 14 ያለውን በአርምሞ ጸሎት እያደረግን በልዩ ስሜት ተሣለምን። ይኸውም ተሸክሞት ከመጣው መስቀል ላይ በብረት የተቸነከረበት ስፍራ፣ የተሠቀለበት ማዕከላዊ ምድር ቀራንዮ፣ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ከመስቀል አውርደው ቅዱስ ሥጋውን የገነዙበት ስፍራና በመጨረሻም ትንሣኤው እሙን ይሆን ዘንድ በአዲስ ጎቱም መቃብር ሥጋውን ያሳረፉበት ጎልጎታ ነው።

ዕድሜ ዘመኑን በስሙ አምኖ ለተጠመቀና የሞቱንና የትንሣኤውን ነገር ሲሰማ ለኖረ ክርስቲያን በእውን ሥፍራዎቹን ማየት፣ መንካትና መሳለም የሚፈጥረው ስሜትና የሚያገኑናፅፊው ጸጋ እንዲህ

አልነበረም። ይህን ሁሉ ታሪካዊና መንፈሳዊ ሥነ በጽሁፍ የሚገለፅ አልነበረም። ይህን ሁሉ ታሪካዊና መንፈሳዊ ሥርዓት ጨርሰን ከትልቁ ሕንፃ ወጥተን ገላጣው አደባባይ ስንደርስ ከፊታችን የነበረችው ዘማሪዋ ወጣት ቆም ብላ እየጠበቀችን አገኘናት። ተከተልናትና ከአደባባዩ ወደ አንዱ ደረጃ ሄደን ቁጭ አልን።

" ከኢትዮጵያ ነው የመጣችሁት? " አለችን።

" አዎን አንቺስ? " አለች ባለቤቴ

" እንኳን ለዚህ አበቃችሁ " አለች።

" አሜን እግዚአብሔር ቸር ነው " አልኩና ባለቤቴ የጠየቀችውን ደገምኩት።

" እኔ እንኳ የምኖረው እዚሁ ኢየሩሳሌም ነው " አለች

"ውይ ታድለሽ ፲ጊት ማታ እዚህ ትመጫለሽ" አለች ባለቤቴ።

"እውነት ነው እነዚህን ስፍራዎች ጧት ማታ መሳለም አይጠገብም። ቢሆንም ለኑሮ ግን ማን እንደ ሀገሬ ኢትዮጵያ " አለች።

" ታዲያ እንዴት ከዚህ መኖር መረጥሽ? " አልኩኝ ውስጤ የሆነ ነገር እያቃጨለ ነበር።

" ለአያቴ ስል ነው የምኖረው " አለች።

" ምነው አያትሽ የዚህ አገር ዜጋ ናቸው እንዴ? " አልኩኝ።

" ኧረ አይደለችም፤ ብቻ ታሪኩ ረጅም ነው " አለች።

የተለመደው ሁሉን የማወቅና የመመርመር በሽታዬ ተቀሰቀሰና፦

" ለምን አትነግሪንም? " አልኳት።





ባለቤቴ ጣልቃ ገብታ "እንዴ! ስትዘምር እኮ ነው የዋለች፤ ይደክማታል እኮ! " አለች።

" ኧረ ግዴለም " አለችና "እ...ወንዱ አያቱ በጃንሆይ ዘመን ትልቅ ባለሥልጣን ነበሩ። ደርግ ሲመጣ በግፍ ከገደላቸው መካከል ናቸው። እርሳቸው መገደላቸው ብቻ ሳይሆን ሀብት ንብረታቸው ተወርሶ ሴት አያቴ የኔን እባት ጨምሮ ልጆቿን ለማሳደግ ብዙ መከራ ደረሰባት። ብቻ በፈጣሪ እርዳታ ልጆቿን አሳድጋ ለቁም ነገር አደረሰች። ሁሉም በታ ሲይዙላት ቀሪ ዘመኔን በቅድስት አገር ኢየሩሳሌም ማሳለፍ አለብኝ ብላ ወደዚህ ስትመጣ አብሬያት እንድመጣ ተደረገ። እዚሁ ተማርኩ። አሁን የራሴ የሆነ የንግድ ድርጅት በኢየሩሳሌም ከፍቼ እስከዚያው እየሠራሁ ነው" አለች።

" እስከዚያው ስትይ...." ስል

" አይ አያቴ እየደከመች ነው፤ ዕለተ ቀኗ ደርሶ እርሷን በክብር እስካሳርፍ ነው እንጅ እኔ እንኳን መኖር የምፈልገው ኢትዮጵያ ውስጥ ስለሆነ መምጣቱ አይቀርም ብዬ ነው" አለች።

" በጣም ዕድለኛ ሰው ነሽ። የአያት ምርቃት ቀላል እንዳይመስልሽ " አለች ባለቤቴ።

" እውነት ነው እህቴ" ስትል ቀበል አደረኩና

" ለመሆኑ ምን አይነት የንግድ ሥራ ነው የምትሠሪ?" አልኩኝ።

" ከኢትዮጵያ ምግብ ነክ ነገሮችን እንደ ሽሮ፣ በርበሬ፣ ቅመማቅመም፣ አልባሳት አስመጣለሁ። በተጨማሪም የሀዋላ አገልግሎትም እሠራለሁ" አለች።

" እና ገቢያው ጥሩ ነው ያዋጣሻል? " አልኩ

" አዎን በርካታ ቤተ-እስራኤላውያን እና ሌሎች ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ስላሉ ጥሩ ነው" አለች።

‹ቤተ-እስራኤላውያን› ስትል ሰውነቴ ትርትር አለ። ተቅበጠበጥኩ።

"እኔ እምልሽ ከቤተ-እስራኤላውያን ጋር ትገናኛለሽ ማለት ነው?" አልኩ። ጉጉቴ የፈጠረው ጅላጅል ጥያቄ ነው።

"እንዴ ዋና ደንበኞቼ እነርሱ አይደሉ? እንዲያውም ከብዙዎቹ ጋር ወዳጆች ነን። እንደ ሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በሐዘን በደስታ እንጠያየቃለን" አለችኝ።

አባ መዐዛ ‹የዚች ሴት አምላክ ምልክት ይሰጥሃል ያለኝ ዕድሉ አሁን ነው› አልኩ ለራሴ።

" እንዲያው የማላስቸግርሽ ከሆነ..." ከማለቴ ባለቤቴ በአግራሞት አፈጠጠችብኝ።

" ምንድን ነው?" አለች ወጣቷ

" ከዚያ በፊት ግን እኮ ስማችንን አልተዋወቅንም" አልኩና የባለቤቴን ስም አስቀድሜ የኔንም ስነግራት

" መስህለ-ማርያም እባላለሁ" አለች በተራዋ።

" ስምሽ ደስ ይላል" አለቻት ባለቤቴ።





" አዎን! አያቴ ናት ያወጣችልኝ አለችና "ቅድም ምን ልትጠይቀኝ ፈልገህ ነበር?" ስትል

"እየውልሽ መስህለ-ማርያም! እ... አንድ ብርቱ ምሥጢር ለመረዳት ከቤተ-እስራኤላውያን መሪዎች ወይም አዛውንት አንዱን ማግኘት እንድችል ትረጅኝ እንደሁ ብዬ ነው" አልኳት።

ባለቤቴ "አንተ ሰው! የመጣንበትን መካናትን መሳለም ትተህ ደግሞ ሌላ ነገር እዚህ ማነፍነፍ ልትጀምር ነው? እሷንስ ባታስቸግር ምናለበት" አለች በቁጣ።

" እየውልሽ ይህን ዕድል ድጋሜ አላገኘውም። ከመጣሁ አይቀር ምናለ በልቤ ያለውን ምሥጢር ጠይቄ ብረዳ። ወዲህ ጉዳዩን እንዳጣራ የአባቶች አደራ አለብኝ" አልኳት። የሆነ ነገር ከጀመርኩ እንዲህ በቀላሉ እንደማልተዋው ስለምታውቅ፦

"በል እንደፈለክ" አለች እጇን እያወናጨፈች።

መስህለ-ማርያም ጣልቃ ገብታ፦

"ኧረ የሚያስቸግር ጉዳይ አይደለም። ጉብኝታችሁንም አያዛባም። ከቤተ-እስራኤላውያን መንፈሳዊ መሪዎች መካከል ቴላቪብ አቅራቢያ ኒታንያ ከምትባል ከተማ የሚኖሩ አባት ጋር ላገናኝህ እችላለሁ" ስትል

" እውነትሽን ነው? በቀላሉ ታገኛቸዋለሽ?" አልኳት።

"እንዴ! አያቴን ጠያቂ ወዳጃችን ናቸው እኮ። እንደ ቤተሰብ ነን" ስትል የሰማሁትን ለማመን ከብዶኝ አጋጣሚውን እያደነኩ እያለ፤

"ይልቁንስ የጉብኝታችሁን መርሐ ግብር አሳየኝ" አለችና ከቦርሳዬ አውጥቼ አብረን ስንመለከተው በሚቀጥለው ዐርብ ላይ ከአራት ሰዓት ጀምሮ የሥነ-ስቅለቱን ምዕራፎች በድጋሚ የሚጎበኝበት መሆኑን ተረዳሁ። በዛሬው ጉብኝት መጨናነቅ ስለነበረ እያንዳንዱን ምዕራፍ ሁሉም ሰው እንዲያየው ሲባል የሚደገም ነው።

ለእኔ ግን በበቂ መጠን ሁሉንም ስላየሁ ጊዜውን ለመጠቀም ፈለኩና፦

" ዐርብ ከአራት ሰዓት ጀምሮ ቢሆንልኝስ?" አልኳት።

" በጣም ጥሩ ነው። ስንበታቸው ከመግባቱ በፊት ለመጨረስ በቂ ጊዜ ይኖርሃል። ልክ አራት ሰዓት ላይ የጠዋቱን ጉብኝት ጨርሳችሁ ወደ ሊጦስጥራ ከመሄዳችሁ በፊት ‹የበጎች በር› ከሚባለው ላይ ትጠብቀኛለህ። ስንመለስ እዛው ሆቴላችሁ አደርስሃለው" አለች።

" እግዚአብሔር ዋጋሽን ይክፈልሽ፤ ትልቅ ሸክም ልታቀይልኝ ነው" አልኳት።

" ምንም አይደለም። እንግዳን ማስተናገድ እኮ ኢትዮጵያዊ ባህላችን ነው" አለችና "እንዲያውም ዛሬ ደውዬ ቀጠሮ አስይዝልሃለው። ለማንኛውም..." ብላ አድራሻዋን የያዘ ካርድ አውጥታ ሰጠችኝ።

የዕለቱን ሥርሐተ ሕዝብ ጸሎት በኢየሩሳሌም አብረን ተካፍለን ምዕመናን ያመጡትን እህል ውኃ ተቃምሰን ተሰነባበትን።

ወደ ሆቴል ስንመለስ ደስታዬ መጠን በማለፉ የምይዘውን የምጨብጠውን ሳጣ ያየችው ባለቤቴ፦





"ደግሞ እዚህ መጥተህ ሌላ ነገር ትቆፍራለህ ብዬ እንዴት ላስብ እችላለሁ?" ብላ ሳቀችና "ያለ ነገር ድንገት ተነሥትህ ቅድስት ሀገር እንሂድ መቼ አልከኝ?" አለች።

"እረ ተይ እንዳትኮነኚ አልኩ" ለማስመሰል።

"ግን ምንም ቢሆንም ግድ የለኝም። እንኳንም መጣን!" አለች።



Scanned with CamScanner



# ምዕራፍ - ፬

**አ**ሁን የቅዱሳን መካናት ጉብኝታችን እጅግ የተረጋጋና አስደሳች ሆነልኝ። በብዙ ነገር ውስጤ ሲጾዳ ሕሊናዬ ሲረጋጋ ይታወቀኝ ነበር፡፡ ብዙ ዓለማትንና የመስህብ ቦታዎችን ያየሁ ቢሆንም ሁሉም ቦታዎች ያስደሰቱኝና ያስደመሙኝ ቢሆኑም እንኳን ሥጋዬን እንጅ ነፍሴን፣ አዕምሮዬን እንጅ ልቤን እንዳልነበር በአግራሞት ተረዳሁ። ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነገረ ድሕነት በመጽሐፍ ቅዱስ በቅዱስ ወንጌል ሳነብ የኖርኩትን በአካል ማየት የዘመን ክስተት ነበር።





እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ብሥራት ከተቀበለችበት ናዝሬት እስከ ተራራማው ሀገር ‹አይነ ከርም› ጉብኝቷ፣ የመውለጃዋ ጊዜ ስለደረሰ ለቆጠራ ከዮሴፍ ጋር እንደሄደች የወለደችበት የከብቶች ግርግም መገኛ በቤተልሔም፣ ጌታ ማስተማር የጀመረበትና ደቀመዛሙርቱን የመረጠበት የገሊላ ባሕርና ዙሪያው፣ የደብረ ታቦር ተራራና የአርማጌዶን ሜዳ፣ የተጠመቀበት የዮርዳኖስ ወንዝ፣ የቆሮንጦስ ገዳም፣ ብዙ ጊዜ በማስተማር ያሳለፈበት የኤሊዮን ዋሻ፣ የደብረ ዘይት ተራራ፣ ያረገበት የቢታኒያ ተራራ፣ የጌቴሰማኒ የአትክልቱ ሥፍራ፣ የድንግል ማርያም ክብርት ሥጋዋ ያረፈበት ጌቴሰማኒ መቃብር፣ የቅዱስ እስጢፋኖስ መቃብር፣ ቀራንዮ ጎልጎታ ስንቱ ይቆጠራል፡ ፡ እያንዳንዱ የተኣምር ሥፍራና ታሪካዊ ቦታ በተለያዩ አብያተ ክርስትያናት ከላዩ ላይ መቅደስ የተገነባበት ቢሆንም ለጉብኝዎች ምቹ እንዲሆን ተደርጉ የተዘጋጀ ነው፡፡ በዙሪያው የሚታየው ነገር ሁሉ ለታሪኩ የሚመጥን እንዲሆን ንጽሕናውና ደኅንነቱ በአግባቡ የተጠበቀ መሆኑ ለምዕመናን የመንፈስ ደስታን ያጎናፅፋል፡፡ የእስራኤል መንግሥትም መሠረተ ልማቱን በጽዳትና በጥራት ለጉብኝት ምቹ እንዲሆን አድርጎ ማልማቱና ቦታዎቹንም ታሪካዊ ይዞታዎቻቸውን ሳይለቁ ጠብቆ ማቆየቱ ያስመሰግነዋል፡፡ በእርግጥ በበጎ የዘራውን በእጥፍ ከጎብኝዎች በየጊዜው ያጭዳል፡፡

ልዳ የቅዱስ ጊዮርጊስ መቃብር፣ የጥንቷ ጃፋ፣ የኤልያስ ዋሻ ሁሉም 2000 ዓመት ወደ ኋላ በመሄድ ሳይሆን አሁን የሆነ ያክል ወደ ፊት አምጥቶ ያስደምማል፡፡ ከመንፈሳዊና ታሪካዊ መካናት በላይ ሀገሪቱ ራሷ ታስደምማለች፡፡ ከታሪክ ተቋርጣ የነበረች ሚጢጥዬ ሀገር፣ የደረቀ መሬትና ድንጋይ ታቅፋ፣ ዙሪያዋን በጠላት ተከባም ቢሆን ለጠላቶቿ የብረት አለሎ፣ የእሣት ክንድ ለዜጎቿ ደግሞ ማርና ወተት

የምታፈስ የሠለጠነችና የበለፀገች ሀገር መሆኗ በራሱ ይደንቃል። በስንቱ ይቀናል?

በጉብኝቱ ወቅት ካስቆጩኝ ነገሮች ውስጥ በቅዱሳት መካናት አሻራቸውን ቀድመው ካስቀመጡ ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ ተቀዳሚ የነበረች መሆኗ ነው። ናዝሬት ከዮሴፍ ቤትና ድንግል ማርያም ብስራት ከተቀበለችበት ቤተ መቅደስ ግቢ በስተምዕራብ በኩል በተለምዶ ‹ምስለ ፍቁር ወልዳ› (እመቤታችን ተወዳጅ ልጇን ታቅፋ) የሚያሣየው ምስል በየሀገራቱ ያሳሳል ዘይቤ በሞዛይክ ተሠርቶ ተሰጥቷል። ከመጀመሪያው ረድፍ ካሉት ስዕሎች የኢትዮጵያ ምስለ ፍቁር ወልዳ አሳሳል ዘይቤ ይገኝበታል። ጌታችን ደቀ መዛሙርትን ‹አባታችን ሆይ› የሚለውን ጸሎት ባስተማረበት ስፍራ ላይ በዓለም ሁሉ ቋንቋ ጸሎቱ ግድግዳ ላይ ተነቅሷል። ከዚህም ከመጀመሪያው ረድፍ ላይ በግእዝ ተጽፎ ይገኛል።

‹አይነ ከርም› በተባለው ስፍራ ድንግል ማርያም ከኤልሳቤጥ ጋር ሲገናኙ ኤልሳቤጥ ደስታዋንና ምስጋናዋን በማሕፀኗ ውስጥ ካለው ፅንስ ጋር ሆና ስትገልፅ እመቤታችን የተናገረችው ትንቢታዊ ጸሎት በዓለም ሁሉ ቋንቋ ሲጻፍ እዚህም ላይ የኢትዮጵያ ግእዝ ግንባር ቀደም ስፍራ ይዞ ይታያል። ክርስትናን እንዳቀባበላቸውና ከጥንቷ እስራኤል ጋር እንደነበራቸው ታሪካዊ ቁርኝት የሀገራት የጽሑፍ ተርታ በጥንቃቄ ተደርድሯል። የኢትዮጵያ ከቀዳሚዎቹ ተርታ ተጽፎ ሲታይ የሆነ የክፍታ ስሜት ይፈጥራል።

በብዙ ስፍራዎች ኢትዮጵያ ገዳማትና ይዞታዎች ከጥንት ጀምሮ እንደነበሯት ቢታወቅም አሁን ላይ በእጃችን ላይ የቀረን ግን በጣም ጥቂትና ያም በውዝግብ የተሞላ ነው። እነዚህ ሁሉ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ትልቅ ክብር ያላቸው ቀደምት አማኞች ለመሆናቸው





ሕያው ምስክር ናቸው። ይሁን እንጅ አሁን አሁን ግን ድህነት ከታሪክ መድረክ ገፍትሮ ሲያስወጣን ጫፍ ላይ መድረሱን መረዳት ልብ ያደማል። የሰቀሉትም ያሰቀሉትም ከኋላ መጥተው ሲገፈትሩን ሲሞክሩ ማየት በጣም ያማል።

ጉብኝት በጀመርን በሳምንቱ ሐሙስ ጌታ የተወለደበትን በፍልስጤማውያን ግዛት የምትገኘውን ቤተልሔምን ለመጎብኘት ሄድን። አረጋዊው ዮሴፍ ኗሪነቱ ናዝሬት ቢሆን ነገዱ ከይሁዳ ስለነበር የአውግስጦስ ቄሳርን ትዕዛዝ ተቀብሎ ለመቆጠር ቅድስት ድንግል ማርያምን ይዞ የሦስትና የአራት ቀን ጉዞ አድርገው ቤተልሔም ደረሱ።

ቤተልሔም ሲደርሱ በርካታ ሕዝብ ለመቆጠር መጥቶ ስለነበር ከተማዋ ተጨናንቃ ደረሱ። እንደማንኛው ዜጋ ረጅም ሰልፍ ይዘው ተራ ጠብቀው ተቆጠሩ። ምሽቱ ሲቃረብ ማረፊያና ማደሪያ ፍለጋ ተዘዋወሩ። የሚያስጠጋቸው አልነበረም። ባለፀጋ አይደሉ አይከራዩ፣ መኳንንት አይደሉ ከባለፀጎች አይመሩ። ያላቸው ብቸኛ አማራጭ የከብቶች ማደሪያ ግርግም ዘንድ ሂደው መጠጋት ብቻ ነበር።

በዚያ የበኩር ልጇን ወለደችው፣ በጨርቅም ጠቀለለችው፣ ከብቶችና አህዮች በትንፋሻቸው ያሞቁት ዘንድ በግርግም አስተኛችው። አሁን ያንን ስፍራ ሰብዓ ዓለም ረጅም ሠልፍ ይዞ ከሦስት ሰዓት በላይ ጠብቆ ተንበርክኮ ይሳለመዋል። እኛም ከሦስት ሰዓት በላይ ቆመን ጠብቀን ለመሳለም በቃን። ከጉብኝት በኋላ ምቾት ባለው አውቶብስ ተጉዘን፣ ከባለ አራት ኮከብ ሆቴላችን ገብተን፣ በሠልፍ ቁመት የዛለውን ገላችንን በሙቅ ውኃ ተለቃልቀን አበረታን። ምግብ በየዓይነቱ ተመግበን ወገብ በሚያሳርፍ ንጹሕ አልጋ ላይ ተኛን። እንግዶች ብንሆንም ምቾት ያለው ማረፊያ አገኘን። ለድንግል ማርያም ግን በዚያ ምሽት ማደሪያ

መጠሪያ አልነበራትምና በበረት ውስጥ በከብቶች መካከል ለማረፍ ተገደደች። ይህን ንጽጽር ለባለቤቷ ስትነግራት ድንገት ካልጋው ወረደችና "ባይሆን ዛሬስ አልጋው ላይ መተኛቱ ይቅርብኝ" ብላ ወለል ላይ ጥቅልል ብላ ተኛች።





# ምዕራፍ - ፩

ቀናት ጣፋጭ ይሁኑም መራራ፣ አስደሳችም ይሁኑም መከራ ማለፋቸው አይቀርምና ጣፋጩ ሳምንት አለቀ። አርብ በቀጠሯችን መሠረት ቀናዋ ወጣት መስህሉ-ማርያም መኪናዎን ይዛ ከተቀጣጠርንበት ስፍራ ደረሰች።

ባለቤቴን ከሌሎች ጉብኚ ምዕመናን ጋር ትቻት እኔ በመስህሉ- ማርያም መኪና ተሣፍሬ ወደ ኒታንያ አመራን።

በርከት ያሉ ኢትዮጵያውያን አይሁዶች የሚኖሩባት ማዕከላዊ እስራኤል በባሕር ዳርቻ የምትገኝ ከተማ ነች ‹ኒታንያ›።

ኩሶሻቪቭ በስተሰሜን 30 ኪ/ሜ ከኢየሩሳሌም ደግሞ 96 ኪ/ሜ አካባቢ የምትርቀው ኒታንያ ለመድረስ አንድ ሰዓት ከሃያ በላይ እንደማይፈጅብን መስህሉ-ማርያም ነገረችኝ።

ወደ ቴላቪቭ አቅጣጫ ተከትላ መስህሉ-ማርያም መኪናዋን ስታከንፍ የእኔም ሐሳብ ቀድሞ ይከንፍ ጀመር።

‹አሁን ድንገት ዘው ብዬ ልዩ ምሥጢር ያለውን የከበረን ቅርስ ስጡኝ ስል ምን ይሆን የሚሉኝ?›

‹የማነው ከረፈፍ ብለው ያሳፍሩኝ ይሆን?›

‹መቼም ምንም ቢሆን ኢትዮጵያዊ መንፈስ አላቸውና የሴቷን ሕመምና መከራ ስነግራቸው አይጨክኑም› እያልኩ እራሴን ለማፅናናት ስሞክር፣

"አሁን የምታገኛቸው አባት በኢትዮጵያውያን አይሁድ ዘንድ የተከበሩ የሃይማኖት መሪ፣ በሌላው ስደተኛ ዘንድም መካሪና አስታራቂ ናቸው፡ ፡ ‹አባ ዮናታን› ይባላሉ" አለች መስህሉ-ማርያም።

"ስትጠይቂያቸው አላስቸገሩሽም?" አልኳት፤ ሁኔታውን ለመገምገም።

"ከኢትዮጵያ ባሕር ዳር እንደመጣህ ስነግራቸው እንዲያውም ለማግኘት ጓጉ። ያው የሰውና የሀገር ናፍቆት አለባቸው አይደል?" አለችኝ።

ቀጠል አደረኩና "ግን ኢትዮጵያውያን አይሁዶች በዚህ በእስራኤል የጠበቁትን ያክል ተመችቷቸዋል?" አልኩ።

"በርግጥ ጥሩ መኖሪያ ቤት፣ በቂ ምግብና አልባሳት ተሟልቶላቸው በምቾት ነው የሚኖሩት። መማር ለሚፈልጉትም የትምህርት ዕድል





አለ ብቻ ግን...." ስትል

"ብቻ ምን?" አልኳት

"ያው የዘረኝነት ተፅዕኖ ብዙ አንገላቷቸዋል" አለች።

"እስራኤላውያን እንደሆኑ ታምኖባቸው አይደል እንዴ በረቀቀ ኦፕሬሽን ከኢትዮጵያ ያመጧቸው። ተጽዕኖ ታዲያ ከምን የመነጨ ነው?" አልኩ።

"ኢትዮጵያውያን አይሁዶች እንደ ምዕራባውያኑ አይሁዶች በዘመናዊነትና በፖለቲካ የታሸ ሳይሆን ያልተበረዘ ያልተከለሰ ይሁዲነትን ይዘው የተመለሱ ናቸው። በኢትዮጵያ በኖሩበት ዘመን ከይሁዳ ምድር ውጪ ጠንቅቀው ይሁዲነትን የኖሩ የታመኑ ናቸው። አውሮፓውያን ራሳቸው ተቀይረውና ተቀይጠው ሲመለሱ ጊዜ የጥንቱን ጠባቂዎች ኢትዮጵያውያን አይሁዶችን መጠራጠራቸው የሞራል ሚዛን የሚደፋ አልነበረም። የሆነ ሆኖ ግን ‹አፍ ያለው ያግባሽ ወይስ ሀብት ያለው› እንደተባለው አፍም ሀብትም ያላቸው ምዕራባውያኑ ተመላሾች ንጹሕ ይሁዲ እንደሆኑ ራሳቸውን ቆጥረው ከኢትዮጵያ የመጡትን እንደተቀየጡ መቁጠራቸውና ካውሮፓ ይዘውት የተመለሱት የነጭነት ትምክህት ልክፍት ሊለቃቸው ስላልቻለ ነው።" ስትል

"ያሳዝናል" አልኩ።

"አንድ ምሁራቸው እንዲያውም ‹ይሁዲ አይደሉም› አለና ‹ግን በተለየ መልኩ ይሁዲ ናቸው› ብሏል። እውነትነት አለው። በተለየ የሚለው በጥንቱ መልክ ይሁዲ መሆናቸው ለመቀበል ቢከብደውም ሀቁ እርሱ ነው። ያም ተባለ ይህ የተለወጡት ያልተለወጡትን፣ የተቀየጡት ያልተቀየጡትን መሥፈርት አበጅተው ሥርዓት ሠርተው



Scanned with CamScanner

‹መለወጥ ለምሉዕነት /Converstion to Complestion› በሚል ፊቢጥ ግራ ያጋቧቸዋል። ምርር ሲላቸውም ‹እኛ እኮ ይሁዲዎች ነን፣ እኛ እኮ የበለጠ ኢትዮጵያ ውስጥ ሃይማኖተኞች ነበርን› ይላሉ። ‹ያልተበረዝን ያልተከለስን ነን› ይላሉ። የሰንበት አከባበር፣ የእንስሳት አርድ ሁሉ ዝብርቅርቅ ይልባቸዋል። አንዳንዶች እንዲያውም ሥጋ መብላት ትተዋል።" አለች በቁጭት።

"ኢትዮጵያን ግን የረሱ ወይም የሚረሱ ይመስልሻል?" አልኳት።

"በፍጹም!" አለችና "ኢትዮጵያ ውስጥ ሲኖሩ ቤተ-እስራኤላውያን መባልን እንደሚመርጡት ሁሉ እስራኤል ውስጥ ደግሞ ኢትዮጵያውያን አይሁዶች መባልን ይመርጣሉ። የሚያኮራቸው መጠሪያቸውም ነው።የሁለቱ ሀገሮች ጥንታዊ ታሪክ እንዳይበጠስ ማስተሳሰሪያ ገመዶች ናቸው እኮ! " አለችኝ ፈርጠም ብላ።

መስህሉ-ማርያም ይህን ሁሉ ስለ ቤተ-እስራኤላውያን ስትነግረኝ በመቆርቆር ስሜት ስለነበር፣

"በጣም የምትቆረቆሪላቸው ይመስላል" አልኳት።

"እንዴ በጣም እንጂ። ወገኖቼ አይደሉ እንዴ?" አለች።

"አይ... እንዲያው አጥባቂ ክርስትያን ሁነሽ እንዲህ ይሁዲ ለሆኑት መቆርቆርሽ ገርሞኝ ነው" ስላት

"ክርስትያን ብሆንስ?" አለች።

"ክርስቶስ ተብሎ ክርስትያን ያሰኘሽን ገርፈው ወግረው የሰቀሉት አይሁዶች ስለሆኑ ብዬ ነው" አልኳት ስሜቷን ለመረዳት።



"ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ሲሰቀል ኢትዮጵያውያን አይሁዶች በኢትዮጵያ ስለነበሩ ከደሙ ንጹሕ ስለሆኑ ነው" ስትለኝ ከልቤ ከት ከት ብዬ ሳኩ። እርሷም አብራኝ ትስቅ ጀመር።

በሰጠችኝ መልስ በእጅጉ ተደንቄ ‹ይህ ኢትዮጵያዊነት የሚባለው ማስተሣሠሪያ ገመድ እንዴት ረቂቅና ኃያል ነው!› አልኩ ለራሴ። ትንሽ ሥጋ እንደ መርፌ ትወጋ ሆኖባት ነው እንጂ ከታሪክ ድርሳን እንጻር ሲታይ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት ቤተ እስራኤላውያን በሙሉ ከሚኒሊክ ጋር የመጡት ብቻ ሳይሆኑ ኋላ ላይ ከክርስቶስ ልደት በኋላም ፈልሰው የመጡ እንዳሉ ይታወቃል። ይሁን እንጂ ይህንን ታሪክ ጠቅሼ ቅን ፍቅሯን ማደብዘዝ አልፈለኩም።

ቱላቪብን ወደ ቀኝ ትተን አንድ ሀያ ኪሎሜትር ከተጓዝን በኋላ ኒታንያ መድረሳችንን የመንገድ ምልክቱ ጠቆመን። የልቤ ምት ፍጥነት እየጨመረ ሰውነቴን ሁሉ ላብ ያጠምቀኝ ጀምሯል። መስህሉ-ማርያም መኪናዎን ግራና ቀኝ እያጣደፈች ብሎኮችን ካለፈች በኋላ መድረሳችንን ነግራኝ ከአንድ ግዙፍ አፓርትመንት ፊትለፊት ካለ የመኪና ማቆሚያ አቆመችና ከመኪናዋ እንድወርድ አመለከተችኝ።

"እንግዲህ የምታገኛቸው ሰው ከሊቀ ካህናቱ አንዱና በብዙ መልኩ ከሰው ጋር ተግባቢ የሆኑ ናቸው። ሁሉም ሰው ‹አባ ዮናታን› ይላቸዋል።" አለችና በድጋሚ "የምትሻውን እንደምታገኝ ተስፋ አለኝ" ብላ ወደ አፓርትመንቱ አመራች።

እኔም በልቤ ‹እንደ አፍሽ ያድርግልኝ› ብዬ ተከተልኳት።

ወደ አፓርትመንቱ እንደገባን አንድ ፎቅ በደረጃ ወጥተን ወደ ሦስት አቅጣጫ የሚወስድ ሠፊ ኮሪደር አገኘን። ወደ ሦስቱም አቅጣቻዎች

የሚወስዱት በሮቹ ተዘግተው ተመለከትን። ወደ አንዳኛው በር ሄዳ ከተደረደሩ ቁልፎች መካከል አንዱን ስትጫን ድምፅ ተሰማ።

"መስህለ-ማርያም ነኝ" አለች።

በሩ በኤሌክትሪክ የሚሠራ ስለሆነ በራሱ ጊዜ ሲከፈት የእንግባ ምልክት አሳይታኝ ተከተልኳት። ሌላ ከበፊቱ ጠበብ ያለ ኮሪደር አልፈን ወደ ሳሎን ዘለቅን።

ረጅም ባለ ግርማ ሰው ቆመው ሲጠብቁን አየሁ። ‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ካህን ናቸው እንዴ?› አልኩ ለራሴ።

ነጭ የሻሸ ጥምጥም፣ በወርቀዘቦ የተጠለፈ ጥቁር ካባ፣ ከውስጥ ነጭ ጋቢ፣ ከሥር ደግሞ ሙሉ ነጭ ኮት ከነጭ ሱሪ ጋር ለብሰዋል። ደስ የሚል ረጅም የሸበተ ፂም፣ ግንባራቸው ላይ መሸብሸብ የጀመረ ደርባባ ጠይም ፊት ይታየኛል። በእጃቸው የብረት ወይም የእንጨት መስቀል የለም እንጂ ቁርጥ የጎንደር አድባራት ካህን ወይም ሊቅ ይመስላሉ።

መሥህለ-ማርያም "እንዴት ሠነበቱ?" አለችና ጉልበታቸውን ለመሣም ደፋ ስትል፡-

"ተይ እንጅ ልጄ!" ብለው ቀና አድርገው አገጯን በቀኝ እጃቸው ይዘው ጉንጮቿን አገላብጠው ሳሟት።

ወደ እኔ ዘወር አለችና "እንግዳዬ እርሱ ነው፤ አቶ ሲሳይ ይባላል" አለች።





እኔም እንደርሷ ቀረብ ብዬ ጉልበታቸውን ለመሳም ጐንበስ ስል " ልጄ! ተው እንጅ፤ አይገባም እኮ!" አሉና ቀና አድርገው ትከሻዬን ሳሙኝ።

"አይ መስህለ-ማርያም! ጥቁር እንግዳ ሰው በሌለበት ቀን ይዘሽብኝ ትመጪ? ነገ ሰንበት ስለሆነ ሁሉም ወደ ገቢያ ሂደው ብቻዬን ነኝ" አሉ።

"ችግር የለም ቤቱን ይዘውት አልሄዱ፤ ሻይ እንደሆነ እኔ አፈላለሁ" አለች መስህለ።

"በይ ልጄ ደግ ነው፤ ቤትሽ እኮ ነው" አሉ።

የቤቱን ዙሪያ ስቃኝ ሁሉ ነገሩ ደስ የሚል ኢትዮጵያዊ ቤት ነው። የሚያማምሩ በዳዊት ኮከብ አምሳል የተሠሩ ስፌቶች ግድግዳው ላይ አልፎ አልፎ ተሰቅለዋል። በአለላ የተንቆጠቆጠ ትልቅ መሶብ አንድ ጥግ ላይ ጉብ ብሏል። የኢትዮጵያና የእስራኤል ባንዲራ ከአንድ መደብ ላይ ተሰክተው ግራ ቀኝ ተዘርግተው ልዩ ልዩ ፎቶግራፎች ከተደረደሩበት ጠረጴዛ ላይ ያታያሉ።

"በል የኔ ልጅ አረፍ በል" አሉኝና ወደ ሶፋው አመለከቱኝ። እርሳቸው መቀመጣቸውን ጠብቄ እኔም ቁጭ አልኩ።

"ከኢትዮጵያ እንደመጣህ መስህለ-ማርያም ነግራኛለች" አሉና "ሀገር፣ መንደሩ፣ ቀየው ደኅና ነው?" አሉኝ።

"ደኅና ነው አባታችን" አልኩ።

"ዘናቡስ? አዝመራውስ?"

"አሁን ሁሉም ነገር ደኅና እየሆነ ነው" ብዬ መለስኩ።

"ኢትዮጵያ እኮ ሰላም ብታገኝ ጠንካራ አገር የምትሆን ናት" አሉና ረጅም ፅህማቸውን እየላጉ ትክዝ ብለው ቀሩ።

መስህሉ-ማሪያም ሳንስተናገድ ተመልሰን ቅር እንዳይላችው ቶሎ ሻይ አፍልታ አቀረበች። ዱባ የሚያክል የጃፉ ብርቱካንም ቆርጣ አቀረበች። መቼም ቅንነቷና ቅልጥፍናዋ ግሩም ነው።

"ለፋሲካ ስመሣለም መጥተህ ነው?" አሉ አባ ዮናታን።

"አዎን ትንሣኤውን እዚህ ለማሳለፍ በዚያው ቅዱሳን መካናትን ስመሣለም ነው" አልኩ።

"ደግ አደረክ የኔ ልጅ!" አሉ።

ዕድሉ እንዳያመልጠኝ አልፈለኩምና "በእውነቱ ሌላም ጥብቅ ጉዳይ ነበረኝ" አልኳቸው።

"እና ተፈጠመልህ?" አሉ

"ገና ዛሬ የሚታይ ነው" አልኳቸው። ‹ፈጣሪ ልቦናዎትን ያራራልኝ እንደሆነ ይሆናል አሰበለዚያ እያዘንኩ መመለሴ ነው› አልኩ ለራሴ። ድንገት ያቺ ምስኪን ሴት ስታቃስት የሰማኋት መሰለኝና ውስጤ እንደገና ይተራመስ ጀመር።

"ሁሉም በአምላክ ፈቃድ ይፈጠማል" አሉ።

እኔ ደግሞ ‹ወደ አምላክ አይሰደዱ በርስዎ ፈቃድ ነው የሚፈጸም› አልኩና በልቤ፡-





"ያው እ... ሳገኝዎት የፈለኩት ጉዳዬን እርስዎ ያግዙኛል ብዬ ነው... አባቴ" አልኩኝ።

"የሚቻለኝ ተሆነ ምን ችግር አለው ልጄ?" ሲሉኝ

"ሻይው ሳይበርድ ጠጡና ውስጥ ገብታችሁ ትነጋገራላችሁ" አለች መስህሉ-ማርያም።

"ማለፊያ ነው በል እኮ ቅመሰው" አሉ።

መጀመሪያ አንዱን የብርቱካን ኩርማን አንስቼ በላሁና ሻሂዬን ከሐሳቤ ጋር እያወራረድኩ ጠጣሁ። ሻይውን ጠጥተን መጨረሳችንን ስታይ መስህሉ-ማርያም፡-

"በሉ ከአባ ንባብ ክፍል ግቡና ተነጋገሩ" አለች።

የልብ አውቃ በመሆኗ በልቤ ደጋግሜ መረቅኋት። እኔ እራሴ ትዕግስት የሌለኝ ሰው ነኝ! ያሰብኩትን ጠይቄ እስክወረደው ድረስ የምቅበጠበጥ ነኝ። እርሷ አሁን ያልሆነ ወግ አምጥታ ብታስቀይሰን ወይ ደግሞ የተንዛዛ ጨዋታ ውስጥ ብንገባ ጨንራዬ መሳጡ ነበር።

"እውነትሽን ነው የኔ ልጅ" አሉና ቀልጠፍ ብለው ተነሥተው አልፈነው ወደ መጣነው ኮሪደር ተመልሰው አንድ በር ከፍተው ሲገቡ ተከተልኳቸው። የሚያምር የፋርስ ምንጣፍ ተነጥፎበታል። በሁለት ማዕዘን ባሉ ሸልፎች በርካታ መጽሐፍት ተደርድረዋል። በአንደኛው ግድግዳ የዳዊት ኮከብ በትልቁ ተቀርፆ ተቀምጧል። ከወለሉ ምንጣፍ መካከል አንድ በቀይ ሀር ጨርቅ የተሸፈነ መጽሐፍ በአትሮንስ ላይ ተቀምጧል። ‹ቶራ› መሆን አለበት አልኩ። ከጐኑ ቤተ ክርስቲያን የምናየው ዓይነት ወርቃማ አብረቅራቂ ጥላ ተዘርግቷል። በአንደኛው

ገድግዳ በትልቁ ፍሬም የተዘጋጀ ኢትዮጵያውያን ከአውሮፕላን ሲወርዱ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ ተሰቅሏል፡፡ ‹የዘመቻ ሙሴ አለዚያም ዘመቻ ሰሎሞን ማስታወሻ ይሆናል› አልኩ በልቤ፡፡ የዳዊት ኮከብ በተሰቀለበት ግድግዳ ከሥር ጠረንጴዛ ላይ በሻማ ቅላጭ የጠቋቆረ ባለ 7 ልሳን የዕብራውያን የመብራት መቅረዝ ተቀምጧል፡፡

አባ ዮናታን ከአንድ ታጣፊ የእንጨት ወንበር ላይ አመለከቱኝና እርሳቸው እንዲሁ ከተመሳሳይ ወንበር ላይ ፊት ለፊቴ ተቀመጡ፡፡

‹ሰዓቱ ደረሰ ማለት ነው፤ አሁን ምን ብዬ ነው የምጀምረው? የከበረውን ቅርስ ስጡኝ ነው የምል? ወይ ጉድ!› አልኩ ለራሴ ግራ ግብት ብሎኝ፡፡

"የኔ ልጅ ምንድን ጉዳይ ገጥሞህ ነው?" አሉኝ በአባታዊ ቃና ጭንቀት ውስጥ እንዳለሁ የተረዱ ይመስላል፡፡

"አባታችን ጉዳዩ እንኳን የኔ የግሌ አይደለም እ.... " ስል

"ዛዲያ የማን ነው?" አሉ ለዘብ ብለው፡፡ የንግግር ቃናቸው የጎንደር ዙሪያ እንደ ወረደ ነው፡፡

"እ... እኔም ታዝገኔ ነው" አልኩ፡፡ እንዲያገዘኑልኝ መሆኑ ነው፡፡

"ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የገዳም አባቶች ናቸው ጠርተው ያዘዙኝ" አልኩ፡፡ እግዜር ያሳየዎት እንደማለት እያሳጣሁ፡፡

"እኮ ምንድን ነው ያዘዙህ?" አሉ ጢማቸውን እየላጉ፡፡ እርጋታቸውና ነገረ ሥራቸው ሁሉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ካህንና መነኩሳትን ነው የሚመስለው፡፡





አዕምሮዬን በደንብ ሳሠራው የክርስቲያን ዕምነት ተከታዮች የሆኑ ገዳማውያን ከአይሁድ ሊቃውንት ዘንድ የሆነ ነገር እንደፈለጉ አድርጌ ማቅረቤ ጅል አቀራረብ መስሎ ተሰማኝ፡፡ እርግጥ ብዙ የሚያመሳስላቸው ነገር አለ፡፡ የክርስትና ዕምነት ከብሉይ ትንቢት ተመሥርቶ ወደ ሐዲስ ኪዳን የሄደ ሲሆን የአይሁድ ዕምነት ግን ብሉይ ላይ የቆመና የራሱን ትንቢትና ፍፃሜ ገና የሚጠብቅ ነው። በብሉይ ጉዳይና በኦሪት ሕግና ሥርዓት አንድ ዓይነት ታሪክ ይጋራሉ ማለት ነው፡፡ ከዚህ በላይ ኢትዮጵያ የሚለው ቃል በእርግጥ ለኢትዮጵያውያን አይሁዶችና ለኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ሌላው ጥልቁ የሚያስተሳስራቸው ገመድ ነው፡፡ ‹ቢሆንም አቀራረቤን የበለጠ ስሜታቸውን እንዲገዛው ማድረግ አለብኝ› ብዬ አሰብኩ፡፡

"ብዙ ጊዜ አባቶች አንዳንድ የሚያስፈልጋቸው ጉዳይና ከገዳም የሚያስወጣ ችግር ሲገጥማቸው ጠርተው ያዙኛል" አልኩ፡፡

"መታዘዝ እኮ ማለፊያ ነው፤ የኔ ልጅ አበጅህ እንጂ" አሉ፡፡

"እና...የብዙዎች እናት የሆነች አንዲት ሴት...እ... በከባድ ሕመምና ስቃይ ውስጥ ሆና ከአንድ ገዳም አባቶች ዘንድ መዳኗን በተስፋ ትጠባበቃለች" አልኩ

"እናቴን! ምን አገኛት? ምን ሆነች?" አሉ፡፡

"ምክንያቱ ብዙ ነው ይባላል፡፡ ብቻ ደም ይፈሳታል፡፡ በዚህም የተነሳ ክብሯም፣ ሀብቷም፣ ጤናዋም ተንሳቁሏል፡፡ ውብ ስትሆን ገርጥታ፣ ሀብታም ስትሆን እንደ መናጢ አንድ ጥግ ተጣጥፋ ተኝታ የመዳኗን ቀን ትጠብቃለች" አልኩና ሳላስበው ሁኔታዋ በዐይኔ ሕሊናዬ መጣና እንባዬ ፍልቅ አለ፡፡



Scanned with CamScanner

ይሆን ያዩት አባ ዮናታን፡-

"ልጅ እንደሱም አይደል፡፡ ማልቀስ መፍትሄ አይሆንም፡፡ መፍትሄው ተረጋግቶ መፍትሄ መፈለግ ብቻ ነው" አሉ፡፡

"እውነት ነው አባቴ፤ እሱማ ለዚህም እኮ ነው እዚህ ድረስ የመጣሁት" አልኩ፡፡

"እኮ ምን ፍለጋ?" አሉ ትኩር ብለው እያዩኝ፡፡

"እ…አባቶች እንደነገሩኝ ለመዳን ከሚያስፈልጉት ነገሮች አንዱ እ… እዚህ …" አልኩና እጄን ማፍተልተል ጀመርኩ፡፡

"ተዚህ ምን ?" አሉ አሁንም ዐይን ዐይኔን እያዩኝ፡፡ ሁኔታቸውን ሳይ ጉጉት ያደረባቸው መሰለኝና፡-

"ያው… በቀጥታ እርስዎ ዘንድ ባይሆንም…እ.. ከእናንተ ከቤተ እስራኤላውያን እጅ እንደሚገኝና ፈቃዳችሁ ከሆነ ይገፔ እንድሄድ ነበር" አልኩ፡፡

"እኮ ምንድን ነው የተፈለገው?" አሉ ረጋ ብለው፡፡

"በእርግጥ ከእርስዎ ዘንድ ላይሆን ይችላል፡፡ መቼም አባትም ሲቅም ነዎትና አይጠፋዎትም ብዬ ነው እንጂ?" አልኩ፡፡ ለራሴ ደግሞ ‹ምንድን ነው ተራራውን የሚያዞረኝ?› አልኩ፡፡

"መቼም የኔ ልጅ ግልጥ አድርገህ ታልነገርከኝ፤ ተእኔ ዘንድም ይሁን ተሌላው እንዴት አባቱ አድርጌ ላውቅ እችላለሁ?" አሉ ሁኔታዬ ግራ አጋብቷቸው፡፡





እኔም ራሴ ግራ የገባኝ መሆኑን ቢረዱልኝ መልካም ነበር አልኩና፡-

"እንትን ነው አምጣ የተባልኩ" ስል ‹ይሄ ልጅ ጤናም አይደለም?› የሚሉ መሰለኝና

"እ…" እያልኩ ራሴን ስፎክት ቆይቼ በገልጽ ነገርኳቸው፡፡ ‹ቡ..ም› የሄዘቦላን ቦንብ ያፈነዳሁ መሰለኝ፡፡

የመገረምም ይሁን የመከፋት ስሜት ፊታቸው ላይ ማየት አልቻልኩም። ብቻ ዝም ብለው ረጅም ነጭ ጺማቸውን እየላጉ የዳዊት ኮከብን አሻግረው እያዩ ለበርካታ ሴኮንዶች ቆዩ፡፡

"ተዚህ ተኛ ዘንድ ይገኛል ብለው እንዴት የገመቱ ይመስልሃል?" አሉኝ፡፡

"ታሪኩ ረጅም ነው፡፡ ብቻ እንዳላስለችዎት?" አልኩ፡፡

"የኔ ልጅ ፍሬ ያለው ነገር እኮ ነው የምንነጋገረው፤ ተዚህ ድረስ የመጣህስ ጉዳዩ ብርቱ ቢሆን አይደል?" አሉ፡፡

"እርሱማ ነው፤ ከምን እንደምጀምር ግራ ገብቶኝ ነው እንጂ" አልኩ፡፡

"ግዴለም ተመጀመሪያው እስተመጨረሻው ንገረኝ" አሉ፡፡

በሙሉ ልብ ለመስማት እንደተዘጋጁ ስረዳ በዝርዝር ለመንገር ተገፋፋሁ፡፡



# ምዕራፍ - ፮

‹‹ይገርመዎታል! ራስ ደጀንን የተራሮች ንጉሥ ብንለው ይኸኛው ደግሞ የተራሮች መስፍን ሊባል ይገባዋል። ጥበበኛ ቀራጺ ከምድር ከፍ አድርጎ ለጌጥ እንዳቆመው ሃውልት ከርቀት በሁሉም አቅጣጫ በግርማ የሚታየው ይህ የተራራ መስፍን አናቱ በድምድም ጎፈሬ አምሳል በደን የተሸፈነ ነው። ደኑ ውስጥ የብዙ መናኞች መኖሪያ የሆነው ገዳም እንደ ብር ወለባ ከከምከሙ የደን ጎፈሬ መካከል ከርቀት ይታያል። ከመስፍኑ ጉያ ውስጥ ደግሞ በላሊበላው





ቤተ ገብርኤል አምሳል ከቋጥኝ ተፈልፍሎ የተሠራ ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን ይገኛል። ከዚህ ቤተ ክርስቲያን ስደርስ የቀኑ ሙቀት መጀመሩን ወበቁ ያሳብቃል። የበለሳ አየር ንብረት እንኳንስ በጥርና በየካቲት ለወትሮውም ቢሆን ሙቀቱ ከባድ ነው። የወበቁንና የዳገቱን ድካም ለማሳለፍ ከቤተ ክርስቲያኑ ቅፅር እንደገባሁ ጠፍጣፋ ድንጋይ ፈልጌ አረፍ አልኩ።

ከአኗኗር ዘይቤዬ ይሁን ከዕድሜዬ ጋር ተያይዞ ብቻ አቅመቢስ እየሆንኩ፣ ጉልበቴም እየከዳኝ እንደሆነ ይታወቀኝ ጀምሯል። አንድ ነባራዊ ሀቅ ያለና ለሁላችንም የሚሠራ ቢሆንም ከግብዝነታችን የተነሣ እውነታው ሲገለጥልን ወይ እንደነግጣለን አለበለዚያም ለመካድ እንሞክራለን። በዕድሜ ዘመናችን መጀመሪያ ወደ መጠንከርና መበርታት ቀጥሎ ኋላ ላይ ደግሞ ወደ መጠውለግና መጨማደድ መቀየራችንን እንረሳዋለን። ይህ የተፈጥሮ ሕግ የማይቀየርና የማይቀር በመሆኑ ዋናው ነገር ለሁሉም ነገር በተገቢው መዘጋጀት እንጂ ለመርሳት መሞከር ግብዝነት ይሆናል።

መድከምና መዛል ወይም መጠውለግና መጨማደድ ብቻ ሳይሆን ካልተዘጋጀን መጠንከርና መጎልመስ፣ መጎምራትና ማማርም አስቸጋሪ ይሆናሉ። ጉልበትና ውበት የሞት ወጥመድ ሆኖ ሊመጣ ይችላል። ወጣትነትም፣ ጉልምስናም፣ እርጅናም የራሱ የሥነ ልቦና ዝግጅት ይፈልጋል። አእምሯችንን ከአካላችን ለውጥ ጋር ካላገናኘነው ከሥጋ አካላችን ቀድሞ መገርጀፍ ወይም ከፈዘዘ አካላችን ጋር ያልተቀናጀ አስተሳሰብ ይዘን ሽማግሌ ሕጻን ወይም ሕጻን ሽማግሌ ልንሆን እንችላለን።

በዳገቱ የዛለውን ጉልበቴን አሳርፌ የሚቆራረጠውን ትንፋሼን አረጋግቼ ሳበቃ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ጠጋ ብዬ ጸሎት ቢጤ አደረስኩ።

ጸሎት ማድረግ የምችል አይመስለኝም። ሁልጊዜ ለጸሎት ስቆምም ሆነ ስንበረከክ የምለው ይጠፋብኛል። ምስጋና ሳበዛ የጎደለኝ ትዝ ይለኛል። ጥያቄ ሳበዛ የተደረገልኝ በዐይነ ሕሊናዬ ይመጣና ውለታ በላ የሆንኩ ይመስለኛል። ወዲያው ደግሞ ግሳንግሱ ኃጢአቴ ትዝ ይለኝና የማመልከትም የመጠየቅም ሐሳቤ ይጠፋና ሀፍረቱ ይመጣል። ለማመጣጠን ስሞክር ደግሞ ጸሎቱን ትቼ ሥራ የያዝኩ ይመስለኛል። በቃል ያጠናሁትን የተለመደ ጸሎት ባደርግ ይሻላል ብዬ ስጀምር ራሴን መጨረሻው ላይ አገኘዋለሁ። በንባብም ቢሆን ያው ነው። አንዳንዴ ለራሴ፦

ሰው እንዴት ከፈጣሪው ጋር መነጋገር ያቅተዋል? ከሰነፉ የሰው ዓይነት ጋር እየተግባባሁ እንዴት ከአምላኬ ጋር መግባባት ያቅተኛል? እያልኩ በራሴ አዝናለሁ።

መጽናኛዬ ግን ሁለት ነገሮች ናቸው፤

ጌታዬና ፈጣሪዬ የሆንከው አንተ ሁሉን ታውቃለህ፣ ስልና የምወዳቸውን አባቶችና እናቶች በጸሎታችሁ አስቡኝ፣ ስል ፈጣሪ በትክክል የሚሰማኝ ይመስለኛል። ያም ሆነ ይህ እስካሁን ከአምላኬ ጋር ላለመግባባቴ ዋናው ምክንያት እኔ በመሆኔ እኔ ስስተካከል ግንኙነቱ ይስተካከላል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

የተለመደውን የተምታታ ጸሎት ቢጤ ጨረስኩና ከቤተ ክርስቲያኑ በስተምሥራቅ በኩል በድንጋይ አጥር ወደ ተከበበው ፍልፍል ቤተ ክርስቲያን የፊት ገጽ ዘለቅኩ።

ለመነኮሳትና ለምዕመናን መቀመጫ እንዲሆኑ ጠፍጣፋ ድንጋዮች ከጠባቡ ግቢ ውስጥ አጥሩን ተከትለው ተደርድረዋል። እኔ ስደርስ የዕለቱ ስንክሳር በአትሮንስ ላይ ተዘርግቶ እየተነበበ ነበር። ወዝ





መነኮሳት ፈንጠር ፈንጠር ብለው አንገታቸውን አቀርቅረው ታሪኩን በጽሞና ያዳምጣሉ። ከፍልፍሉ ቤተ ክርስቲያን መግቢያ በስተውጭ በኩል ወንበር ላይ ታላቁ አባት አባ አካለ ወልድ ተቀምጠዋል። ለምላሚዋ ያልተለያት ሰፋፊ ቅጠል ያላት የዕፅ ዝንጣፊ ይዘው እንደ ጭራ ቀኝና ግራ እያወዛወዙ ንባቡን ይከታተላሉ። የእኔን መምጣት ሲያዩ በዕጹ ዝንጣፊ ከአንዱ ጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ እንድቀመጥ እያመላከቱ በፈገግታ ተቀበሉኝ። ከወገቤ ጎንበስ ብዬ ሰላምታና ምስጋና አቅርቤ ከአንደኛው ጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ ተቀመጥኩ።

ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ከመድረሴ በፊት ፈዛዛ ቀለም ያለው ፎጣ በትእምርተ መስቀል አምሳል ለብሼ ስለነበር ከድንጋዩ ላይ ስቀመጥ ቆብ የለኝም እንጂ አመክሮ ላይ ያለ መነኩሴ መሰልኩ። መመሳሰሌን ሳይ እዚያ መገኘቴ ብዙም አላሳቀቀኝም። ያው መሆን እንጂ ከባድ መምሰል ቀላል አይደል? እውነታው ግን ክርስቲያን በፍጹም ልባቸውና ነፍሳቸው ወደው በንጽሕና ሆነው መምጣቱን ከሚጠባበቁት ከነዚህ ጋር አብሮ ለመቆጠር ቀርቶ ለአፍታ እንኳን አብሮ ለመቀመጥ የማይገባኝ ነኝ። የምወደውን መምሰል እንጂ መሆን ያልቻልኩ፤ የማከብረውን መቅረብ እንጂ መንካት ያልተሳካልኝ የዚህ ዓለም ሰው ነኝ። የዚህ ዓለም ሰው ነኝ ስል ግን ዓለሙን ሁሉ በእጃቸው ያስገቡ ዓለምን ከሚገዙት ነኝ ማለቴም አይደለም። ከዚህኛውም ዓለም ቢሆን ከታች ነኝ። ከአዋቂዎች በታች፤ ከመሪዎች በታች፤ ከሃብታሞች በታች ሆኜ እነርሱ በቀደዱት ቦይ የምፈስ የራሴ ራዕይና ግብ ሳይኖረኝ ከኋላ እየተጎተትኩ የምከተል ነኝ።

የወደድኩትን የማልመርጥ፤ የመረጥኩትን የማላገኝ፤ የለፋሁበትን ሳይሆን የተከፈልኩትን የምወስድ፤ የሚበቃኝን ሳይሆን የተሰጠሁትን የምቀበል በሌሎች ዓለም የምኖር መፃተኛ ነኝ። ለሀገሬ ባዳ ለሌሎች ስደተኛ የሆንኩ ምስኪን ነኝ። በዚህ ዓለም ብኖርም የራሴን ዓለም

አልፈጠርኩም። የጋራ የሆነችውን ዓለም ለሌሎች አስረክቤ በድርጉ የምኖር መናኝ ነኝ። ‹መናኝ› ነኝ ስል ፈልጌ ንቂው አይደለም አቅቶኝ እንጂ። ሥርዓተ መንግሥቱ ባይስማማኝ፣ ማኅበረሰባዊ ሥርዓቱ ቢጎረብጠኝ፣ ነፃነቱ ቢገፋፍ ክብሬ ቢነካም፣ በቁመቴ ልክ ቀና ብዬ የማልሄድ ከጉበጡ አለቆቼ ኋላ ጎብጬ የምሄድ፣ በጩልሌዎች ዓለም የምኖር ከአቅመ ቢሶች ኋላ ተሰልፌ አቅሜን ያጣሁ ምስኪን ነኝ።

ከፊቱ የተቀመጡት አባቶች ግን እኔ የምወደውን ግን የተሸነፍኩበትን ዓለም ናቁት። እነዚህን ማዋረድ አይቻልም ክብርን አይፈልጉምና፣ እነዚህን ማራቆት አይቻልም በልብስ ማጌጥ አይሹምና፣ እነዚህን መቀማት አይቻልም ምንም የላቸውምና፣ መግደል አይቻልም ለዓለም ሙታን ናቸውና፣ ልታሸንፋቸው አትችልም ዓለሙን ካሸነፉ ቆይተዋልና። ‹ታዲያ ለምን በመካከላችን ይኖራሉ?› ብትል ለብሰን የሚበርደንን፣ በልተን የሚርበንን፣ ከብረን የተዋረድነዉን፣ ተምረን የደነቆርነውን፣ ሃብታም ሁነን ውስጣችን የደኸየውን፣ ተዋልደን የምንጋደለውን እድፋችንን እናስተውልባቸው ዘንድ እንደ መስታወት እንመለከትባቸው ዘንድ ለምስክርነት የሚኖሩ ናቸው።

እንደ ሁልጊዜው የሕይወት ዘመኔ እንዲህ በሐሳብ እየተንገላታሁ የተነበበውን ቅዱስ ቃል ሳልሰማ ንባቡ አልቆ በጸሎት ተዘጋ። ዛሬም በቅዱሱ ስፍራ አለሁ ግን የለሁም፣ በቅርብ አለሁ ግን እርቂያለሁ፣ ሲነበብ ሰምቻለሁ ምን እንደተባለ ግን አላዳመጥኩም፣ ከዛው ከቅዱሶቹ መሃል ነበርኩ ግን አልነበርኩም፣ አዎን ከእነርሱ ጋር ቆይቻለሁ ግን አብሬያቸው አልነበርኩም። እየኖሩ አለመኖር እጣ ፈንታዬ ሁኗልና።

ጸሎቱ አልቆ ሁሉም በየተራ በግምጃ የተጠቀለለውን ስንክሳር ከተሳለሙ በኋላ ከአባ ዘንድ በርከክ እያሉ የእግራቸውን ጫማ እየሳሙ፣ በመስቀል እየተባረኩ ወደ የበኣታቸው ሲያመሩ አንድ ሰው





ብቻ ከአባ ጎን ቆሟል። ማን መሆኑን አላጣሁትም ነበር።

ለመባረክ ወደ አባ ስጠጋ ሳብ አድርገው አቅፈው ግንባሬን ሳሙኝና ቀና ስል መስቀላቸውን ዘረጉልኝ። ተሳልሜ ሳበቃ፡-

“እንዴት አለህ የኔ ልጅ? በደኅና መጣህ?” አሉኝ።

“ደኅና፤ እምላክ ይመስገን” ብዬ ከጎናቸዉ ወደቆመው ሰው ሳማትር ተንደርድሮ መጥቶ አቀፈኝ።

ሲያቅፈኝ ሆድ ባሰኝና አለቀስኩ። እርሱ ወደ ምንኩስናው ዓለም ከገባ ወዲህ ሁልጊዜ ብቸኝነት ውስጤን እንደሟጠጠው ነው።

“ምነው ወንድም ሲሳይ ማልቀስ እኮ አይገባም” አለኝ።”

“ማነው እርሱ?” አሉ አባ ዮናታን ጣልቃ ገብተው። ታሪኩን በጥሞና እየተከታተሉኝ እንደሆነ ገባኝና፡-

“ቀድሞ ዶ/ር ክብረ በዓል ይባል የነበረ በኋላ መንኩሶ አባ መዐዛ ቅዱሳን ተብሎ ገዳም የገባ ባልንጀራዬና የልብ ወዳጅ የነበረ ሰው ነው። ” አልኳቸው።

“ግሩም!” አሉና “በል ቀጥል ታሪኩን” አሉ።

“እንባዬን ጠራርጌ “እንዴት ነህ? እንዴት ነዎት?” አልኩት ተምታታብኝ።

ፈገግ አለና “ደኅና ነኝ፤ ግዴለም አንተ በለኝ” አለኝ።

እዛ እንደማገኘው አውቄ ነበር የሄድኩት። ቀደም ብለው እኒህ አባት

‹ፆሙ ከመግባቱ በፊት አደራ እንዳትቀር› ብለው ልከውብኝ ስለነበር አመጣጤም በዚሁ መነሻነት ነው፡፡ ከመልእክቱ ውስጥ ‹የጸሎቱን መጽሐፍ ሌላ ሰው ይዞት ይመጣል› የሚል ነበረው፡፡ ‹ሌላ ሰው› የተባለው እርሱ ሊሆን እንደሚችል ሙሉ ዕምነት ነበረኝ፡፡

ራሴን እያሻሽ ስለቤተሰብ ስለሥራ ከጠያየቀኝ በኋላ ወደ አባ ዘወር ብሎ፡-

"እንግዲህ ወንድሜ ከመጣ ሥራውን እንጀምር እንጅ?" አላቸው፡፡

ፈገግ ብለው "ማለፊያ ነው" አሉና እጃቸውን ትከሻዬ ላይ ጭነው ከፍልፍሉ ቤተ ክርስቲያን የድንጋይ እጥር ወጥተን ቁልቁል የምሥራቁን አቅጣጫ ይዘው ሲወርዱ እኔም እርምጃዬን አስተካክዬ ተከተልኩ፡፡

"አባ መዝገበ ሥላሴ ደኅና ናቸው? ሂደህ ትጠይቃቸዋለህ አይደል?" አሉኝ፡፡

"ሥራ እየበዛብኝ ብዙ ጊዜም አልሄድኩ፤ ብቻ ደኅና ናቸው እከታተላለሁ" አልኳቸው፡፡

በልቤ ‹አሁን የእርሳቸው ደኅንነት ለእርስዎ፣ የእርስዎስ ደኅንነት ለእርሳቸው ጠፍቷችሁ ነው?› አልኩኝ፡፡ በአንድ መንፈስ ተሣሥረው በተለያዩ አካላት የሚኖሩ ብፁዓን እንደሆኑ ከተረዳሁ ቆይቻለሁና፡፡ ይሁን እንጂ የጥያቄው ዓላማ የእኔን ወረተኛነት ለማሳሰብ ይመስላል፡ ፡ በፊት የተሰወረ የመሰለኝን ምሥጢር ለማወቅ ስል ሂድ ቢሉኝም እንቢ ብዬ ከስራቸው አልጠፋም ያልኩት ሰውዬ አሁን ሁሉን ስረዳ መጥፋቴ ምን ይባላል?





"እንዲያው የኔ ልጅ ደግ አሳደረክም" አሉኝ፤ መልስ አልሰጠሁም፡፡

‹እኔ ምን ደግ ነገር አድርጌ አውቃለሁ? ደግ ነገር የምጠብቅ እንጅ› አልኩና በራሴ ላይ አጉረመረምኩ፡፡ አባ መዐዛ ቅዱሳን ከኋላ በቅርብ ርቀት ይከተሉናል፡፡

አባ ቀጠሉ፡-

"ተቆልፎ የኖረውን በር ዘው ብለህ ከፍተህ ስታበቃ ገርበብ አድርገህ መተው እኮ አይቻልም" አሉኝ፡፡ ረጋ ብለው ነው የሚናገሩት፡፡ ነገር ግን ንግግራቸው ቀገ፤ቃዛ ወላፈን እንደሆነ ልቤ ገብቶታል፡፡ ቁልቁለቱንም እየወረዱ ነው፤ ቀጠሉ፡-

"ጉጉትህ ሲያልቅ፣ ወረትህ ሲያልፍ፣ ምሥጢር የማወቅ እነፍናፊ ልብህ ቁም ነገር መሥራት ተሣነው እሳ?" ብለው ትንሽ ዝም ብለው ቆዩና፡-

"ቀደም ሲል ያዘዝንህን መፈፀምህ መልካም ነው፤ ግን ዋናው ተግባርህ አልተጀመረም፡፡ ቀጥፈህ ያመጣኻቸው ዕፆች ለጥበብ ይደርሱ ዘንድ፣ ለፈውስ ይበቁ ዘንድ የሚቀርህ አለ" አሉ ጠንከር ብለው፡፡

"ምንድነው የቀረኝ አባ?" አልኩኝ ፍላጐት በከዳው ድምፀት፡፡

"ግዴለም እርሱን እናስታውቅሃለን" አሉና አባ መዐዛ ቅዱሳንን ዘወር ብለው ሲያዩ እርሱም ፈጠን ብሎ በጐናቸው በኩል መጣ፡፡ ጠጋ ሲላቸው በጆሮው የሆነ ነገር ነገሩት፡፡ ምን እንደተባባሉ አልሰማሁም፡፡

እኔ ራሴ ምሬት ላይ ነበርኩ፡፡ ‹ወይ እንደኛዬን ለይቶልኝ ከእነርሱ ጋር አልሆንኩ፤ ከዓለሙም ከእነርሱም ዥዋዥዌ እያልኩ እንዴት እችላለሁ?› እያልኩ ገና የሚያዙኝን ሳልሰማ ሀሞቴ እየፈሰሰ ነበር፡፡"





# ምዕራፍ - ፯

"ቁልቁለቱን ወርደን ረባዳው ላይ ስንደርስ ከቤቶቹ መካከል ላይ ከሚገኝ ወደ አንድ ትልቅ የዋርካ ዛፍ አመራን፡፡ በጣም ግዙፍ ዋርካ ነው፡፡ ግንዱን የሁለት ሰው እቅፍ አይሞላውም፤ ቅርንጫፎቹ እስከ አባ ቤት ድረስ ተዘርግተዋል፡፡ በዛፉ ግንድ ዙሪያ ለመቀመጫ እንዲሆኑ አልፎ አልፎ የተደረደሩ ጠፍጣፋ ድንጋዮች አሉ። ወደ ዛፉ እየተጠጋን ስንመጣ አንዲት ሴት ኩርምት ብላ ካንደኛው ድንጋይ ላይ ተቀምጣለች፡፡ እረፋዱ ላይ መጥቼ ወደ ተራራው ጥግ ወዳለው

ፍልፍል ቤተ ክርስቲያን ሳመራ በዚህ በኩል ነበር እልፌ የሄድኩት።
ለሳስተዋልኳትም ነበር ማለት ነው።

አባ አካለ ወልድ ጠጋ አሉና የሆነ ስም ሲጠሩ ካቀረቀረችበት ፈገግ ለማለት እየሞከረች ቀና አለች። አባ መስቀላቸውን አሳለሟት። እንዲህ ያለ የክርስትናም ሆነ የዓለም ስም ሰምቼ አላውቅም። ‹ሚተራሊዮን› ብለው ነበር የጠሯት። በግርምት አተኩሬ አየኋት።

ያልተበጠረው ዞማ ፀጉሯ፣ ያልተከረከመው ለስላሳ ጥፍሯ፣ የገረጣው ፊቷ፣ የተዛነፈው ቅርጿ፣ የተቀዳደደው ድሪቶ ልብሷ ውበቷን አደበዘዘው እንጂ አላጠፋውም ነበር። ሥጋ አጥቶ በገጠጠው ቅንድቧ ስር ዋሻ ውስጥ ያለ እንቁ መስለው የሚንከባለሉት ርግብ ዐይኖቿን፣ በደረቀው ከንፈሯ የተሸሸጉት የወተት አረፋ ጥርሶቿን እና በደመና ፊቷ የተጋረደው ቁጥብ ፈገግታዋን ላስተዋለው ግን ግሩም ቁንጅናዋ በአቧራ እንደተሸፈነ ወርቅ ለመደበቁ እርግጠኛ ይሆናል። ከጉስቁልናዋና ከለበሰችው አዳፋ ልብስ ጋር አብረው የማይሄዱ የሚመስሉ ውብ ቅርጽ ያላቸውን እድሜ ጠገብ ጌጦች ባንገቷ ዙሪያ አስራለች።

ሁኔታዋ አንጀቴን ስፍስፍ አደረገውና፡-

"ማናት አባ? ምን ሆና ነው?" አልኩኝ አንድ ጊዜ አባ አካለ ወልድን ሌላ ጊዜ አባ መዐዛን እየተመለከትኩ።

"ታሪኳ ረጅም ነው" አሉና ትክዝ ብለው ቆይተው፡-

"እየውልህ ከረጅም ዘመን ጀምሮ ደም ይፈሳታል። የሚፈሳት ደም ክብሯን፣ ፀጋዋን፣ ሀብቷን፣ አካሏንም ጭምር እንዲህ እንደምታየው አጎሳቁሎታል" አሉ በጥልቅ ትካዜ። ቀጠሉና፡-





"የዚህ ሁሉ መከራ ምንጭ መንታ ችግር ነው። በየዘመኑ ያገባቻቸው ክፉና ስግብግብ ባሎቿ እንዲሁም የባሎቿን ራስ ወዳድነትና ጭካኔ የወረሱት አመለ ኘርንጉርጉር ልጆቿ ናቸው። ጀግናና ፈሪ፣ ኀበዝና ሰነፍ፣ ለጋስና ቀማኛ፣ አማኝና ከሀዲ የወለደችበትን ማሕፀኗን፣ ያልበላ አንጀቷን ተደግፈው ሲራገጡ የኖሩት ልጆቿ ችግሯን ካለማወቃቸው የተነሣ ይኸው ለእርሷ ጤና ማጣት ለራሳቸው ደግሞ መከራን ጋበዙ። ረኀብ፣ እርዛት፣ ጦርነትና ስደት ዕጣ ፈንታቸው ሆነ። እርሷም የወላድ መካን የሆነች ያክል ለሕመሟ ማስታገሻ ለችግሯ መፍቻ ከልጆቿ ዘንድ እስካሁን አላገኘችም።" ብለው ዝም ብለው ቆዩና ድንገት ጥንካሬና ኃይል በተሞላ ድምፀት፡-

"ነገር ግን ከአካሏ መራቆት፣ ከገጠማት መከራ በላይ የመንፈሷ ልዕልና፣ የነፍሷ ንጽሕና ከፍ ያለ ነው። ሐዘኗ እንደ ኮረት ቢጠጥርም ተስፋዋ ግን እንደቋጥኝ የገዘፈ ነው" አሉና

"ካዘቅቱ ትወጣ ዘንድ የተጣባት ክፉ መንፈስ ይለቃት ዘንድ በሠንሠለት ታሥራም ቢሆን ፈውስን ታልማለች" አሉ።

ጭንቀቴ ትንፋሼን የዘጋው መሰለኝና እንደምንም ታግዬ፡-

"አባ ምነው እናንተስ መፈወስ አቃታችሁ?" አልኳቸውና ወደ አባ መዐዛ ቅዱሳን ዙሬ በዐይኔና በእጄ ለምን አያድኗትም አይነት ጥያቄ አቀረብኩላት። በተለመደው ፈገግታው ዝም ብሎ ተመለከተኝ።

አባ ቀጠሉ "አየህ የእኔ ልጅ፤ ሳንፈልግ ወይም ሳንችል ቀርተን አይደለም" አሉና ትኩር ብለው ተመለከቷት። እርሷም በደከመ ፈገግታዋ ቀና ብላ ቡዝዝ ባሉ ዐይኖቿ ተመለከተቻቸው። የሆነ የሚግባቡበት ሥውር ቋንቋ ያለ ይመስላል።

"ታዲያ ችግሩ ምንድን ነው? ለምን አትፈውሷትም?" አልኩ። የተለመደው እኔነቴ ገነፈለ ማለት ነው። ያለይሉኝታ መጠየቅ፣ የተሠወረ የመሰለኝን ለማውጣት መታተት፣ መልስ ለማግኘት መጓጓት። ጠባዬን ጠንቅቆ የሚያውቀው አባ መዐዛ ቅዱሳን ዛሬም አለመለወጤ ደንቆት በአግራሞት ፈገግታ ያየኛል ።

"አየህ የእኔ ልጅ የዚች ሴት ችግር ሕመም ብቻ አይደለም። ሕመሟም ቢሆን ታክሞ ቢድንም የሚያገረሽ ነው" አሉ።

"ታዲያ ተስፋዋ ምንድን ነው?" አልኩ እልህ በተሞላበት ሐዘኔታ። በዚህ ሁኔታም የሚንጸባረቀው የእነ አባ ትዕግስት በፊትም እንደሚያበሳጩኝ አሁንም ሊያበሳጩኝ ጀምሯል።

"ከሕመሟ፣ ከችግሯም፣ ከሁሉም መከራዋ የምትላቀቀው እንደገና ስትወለድ ነው" አሉ። ‹የቆላው ሙቀት እራሴን አሳተኝ ወይስ እኚህ ትልቅ አባት ምንድን ነው የሚሉኝ› አልኩና ለራሴ:-

"‹እንደገና ስትወለድ ነው› ነው ያሉኝ?" አልኳቸው በግርታ ፊታቸውን እያየሁ።

"አዎን የእኔ ልጅ! እንደገና ትወለድ ዘንድ ይገባታል" አሉኝና "አንተንም የጠራንህ ለዚህ ተግባር እንድታግዘን ነው" ብለው ሁኔታዬን ለማጥናት ይሆናል ትኩር ብለው ያዩኝ ጀመር።

‹አያሾፉብኝ ነው!› አልኩና ለራሴ ‹ምነው ሸዋ! ስንት ስራ እያለኝ ለዚህ ፌዝ ነው እንዴ የተጠራሁት› ብዬ ውስጤ ሲመናጨቅ አባ መዐዛ ቅዱሳን ጣልቃ ገብቶ:-





"ግዴለም ቀስ ብለህ ትረዳዋለህ" አለኝ።

"ምኑን ነው ቀስ ብዬ የምረዳው?" አልኩት።

"ያንተ ነገር ሁልጊዜ ችኮላ" አለና ትከሻዬን መታ መታ አደረገው።

"እንደገና ትወለዳለች ስላልኩኝ ግራ አይግባህ የእኔ ልጅ፣ ወደ እናቷ ማሕፀን ተመልሳ እንደገና ትወለዳለች ማለቴ አይደለም" አሉ።

"ታዲያ እንዴት ነው ነገሩ?" አልኩኝ።

"ግዴለም የእኔ ልጅ ማታ ላይ ጊዜ ወስደን ቀስ ብለን እንወያያለን" ብለው "በሉማ ደግፋችሁ ወደቤት አስገቧት፣ ትረፍ" አሉን እኔንና አባ መዐዛ ቅዱሳን በእጃቸው ወደ እርሷ እያመለከቱ።

"ሚተራሊዮን በይ ተነሽ" አሏት። ለእኔ እንግዳ የሆነውን ስሟን ድጋሜ ሲጠሩት መገረሜ አልቀረም።

እኔና አባ መዐዛ ቅዱሳን ደግፈናት ወደ አባ ቤት ስናመራ ከአካሏ ጉስቁልና፣ ከሚፈሳት ደም እንዲሁም ከነተበው ልብሷ ተነሥቼ ጠረኗ መጥፎ ይሆናል ብዬ ገምቼ ነበር። ግን መሣሣቴን ያወኩት ጠጋ ብዬ ስደግፋት ነበር። እጣን፣ ከርቤ፣ አደስ፣ ናትራ፣ አርቲ፣ ሮዳስ፣ የዶንጋና የጽጌረዳ አበባ አንድ ላይ ቢቀመሙ እንኳን እንዲህ ያለ ውብ መዐዛ አይሰጡም። በጣም ከመደነቄ የተነሣ "ምን ተኣምር ነው" አልኩኝ ሳላስበው።

አባ መዐዛ ቅዱሳን ገብቶታል፣ ነገሬን ሁሉ ያውቀዋልና።



Scanned with CamScanner

"አቤት ወንድም ሲሳይ! በቃ በአሳምሽን (Assumption) እየኖርክ እኮ ተቸገርክ" አለኝ።

"እንግሊዝኛው አልጠፋህም?" አልኩት የቀድሞው መተራረባችን ትዝ ብሎኝ።

"ገዳም የገባሁት ከዕውቀት ነፃ ለመሆን መሰለህ እንዴ?" አለኝ እየሳቀ።

"አይ እንግሊዝኛ መናገር የምትተው መስሎኝ ነበር" አልኩ እኔም እየሳኩ።

"ባይሆን እንግሊዝነትን እንጂ እንግሊዝኛን አልተውም" አለኝ። መልዕክቱ ገባኝና እንደገና ሳቅኩ።

የመሸከም ያክል ደግፈናት ቀስ አድርገን ከአባ ቤት አስገብተን ከአንድ ቁርበት ከተነጠፈበት ከላዩ ላይ ደግሞ የጨርቅ ድብዳብ የተደረገበት መደብ ላይ አስቀመጥናት። ጥቅልል ብላ ልትተኛ ስትል አባ አካለ ወልድ፦

"ቆይ እንጂ ሚተራሊዮን ትንሽ እህል ቅመሺ" አሉና ዳቤ ቆርሰው ከነሐስ ማንቆርቆሪያ ምን መጠጥ እንደሆነ ያላወኩትን ቀድተው በጽዋ አቀረቡላት። እንደምንም ቀና አለችና መጀመሪያ ከሚጠጣው ቀጥሎ ከዳቤው ቆረስ አድርጋ ቀማምሳ ተወችው። ወዲያው ጥቅልል ብላ ተኛች።

ሁኔታዋ ሁሉ ሁለመናዬን ረበሸው። የለበስኩትን ፎጣ ከላዩ ላይ አወለኩና ወስጄ ልደርብላት ስል "ተባረክ ልጄ፤ ግን ምንም አያግዛትም" አሉ አባ አካለ ወልድ።





ገራ ገብቶኝ አንድ ጥግ ሄጄ ቁጭ አልኩ። ለእኛም ዳቤ ተሠጠን እርሱን በልተን ስናበቃ አባ በሉ እናንተ ተነጋገሩ መጣሁ ብለው ወጥተው ሄዱ።

አባ መብዓ ቅዱሳን ጋር መካነ ሕርመት በተአምራዊ ትዕይንት ተገናኝተን ከተለያዩን በኋላ በአካለ ሥጋ ተገናኝተን አናውቅም። በተለያዩ መልኩ ግን አድራሻ የሌላቸው መልዕክቶች ስለሚደርሱኝ ግንኙነታችን አልተቋረጠም። እንዲያውም አንድ ጊዜ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከሚገኘው የከፋ መካነ ሕይወት (kaffa Biosphere) የሆነ ዕፀዋት ፍሬ፣ ከአፈር ናሙና ጋር እንዳመጣለትና አንድ የመነፅር ማይክሮስኮፕ እንድልክለት ጠይቆኝ ልኬለታለሁ። መድረሱንም አረጋግጦልኛል። ይሁን እንጂ ያለበትን ስፍራ ለማወቅም ሆነ በአካል ለማግኘት ሞክሬ አላውቅም። ድሮም በዓለም እያለ የሐሳቡን ጥልቀት የማልደርስበትን ሰው አሁን ሰይቶለት ወደ መንፈሳዊው ዓለም ጠቅሎ ሲገባ ባለሁበት ቆሜ የቀረሁት ሰው ለምን ወደ ኋላ እንትትተዋለሁ ብዬ ትቸዋለሁ። ባገኘው ‹ከከፍታ ማውረድ፣ ከንጽሕና ማጉደፍ እንጂ ምን እጨምርለታለሁ? ከእንግዲህ እኔ ለእርሱ ፈተና እንጂ እቻ ጓደኛ ልሆን አልችልም› ብዬ ትቸው ነበር።

"ያለህበትን አድራሻ ለማፈላለግም ሆነ ለማግኘት አልሞከርኩም" አልኩት።

"ለምን?" አለኝ ፈገግ ብሎ።

"ያው መረበሽና ሐሳብህን መበተን አልፈለኩም። ስትፈልግ አንተ ታገኘኛለህ ብዬ" አልኩት።

"መልካም ሐሳብ ነው፤ ለእኔ ግን ሁሌም አብረኸኝ ያለህ ያክል ይሰማኝ ነበር" አለኝ።

ይህን ሲነግረኝ ልቤ ሐሤት አደረገች። ‹በዚህ ሞራል ጠንካራና መንፈሳዊ ሰው ሕሊና ውስጥ ሁሌ ከታሰብኩ ፈጣሪም አይተውኝም ማለት ነው› አልኩ ለራሴ።

"እኔ ግን ባስብኩህ ቁጥር ብቸኝነትና ተስፋ መቁረጥ ይሰማኝ ነበር" አልኩት።

"እንዴ፤ ለምን?" አለኝ።

"የሆነ ቦታ ላይ ተቋርጦ የቀረ ከመንጋው ተለይቶ የጠፋ እንስሣ ታውቃለህ? በቃ እንደዚያ ይሰማኝ ነበር" አልኩት።

"እንደዚያማ ሊሰማህ አይገባም ነበር። እንዲያውም መካነ-ሕርመት ያልኩህን አታስታውስም?"

" ምን ነበር ያልከኝ?" አልኩት

"‹እኔና አንተ በአንድ ቀንበር የምንጠመድ የቀኝና የግራ በሬዎች ነን› ነበር ያልኩህ" አለኝ

"አዎን አስታወስኩ" አልኩት።

"በእኔ በኩል ያለው ሐሳብ አሁንም ያው ነው" አለኝና ስለቤተሰቤ፣ ስለምርምር ሥራዎቼ በዝርዝር እየጠየቀኝ ሁሉም ነገር መልካም እንደሆነ ስመልስ ቆይቼ፡-





"በግሌ ደኅና ነኝ ብቻ..." ብዬ ዝም ስል

"ብቻ ምን?" አለኝ

"የሀገራችን ሁኔታ በጣም ይረብሻል። የፖለቲከኞቻችን ነገረ ሥራ ሁሉ ከተስፋ ይልቅ የመከራ ነጋሪት የሚጎስም ነው" አልኩት።

"ንቀህ ማለፍ ነው እንጂ" አለኝ።

"ይለለቻል አባ መዐዛ! የምወዳትን፣ የምመካባትን፣ ሀገሬ ክብሬ፣ የምላትን ኢትዮጵያን ትፈርሳለች፣ ትበታተናለች እያሉ ያሟርታሉ። እንደ ቁራ ተሰብስበው መበተኗ አይቀሬ መሆኑን ይለፋሉ። በቃ ትውልዱን ተስፋ ያስቆርጡታል" አልኩ እየተንገሸገሽኩ።

"አየህ ወንድም ሲሳይ!" አለና ዝም ብሎ ለጥቂት ደቂቃዎች ቆየና፡-

"አይምሰልህ! ይህ ከ60ዎቹ ጀምሮ በኢትዮጵያ የሥልጣን ማግኛ ዘዴ ሆኗል። ኢትዮጵያዊ ለሀገሩ ቀናዒ እንደሆነ ሀገሩን ከሃይማኖቱ ለይቶ የማያይ ልበ ስሱ፣ አንጀተ ርኅሩህ መሆኑን ስለሚያውቁ በሚወደው ነገር እያስፈራሩ ዝም እንዲል አድርገው ወደ ሥልጣን መንጠላጠል የታወቀ ዘዴ ሆኗል። በሀገሪቱ አንድ ማዕዘን ላይ ያለን ነገድ ሰበብ አድርገው ‹እገነጥላለሁ እበታትናለሁ› ሲሉ ‹በቃ ይሁንልህ አንተ እንደወደድክ ይደረግ› ተብሎ ማዕከላዊውን ስልጣን እንዲሰጠው አንተም ተረገጥኩ ተበደልኩ ብለህ እንዳትናገር ነው። እንደ ፖለቲከኞቻችን ከሆነ ኢትዮጵያ የጨው ክምር ነች። እንኳን ጥንታዊ ሀገር ጢስ የጠገበ ቤት እንኳን ይፈርሳል ሲባል ይጨንቃል። ኢትዮጵያ በሕሊናችን ውስጥ በፅኑ ተስላ በፍቅር ታትማ እንዳትኖር በጥፍራቸው እየቧጨሩ ሕሊናችንን ያደሙታል። በውኑ ለኢትዮጵያዊ



Scanned with CamScanner

ከኢትዮጵያ በላይ ምን ተስፋ አለው? እነርሱ ግን ያንተን ኢትዮጵያ ቀምተው የራሣቸውን ኢትዮጵያ ሲሰጡህ ያንገላቱሃል። በመጨረሻ ጥንታዊቷንና ታሪካዊቷን ኢትዮጵያን ከአዕምሮህ ይፍቁና ፍሻሌ የሆነችውን በውራጅ አስተሳሰብ የተገነባችውን 'አዲሲቷን ኢትዮጵያን' አዕምሮህ ላይ ስለው ተስፋ ቆርጠህ አንገትህን ደፍተህ እንድትኖር ወይም እንድትሰደድ ሲገፉህ እየሞከሩ መሆኑን ልብ በል" አለ በተለመደው የረጋና በራስ መተማመን የተላበሰ ንግግሩ።

ቀጠለ፡-

"ከሥልጣን እስኪወጡ ድረስ ኢትዮጵያ እንደምትፈርስ ይነግሩናል። ሥልጣን ላይ ሲወጡ ደግሞ ከመቅጽበት አንድነቷ የተጠበቀ መሠረቷ የፀና አድርገው ያቀርባሉ። እስከዛሬ ያየናቸው ጎጠኞችና ኮራጆች በሙሉ እነርሱ ወደ ሥልጣን ከመምጣታቸው በፊት ኢትዮጵያ ተስፋ የሌላት የጎስቋላ  ምድር ባለቤት እንደሆነች፣ ሕዝቧም የተለያየና የማይተማመን እንደሆነ ይነግሩሃል። አንተን እንደዚህ ተስፋ አስቆርጠው ስትሸመደመድላቸው ሥልጣን ላይ ድንገት ፊጥ ይሉና ከመቅፅበት ‹ኢትዮጵያ በተስፋ የተሞላች፣ በዕድገት ጎዳና እየተራመደች ያለች፣ ጭቆና ቀርቶ ነፃነትና ዲሞክራሲ የሰፈነባት ህዝቧም በአንድነት የሚዘምር› አድርገው ያቀርቡልሃል። ኢትዮጵያ እነርሱ ሥልጣን ላይ እስካሉ ድረስ ምቹ የተረጋጋች ሀገር፣ ሲወርዱ አብራቸው የምትወርድ የእንቧይ ካብ ያደርጓታል። ከዚህ የማስፈራራት ፖለቲካ፣ ከዚህ እኔ ከሞትኩ ሠርዶ አይብቀል አስተሳሰብ ወጥቶ የተስፋና የቅንነት ፖለቲካ ይመጣል። እስከዚያ ‹እንቁራሪቶቹ ሲጮሁ ባሕሩ ሁሉ የእነርሱ ብቻ ይመስላቸዋል› እንደተባለ ከእነርሱ የሚገዘፍ፣ የሚበልጥ፣ የሰከነ መረዋ ድምፅ ሲመጣ ቃጭል ድምፃቸውን ይዘው ለመጨረሻ ጊዜ ከላይዋ ላይ እንደ ትቢያ ይራገፋሉ። ይህንን እመን" አለኝ።





ልፍለፍሉ ልቤ ቀና ያለ መሰለኝና "እንደ ቃልህ ይሁን" አልኩት። ለደቂቃዎች ዝም ብለን ቆየን።

ቆይቼ፡-

"አንተስ እንዴት ነህ?" አልኩት።

"እኔማ ያው ካለሁበት ገዳም ካሉ አባቶችና ወንድሞች እምነታቸውንና ቡራኬያቸውን እስካገኝ በትጋት አገልግሎት መስጠት ነበረብኝ። አሁን እምነታቸውን ስለጣሉብኝ በልቤ ውስጥ ያለውን ሸክም አውጥቼ ለመናገር ዕድል እያገኘሁ ነው" አለኝ።

"ከቶ አንተን ሲሰማ የማይፈቅድ ማን ይኖራል?" አልኩት። እንዲህ ያለ ጠልፎ የሚጥል ቃል እንደማይወድ ባውቅም አምልጦኝ ግን ከልቤ ነበር የተናገርኩት።

"አይይ! እርሱን ተወው" አለና

"እናም ሐሳቤን በየዘርፉ በጽሑፍ አስፍሬ ለገዳሙ ትልልቅ አባቶች አቅርቤላቸው ወደውታል።  ሐሳቤ ወደ ተግባር እንዲቀየር ቡራኬ ሠጥተውኝ ይህንኑ የማደራጀት ሥራ እየሠራሁ ነው" አለኝ ፍክት ብሎ።

"ግሩም" አልኩና "ዋናው ሐሳብህ ግን ምንድን ነው?" አልኩት

"ሁለንተናዊ ሥነ ሥርዓትና ዘላቂ ልማት የተሟላለት ገዳም መገንባት ነው" አለኝ

"ምን ማለት ነው? ሥነ-ሥርዓት ያለው ገዳም አይደል እንዴ?

ምኑን ነው የምትገነባው?" አልኩኝ። "ልክ ነህ! በሀገራችን ከብዙ ሰፍራዎች ከሚታየው መረን የለቀቀ ሕይወት አንጻር ገዳሞቻችን ደኅና ናቸው ሊባሉ ይችላሉ። ነገር ግን እነርሱም ቢሆን ከጥንት ስሪታቸው እየተንሸራተቱ የዓለሙ ገንዘብ መውደድና ክብር መፈለግ ተፅዕኖ እያሳደረባቸው ነው። በጎ ተፅዕኖ አድራሽ ሳይሆኑ ክፉ ተፅዕኖ ተቀባይ እየሆኑ ነው። እናም ታሪካቸው፣ መንፈሳዊ እሴታቸውና ትውፊታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሾልኮ የገባው ተፅዕኖ መጥራት ይኖርበታል። ሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓት፣ ገዳማዊ ሥነ-ሥርዓት እና ሀገራዊ ሥነ-ሥርዓት ወደ ቀደመ ክብሩ መመለስ አለበት። ልማት ያልኩህ ደግሞ መንፈሳዊ፣ አዕምሯዊ፣ እንዲሁም አካላዊ (ፊዚካላዊ) እና አካባቢያዊ ጥበብና ልማት መጠንሰሺያና ማስጀመሪያ ስፍራ መሆን ይችሉ ዘንድ መሥራት ነው" አለኝ።

"ሐሳብህ ድንቅ ነው፤ ግን ፈታኝ እኮ ነው" አልኩት።

"ፈታኝ ካልሆነ ምኑን አዲስ ሐሳብ አመጣሁ እላለሁ?" አለኝና

"ደግሞ በጎ ሐሳብ ከተጀመረ ወደፊት መግፋቱ አይቀርም። በዚህ መልክ ጀምረው ብዙ የተጓዙ አባቶችና እናቶች ያሉበት ገዳም እኮ አለ" አለኝ።

"ለምሣሌ የት?" አልኩት በጥርጣሬ።

"ከዚህ በፊት እኮ አንድ መልዕክት ልኬልህ ነበር" አለኝ

"ምን ዓይነት መልዕክት" ስለው "ከመኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን ምዕራፍ 7፡-11-12 ያለውን ጠቅሼ ልኬልህ ነበር። መቼም አጅሬ አነፍንፎ መልዕክቱን ተረድቶ ወደ ሥፍራው ይሄዳል ብዬ ነበር" አለኝ።





"ሆሆ ምሥጢር ማነፍነፍ መዘዙ ብዙ መሆኑን ስለተረዳሁ ወደመተው እየተቃረብኩ ነው። ነገር ግን እንዲህ ዓይነት መልዕክት እንደላክልኝ አላስታውስም" አልኩት።

"ለዚያ ይሆናል እንጅ አጅሬ" አለና ፈገግ አለ።

"የሆነስ ሆነና ከመኃለየ መኃልይ ዘሰለሞን ላይ የላከው መልዕክት ምን የሚል ነበር" አልኩ።

"ወደዚያው እንድሄድ አንድ አባት ሠጥተውኝ ነው። እንዲህ የሚል ነበር፡-

*‹የወንዙን ዳር ልምላሜ አይ ዘንድ፣ ወይኑ አብቦ ሮማኑም አፍርቶ እንደሆነ እመለከት ዘንድ፣ ወደ ገውዝ ገነት ወረድሁ።ሳላውቅ ነፍሴ በከበረው ሰረገላ ላይ አስቀመጠችኝ›"*

"ታዲያ ይሄ እንዴት አድራሻን ያመለክታል?" አልኩት

"እርሳቸው ሲሰጡኝ ‹ገውዝ ገነት› የሚለውን ‹አጥበራ ገነት› ብለው ነበር" አለ።

" እርሱም ቢሆን ግልፅ አይደለም" አልኩት።

"አንተ ደግሞ አጥበራ እኮ የተከዜ የጥንት ስሙ ነው" ሲል

"አሃ! በተከዜ ወንዝ ዳርቻ ያለ ገዳምን ለማመላከት ነው?" ስለው

አንገቱን በአዎንታ ነቀነቀና፡-

"ከገዳሙ ደርሰህ ከወንዙ ዳርቻ አፋፍ ላይ ቁመህ ገዳሙን ስትመለከትና በውስጡ የተሠካውን ሥነ-ሥርዓትና የልማት መረዳት ስታይ

የመልዕክቱ ምሥጢር ይገባሃል" አለኝ።

ጥሚገርም ነው። ተክዜ ገዳም ሲባል እሰማለሁ፣ ግን አንተ በገለፅኸው መንገድ ተረድቼው አላውቅም" ስለው።

"አየህ ህልሜ እውን ሊሆን እንደሚችል ያረጋገጥኩበት ሥፍራ ነው ተክዜ ምዕራፈ ቅዱሳን ኪዳነ ምሕረት ወሐዋርያው ክርስቶስ አንድነት ገዳም" ሲለኝ አድናቆቱ ከፊቱ አልጠፋም ነበር።

ይህን እየተነጋገርን እያለ ተጣጥፋ የተኛችው ሕመምተኛ በሚቃትት ትንፋሽ ለመገላበጥ ስትሞክር የሁለታችንም ስሜት ወደ እርሷ ሆነ። ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ሁኔታዋ ያሳደረብኝን ሰቀቀን ረስቼው የነበረ ሲሆን እንደገና ተቀሰቀሰብኝ።

"እኔ እምለው ቅድም አባ ልጆች አሏት ብለው አልነበረም? እንዴት አንድ ሰው እንኳ ቀርቦ የሚያስታምማት ታጣለች?" አልኩ በመገረምና በሐዘኔታ።

"አይ አንተ" አለና "ልጆቿ ራሳቸው ሕመምተኞች ሆነዋል። እናም ሁሉም የግሉን ሕመም እንጅ አንዱ የአንዱን ሕመምና ችግር አያይም። ሁሉም ጥጉን ይዞ ግማሹ የዳነውን ቁስሉን እየቀረፋ፣ ግማሹ አዲሱን እያመገለ በየቤቱ ሙሾ ያወርዳል። ‹ተበዳይ ነኝ የሚል እንጅ በዳይ ነኝ› የሚል የለም። ሁሉም ‹ተገፋሁ የሚል እንጅ ገፋሁ› የሚል የለም። አንዳንዶቹም የአንዱ ቁስል ከሌላው እንደሚበልጥ ትንታኔ በመስጠት ተጠምደዋል። ሁሉም ሕመምተኛ፣ ሁሉም አልቃሽ በመሆኑ ማን ከራሱ አልፎ ይችን ምስኪን እናቱን ያስታውሳታል" አለኝ።





አሻግሬ ሁኔታዋን ሳያት ዐይኖቼ በእምባ ተሞሉና እንባዬን በእጄ እየጠረኩና እየተነፋረቅኩ፦

"እንዴት አንድ እንኳ ደሕና ኗሪ፣ ልብ የገዛ ልጅ ታጣለች?" አልኩ በሲቃ።

"እውነትክን ነው። የሞላለት፣ ዕድል የቀናው፣ እውቀት የዘለቀው ቢኖር እንኳን ድምፁን ከፍ አድርጎ ‹እናታችንን እናድን› ቢል የሚፈጠርበትን ጫጫታና ትችት በመፍራት ያገኘውን ይዞ እንደ ቀንድ አውጣ ሼል ውስጥ ተደብቆ ወይ እንደ ኤሊ ከለበሰው ድንጋይ ውስጥ አንገቱን ቀብሮ ከፉዎች ቸር፣ ቀማኞች ለጋስ፣ ደንቆሮዎች ሊቅ፣ ነፍሰ ገዳዮች ነፍስ አዳኝ እስኪሆኑ ያልተቆጠረ ዘመን ያልተያዘ ሱባዔ ይጠብቃል" አለኝ።

"ታዲያ ተስፋዋስ ምንድን ነው? ረዳቷስ ከየት ይመጣል?" አልኩኝ እንደገና የገነፈለውን እንባዬን ባይበሉባዬ እየጠረኩ።

"ተስፋዋ ከፈጣሪዋ፣ ካንተም፣ ከእኔም፣ ከሌሎችም ነው" አለኝ ትከሻዬን መታ መታ እያደረገ።

"እኔ ደግሞ ምን አቅም አለኝ?" አልኩ።

"አየህ ወንድም ሲሳይ! በእንዲህ ያለ የፈተና ወቅት መፍትሄ አቅም አይደለም፣ በጎነትና ቅንነት እንጅ! ራስክን መጠየቅ ያለብህ ይህችን ሴት ለማዳን ‹አቅም አለኝ ወይ ሳይሆን በጎነት አለኝ ወይ?› ነው" ብሎ አለኝም የለኝምም ለማለት የሚከብድ የሞራል ጥያቄ አምጥቶ መፈናፈኛ አሳጣኝና ዝም አልኩ።



Scanned with CamScanner

ቆይቼ "መሆኑ ‹ሚተራሊዮን› ማለት ምን ማለት ነው?" አልኩት።

"ቃሉ የግሪክ ወይም ዕርዕ ይመስላል። አባ አካለ ወልድ ዕርና ዕብራይስጥ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ያወጡላት ምሥጢራዊ ስም ይሆናል። ለማንኛውም አባ ማታ ሁሉንም ነገር ያብራሩልናል" አለና ወደ ውጭ ወጣ። የሠርክ ጸሎት ስለደረሰ እንደሆነ ገብቶኛል። እኔ ግን የእርሱን መውጣት ተከትዬ ከደረቀው መደብ ላይ ጉኔን እያንቋቋሁ ጋደም አልኩኝ።

ሐሳቤ ሁሉ በአሻጋሪ ከደረቀው መደብ ላይ ኩርምት ብላ በስቃይ ውስጥ ስላለችው ምስኪን ሴት ነበር። ‹ማን ናት? እንዴት ማዳን አይቻልም? እነዚህ አባቶች ምን እያሰቡ ይሆን? የእኔ እገዛ ምን ይሆን? ለምን አልጠይቃትም?› አልኩና ሳንሰላስል የለበስኩትን ፎጣ ቅድም ላልብሳት ስል አባ እንደከለከሉኝ ትዝ አለኝና ምናልባት አይፈቀድልኝ ይሆናል ብዬ ተውኩት።"

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)





# ምዕራፍ - ፲

አባ አካለ ወልድ ምሽቱ ለዐይን ያዝ ሲደርግ አባ መዐዛ ቅዱሳንን አስከትለው፦

"ትቻችሁ በዚያው ጠፋሁ አይደል? እንዴት ናችሁ?" እያሉ ሲገቡ ከነበርኩበት ግማሽ ሰመመን ነቃሁና ተነስቼ በደመነፍስ ቁጭ አልኩ። ‹ገዳም ድረስ መጥቶ እንኳ ለጸሎት የማይተጋ ምን አይነት ግንድ ነገር ነው› ያሉኝ መሰለኝ።

"ደህና ነን፣ ምንም አይደል" አልኩ።



Scanned with CamScanner

በአንድ ጥግ ወዳለው የኋላ በር ሄዱና ከፍተው ከውጭ ታጥቦ የተሰጣ የሚመስል የጨርቅ ድልዳል ይዘው መጡና፡-

“ሚተራሊዮን እስኪ ተነሽ ድብዳቡን ልቀይርልሽ” ሲሏት ተጠቅልላ ከተኛችበት ቀስ ብላ ተነሣችና ለመቀበል እጇን ዘረጋች።

“ግዴለም ትንሽ ቀስ ብለሽ ሸርተት በይ፤ እኔ አንሥቼ እቀይረዋለሁ” አሏት።

“ምነው አባ የኔን ደም እርስዎ ሊጠርጉ?” አለች ድክም ባለ ድምፅ። ከመጣሁ ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ስትናገር መስማቴ ነበር። እንደዚህ ያለ የደከመ ግን ቃናው የሚጥም የሴት ድምፅ ሰምቼ ማወቄን ተጠራጠርኩ። የገነት ወፍ የተናገረች መሰለኝ። እኔ የድምጿን ሁኔታ ሳደንቅ ድንገት አባ መዐዛ ቅዱሳን ፈንጠር ብሎ ሄደና፡-

“አባ እኔ እያለሁ፤ የኔ እናት አንቺም አትሳቀቂ” አለና ለማንሣት ሲሞክር በፍጥነት ተነሥቼ ሄድኩና እኔ በሁለት እጆቼ ከጀርባዋ ሆኜ እቅፍ አድርጌ ሳነሣት እርሱ ድብዳቡን ከመደቡ ጐትቶ ወለሉ ላይ ሲጥል አባ ቀልጠፍ ብለው የተቀየረውን ድብዳብ አመቻችተው አነጠፉላት። ወዲያው ቀስ አድርጌ አስተኛኋት። አባ መዐዛ ከመሬት የወደቀውን ድብዳብ ሲያነሣ በደም ተነከሯል። ‹ይህ ሁሉ ደም እየፈሰሳት እንዴት በሕይወት መቆየት ቻለች? ስቃዩንስ እንደምን ቻለችው?› አልኩ በሐዘን በተወጋው ልቤ።

ድብዳቡ ሲነሣ ደሙ ወለሉ ላይ ሲንጠባጠብ መሳቀቋን ያዩት አባ፡-

“አይዞሽ ሰው ሁሉ እኮ ከሥጋና ከደም የተሠራ ነው” አሉ።





በቤቱ ጀርባ በተቀመጠው የእንጨት ገበታ በውኃ እንዲያጥበው አባ መዐዛን ለማሳየት ወደ ውጭ ወጡ። እኔም ተከትዬ ወጣሁና ለአባ መዐዛ ውኃ እየጨመርኩለት የተቀየረውን ድብዳብ ሲያጥብ፡-

“ለዛሬው ነው እንጂ ነገ ወደ እናቶች ልከናት እነርሱ በወጉ ይንከባከቧታል፤ ከዚህ አናሳቅቃትም። ዛሬም እዚህ ያመጣናት አንተ መከራዋንና ስቃይዋን እንድታይና እንድታዝንላት ብለን ነው” አሉኝ ወደ እኔ እየተመለከቱ።

መርግ የወደቀብኝ ያክል ደነዘዝኩ። ‹ምነው እንዲህ ስቃይዋን የሚያሳዩኝ? እንዴት ያለ ልበ ደንዳና አድርገው ቢገምቱኝ ነው?› አልኩ ለራሴ።

ድልዳሉ ታጥቦ ከተሠጣ በኋላ ተመልሰን እቤት እንደገባን አባ እጃቸውን ታጥበው በጨርቅ ተሸፍና የተቀመጠችውን የኒሐስ ኩስኩስት አነሡና በፅዋ ላይ ቀድተው፡-

“ሚተራሊዮን! እስኪ ተነሽ ዳቤውስ መቼም አይበላሽም ባይሆን ይህን ተጐንጪ” ብለው እንደቀኑ ሰጧት። ‹እሺ› ብላ ተቀብላ መጠጣት ስትጀምር ‹ጉርጉጭ… ጉርጉጭ…› ሲል ይሰማል በደረቀው ጉሮሮዋ አልፎ ሲወርድ።

አባ ተመለሱና ዳቤ ቆርሰው ለእኔ ደግሞ ሰጡኝ። እጅ ነስቼ ተቀበልኩና መብላት ጀመርኩ። ራት መሆኑ ነው። እርሳቸውና አባ መዐዛ ቅዱሳን ቀን ከቀመሱ ድጋሚ እንደማያስቡ ስለማውቅ ብዙ አልገረመኝም።

ቀት ጊዜውን ጨርሶ ለምሽቱ አስረከቧል። አባ አንድ ጥግ ላይ በሸክላ ከተሞላው ዘይት ላይ የተንከረውን ፈትል ለኮሱና መጠነኛ ብርሃን ቤቱን ሞላው። ጧፍ ለኮሱና አንድ ተቆልፎ የተቀመጠ ሣጥን ከፍተው በግምጃ የተጠቀለለ ከብራና የተሠራ መጽሐፍ አውጥተው ሲገልጡ ሲሉ አባ መዐዛ ቅዱሳን ቀልጠፍ ብሎ ጧፉን ተቀበላቸውና ያበራላቸው ጀመር።

መጽሐፉን ገለጥ ገለጥ አደረጉና የሚፈልጉትን ገፅ ያገኙ ሲመስል፡-

"ና ወደ ዚህ የኔ ልጅ" አሉኝ ከማዶ የተቀመጥኩትን እኔን።

ከአባ አካለ ወልድ ጋር የተዋወቅነው መካነ ሕርመት በአጭር ጊዜ ግንኙነት ሲሆን እሱም ዶ/ር ከብረ በዓል ሥርዓተ ምንኩስናን ሲፈጽምለት ለሠርጉ እንዳትቀሩ እየተባሉ ከተጠሩት አረጋውያን አባቶች አንዱ ሆነው መጥተው በነበረበት አጋጣሚ ነበር። ከዚያ ወዲህ አንድ ጊዜ ተገናኝተናል። እንደ ሌሎች የገዳም አባቶች ሁሉ ብዙ የማይናገሩ፣ ፈገግታ ከፊታቸው የማይጠፋ፣ ረጅም ጥላ ያለ ፂም፣ ቁመታቸው አጭር ሊባሉ የሚችሉ ደቃቃ ሰውነት ያላቸው ናቸው። በልጅነታቸው ዕውቀትን ፍለጋ ከትውልድ መንደራቸው ደጋ ተንቤን ተነሥተው ንብ ልዩ ልዩ አበቦችን እንደምትቀስም በኢትዮጵያ ከሚገኙ ጉባኤ ቤቶች እየተዘዋወሩ የአብነት ትምህርታቸውን አደላድለዋል። በኋላም ወደ ግሪክ አቅንተው ከሥነ-መለኮት ኮሌጆች የዘለቀ ጥንትቅ ያለ ትምህርት ያላቸው ናቸው። በኢየሩሳሌም ገዳማት በርካታ ዘመናቸውን በብሕትውና ያሳለፉ በመሆናቸው ዕርዕና እብራይስጥን አቀላጥፈው ይናገራሉ። ከማንበብ የማይለዩ ንባብ ምግብና መጠጥ የሆነላቸው በላኤ መጻሕፍት ናቸው። ቤታቸውን የሞሉት መጽሐፍትም ለዚህ ምስክር ናቸው።





‹ቅድም እንደገና ስለመወለድ ስነግርህ ትንሽ ግር ብሎህ ነበር" ሲሉ በዚያው ቅፅበት "እ... እህ..." ብላ ለመገላበጥ ስትሞክር የሥቃይ ድምፅ አሰማች። ስቃይዋ ከታመመችው ከእርሷ አልፎ የሚሰማትን ሁሉ ያንሰፈስፋል። የፈሰሰውን ደሟን ያዩ ሟሙታ የምታልቅ ውኃ ውስጥ የገባ አሞሌን ያስባል። ሁኔታዋ በእጅጉ ስላስጨነቀኝ ሀተታው ቀርቶ ‹ምናለ የሚያደርጉትን አድርገው በፈወሷት› አልኩ በልቤ። እነዚህን አባቶች ካወኩበት ጊዜ ጀምሮ የኔ ችኩልነትና የእነርሱ ትዕግስት የሰማይና የምድር ያክል ስለሚራራቅ ጨንራዬ እንደተሳጠ ነው።

"እንደምትሰማት ስቃይዋ ከባድ ነው፤ የዘመን ጥርቅም ዘርፈ ብዙ ነው። አንዱን የአካል ክፍሏን ብንፈውስ ሌላው ይታመማል። ደሟን ከመፍሰስ ብናቆመው እንኳ የታጠፈው አንጀቷ፣ በበደል ያረረው ቆሽቷ፣ በግፍ የሚደማው ልቧ፣ በሽፍጥ የቆሰለው ሕሊናዋ እንዲህ በቀላሉ አይድንም። ሕመሟ ጥልቅ ነው፤ በሽታዋ ንብርብር ነው።" አሉና በከባዱ ተንፍሰው "ያቆሰሏት ብዙ ናቸው። ባሎቿ፣ ልጆቿ፣ የሩቅም የቅርብም ጎረቤቶቿ ለእርሷ የሚያዝኑላት አልነበረም። ባሎቿ ከላይ ሲመነሽሯት፣ ልጆቿ ከውስጥ ሲያንገላቷት፣ የዕብድ ገላጋይ ጉረቤቶቿ ለምትወገርበት ድንጋይ፣ ለምትቆስልበት ጦር ያቀብላሉ" አሉ።

"ግን ምን አደረገች?" አልኩ እንባ እየተናነቀኝ።

"ምንም!" አሉ አባ። "ወልዳ መገኘቷ፣ ለምልማ መታየቷ፣ እኔን ራሴን ሁኚ ልኑር ማለቷ ነው እንጂ። ከሰው አትድረስ፣ ሰው አትንካ፣ ትዳሯን አከባሪ፣ ፈጣሪዋን ፈሪ፣ እንግዳ ተቀባይ ከመሆኗ ውጭ ባለ ብዙ ልሳን ባለ ብዙ መልክ ልጆችን መውለዷ ጸጋ መሆኑ ቀርቶ

ፈተና ሆነባት እንጂ በደልስ አልተገኘባትም" አሉና ዐይናቸውን እርሷ ላይ ተክለው፦

"እየሀ የእኔ ልጅ! ዛሬ እንዲህ ተጣጥፋ መተኛቷን ተጎሳቁላ መገኘቷን አትይ። እንዲህም ሆና መዳኗ ሞት የሚሆንባቸው፣ መጠንከሯ ድካም የሚያመጣባቸው፣ መበልጸጓ የሚያደኸያቸው፣ መከበሯ የሚያዋርዳቸው፣ ውበቷ ጥላሸት የሚቀባቸው የሚመስላቸው፣ አብሮ መኖር እቻ ሆኖ መታዬት የሚያስፈራቸው የቅርብም የሩቅም ጠላቶች አሏት። እነህ ጠላቶቿ የሰለቧቸውና ያደነዘዟቸው ልጆች ደግሞ አሏት።" አሉ

"ምነው ሁሉን የሚያውቅ፣ ሁሉን ቻይ አምላክ ዝም አለ?" አልኩኝ በምሬት።

"የለም የለም፤ ዝም አላለም" አሉና "ብቻ ልጆቿ ሁሉንም ተረድተው ወደ ልባቸው እስኪመለሱ የፈጣሪ ትዕግስት ብዙ ነው" ሲሉ።

"ምነው ጥሬው እስኪበስል የበሰለው እኮ ያራል?" አልኩኝ።

"አበጀህ የኔ ልጅ" አሉና "ለዚህ ነው እንደገና መወለድ ይገባታል፤ የምትወለድበት ቀንም ደርሷል ያልኩህ" አሉ።

ቀን በድንግዝግዝ ያለፍኩት ሐሳብ እንደገና መጣ ማለት ነው። ‹የመረዳቴ ጊዜ አሁን ነው› አልኩና፦

"እንደገና መወለድ ሲሉ አልገባኝም። እንዴት ነው የሚሆነው" አልኩኝ።

"እንደገና መወለድ  ሲባል ወደ እናት ማሕፀን ተመልሶ ገብቶ ድጋሚ





መወለድ ማለት አይደለም" ሲሉ

ቀበል አደረኩና "ታዲያ እንዴት ነው ነገሩ?" አልኩ ግራ ገብቶኝ።

"ከውኃና ከመንፈስ እንደገና መወለድ አለባት ነው የምልህ" ሲሉ

"እ... እንደዚያ ነው እንዴ! ትጠመቅ ማለትዎ ነው?" አልኩኝ።

አባ መዐዛ ቅዱሳን ጣልቃ ገባና "አይ ወንድም ሲሳይ! እንዲያው ረጋ ብትል ምን አለበት። ቅድም አከበድከው አሁን ደግሞ አቀለልከው። ቅድም ያልተረዳኸው ድፍን ቅል ነበር፤ አሁን ደግሞ ሁሉን የምታውቀው የእጅህ መዳፍ አስመሰልከው እኮ" አለኝ።

‹እኔ ምን እንደሚያንቀዠቅዠኝ ምን አውቃለሁ! ምናለ እኔንም ዳግም እንድወለድ ቢያደርጉ› አልኩ በልቤ።

በአንድ ወቅት ዶ/ር ጆኒን የተባለች የግሪክ ኦርቶዶክስ ሥነ-መለኮት ሊቅ ሴት ‹ስለማወቅና እውቀት› ስታስተምር፡

> "አንድ ልጅ ብቻ ነው ያለኝ፤ ተጨማሪ ልጆች እንዲኖሩኝ እፈልግ ነበር። በጸሎት ብዙ ጊዜ አምላክን ከጠየኩ በኋላ ምናልባት የሕክምና እርዳታ ባገኝ ብዬ ወደ አንድ የማሕፀን ስፔሻሊስት ሄድኩ። ሐኪሙም ችግሬን ካደመጠ በኋላ ‹አራት መሠረታዊ ምክንያቶች አሉ› ብሎ አራቱን ከዘረዘረልኝ በኋላ ‹ገብቶኛል› አልኩት። ቆየና ‹አራቱን ዋና ዋና ምክንያቶች ነው እስካሁን የነገርኩሽ። በእያንዳንዳቸው ስር ደግሞ አራትና አምስት ንዑሳን ምክንያቶች አሉ› አለኝ። ወዲያው የተረዳሁት የመሰለኝ ችግሬ ጫፉን እንኳን ባግባቡ አለመረዳቴን ተገነዘብኩ። ዕውቀት ትዕግስት ይሻል። እውቀት የመጀመሪያው ጫፉ አንጅ ሌላኛው ጫፉ

የማይደረስበት የትየለሌ ርዝመት ያለው ገመድ ነው" ብላ ነበር።

እኔ ግን ይህን ሁሉ ትምህርትም አዳምጬ ዛሬም ግልብ ነኝ።

አባ የኔን ነገር ችላ ብለው ገለጻቸውን ቀጠሉ፡-

"እርሷም ልጆቿም እንደገና ከቅዱሱ ውኃ ከቅዱሱ መንፈስ ሊወለዱ ይገባል!" ሲሉ ቀበል አደረኩና

"ምነው አባ መፍትሄው ይሄ ከሆነ ውኃ ችግረ እንዴ? ምነው በአትራቢያ አፍላጋትና ምንጮች ሞልተው የለም ወይ?" አልኩኝ።

አባ መዐዛ ቅዱሳን ቀበል አድርገው "ምነው ወንድም ሲሳይ ረጋ ብትልና የሚሉትን ብታዳምጥ?" አሉኝ።

ኩምሽሽ አልኩና ‹ በቃ ምን ላድርግ? ከሰው አፍ ሞጭልፎ መፍትሄ አመንጭ መስሎ መታዬት፣ የሰውን ጅምር ሐሳብ ወስዶ የራስ አድርጉ ማቅረብ ጠባዬ ሆነ፣ ምን አባቴ ላድርግ?› ብዬ አጉተመተምኩ ለራሴ።

"ግዮለም መዳኗን የመሻት ጉጉቱ ነው፣ ጭንቀቷ ጩኸቶት፣ ስቃይዋ ስቅይቶት ነው" አሉና "አየህ የኔ ልጅ! እውነትክን ነው ውኃ አልቸገረ፴ አገሩ የውኃ አገር ነው። ከምንጭ እስከ ሐይቅ፣ ከጅረት እስከ ወንዝ የታደለ ነው። ወዲህ አጥበራ ወዲያ ዐባይና ጣና፣ በስተዚህ አዋሽና ሸበሌ ዝቅ ብሎ ኦሞ ጊቤ፣ ገናሌና ዳዋ፣ ባሮና አኮቦ፣ አብያታና ጫሞ ውኃ መቼ ቸግሯቸው። ግና..." ብለው ዝም ሲሉ "ግና ምን?" አልኩኝ።





"የእነዚህ ሁሉ ውኃ ራሱ እንደገና ከውኃ መወለድ አለበት!" አሉኝ ፈርጠም ብለው።

የባሰ ተምታታብኝና "አባ ምኑም የሚገባኝ አልሆነም" ብዬ ኩርምት አልኩ።

"አየህ! እነዚህ ሁሉ የሀገራችን ውኃዎች በማሕፀን እንዳለ ፅንስ ናቸው። ገና አልተወለዱም የሚወለዱበት ቀን ለመድረሱ ግን ምልክቱ ታይቷል"። አሉና "በማሕፀን ያለ ፅንስ ተስፋ ነው። የልጅ አበባ፣ ጧሪ ቀባሪ፣ ደጋፊ ጋሻ መከታ ይሆን ዘንድ መወለድ አለበት፤ እስከዚያ ቁጥሩ እንደ ሰው ቢሆንም ተስፋ ነው። በዚች ሀገር ያልተፈቱ ሕልሞች፣ ያልተፈጸሙ ራዕዮች፣ ያልተወለዱ ፅንሶች ብዙ ናቸው" አሉ።

"ታዲያ እርሷንም የወንዙንም የሐይቁንም ውኃ እንደገና የሚወልድ ውኃ እንደምን ያለ ነው?" አልኩኝ።

"አሁን ወደ ነጥቡ መጣህ" አለኝ አባ መዐዛ ቅዱሳን።

"ውኃ ትልቅ ምሥጢር ነው የኔ ልጅ! ውኃ የእግዚአብሔርን መንፈስ የሚሸከም፣ ሰማይና ምድርን የሚያገናኝ፣ ፍጥረታትን የሚያስተሳስር ምሥጢራዊ ፍጥረት ነው" አሉና አባ የያዙትን መጽሐፍ የንባብ መነጽራቸውን አድርገው በትኩረት መመልከት ጀመሩ።

እንደገና መወለድ የሚለውን ሃሳብ ሳውጠነጥን ትልቅ ጥያቄ በአእምሮዬ ተፈጠረብኝና፡-

"እ...አባ" አልኩ



Scanned with CamScanner

"እቤት ልጅ" አሉ ቀና ብለው

"እንደገና ስትወለድ ታሪኳ ማንነቷ አይጠፋም እንዴ?"

"ደግ አስተዋልክ ልጄ! ነገር ግን እንደገና ትወለድ እንጅ፤ ድጋሚ ትፈጠር አልተባለችም። ድጋሚ በመወለድ በጥንተ ተፈጥሮ የነበረ ክብርና ጸጋ፣ ጥበብና ኃይል እንዲሁም ማንነት አይቀየርም። ከአምላክ ያገኘችው በጎ ነገር ሁሉ አብሯት ዳግም ይወለዳል። የሚቀረው በዘመን ክፋት ከኋላ የመጣው ውርደትና ድቀት፣ ሕመምና መከራ፤ ድንቁርናና ስንፍና፣ መለያየትና መጠፋፋቱ ነው" አሉና "እንደገና መወለዷ ወደ ቀደመ ንጽሕናዋና ጤንነቷ መመለስ ነው። ወደ ቀደመ ክብሯ መመለስ ነው። ወደ ቀደመ ክብሯ መመለስ ሲባል ዓለም ሁሉ በዋሻ ሲኖር እልፍኝ አዳራሽ አሠርታ እንግዳ የተቀበለችበት፣ አሕዛብ ወንዝ ተራራ ሲያመልክ ቤተ መቅደስ ከዐለት አስፈልፍላ አንድ አምላክ ወዳመለከችበት ዘመን፣ ከደጇ ከቀዬዋ ስለልጆቿ ጥበበኛነት ምስክር ይሆን ዘንድ የድንጋይ አምድ ወዳቆመችበት ማንነቷ መመለስ ነው!" ብለው ወደ ንባባቸው ተመለሱ።

ትንሽ እንደቆዩ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ማንበብ ጀመሩ። የሚያነቡት በግእዝ የተጻፈ ነገር ነው። ብቻ አልፎ አልፎ ከግእዝ ልሳን ወጣ ያለ የዕብራይስጥ የሚመስሉ ቃላት አሉበት።

ትንሽ አንብበው ቀና ብለው አባ መዐዛ ቅዱሳንን ሲያዩት እርሱም የሆነ ሐሳብ ይጨምርበታል።

"እንዲህ ለማለት ይሆን?" ይላል። አባም በሐሳቡ ይስማማሉ። የሚነጋገሩትን ነገርም ሆነ የሚያነቡትን ለመረዳት ፈጽሞ ከአቅሜ በላይ ሆነ።





አባ መዐዛ ቅዱሳን ከመባሉ በፊት የማውቀው ጓደኛዬ ዶ/ር ክብረ በዓል በአንድ ሙያ የተሰለፍን፣ በብዙ ነገር የምንግባባ የነበርን ቢሆንም አሁን ግን እርቆኝ እንደሄደ ገባኝ። እኔ ባሰሁበት እንደ ሮመር ሰዓት ቆሜ መቅረቴ ብቻ ሳይሆን እርሱ ወደ ጥንቱ ዕውቀት ዘልቆ የገባበት ፍጥነት በእጅጉ አስደምሞኝ አንገቱን ደፍቼ አቀረቀርኩ።"



# ምዕራፍ - ፱

*ሬየማየ ገበ ቅዱስ እምግዮን በኩር ይትቀዳሕ*

*ወኪያሁ በዕብነ ኩሕል ይነጥርዎ*

*ወዕብነ ኩሕል እምኢትዮጵያ ዘተወልዱ በኀበ እስራኤል ይትረከብ* የሚለውን አንብበው ሲጨርሱ፡-

"እንግዲህ ሁለት ነገር ነው የምንሻው። አንዱ ‹ማየ ገበ ቅዱስ› ሲሆን ይኸውም በኩረ ግዮን ውስጥ እንደሚገኝ ያመለክታል" ሲሉ





ግውነት ነው። ብቻ በኩረ ግዮን ያለው የት እንደሆነ ለመረዳት ተጨማሪ መረጃ ያስፈልጋል" ሲል

"እርሱን በሌላኛው ክፍል ታገኘዋለህ" አሉ መጽሐፉን እያመለከቱ።

"መልካም ነው" አለ።

"ሁለተኛው ደግሞ የኩሕል ድንጋይ ነው። ይሄ እንግዲህ ማየ ገቦውን ማለዘቢያና ማንጠሪያ ነው" ሲሉ አባ መዐዛ ቀበል አድርጎ "እርሱም ከእስራኤል ዘንድ ከኢትዮጵያ ከተወለዱት የሚገኝ ነው ማለቱ ይሆን?" አለ።

"እንግዲህ እርሱን እናንተ ፍቱት። ብቻ ትጉሃንና ቅኑዓን ሁኑ። እርፍ ይዞ ወደ ኋላ የሚመለከት የለምና።" አሉና

"የዚች መከረኛ ሴት እንደገና መወለድ በእናንተ ትከሻ ወድቋል። እኛ ጥበቡን ብናውቅም መውጣትና መውረድ አንችልም። ፈጣሪ ቀናውን መንገድ ይመራችኋል፤ ስለዚህም እኛ እንጸልያለን።" አሉና መጽሐፉን ለአባ መዐዛ ቅዱሳን ሰጥተው ብቻቸውን ወደ ሚጸልዩበት ትንሽዬ በዓታቸው ለመሄድ ተነሡ።

ትንሽ ከተራመዱ በኋላ መለስ ብለው "እነዚህ ሁለቱ ነገሮች እንደገና እንድትወለድ ከማድረግ በላይ የወደፊት ኑሮዋንና ትዳሯን ለማደላደልና ለመፍጠር ሌላ ትልቅ ተግባር አላቸው" አሉና ወደ አባ መዐዛ ጠጋ ብለው፡-

"ይህን በጎ ተግባር አለመፈጸም ከጸጋ መጉደል ብቻ ሳይሆን የበደል ተካፋይም የሚያደርግ መሆኑን ወንድምከን በደንብ አስገንዝበው!" ብለው ወጥተው ሄዱ።

ይህን ሲናገሩ ወገብ ዛላዬ ከሁለት የተከፈለ መሠለኝ። ‹ወንድምክን እስተንዘበው› ያሉት እኔን መሆኑ ግልጽ ነበር። ሰልችቼ ልተወው አገደምችል ገምተዋል።

"እንዴት ያለ ዕዳ ነው የሚያሸክሙኝ? ለምን ፈቃዱና ፍላጐቱስ አይጠየቅም?" አልኩ በከፊሉ ጨለማ አባ መዐዛ ላይ አፍጥጬ።

"ወንድም ሲሳይ! ሲጀመር እነዚህ አባቶች ዘንድ አንተ መጣህ እንጅ እነርሱ አልመጡብህም፤ ልትመረምራቸው ስትሻ እነርሱ ቀድመው መረመሩህ፤ ልታጠምዳቸው ስትፈልግ እነርሱ አጠመዱህ" አሉ።

"ያ እኮ አንዴ ሆነ! ድፍረቱን አምኜ ትዕዛዛቸውን በብዙ ድካምና ትጋት ፈጸምኩ አለቀ!" አልኩኝ።

"አየህ! አንድ ሰው የዓሣ ማጥመጃው መንጠ ላይ ቁራጭ ሥጋ ሰክቶ ወደ ባሕር በረጅም ገመድ አሥሮ ይወረውረዋል። ዓሣው ሥጋ አገኘሁ ብሎ መንጠው ላይ ይሠካል። ልብ በል! መንጠው ላይ የሚሠካው ሥጋ ፈልጎ እራሱ ነው። መንጠው ካፉ ውስጥ ከተሰነቀረ በኋላ ፈቃዱ ከውኃ ዳር ቁጭ ያለው ሰው ነው። ገመዱን ሲስበው ተከትሎ ከውኃው መውጣት ዕጣ ፈንታው ነው። የአንተም እንደዚያው ነው። " ሲል

"ምን ማለት ነው ይሄ?" አልኩ በስጨት ብዬ።

"ባይሆን በዓሣውና በአንተ መካከል ያለው ልዩነት የዓሣው ዕጣ ፈንታ ተጠብሶ መበላት ሲሆን የአንተ ግን ወደ ታላቅ በረከት መድረስ ነው" ሲል።





"ታዲያ በፍላጐቴ ሲሆን እንጅ በተጽዕኖ ነው እንዴ?" ብዬ ሳጉረመርም ያቺ መከረኛ ሴት ‹አ...አ...ኧህ › ብላ በሲቃ ስትገላበጥ አመፃዬን የሰማች መሰለኝና ስቅጥጥ አልኝ።

"ፈጣሪ ያለህ እንዴት ያለሁት ነውረኛ ነኝ! ይህ ሁሉ ነገር ለእርሷ መዳን መሆኑን እንዴት አላሰብኩም?"

‹እኔ፤ መብቴ፤ ክብሬ፤ ጥቅሜ› የሚለው የራስ ወዳድነት በሽታ ምን ያክል እንደሚያደነዝዝ፤ ከስብዕናና ከሞራል እንደሚያጉድል አጥንቴ ድረስ ዘልቆ ተሠማኝ።

የአባ መዐዛ ቅዱሳንን እጆች ይገፍ "ይቅርታ ወንድሜና አባቴ! ከራሴ ጋር እየታገልኩ የምኖር የማዕበል ዋናተኛ እንደሆንኩ ታውቃለህ" አልኩትና አነባሁ።

"አይዞህ ወንድም ሲሳይ! ትወድቃለህ እንጂ አትሰበርም፤ ትስታለህ እንጂ አትክድም። ይሄ ደግሞ የሰው ልጅ ጠባይ ነው" አሉና "ይልቅስ ወደ ጉዳያችን እንግባ። ነገ በጠዋት ከዚህ መሄድ ይኖርብሃል ጊዜ የለንም" አሉ።

"እሽ ብቻ ነገሮቹ በደንብ አልገቡኝም ተጨማሪ ነገር ብትገልጽልኝ" አልኩት።

"የመጀመሪያው ነገር ‹ማየ ገቦ ቅዱስ› የሚለው ሲሆን ከጐን የሚፈስ ቅዱስ ውኃ እንደማለት ነው። መነሻው የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ስቅለት ነው። ጌታችን በተሰቀለ ጊዜ ጎኑን ለንጊኖስ የተባለ ሰው ሲወጋው ደምና ውኃ ተቀላቅሎ ፈሰሰ። ይህ ውኃ ‹ማየ ገቦ› ይባላል። አሁን የተጠቀሰው ግን ከማን ጐን የሚፈስ ውኃ እንደሆነ እኔንም

አልገባኝም፡፡ ምሥጢሩን ከመጽሐፉ ላይ የበለጠ መረዳት ይኖርብሻል፡፡ የሆነ ሆኖ ይህ ‹ማዬ ገቦ› ከግዮን ወንዝ ሥር የሚፈልቅ ነው ይላል፡፡ ‹ግዮን ያለው ማነን ነው? የት ነው ያለው?› የሚለው ለጊዜው አልገባኝም፡፡ ይህንን እኔ እያጠናሁት እዚሁ ልቆይ ለአሁኑ ሁለተኛው ላይ እናተኩር" አለ፡፡

"እሽ ይሁን! ሁለተኛው ደግሞ ምንድን ነው?" አልኩት

"ሁለተኛው ደግሞ ‹ማየ ገቦው› ከተገኘ በኋላ ውኃውን የሚያለዝበውና ቆይቶ ደግሞ ወደሚፈለገው ኃይል የሚቀይረው ማንጠሪያው ነው፡፡ ይኸውም ኩሕል የተባለ ድንጋይ ነው" ሲል

"ማለዘብ ማለት እንዴት ነው?" ስለው

"እኔም ገና በውል አልተረዳሁትም፡፡ ግምቴ ግን ‹ማየ ገቦ› የተባለው የተለየ መለኮታዊ ኃይል ሳይኖረው አይቀርም፡፡ እናም ዝም ብሎ እንደምንጭ ውኃ የሚቀዳ ሳይሆን ይችላል ወይም እንደገና ለመውሰድ መለወጥ ይኖርበት ይሆናል፡፡ እኛ ብቻ የታዘዝነውን መፈጸም ነው" አለ፡፡

"ይሁን! ታዲያ እርሱን የት ነው የምናገኘው?" አልኩ፡፡

"የሚገኘው እስራኤል ነው፡፡ እንደ ገባኝ ከሆነ እስራኤል ብሎ ውሉ ደ ኢትዮጵያ ያለው እስራኤል የሚገኙትን ቤተ-እስራኤላውያን ወይም ኢትዮጵያዊ አይሁዳውያንን ሊሆን ይችላል፡፡" አለኝ

"እና እስራኤል ሀገር መሄድ ግድ ሊሆን ነው ማለት ነው?" አልኩት፡፡





"አዎን ወንድም ሲሳይ! እስራኤል በፍጥነት መሄድ ይኖርብሃል" አለኝ፡፡

ግራ በመጋባት ሳስብ ቆየሁና፡-

"እሺ መሄዱንስ ልሂድ፡፡ ከሄድኩ በኋላ ከማን ብዬ ነው እምፈልገው?" ስለው

"የዚች ሴት አምላክ መንገዱን ይመራሃል! ምልክቱን ያሳቀምጥልሃል! አሁን ባለንበት ሁኔታ ከማመን ውጭ ሌላ ነገር የለንም" አለኝ፡፡

"እኔ እኮ እምነቱ ደካማ ነው" ስለው

"የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል እምነት እንኳን ብዙ ነው" አለኝ፡፡

"እንዴት ያለ ፈተና ውስጥ ነው የገባሁት" ብዬ በጨለማው ጭንቅላቴን ጭምድድ አድርጌ ስይዝ ከእኛ ባሻገር የተኛችው ሴት አሁንም ‹ሕ...እ..› የሚለውን የተለመደ ስቃይዋን የሚያስታውስ ድምፅ አሰምታ ተገላበጠች፡፡ የስቃይዋን ድምፅ ስሰማ ‹እንኳን እስራኤል የዓለም ጫፍ፣ የውቅያኖስ ጥልቅ በርባሮስም ቢሆን መሄድ አለብኝ› የሚል ስሜት ውስጤን ሲወረው ተሰማኝ፡፡

"እኔ እምልህ! እስራኤል ሄድኩ እንበል፤ የሆነ ሰው ዘንድ ደረስኩ እንበል፤ ይኼ ነው ቢለኝ እንዴት አውቀዋለሁ?" አልኩት

"እኔም እርሱን እያሰብኩ ነበር፡፡ ግን ጓደኛዬና ወንድሜ ነቢልን አግኝተህ ብትጠይቀው እርሱ አይጠፋውም፡፡ ከእርሱ በላይ ሊቅ ማን አለ?" አለኝ፡፡

"እው ዜል የማያውቀው ሰለት፣ ድንጋይና ማዕድን የታሰገ" አልኩና ተጸናናሁ።

ዝል እረፍ በል። በጠዋት ተነሥተን በየፊናችን መስማራት ይኖርብናል፡ አልና እርሱ ለጸሎት ሲቆም እኔ ተደሳድዩ ወደ እንቅልፍ ዓለም ገባሁ።

በማግስቱ በጠዋት ተነሥተን ከአባ መዐዛ ቅዱሳን ጋር በየፊናችን ለመሰማራት ከመሲያየታችን በፊት እርሱን ስፈልግ የምንገናኝበትን ምሥጢራዊ መስመር ነግሮኝ ጉዞዬን ለመጀመር ወደ ውጭ ሳመራ ስለ "ሚተራሊዮንን ለምን አልሰናበታትም?" አልኩ።

"ማናገር አይፈቀድልኝ ይሆን? ለምን ፎጣዬን ሳለብሳት ስል ከለከሉኝ? የፈለገው ይሁን ደኅና ሁኚ ሳልላት አልሄድም" አልኩና ወደተኛንበት መደብ ጠጋ ብዬ ከወገቤ ጎንበስ ስል ያ ልዩ መዐዛዋ አወደኝ።

አቤት የፈጣሪ ምሥጢር አልኩና፦

"ሚተራሊዮን! ፈጣሪ ምሕረቱን ይላክልሽ ደኅና ሁኚ!" አልኳት። አንድ ጊዜ ብቻ የሰማሁትን ድምጿን ምናለ ብትደግመው እያልኩ ሳንሰላስል ከተኛንበት ትንሽ ቀና ብላ ስቃይ በሚታገለው ፊቷ ፈገግ ብላ አየችኝ። ሰውነቴ ከላይ እስከ ታች ትርትር ያለ መሰለኝ። ያንጸት ሕመምተኛ ፊት ፈገግታ ሳይሆን የመብረቅ ብልጭታ ያየሁ ነው መሰለኝ። መቆየት አልቻልኩም። ውስጤ "ቶሎ ቶሎ ሂድ ብረር" አለኝና ዐይኖቼ በእንባ እንደተሞሉ ወጥቼ ሄድኩ።

ባሕርዳር ከመድረሴ በፊት ወደ አዲስ አበባ በሚቀጥለው ቀን ለመጓዝ ትኬት አመቻቸሁ። የአዲስ አበባ ጉዞዬ ለሁለት ጉዳይ ነበር። አንደኛው ወደ እስራኤል ለመጓዝ የሚያስፈልገኝን የቪዛና ሌሎች





ጉድመ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ዝሌን አግኝቼ ስለ "ዕዝነ ኩሕሉ" የበለጠ ለመረዳት ነበር።

አባ የናታን በመገረምና በጥልቅ ስሜት ሆነው ሲያደምጡኝ ቆይተው፦

"ዝሌ ደግሞ ማነው?" አሉ ።

"የእኔና የአባ መዐዛ ቅዱሳን የልብ ወዳጅ ነው" አልኩ እየተከታተሉኝ በመሆኑ ደስ ብሎኝ።

ይሁን እንጅ ከዝሌ ጋር ያደረኩትን ውይይት ለአባ የናታን መናገር አስፈላጊ መሆኑ ባይታየኝም ውይይታችንን በአእምሮዬ እያሰላሰልኩ ሳላስበው በሃሳብ ነጎድኩ።



# ምዕራፍ - I

ነቢልን የተዋወኩት በቀድሞው ዶ/ር ክብረ በዓል የአሁኑ አባ መዐዛ ቅዱሳን አማካኝነት ነበር። ነቢል ጅማ ተወልዶ ያደገ የመጀመሪያ ዲግሪውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በጅኦሎጂ ከዚያ ማስተርሱን ደግሞ በሃይድሮ ጅኦሎጂ የተካነ ብርቱ ሰው ነው። ነቢል የእስልምና እምነት ተከታይ ሲሆን ሃይማኖቱ በሚያዘው መሠረት በእውነትና በቅንነት የሚኖር ሰው ነው። ከዶ/ር ክብረ በዓል ጋር የተዋወቁት ሁለቱም ለድህረ ምረቃ ትምህርት ውጭ ተጉዘው በአንድ ዩኒቨርሲቲ በመገናኘታቸው ነበር።





ለመጀመሪያ ጊዜ ለእኔ ያስተዋወቀኝ አዲስ አበባ ላይ ነበር። እኔና ዶ/ር ክብረ በዓል ውጭ ለኮንፈረንስ ቆይተን ስንመለስ አንድ ሰው ላስተዋውቅህ ብሎ ደውሎለት መጥቶ ነው። በጥልቅ የሚዋደዱ ጓደኛሞች መሆናቸውን ለመረዳት ጊዜ አልፈጀብኝም ነበር። እንዲያውም በወቅቱ ዶ/ር ክብረ በዓል እንዲህ የሚወድ እኔን ብቻ ይመስለኝ ስለነበር ቅናት ቢጤ ወረፍ አድርጎኝ ነበር።

ነቢል የአፍ መፍቻ ቋንቋው አማርኛ ስላልሆነ አማርኛ ሲናገር ቃናው እንደ ሕጻን ልጅ የሆነ የደስ ደስ አለው። የነቢልንና ክብረ በዓልን እውነተኛ ጓደኝነት ሳስብ የሚገርመኝ፤ አንዱ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሌላኛው ሰሜን ተወልደው፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የተለያየ፤ አንደኛው የእስልምና ሌላኛው የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ሁለቱም ለእምነታቸው ቀናዒ ሃይማኖታቸውን በጥብቅ ዲሲፕሊን የሚከተሉ መሆናቸው ነው። በሙያቸው አንደኛው ሃይድሮ ጅኦሎጂስት (Hydrogcologist) ሌላኛው ኢኮሎጂስት (Ecologist) ቢሆንም ሁለቱም በሙያቸው ጥልቅ ዕውቀት ያላቸው የእውነት ምሁራን ናቸው። ከነዚህ ሰዎች ጋር ስለሳይንስ ጉዳይ ተነሥቶ ከተወራ ድንገት የተገኘ አድማጭ ወዲያውኑ ድንቁርናው ቁልጭ ብሎ ይታየዋል። ሁለቱም የኢትዮጵያን ገጽታ ከጫፍ እስከ ጫፍ ከገጽ እስከ ክርስ ከሙያቸው አንፃር ጠንቅቀው ያውቁታል።

የጓደኝነት ፍቅራቸውን ልክ ለመግለፅ በአንድ አጋጣሚ ሲጫዋወቱ የሰማሁትን መጥቀስ በቂ ይመስለኛል። አንድ ቀን አዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል በመናፈሻው በኩል ቁጭ ብለን እያወራን ነበር። ከተገናኙ ብዙ ጊዜያቸው ስለነበር በጣም ለመነፋፈቃቸው ነጋሪ አያሻም ነበር።

"ስማ! ኪብሬ" አለው፤ ዶ/ር ክብረ በዓልን ‹ኪብሬ› ብሎ ነው የሚጠራው፡፡ "ሰው ሆኖ መጥቶ ወዳጅ ሆኖ መለያየት አይቀርምና አንድ ነገር ልንገርህ ብዬ ነው" አለው፡፡

"ደግሞ ዛሬ ምን ልታመጣ ነው?" ሲል

"እየውልህ! አንተ ለእምነትህ አዳሪ፣ ፈጣሪን የምትፈራ ጥሩ ክርስቲያን ነህ፡፡ እኔም በአላህ ላይ ያለኝ ኢማና፣ ለነብዩ ያለኝ ክብር እንደምታውቀው ጥልቅ ነው፡፡ ሁለታችንም በእውነትና በቅንነት ባመንበት እየተጓዝን ነው" አለና ፈገግ ብሎ "ብቻ ከሁለት አንዳችን መጨረሻ ላይ ስሕተት ሁነን መገኘታችን አይቀርም፡፡" ሲል ሁላችንም ከልብ ሳቅን፡፡

"እና ምን አሰብክ?" አለው ዶ/ር ክብረ በዓል፡፡

"እኔ ትክክል ሆኜ ከአላህ ፊት ስቀርብና ‹ወደ ጀነት ግባ› ስባል አንተ ስሕተተኛ ሆነህ ‹ወደ ጀሃነም ሂድ› ስትባል ‹ቸሩ አላህ ሆይ ኪብሬን ጀነት አብረህ ካላስገባህ ብቻዬን አልገባም› እላለሁ፡ ወይም ደግሞ አንተ ትክክል ሆንክ ክርስቶስ ፊት ስትቀርብ ‹ወደ ጀነት ግባ፣ ነቢል ወደ ጀሃነም ይሂድ› ሲባል ‹እሱንም ጀነት ካላስገባህ እኔንም ጀሃነም አስገባኝ" ትላለህ፡፡ በዚህ መልክ ሁለታችንም Safe እንሆናለን" አለው፡፡

ንግግሩ የዶ/ር ክብረ በዓልን ብቻ ሳይሆን የኔንም እንባ አስመጣው፡፡

ድንገት ክብረ በዓል ብድግ ብሎ ግንባሩን ሳመውና፡-

"አይዞህ! በተለያዩ መንገድ ብንጓዝም በቅንነት እስከሆነ ድረስ ፈጣሪ ቅን ፍርዱን አይነሣንም" አለው፡፡





እዛው እንደተቀመጥኩ ፍቅራቸውና ባልንጀርነታቸው ደንዳናውን ልቤን ፈለፈሎ አወጣው፡፡ ከዚያ በኋላ የሚነጋገሩትን ብዙም አልሰማሁም፡፡ በዚች ምሥጢራዊት ሀገር እንደነዚህ ያሉ ልበ ንጹሓን ሰዎች በመኖራቸው ነው ምንጮች የሚፈልቁት፣ ወንዞች የሚፈሱት፣ በደረት ሰማይ ደመና ዝናብ አርግዞ ጠለ-ምሕረት የሚዘንበው፣ ሰማይ ያለምሰሶ የረጋው፣ ምድር ያለካሥማ የጸናችው" እያልኩ በእጅጉ የመጽናናት መንፈስ ውስጤን አረሰረሰኝ፡፡

በሌላ ጊዜ አግኝቸው የዶ/ር ክብረ በዓልን መመንኮስና ገዳም መግባት ስነግረው ብዙ አልተገረመም ነበር፡፡

"እርሱ ንጹሕ ሆኖ የተመረጠ ነውና ወደ ቅዱሳን አባቶቹ ጠጋ ማለቱ ተገቢ ነው፡፡ በዚህ ነጻሳ ዓለም ቢቆይ ከመጉደፍ በቀር ምን ያገኛል?" ነበር ያለኝ፡፡

ደውዬ እርሱን ለማግኘት ወደ አዲስ አበባ እየመጣሁ እንደሆነ ስነግረው ዶ/ር ክብረ በዓል እንደሚጠራኝ "ወንድም ሲሳይ" አለና "ምንም ችግር የለም እጠብቅሃለሁ" ነበር ያለኝ፡፡

የምጠይቀው ጥያቄ ድንገቴ እንዳይሆንበት ብዬ፡-

"ነቢል ማወቅ የምፈልገው ስለ ኩሕል ነው" አልኩት

"ወይ ጉድ ደግሞ ኩሕል ለምን አስፈለገህ?" አለኝ፡፡

"እርሱን ስመጣ እነግርሃለሁ፡፡ ብቻ ስለ ተፈጥሮ ጠባዩ፣ ጥቅሙ፣ ስርጭቱ፣ በቃ አጠቃላይ መረጃ" አልኩት

"አንዳንድ ግንዛቤዎች አሉኝ፤ ግን የበለጠ እጥንቼ እቆይሃለሁ" አለኝና ቀን ሰዓትና ቦታ ወስነን ስልኩን ዘጋሁ።

አዲስ አበባ ገብቼ በተቀጣጠርንበት ሰዓት ሂልተን መናፈሻው ላይ ባለ ፏፏቴ ገጹና ጠይሙ እንደ ዶ/ር ኩበሬ በዓል ሰዓትና ሰው አክባሪው ነቢል ቀድሞኝ ተቀምጦ ሲጠብቀኝ አገኘሁት። ለነገሩ እኔም በሰዓቱ ነው የተገኘሁት። ሲያየኝ ከመቀመጫው ተነሥቶ ሁለት እጆቹን እንሥቶ አቀፈኝና፦

"የኪብሬ ምትክ ወንድም ሲሳይ እንዴት ነህ?" ሲለኝ

"እርሱን እንኳ አልተካልህም" አልኩት እየሳኩ።

ቁጭ ብለን ጥቂት ስለጤንነታችንና ሥራችን ከተጠያየቅን በኋላ

"አባን አግተኸው ታውቃለህ? እንዴት ነው?" አለኝ።

"ደኅና ነው። እንዲያውም ሰሞኑን ተገናኝተን አንተንም አግኝቼ እንድጠይቅ ያሳሰበኝ እርሱ ነው" አልኩት።

ዐይኖቹ ቡዝዝ ብለው ቀሩ። ናፍቆት መሆኑ ግልጽ ነበር።

"አሁን ያለበትን ገዳም እኔም አላውቀውም። ፈቃዱ ሆኖ የገለጸልኝ ጊዜ ግን ሃደህ ትጠይቀዋለህ" አልኩት ያጽናናሁ መስሎኝ።

"ግዴለም አሳህ ባለው ቀን ይሆናል" አለኝና "ይልቅ ወደ ጉዳይህ ልግባልህ" አለና ከመቀመጫው ተመቻችቶ፦

"ኩሕል በሳይንሳዊ መጠሪያው ‹ስቲቢናይት› (Stibnite) ይባላል። ከጥንት ዘመን ጀምሮ በመካከለኛው ምሥራቅ፣ በህንድ፣ በሰሜን





አፍሪካና በአፍሪቃ ቀንድ የዐይን ብሌንን ለመንከባከብ ለመድኃኒትነት በሚል ጥቅም ላይ ይውላል። ይኸውም አለቱን በመስበርና በመፍጨት እንደ ዱቄት በማድረግ የዐይን ሽፋሽፍትን መቀባት ነው። በዕብራውያን ዘንድ የተለመደ ሲሆን በእስልምናው ዓለምም የዐይን ጤንነት ለመጠበቅ ነቢዩ ፈቅደዋል በሚል ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ ወንዶቹም ሕፃናትም ይኳሉታል። ከዚህ በላይ የቡዳ መንፈስን ይከላከላል ተብሎም ይታመናል።" አለ።

"ስርጭቱስ?" አልኩት

"በመካከለኛው ምሥራቅ በተለይ በዐረቡ አለም ይገኛል"

"በኢትዮጵያስ?" ስለው

"አንገቱን ግራ ቀኝ አወዛውዞ በእርግጠኝነት ከምትቱ ከዚህ ሥፍራ አለ ብሎ ለመናገር በቂ ጥናት የለም። ነገር ግን ‹Geological Formation› በማየት ተከዜ ተፋሰስ ውስጥ ሊኖር ይችላል" አለ።

"ሲታይ ምን ይመስላል?" አልኩት መልሼ።

"የእርሳስ ቀለም ያለው፣ የሆነ አብረቅራቂና ጠንካራ ብዙ ጠርዞች ያሉት፣ ረዘም ያለ ክርስታል ነው" አለና ስዕሉን ከሞባይሉ አውጥቶ አሳየኝ። ባየው ሳውቀው እንደምችል ስለገመትኩ ጭንቀቱ ቀለል አለልኝ። "እዚህ ገበያ ውስጥም በስብርባሪ መልክ ሊገኝ ይችላል" አለኝ።

"እይ አምጣ የተባልኩት ከእስራኤል ነው" ስለው

"ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም በአዘገጃጀት ሂደት ተፈጥሯዊ ጠባዩን ሊያጣ ይችላል" አለኝና "ግን ለምን ተፈልጎ ነው?" አለኝ።

"በእርግጠኛነት ልነግርህ አልችልም። ብቻ ግን ዐይን ስማስቴዋ አልመሰለኝም" አልኩትና "ግን እንዲያው አንተ የምታውቀው ማሉቱ ለባይንስ አንባር የተለየ ጠባይ (property) ይኖረው ይሆን?" አልኩት።

"ማነው እምጣ ያለህ?" አለኝ፣ ጥያቄየን ገሸሽ አድርጎ።

"የገዳም አባቶች ጠርተው ነው እኔንና አባ መዐዛን ያዘዙን። ብቻ አንዲት በጸና የታመመችን ሴት ስለመፈወስ ይመስለኛል" አልኩት በደፈናው።

ዝም ብሎ ማዶ እያየ ሲያስብ ቆየና፦

"ወንድም ሲሳይ የእናንተን የገዳም አባቶች ጥበብና ዕውቀት በቅርብ ባላውቀውም ብዙ ነገር የተረዱ ይመስለኛል። ቢያንስ ኪብሩን መጣረክ መቻላቸው ለእኔ በቂ ምስክር ነው። አንተ ከደወልክልኝ በኋላ ብዙ ሊትሬቸር አገላብጨ ነበር" አለና ዝም ሲል

"እና ምን አገኘህ?" አልኩት ጉጉት ብዬ።

"በጣም አስደናቂ ነገሮችን አንብቤያለሁ" አለኝ።

"ምንድን ነው እርሱ?" አልኩት ጥድፍ ብዬ።

"መጀመሪያ አምጣ የተባልከውን ፈልገህ አምጣና ላዘዙህ አባቶች አስረክብ። ሌላውን ጉዳይ ከዚያ በኋላ እነግርሃለሁ" አለኝ።

"እንዴ ለምን አሁን አትነግረኝም?" ስለው

"ማወቅ ቢኖርብህ ኖሮ እነርሱ ይነግሩህ ነበር። እነርሱ ያልነገሩበት ምክንያት ይኖራቸዋል። እና እኔም ለእነርሱ ታማኝ መሆን አለብኝ።





ጣጣ እንዳታመጣብኝ!" አለና ሳቀ።

ለምን ከዶ/ር ክብረ በዓል ጋር እንደተወዳጀ ለመጀመሪያ ጊዜ ገባኝና ዘሎን ምግባሩ በጣም ተደነቅኩ።

"በል ይሁን እግዚአብሔር ከረዳኝና ከመጣሁ በኋላ ትነግረኛለህ። እውነትክን ነው፣ አሁን ብትነግረኝ ወይ እንቀዋለሁ ወይ በጣም ጉጉቱ ስሕተት ላይ እወድቃለሁ።" አልኩና "ስመለስ ግን ስለእርሱ ብቻ ሳይሆን ስለውኃም ታስረዳኛለህ" አልኩት።

"ኢኮሎጂስት አይደለህ እንዴ ስለ ውኃ ደግሞ ምንድን ነው የማስረዳህ?" አለኝ።

"ነቢል ብዙ ያልገባኝ ነገር አለ። ውኃ ገና ምሥጢር ነው ለእኔ" አልኩት።

"በእርግጥ ውኃ ብዙዎቻችን ከምናስበው በላይ አስገራሚ ተፈጥሮ አለው። ግን ካንተ የተሠወረ አይመስለኝም ብዬ ነው" አለ።

"ግዴለህም ዘመኔን ከእውቀት ማዶ ሆኜ የኖርኩት ዕውቀትን ያወኩት እየመሰለኝ ነው" አልኩት።

"ብቻ በደኅና ተመለስና እንነጋገራለን" አለና "ታዲያ መቼ ወደ እስራኤል ለመሄድ አሰብክ?" አለኝ

"ገና ለጉዞ ዝግጅት የሚሆነኝን መረጃ ላሰባስብ ነው። እንዲያውም እንዳ የመጣሁበት ለዚያ ነው" አልኩትና የተለመደ የሙያ የሀገር የቤተሰብ ወሬ ስናወራ ቆይተን "መልካም እድል" ብሎኝ ተሰነባበትን።



# ምዕራፍ - ፲፩

አባ ዮናታን ለደቂቃዎች በሐሳብ መንጎዱን አይተው በትዕግስት ሲጠብቁኝ ቆዩና መመሰጡ ሲባባቸው፡-

"እ፝ኸ...ኸ..." አሉ። ጎልተኸኝ የት ሄድክ እንደማለት ይመስላል።

እኔም እንደ መባነን አልኩና፡-

"እናም በዚህ ሁኔታ ነበር ወደ እስራኤል ብሎም ወደ እርስዎ የመጣሁት" አልኳቸው በተመስጥኦ ሲዳምጡኝ የቆዩትን አባ ዮናታንን።

"በጣም ይደንቃል!" አሉ አባ ዮናታን።





የነገርኳቸውን ሁሉ ልቅም አድርገው እንደሰሙኝ እርግጠኛ ነበርኩ።

"እና... እንግዲህ ኢትዮጵያ ዘተወልዱ በጎበ እስራኤል፣ ስለሚል ያው እስራኤል የታወቀ ነው ከእስራኤልም ደግሞ ከኢትዮጵያ የተወለዱት እናንተን ስለሚመለከት መሰለኝ ወደዚህ እንድመጣ ያዙኝ አልኩና ዐይን ዐይናቸውን እያየሁ በጉጉት እጠብቅ ጀመር።

አሁንም ፂማቸውን እየላጉ አሻግረው እያዩ ብዙ ቆዩና፡-

"የኔ ልጅ ስለዚህ ጉዳይ ብቻዬን አስተያየት መስጠት አልችልም" አሉ።

"ታዲያ ማንን ልጠይቅ?" አልኳቸው ተስፋ በቆረጠ ስሜት።

"የጉዳዩን ክብደት አንተም ሳትረዳው የቀረህ አይመስለኝም" አሉ።

"ክብደቱንማ እረዳለሁ እንጂ አባቴ። ከባድ ባይሆን ከኢትዮጵያ ተነሥቼ እዚህ እስራኤል ድረስ ለምን እመጣ ነበር?" አልኩኝ።

"እውነት ነው። ይህን ተተረዳህ ተምኩራብ አለቆችና ተሸንጎው ጋር መምከር ይኖርብኛል" አሉ።

"መምከረም ተገቢ ነው። ነገር ግን ወደ ኢትዮጵያ የምመለሰው ተነገ ወዲያ እሑድ ሌሊት ነው" አልኳቸው።

"እስ እንኳን አመጣጥህ ጥሩ ቀን ነው። ነገ ሰንበት ስለሆነ ወደ ምኩራብ እንወጣለን። ጉዳዩን መክሬ እሑድ ጠዋት ብትመለስ እስታውቅሃለው" አሉ።

ነገሩን ሳስበው በሽንንው ነገ ሲመክሩ፡-

"አንድ የማይታወቅ ሰው ተልኮ መጥቶ ከእናንተ ዘንድ ያለውን ዕብነ ኩሕል ስጡኝ ብሏል፡ ብለው ጉዳዩን ሲያቀርቡ የሚነግሩው ውዝግብ ታየኝና ብዙ ተስፋ ያለው አልመሰለህ አለኝ፡፡ ምናልባት ብጹኑ የታመመችን ሴት ለማዳን ነው፡ ብለው ካቀረቡ ሲራሩ ይችሉ ይሆናል፡፡ በዚያ ላይ ተስፋ የሌለው ዝግ ቢሆን እኒህ ብልህ አባውንት ለምን ይቀጥሩኛል በሚል እንደ ክር የቀጠነች ተስፋ ታየችኝ፡፡

እንደ ክር የቀጠነችውን ተስፋ እንደ ገመድ ለማወፈር ፈለኩና፡-

"እንዲያው ግን ተስፋ ያለው ይመስለዎታል?" አልኳቸው፡፡

"ሁሉንም እሑድ ታውቀዋለህ!" አሉኝ፡፡

የከሸፈ ይሁን የሰለለ ተስፋ የእሑድ ቀጠሮዬን ሳንሰላስል መስህለ-ማርያም በሩን ከፈት አድርጋና አንገቷን ሰገግ አድርጋ፡-

"አልጨረሳችሁም" ጋሽ ሲሳይ? ስንበት ከመግባቱ በፊት አባን ነፃ ማድረግ አለብህ" አለችኝ፡፡

"ጨርሰናል፤ እውነትሽን ነው፤ ብዙ አላድክማቸው" አልኩና "አባቴ እሑድ ስንት ሰዓት ልድረስ?" አልኳቸው፡፡

"ታራት ሰዓት ጀምሮ እጠብቅሃለው" አሉኝ፡፡

አመስግኛቸውና ተሰናብቻቸው ወደ መኪናው ስናመራ መስህለ-ማርያም ከኋላዬ ደረሰችና፡-

"ተሳካልህ?" አለችኝ፡፡





"አልተሳካልኝም" አልኳት በለዘቤታ ራት፡፡ ደመናውን ራቱን ስታይ በጣም ጭንቅ አላትና የመኪናውን በር እየከፈተችልኝ፡-

"ለምን? ሲረዱህ አልፈለጉም?" አለች ጭንቀቱ ተጋብቷት፡፡

"ከምኩራብ አሉቶችና ከሽንጎ አባላት ጋር መክሬ ነው፡ አሉ" አልኳት፡፡

መኪናዋን አስነሥታ ወደ ዋናው መንገድ እያስገባች፡-

"ግን ምንድን ነው የፈለከው? ልትነግረኝ ትችላለህ?" አለችኝ እንደዋዛ፡፡

"እረ እንኳን ላንቺ ለሌላም የሚደበቅ አይደለም" አልኩና "ምን መሰለሽ የሆነች ምስኪን ሴት በጸና ታምማ ካንድ ትልቅ ገዳም ትገኛለች፡፡" እና ብዙ ልቀጥል ስል

"ምንድን ነው ሕመሟ?" አለችኝ፡፡

አባ አካለ ወልድ እንደገለጹልኝ "ሕመሟ ብዙ ነው፤ የዘመን ጥርቅም፡፡ ብቻ እኔ እንዳየኋት ደም ያለማቋረጥ ይፈሳታል" አልኩ፡፡

"ው...ይ...ይ" ብላ ሰጥስፍ አለች መስህለ-ማርያም፡፡

"እና ይችን ሴት ለመፈወስ ከሚስፈልጉ ነገሮች አንዱና ዋናው ከቤተ እሥራኤላውን እጅ የሚገኝ መሆኑን የገዳሙ አባቶች ስላወቁ እኔን ወደዚህ ላኩኝ" አልኳት፡፡

"እና ከእኛ ዘንድ የለም አሉህ?" አለችኝ፡፡

"አለም የለምም ሳይሉ ነው መክሬ ልንገርህ ያሉኝ" አልኩ፡፡

"መቼ ነው እንነግርሃለው ያሉህ?" አለችኝ

"ከነገ ወዲያ ኢሉድ" አልኳት።

"መቼ ነው ጉዟችሁ?" አለች መልሳ

"እሱ እንኳን ኢሉድ ሌሊት ነው" አልኩኝ።

"ይሄማ ጥሩ ነው። ኢሉድ በጠዋት እቃችሁን አዘጋጅተህ ለአስጎብኝዎቹ አስረክበህ ባለቤትህን እንደዛሬው ከሌሎች ጎብኝዎች ጋር ትተህ እዚህ ትመጣና ጉዳይህን ጨርሰህ በዚሁ ወደ ኤርፖርት ታመራለህ" አለችኝ።

"እውን! ታክሲ ተኮናትሬ ማድረግ ያለብኝ እንደዚያ ነው" አልኳት።

"የምን ታክሲ እኔ አለሁ አይደል?" አለች።

"ድጋሚ አላስቸግርሽም። የዛሬው ትብብርሽ በራሱ ብዙ ነው። ባይሆን ለባለ ታክሲው አድራሻውን ትነግሪልኛለሽ" አልኩ።

"አሁን እኮ ጉዳዩ ያንተ የግል ጉዳይ ሳይሆን የሌላ መሆኑን ነገርከኝ። በዚህ በጎ ሥራ ያልተባበርኩ ታዲያ በምን ክርስቲያንነቴ ይታወቃል" አለችና

"እንዲያውም ጉዳዩን ለእያቴ እነግራትና ጫና እንድታደርግ እጠይቃታለሁ። በእውነት ከእጃቸው ካለ ሴት ደም እየፈሰሳት አምቢ ሊሉ አይችሉም" አለችኝ።

የሰለለውን ተስፋዬን ነፍስ ስትዘራበት ታወቀኝ። በልቤ አንችን ያገናኘኝ አምላክ የተመሰገነ ይሁን እያልኩ ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ወደ ኢየሩሳሌም አመራን።





ከኒታንያ መልስ ሆቴል ስደርስ እጅግ ደክሞኝና ተሰላችቼ ነበር። መስሀሉ-ማርያምን አመስግኜና ተሰናብቼ ወደ ክፍሌ ስገባ ባለቤቴ በጉጉት ስትጠብቀኝ አገኘኋት።

ገና እንደገባሁ፡-

ግንዴት ሆንክ?" አለችኝ። ሁሉንም በዝርዝር ነግሬያት ስለነበረ ስትጨነቅ ውላለች። የደበዘዘ ትስፋ ይዤ ለኢሉድ እንደ ቀጠሩኝና መስሀሉ-ማርያም መልሳ ልትወስደኝ ፈቃዷ እንደሆነ ነገርኳት።

የዐርብ ምሽት እጅግ ደባሪ ሆኖ አለፈ። የቅዳሜው ጉብኝቱም እንዳለፉት ቀናት አስደሳች አልነበረም።

አሁንም አሁንም የሽንን አበላት ሲወያዩ የምኩራብ አለቆች ሲነታረኩ ይታየኛል።

‹እንዴት ያለ ድፍረት ነው?› ይላል አንዱ ሌላው ይቀበልና ‹እንጡራ ሀብታችን እኮ ነው ዘሎ ስጡኝ ይባላል?› ይላል። ቀኑን ሙሉ አእምሮዬ የጥንቱ የአይሁድ ምኩራብ የክርክር መድረክ ሆኖ ዋለ። የምግብ ፍላጎቴ ተዘጋ።

ባለቤቴ ቢጨንቃት፡-

'ሊሆን ይሳካል፤ ካልተሳካም አንተ ድርሻህን ተወጥተሃል የሚጸጽትህ ነገር አይኖርም" አለች።

ንግግሯ እውነትነት ቢኖረውም ሐሳቤን ግን መግታት አልቻለም። እርግጥ መልፋትና መድከማችን ከጸጸት ያድነን ይሆናል። ነገር

ግን የሥራው ውጤት የሚያመጣውን ጥቅም አይተካልንም ወይም በመሥራቱ ሊቀር የሚችለውን ችግር አያቀልልንም። እናም ልናሳካው ያሰብነው ግብ ሩቅ ሆኖ እስምሯችን እረፍት መንሳቱ፣ ቋሚ ሕመም ሆኖ መተበሱ አይቀርም። በእርግጥም ግድግዳ የሚገሩ ሰው ሥራ ሠራ የሚባለው ግድግዳው ሲንቀሳቀስ እንጅ የሰውዬው ልፋትና ድካም ታስቦ አይደለም። የሰው ልጅ ድካምና ጥረት ዋና ግቡ ከጸጸት መዳን አይደለም፤ እርሱ የሕመሙ ማስታገሻ ኪኒን ነው። ግቡ የታሰበውን ማግኘት ነው፣ የተጀመረውን መጨረስ፣ የተፈለገውን ማግኘት ነው።

ነምዛዛው ቅዳሜም ውሎ መሸ ሰእሁድ ማስረከቡ ግድ ሆነ። እሁድ ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ መልስ ከመስህሉ-ማርያም ጋር ድጋሚ ወደ ኒታንያ አመራን። ከአባ ዮናታን ቤት ስንደርስ ከደርባባዋ ባለቤታቸው ጋር ሲጠብቁን አገኘናቸው። ባለቤታቸው መታውን አንገታቸውን በጎንደር ንቅሳት ያሳመሩ ገራገር እናት ናቸው። መስህሉ-ማርያምን አገላብጠው ስመው ስለአያቷ ሲጠይቋት ቆይተው "የእኔ ነገር ረስቼሀ" አሉና ወደኔ ዞምር ብለው ከዚህ በፊት እንደሚያውቁኝ ሁሉ ጉንጮቼን አገላብጠው ሳሙኝና "በሉ ተቀመጡ" አሉ።

መስህሉ-ማርያም "ጉማማ እኔና እርስዎ እንጫወታልን። እንግዳችን ዛሬ ወደ ኢትዮጵያ ስለሚበር ከአባባ ጋር ውይይታቸውን ይቀጥሉ" አለች።

"እንግዳው እህል ሳይቀምስ?" አሉ።

"ግዴለም እውነቷን ነው። አሁን ነው ቁርስ በልቼ የመጣሁት። ይልቁንስ ከአባ ጋር ያለኝን ጉዳይ ብጨርስ ይሻላል" አልኩ።





መስህሉ-ማርያም እማማን አግባብታ እኔና አባ ዮናታን ወደ ልዩ ክፍላቸው እንድንገባ አደረገች። 'የተማረች፣ የሰለጠነች፣ ዝባዝንኬ የማታውቅ ንጹሕ ልጅ' አልኩ በልቤ።

እኔና አባ ዮናታን ክፍላቸው ገብተን ትንሽ እንደቆየን፡-

"አባ ተወያየችሁበት? እንዴት ሆነ?" አልኩ

"ልጄ በከንቱ ደከምክ!" አሉኝ።

"እርፍ ነው!" አልኩ ለራሴ።

'እርሳቸውስ በቀደም ለምን አይሆንም አይሉኝም ነበር' እያልኩ በውስጤ ጨስኩ። 'ሲጀመር ሰው ዝም ብሎ ዘሎ መጥቶ ስጡኝ ማለት እንዴት ያለ ጅልነት ነው? መጀመሪያውኑ ለምን እሺ አልኩ? አባ መዐዛ ቅዱሳንስ ምን ነካው? እንዲህ ኩም የሚያደርግ ሁኔታ ውስጥ የከተተኝ' እያልኩ ውስጤ ተብተከተከ።

ቁርጥርጥ ያለውን ቁርጤን ለማወቅ ብዬ፡-

"ምነው አባቱ ሸንጎው አይቻልም አለ እንዴ? ሊሰጡኝ አይችሉም ወይስ ከእናንተ ዘንድ የለም?" አልኩኝ ሽኩክ ብዬ ጥያቄ እየደራረብኩ።

"የለም የለም እንደዚያም አይደል!" አሉ እጃቸውን እያወናጨፉ።

"ታዲያ ምንድን ነው ችግሩ?" አልኩ።

"የኔ ልጅ የጉዳዩን ቅን ዓላማ ተረድተነዋል። ይሁን እንጅ የትርጓሜ ዝንፈት አለ" አሉ ፍርጥም ብለው።

"እንዴት ማለት?" አልኩ የበለጠ ግራ እየገባኝ።

"እየህ ገጸ ንባቡ ወደዚህ እኛ ዘንድ ቢያመለክትም ምሥጢሩ ሌላ ነው" ሲሉ

"እይ... በከንቱ ደከምኩ፤ ባዶ እጄን ልመለስ ነው ማለት ነው? ሕመሚስ? ስቃዩስ?" አልኩና በሁለት እጆቼ ራሴን ጭምድድ አድርጌ ያዝኩ። ሆድ ባሰኝና አልቅስ አልቅስ አለኝ።

"ስማኝ የኔ ልጅ፤ ባዶህን አትመለስም!" አሉ።

"ምን ማለትዎ ነው? ያገኙልኛል ማለት ነው?" አልኩ

"እ..ይ.. እዚህ አይገኝም፤ ከእኛ ዘንድ የለም። ከኢትዮጵያ ይዘነው የመጣነው ነገር ቢኖር ናፍቆትና ትዝታ፣ ክብርና ውብ ባህል ብቻ ነው" አሉና "እንዲህ ያለ ወሳኝ ነገር ይዘን አልመጣንም አናመጣምም" አሉ።

"ታዲያ ባዶህን አትመለስም ያሉኝ ምን ይገበ ልመለስ ነው?" አልኩ።

"ትክክለኛውን የመገኛውን አድራሻና ፈቃድ" አሉ።

ድንገት የተቋጠረው ግንባሬ ተፈታ፤ የጠቆረው ፊቴ ፈካ። ምንም እንኳን ሌላ የፍለጋ ዳና የምጀምር መሆኑን ባውቅም ተስፋ መልካም ነውና ደስ አለኝ።

የቀሩትን ጊዜያቶች የጉዳዩን ዝርዝር ምሥጢርና ሌሎች ነገሮችን በፍቅርና በትዝታ ሲያጫውቱኝ ሳይታወቀን ብዙ ሰዓታት አሳለፍን። የንግግራቸው ለዛ፣ የዕውቀታቸው ጥግ፣ አባታዊ ፍቅራቸው፤





ስለኢትዮጵያ ያላቸው ተስፋ በቃ ሁለንገራቸው አይጠገብም።

መስህለ-ማርያም እንደተለመደው መጣችና "ጋሽ ሲሳይ ወደ ኤርፖርት መሄጃህ ጊዜ እተቃረበ ነው" አለችኝ።

"የኔ ነገር ጨዋታቸውን አልጠገብው ብዬ እኮ ነው" አልኩና ለመሠናበት ስነሣ ባለቤታቸው መጥተው ወደ ሳሎን እንድንሄድ ጋበዙን። ሁኔታቸውን ሳየው እህል ውኃ ሳልቀምስ እንደማይለቁኝ ገባኝና ሳልግደረደር ቤት ያፈራውን ከመስህለ-ማርያም ጋር ተጋበዝን። በምቀ መስተንግዶ ተጋብዘን ስንጨርስ ባለቤታቸው አቅፈው ሳሙኝና ወደ ኮሪደሩ በር ስንደርስ አባ ዮናታን ጠጋ ብለው፡-

"የነገርኩህን በአግባቡ መዝግበው። ስትድን የምሥራቹን እንድትልክብኝ። የአብርሃም የይስሐቅ የእስራኤል አምላክ ይከተልህ። እንደምታገኘው አምናለሁ፤ እንደታዘዝከው ወለም ዘለም ሳትል ወስደህ ስጥ" አሉ።

"አሜን! አባቴ እርስዎንም ባለቤትዎንም ፈጣሪ በእድሜ በጤና ይጠብቀዎት" አልኩና ጐንበስ ብዬ ጉልበታቸውን ስሜ እርሳቸውም ትከሻዬን ስመው ተሰነባብተን የቤታቸውን ዋና በር ለማለፍ ራመድ ስል ከተል አሉና፡-

"ጨርሶ ይማርሽ! የመከራ ዳርቻ ያድርግልሽ! በእኛ ዘንድ ስላንቺ ቀድሞም አሁንም አብዝተን እንጨነቃለን በልልኝ ደኅን ሚተራሊዮንን!" አሉ።

"አባ! ያውቋታል እንዴ?!" አልኩ መደነቄ መጠን አጥቶ።

ረጅም ፈገግታ ከደርባባው ፂማቸው ጋር ፊታቸው ላይ ታዬ። ብዙ ትርጉም ያለው ፈገግታ ነበር። ቀኝ እጃቸውን አንስተው እያወዛወዙ በአባታዊ ዘይቤ የደኅና ሁን ምልክት አሳዩኝ። ድብልቅልቅ ያለ ስሜት እየተሰማኝ የቤታቸውን ደረጃ ወረድኩ።

"ተሳካልህ?" አለችኝ መስህለ-ማርያም የሆነውን ሁሉ በጉጉት ስትከታተል ቆይታ ስለነበረ ወደ መኪናዋ ስናመራ።

"ይመስለኛል። ቢያንስ ያንቺ ትንንት፣ የእርሳቸውና የባለቤታቸው ደግነት ፈጣሪ ከእኔ ጋር ለመሆኑ ምልክት ነው" አልኳት።

"የኔን ቅንነት እንኳ አታጋነው። ደግነት እኮ በአዕምሮ ውስጥ ያለን በጐ ሐሳብ ወደ ተግባር የመቀየር እድል ነው። ጉዳዩ የእኔን እርዳታ እንደሚሻ እያወቅኩ ዝም ልል አልችለም" አለች።

"በዚህ ጥድፊያ በሞላበት ዓለም ድንገት መጥቼ ማስቸገሬ ፕሮግራምሽን ያዛባል ብዬ ነው እንጂ" ስላት

"እያቴ፡-

‹እኛ የሌሎችን ጉዳይ ለመፈፀም ወይም ችግር ለመፍታት ስንነሣ እግዚአብሔር የእኛን ጉዳይ ሊፈፅም፣ የእኛን ችግር ሊፈታ ይነሣል። በዚህም ድርጊታችን በእኛ አቅም ሲጦከር የነበረው ችግራችን ሁሉን በሚችል ፈጣሪ ይፈታልናል። አጥብቀን ስለያዝን ከእኛ ጋር የሚቆይ ነገር የለም። በመስጠት ከእኛ የሚጠፋ የለም። እንዲያውም በመስጠት እናገኛለን፣ በመርዳት እንረዳለን፣ ሰዎችን በማገዝ ከፈጣሪ እገዛ እናገኛለን።›





ትለኛለች። እርግጥ ይሄ ተራ የሃሳብ ስሌት አይደለም። በቅንነት የሚሠራ ድርጊት እንጅ። እናም አንተን በማገዜ የሚቀርብኝ ምንም ነገር አይኖርም" አለችኝ።

‹እንዴት ነው የበሰለች? እውቀትን፣ ስልጣኔንና መንፈሳዊነትን እንዴት ግሩም አድርጋ ተላብሳለች?› አልኩ በአድናቆት ለራሴ። በጎነቷ የበለጠ እንድነሣሣ አደረገኝ። በጎነት ወይም ደግነት ሌሎችን የማንቀሳቀስ ኃይል አለው። ለዚህም ነው ቢያንስ በጎ ሳደረጉልን ሰዎች መልሰን በጐ ለማድረግ የምንነሣሣው። ደግነት አንዴ ከአንድ ቦታ ከተጀመረ ወደፊት እየተሽከረከረ የሚጓዝ መንኮራኩር ነው። የአንድ ሰው ደግነት ዓለምን ይቀይራል ሲባል የዚያ ሰው ጥረት ብቻ ማለት አይደለም። ያ ሰው የሚያቀጣጥለው በጎነት እንጅ፤ እናም ለሰው ደግነት ሲኖረን ውጤቱ ወደ ብዙ ሰዎች ይተላለፋል። ደግነት ከአንዱ ወደ አንዱ የሚቀጣጠል ችቦ ነው። አዋቂዎች እንደሚሉት ደግነት ጥሩነት አይደለም ከዚያም በላይ ነው። ጥሩነት የደግነት አነስተኛው ደረጃ ነው። ደግነት በውስጡ ባልንጀርነትን፣ ለጋስነትን፣ ፍቅርንና ትኅትናን የያዘ ነው።

ከኒታንያ ከተማ ስንወጣ የሆነ ከፊቴም ከኋላዬም የከበበኝ በጎ መንፈስ ያለ ያክል ተሰማኝ። ውስጤ በአድናቆትና በተስፋ ደስ እያለው ወደ ቴላቪቭ አውሮፕላን ማረፊያ አመራን።



# ምዕራፍ - ፲፪

ከቴላቪቭ ወደ አዲስ አበባ በረራ ላይ እያለን ምሽት ላይ ስለነበር ባለቤቴን እንቅልፍ ወስዷታል። እኔ ግን እንቅልፍ የማያስወስድ የሐሳብ ትንተና ላይ ነበርኩ።

አባ ዮናታን የነገሩኝን አንድ ባንድ እያስታወስኩ ወደ ማስታዎሻዬ እየገለበጥኩ በዚያውም እንደገና በደንብ እያንሰላሰልኩ ነበር። አባ ዮናታን በነገሩኝ መሠረት የማገኝበትን ስፍራ አስታውሼ ወደ ማስታዎሻዬ ስገለብጥ ዕብነ-ኩሕል ኢትዮጵያ ውስጥ የት አካባቢ ሊገኝ እንደሚችል እንደዋዛ ጣል ያደረገልኝ የነቢልን ንግግር አስታወስኩና በሙያ ብቃቱ በእጅጉ ተደመምኩ።





እስከዛሬ ካየኋቸው ኢትዮጵያውያን መካከል እንደ ዶ/ር ክብረ በዓል (አባ መሀዛ ቅዱሳን) እና ነቢል ያለ በሙያቸው ብቁ የሆኑ አላጋጠሙኝም። የሙያ ብቃታቸው ብቻ ሳይሆን ስብዕናቸው እንደ ወርቅ የነጠረ ነው። መልካም ስብዕና ከሙሉ ባለሙያነት ጋር የተሠናሠሉለት ሰው እንዴት የተባረከ ነው!

በእርግጥ ሃዋርድ ጋርደነር የተባለ የሥነ አዕምሮ ሊቅና ፈላስፋ፡-

'መጥፎ ሰው ጥሩ ባለሙያ ሊሆን አይችልም

መጥፎ ባለሙያም ጥሩ ሰው ሊሆን አይችልም'

በማለት እንደፃፈ አንብቤያለሁ።

እውነት ነው። የተዋጣለት ባለሙያነትን የሚሸከመው የተስተካከለ ስብዕና ይፈልጋል። ሰይፍና ሰገባ፣ ጉራዴና አፎት፣ ዳዊትና ማኅደር፣ ፅላትና ታቦት፣ ነፍስና ሥጋ ናቸው። ሙያና ተግባር የሌለው ጥሩ የሚባል ሰው ‹ጅል› እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም። በሌላ በኩል ብዙ የሚያውቅ፣ ብዙ የተማረ፣ በሙያው የተካነ ቢመስልም ክፉ ሰው ከሆነ ሙያውን አንድም ለግል ጥቅም ማካበቻ፣ ለርካሽ ተወዳጅነት ማፍሪያ፣ አለዚያም ለሰው ልጅ መጥፊያ አውሎት መጨረሻ ክፋቱ ሲገለጥ ሙያውን ያረከሰው እንደሆነ እንጂ አያኮራውም። የመርዝ ጋዝ የተሠራው ክፉ ስብዕና ባላቸው "ጥሩ" ባለሙያዎች ነበር።

ክፉ ሰው መልካም ተግባር ሊወጣው አይችልም። መልካም ተግባር የሚመነጨው ከበጎ ሕሊናና ከንጹሕህ ልብ ብቻ ነው። እርግጥ በጎ ሐሳብ ያመነጨ ሁሉ ወደ ተግባር ሳይቀየር ይችላል። ነገር ግን የበጎ ተግባር ምንጩ በጎ ሐሳብ እና ቅን ልብ ናት። ከኩርንችት በለስ፣ ከበለስም ኩርንችት አይለቀምምና።

"የሀገራችን የትምህርት ሥርዓት ትልቁ ድክመቱ መልካም ሰብዕና ሳይቀርፅ ጥሩ ባለሙያ ለማፍራት ማሰቡ ነው። እናም ብዙ ባለዲግሪዎች፣ ብዙ ባለ ሰርተፍኬቶች ብናፈራም በተግባር ከማይምኑት አልወጣንም። ሰይፉን እንጂ ሰገባውን፣ ጉራዴውን እንጂ አፎቱን አላዘጋጀንም። ያለአፎት የተሳሰው ጉራዴ ያገኘውን ሁሉ ሸረካከተና ብዙ ሳይቆይ ዶለዶመ። ዳግም እንዳይሞረድም ደንደስ አውጥቶ ቀጭ አለ። ነፍስ ሰርተን ሥጋ አልነበረምውና ተንሣፎ መሬት ሳይነካ ሰው ሳይሆን መንፈስ ሆኖ ቀረ።" ይለኝ ነበር ዶ/ር ክብረ በዓል።

ይህን ሳውጠነጥን ለሚቀጥለው የፍለጋ ምዕራፍ ነቢልን ማሳተፍ ወሳኝ ሆኖ ታየኝ። ቦሌ ደርሰን ዕቃችንን ከተረከብን በኋላ የመጀመሪያ ሥራዬ ወደ ነቢል የእጅ ስልክ መደወል ነበር። ስልክ ቁጥሬን ስለሚያውቀው እንሣናና፦

"ሻሎም! ባሩህ ሃባ" አለኝ

"ሻሎም ቶዳ ራባ" አልኩት

ተሣሣቅን።

ስለጉብኙቴ ከጠያየቀኝ በኋላ ወደማታ ማግኘት እንደምፈልግ ስነግረው "በል አረፍ በልና ከተለመደው ቦታ 10 ሰዓት ላይ እንገናኝ" አለኝ።

ወደ ባሕር ዳር ከመመለሴ በፊት እርሱን ማግኘት ወሳኝ ስለበር በቀጠሯችን ተገናኝተን በቀጥታ ከአባ ዮናታን ጋር የነበረኝን ውይይት በዝርዝር ነገርኩት።

"በትንነት እንደነገሩህ መገመት ይቻላል" አለኝና "ታዲያ መቼ ለመሄድ አሰብክ" አለኝ።





"ባለፈው እንደነገርኩህ ሴትዮዋ ስቃይ ላይ ናት። በእኔ በኩል ጊዜ ማጥፋት አልፈልግም እንደተመለስኩ በጥቂት ቀናት መንገዝ አሰብኝ" አልኩት።

"ከደከምህም ተገቢ ነው" አለኝ።

"ነቢል!" አልኩት ድንገት

"ምነው?" አለኝ ግራ ገብቶት።

"አንተ አብረኸኝ መሄድ አለብህ። ያላንተ የኔ ብቻዬን መሄድ ትርጉም የለውም" አልኩት ፈርጠም ብዬ።

"ደስ ይለኛል እንዲያውም ወደ ሰሜን ከሄድኩ ቆይቻለሁ ብቻ..." ብሎ እንደማቅማማት ሲል

"ብቻ ምን?" አልኩ ጭንቅ ብሎኝ

"መጀመሪያ ከቢሮዬ ፈቃድ ማግኘት አለብኝ" አለ።

በወቅቱ በአንድ በነዳጅና ማዕድን ፍለጋ ላይ የተሰማራ የስፔን ዓለማቀፍ ኩባንያ ውስጥ ዋና ጅኦሎጅስት (Chief Geologist) ሆኖ እየሠራ ነበር።

"ፈቃዱንማ ጠይቅ ብቻ እምቢ እንኳን ቢሉህ መሄድህ የግድ ነው" አልኩት።

"አቤት ወንድም ሲሳይ! በቃ አንተ ካወጣኸው መርሐ ግብር ውጭ ሌላው ቦታ የለውም!" አለኝ እየሳቀ።

ትኅትቴንና ችኩልቴን ዶ/ር ክብረ በዓልም እርሱም ያውቁታል። ግን የሚወዱት ይመስለኛል።

ኣሁን እንኳን የጤና ጉዳይ ስለሆነ ነው" አልኩት እንደማፈር ብዬ።

"ግዴለም" አይከለከሉኝም። ብቻ የመስክ ዕቃዎችንና መሣሪያዎችን እስከደራጅ ድረስ ሦስት አራት ቀን ሊፈጅ ይችላል" ብዬ ነው አለ።

ሰፍይተ አልኩና በልቤ

"በል ባሕር ዳር እጠብቅሃለው በተቻለ ፍጥነት ናልኝ" ስለው

"መርሐባ" አለኝ ሁለት እጆቹን ወደ ላይ አንስቶና መዳፎቻቸውን አገናኝቶ።

ጣቶቹ ረጃጅምና ቀጫጭን ስለሆኑ አለንጋ የሚባሉ አይነት ናቸው። ጠይም ፊቱ በሥርዓት ከተያዘው ጺሙ ጋር ደርባባ አድርጎታል። ፊገገቱው ሁሌ አይጠወልግም። "በቃ ያንተ አምፓል ሁሌ እንደበራ ነው" እለዋለሁ ሳገኘው። የራስ ፀጉሩ ሙልት ያለ ነው። አዘውትሮ ሶላትና ስግደት ስለሚያደርስ ይሁን ብቻ የሰውነት ቅርፁ የተስተካከለ ነው። በአብዛኛው ነጭ ሸሚዝ ይወዳል። በያም ወቅት ቤዥ ጀለብያ በስንደል ጫማ ይለብሳል። በተረፈ እንደ ዶ/ር ክብረ በኅል ካልጠየከው በስተተር ስለሃይማኖቱ አንስቶ ካልስማችሁኝ ብሎ አይዘበዝብም ወይም አማኝ መስሎ ለመታዬት አይሞክርም። ከጠየከው ግን እስልምናን ግን ያውቀዋል ከነቢል ወዲያ! ኢትዮጵያዊው ቢላል ሥጋ ለብሶ እንደገና ተወለደ እንዴ ትላለህ!





# ምዕራፍ - ፲፫

ነቢል ቃል በገባልኝ መሠረት የመስክ መሣሪያዎቹን ይዞ ከአዲስ አበባ በአውሮፕላን ተጉዞ ባሕር ዳር ገብቷል። በሚቀጥለው ቀን በተከራየነው የመስክ መኪና ከባሕር ዳር በጠዋት ተነሥተን ደብረ ታቦርንና ላሊበላን አቋርጠን አመሻሹ ላይ ሰቆጣ ከተማ ገባን።

የሰሜን ኢትዮጵያ መልክዓ ምድር ተራራማና ሸንተራራማ የሚበዛው በመሆኑ አድካሚ ቢመስልም ውበቱ አይጠገብም። ባሻገር እያየህ አሁን ደረስኩ ስትል መሐል ላይ ቁልቁል አንደርድሮ ሽቅብ የሚያቃትት መንገድ ይገጥምሃና መንገድህ ሁሉ የህልም ሩጫ ይሆናል።

እንደ ክቢል ላለ የሥነ-ምድር (ጂኦሎጂ) ሙያ ላለው ሰው ግን ትምህርት ቤት ገብቶ በጥሩ አስተማሪ የሰለሳ ትምህርት እንደመውሰድ ነው። ክቢል ሰሜን ኢትዮጵያን በብዛት የሚያውቀው ቢሆንም ይህንን የላስታ-ቀጣ መስመር ግን ሄዶበት አያውቅም።

በእርግጥ የጂኦሎጂ ተማሪ ሆኖ ትግራይን፣ ተከዜ ተፋሰስን፣ የዐባይ ሸለቆን፣ የኦሞ ጊቤን ያላየ ኮርሱን ጨርሷል ለማለት ያስቸግራል ይላል ክቢል። ይህን የላስታ-ሰቆጣ-ዝቋላን መስመር በመጽሐፍ ካልሆነ በስተቀር በአካል አይቶት ስለማያውቅ ደስታው ወደር አልነበረውም። በእውነቱ ያልተጠቀምንበት የቱሪስት መስህብ ነው።

ብዙ ጎብኚዎች በአውሮፕላን ከአዲስ አበባ ላሊበላ መጥተው ወይም ከባሕር ዳር በመኪና መጥተው አሥራ አንዱን ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ጎብኝተው ይመለሳሉ። ነገር ግን የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት የመጨረሻዎች የፍፁምነት ማሣያ ይሁኑ እንጂ ሙሉውን የኢትዮጵያን የዐለትና የቋጥኝ ፍልፍል ኪነ-ሕንፃ ያመለክታሉ ማለት አይቻልም። የላሊበላ ኪነ ሕንፃ ደብረ ሮሃ ላይ ብቻ ሳይሆን ከዚያ የሰፋ መረብ አለው። በምዕራብ ከበለሳው ዞዝ አምባ ጊዮርጊስና ከጃናሞራው ሰርባር በዓለ እግዚአብሔር፣ በስተሰሜን ከጥንታዊ መስቀለ ክርስቶስ፣ በስተደቡብ እስከ ሰዮ ሙጃ የሚሰፋ የኪነ-ሕንፃ ሠንሠለት አለው። የላሊበላን ውቅር አብያተ ክርስቲያናት አጠናሁ ወይም አወቅኩ ለማለት ደብረ ሮሃ ባሉት ብቻ ተነሥቶ ለመናገር ነገሩን ማቅለል ይሆናል።

የአክሱም ሃውልትን ጥበብ ለመረዳት የገርዓልታ የተራራ ሰንሰለቶችን ማጥናት የግድ ነው። ምክንያቱም የመግፈ መነሻዎች (Aspiration) ተራሮቿ ናቸውና። ቀደምት ኢትዮጵያውያን የጥበባቸው መነሻ የሀገራቸው መልክዓ ምድር ስለመሆኑ ግሩም ማስረጃ ነው።





የላሊበላን ጥበብ ለመረዳት ከደብረ ሮሃ ተነሥተህ ወደ ዝቋላ ከሌሎቹ፣ የአክሱምን ሃውልት ጉብኝተህ ገርዓልታን ካላየህ ማግኘት ፈት አያስችህ ተደንቅክ ማለት ነው።

ክቢል በአእምሮዬ የሚመላለሰውን ይህን ሐሳቤን የተረዳው ይመስላል።

የእኛ ሀገር የቱሪዝም ሥራ ነጥብ ላይ ያተኮረ (Spot Tourism) እንጂ መስመር ያለው (Route Based) ነው ለማለት ያስቸግራል። የጉብኝቱ ፕሮግራም ቢሆን ያሉትን ቅርሶች ከሚያዛምዱ ታሪካዊ ጋር መነሻ አያሳየን፣ ከፊት የነበርን ከኋላ መቅረታችንን እያስጨነቀን የምናስጎበኘው በመሆኑ ቱሪስቱን ከማስደነቅ ይልቅ አሁን ያለንበትን ሁኔታ እንዲሳቀቅ የሚያደርግ ነው። በየትኛውም ዓለም ላይ የማያገኙ ቅርሶችን ጽዳት በጎደለው አካባቢ በልመናና በወከባ አጀበን አስጎብኝተን ገንዘብ ለማግኘት የምንጥር ጉዶች ነን" አለ።

ከዚህም በላይ ከዋሻው ያዳለተተ፣ እየፈራረሰ ያለ ግንቦች የቆመ ሃውልት በማሳየት ብቻ የተመሠረተ ነው። ምናልባት ከላሊበላ በተቀር ቤተ መንግሥቶች ውስጥ ምን ዓይነት ምግብና መጠጥ ያቀርብ ነበር? አቀራረቡና አዘገጃጀቱ እንዴት ነበር? የመኝታ ቤት፣ የልፍኝ፣ የማጀ ቤት፣ የባልደረቦ ቁሳቁሶች፣ የአልባሳት ዓይነት በማሳየት፣ የሰው አቀማመጥ በጾታና በማዕረግ በዘዋሪ መልክ አብሮ ሊገኝ ይገባው ነበር። ሕንፃዎቹና ሃውልቶቹ የተሠሩበት ጥበብና ቴክ ከዋሻ ሞዴል (simulation) ያስተተ አይደለም። በጥቅሉ ከዋሻ የሌለው በመሆኑ ቱሪስቱን የማያሳትፍ ከመሆኑም በላይ ቆይታውንም የተጣደፈ ያደርገዋል። የመሠረተ ልማት ችግር፣ ያለንን ሀብት ቆጥረን አለማወቅ፣ ለተፈጥሮ ውበት ያለን ያነሰ ግንዛቤ፣ የሰላምና ጸጥታ ችግር ተዳምሮ ድንቅ ውበትና ጥንታዊ ታሪክ ታቅፈን በድህነት እንሳቀቃለን።" አለ በቁጭት።

የነቢል ንግግር ቁልጭ ያለ እውነት ነው። ባጠቃላይ ለቱሪዝም የሰጠነው ትኩረት እጅግ ዝቅተኛ ነው። ለኢንዱስትሪ ፓርኮች ግንባታ የሰጠነውን ግማሽ ያክል እንኳን ብንሰጥ ኖሮ በገቢ እጥፍ እናተርፍ ነበር። ባለሃብቶች ከውጭ መጥተው፣ ፋብሪካ ተክለው፣ ምርቱ ውጭ ሂዶ ተሸጦ የኢኮኖሚ ሽግግር ወይም ማዕደት (Economic Transformation) እናመጣለን ማለት የዓለምን ውድድርና ሽፍጥ አለማወቅ ነው። ይህ ፖሊሲ ኢኮኖሚያችንን ትንሽ እንቀሳቅሶ ለዋናው በራሳችን ለሚመራው ልማት በመጠኑ ጥሪትና ወረት ይሆን እንደሆነ እንጂ እርሱ ራሱ መሠረት አይሆንንም። የመመራመሪያ መሣሪያውን ራሱ ያልፈለሰፈ ሰው ወይም አገር በምርምር ሲቀድም አይችልም! አዲስ ነገር የሚፈጠረው ራስህ በፈጠርከው መሣሪያና ጥበብ ብቻ ነው። ፋብሪካውን ያልሠራ አገር በፋብሪካው ምርት መወዳደር ከባድ ነው። አንድ ቀን በመለዋወጫ እቃ ችግር መቀደሙ አይቀርም። ተስፋችን በእጃችን እንዲሆን ወደ ድንግል የተፈጥሮ ሀብታችን፣ ታይቶ ወደማይጠገበው መልክዓ ምድራችን፣ ባህላችንና ቅርሳችንን ወደ ማልማት ስንዞር ነው ነጻና መሠረታዊ ሽግግር የምናመጣው። የተፈጥሮ ሀብት ሲባል መሬት፣ መልክዓ ምድር፣ ውኃ፣ የሰው አዕምሮና ጉልበት እንዲሁም ሥነ-ውበት ነው።

የእኔና የነቢል መዳረሻ ከሰቆጣ ከተማ ወደ ዝቋላ በሚወስደው መንገድ 25 ኪ/ሜ ርቀት ላይ የምትገኝ ጥንታዊት ከተማ ነች። በሚቀጥለው ቀን ቁርሳችንን ጥብስቅ አድርገን በልተን ከሰቆጣ ከተማ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ይዘን ካርታችንን ተከትለን ተጓዝን። ከ45 ደቂቃ በኋላ የጉዞ መዳረሻችን አንድ አነስተኛ የገጠር ከተማ መሆኑን ታፔላ ላይ የተጻፈ ጽሕፍ አበሰረን።





‹የሰራኤል ከተማ ማዘጋጃ ቤት› ይላል

ዋናው ምልክት ‹ሰራኤል› የሚለው ነው። የአካባቢው ሰው ‹ሰርኤል› እያለ ነው የሚጠራት።

ከሺህ ዓመታት በፊት ከብዙ ከተሞች በፊት የተቆረቆረች ብረት ተነጥሮ ማረሻ ወገል የተሠራባት፣ አፈር ተቦክቶ ተጠብሶ ልዩ ልዩ ሸክላዎች የተሠሩባት፣ ጥጥ ተፈትሎ ድር ተደርቶ ሸማ የተሸመነባት የዕደ ጥበብ መናኸሪያ ከተማ የነበረች። ከፊት የነበረች ብትሆንም አሁን ከኋላ ቀርታለች። አሁን ላይ ከተማ ናት ብሎ ለመቀበል ያዳግታል። ጥበቧ ተቀድቶ ቢስፋፋም እርሷን ሳያሳድጋት ታሪክ ሆና የቀረች ምስኪን ከተማ ነች። መሥራቾቿ ተሰፋ ቆርጠውባት ትተዋት የሄዱ፣ አዲሶቹ ነዋሪዎቿም ጥበቧን ሳይረዱላት ምሥጢሯን ሳይፈቱ እንደነገሩ የሚኖሩባት ውስጥን የምትረብሽ የታሪክ ቅሪት ናት።

"ይች ናት መዳረሻችን" አልኩት ነቢልን።

"እርግጠኛ ነህ አቅጣጫ ምናምን አልሳትክም?" አለኝ። የተረኩለት ሁሉ ባዶ ተረት መስሎት ይሆናል።

"እርግጠኛ ነኝ" አልኩትና መኪናችንን ከዋናው መንገድ ወጣ አድርገን ወደ ውስጥ ገባ አድርገን አቁመን ወረድን።

ዓለም ከኋላችን ተነሥቶ ከብረት ማንጠር ወደ ኒውክለር ማብላላት ተሸጋግሯል፤ ከሸክላ ሥራ ወደ ሴራሚክና ብርጭቆ ማምረት አድጓል፤ ከሸማ ስራ ወደ ቴክስታይልና ጋርመንት ተመንድጓል፤ ከበሬ ጉልበትና ከዶማ ቁፋሮ ወጥቶ ወደ ትራክተርና ከምባይነር መጥቋል። ‹ሰርኤል› አሁንም ከጀመረችበት ናት። አሁንም በዶማ ተቆፍሮ ይበሳል፤ ጉድጓድ ውስጥ ተቀብሮ ተሸምኖ ይለበሳል፤ በወናፍ ክሰል ተከስሶ



Scanned with CamScanner

ማረሻ ይሠራል፤ አሁንም አፈር ተቦክቶ 25 ኪ/ግ የሚመዝን የቤትን ልጅ ወገብ የሚሰብር እንስራ ይሠራል። አዲስ ነገር የለም ‹ስርኤል› ከተማ። አዲስ ነገር ቢኖር ባፍላዋ ጊዜ ያላየችው ችጋርና ጉስቁልና ብቻ ነው። ሌላው ያገራችን ክፍልም ከስርኤል ብዙ አይሻልም።

ከሁለት ሺ ዓመታት በኋላ የስርኤልን ጥበብ ለማስቀጠል በፖሊሲ ደረጃ የሞከሩት አጤ ቴዎድሮስ ነበሩ። ንጉሡ ሀገርን በስልጣኔና በራስ አቅም ለማነፅ በነበራቸው ራዕይ አፈር አንጥሮ፣ ብረት አቅልጦ መድፍና መንኮራኩር ለመሥራት በጋፋት ሞክረው ነበር። በዚህ ሙከራ የመጀመሪያው መድፍ ቅርፅ ይዞ እንደወጣ ሣይበርድ በስሜት ንጉሡ ተንደርድረው ሂደው ሲስሙት ከንፈራቸው ተላጠ። ከንፈራቸው የተላጠው ራስን የመቻል ህልማቸው ዕውን የሆነ መስሏቸው ነበር። የሳሙት የጋለውን ብረት አልነበረም ወደ ተግባር መለወጥ የጀመረውን ህልምና ራዕይ እንጂ። የለመጠጠው ወላፈን የህልማቸው ልዕልና ከፍታ ነበር። ይሄኔ እንደ አጤ ቴዎድሮስ ምኞትና ጥረት ቢሆን ኖሮ የብረት አረር የሚወረውረው መድፍ ብቻ ሳይሆን ኒውክሌር እንታጠቅ ነበር። ብረት አንጥረን ብቻ ሳይሆን ዩራኒዬም አብላልተን ከጥንታዊ ማንነታችን ጋር የሚመጥን ልዕልና ይኖረን ነበር። ብቻ እንደ ስርኤል በዚያው አንቀላፍተን በዛው ስለቀረን ገና ‹ሀ› ብላ እየተገነባች ያለች ሀገር አሁን ድረስ አንድ የረባ የብረት ማንጠሪያ ‹ጋፋት› እንኳን የላትም። የገበሬ ሀገር ኢትዮጵያ አንድ የማዳበሪያ ፋብሪካ የላትም። ሌላው ቀርቶ አባቶቻችን የሠሩትን ቅርስ መድገም ቀርቶ ቅርሱን ማደስ አቅቶን ጥበብና ገንዘብ ፍለጋ ዕርዳታ የምንጠይቅ ምስኪኖች ሆነናል።

አሁንም ለሀገራችን ባይተዋሮች ነን። ለዕድገታችን ለልማታችን ባይተዋሮች ነን። ፈረንጅና ቻይና አቅደውልን፣ እነርሱው አበድረውን፣ እነርሱ እንደነገሩ ሠርተውልን ለመበልጸግ የምንጥር ባይተዋሮች





ነን። ‹አሜሪካኖች ሲሠሩት ነው እሱ፤ ቻይናዎች ሲገነቡት ነው እሱ፤ የዓለም ባንክ ሲያበድረን ፊትዷል እሱ፤ ሩሲያኖች እንትኑን ሲያዘምኑልን ነው እሱ!› እያልን ተስፋ ምናደርግ አቅመቢሶች ሆነናል።

ራስን ለመቻል ትልቅ ራዕይ የነበራቸው አጤ ቴዎድሮስ ሁሉ ነገር ከእጃቸው ሲያመልጥ ራሳቸውን ያጠፉበትን ሪቮልቨሪ ሽጉጥ ንግሥት ቪክቶሪያ ለወዳጅነት ቀደም ብለው የላኩላቸው ስጦታ ነበር። አጤ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ ሕዝብና ለንግሥት ቪክቶሪያ ወዳጅነት ቢቃትቱም ያገኙት እርዳታ ቢኖር የኋላ ኋላ መጥፊያቸው የሆነውን ሽጉጥ ብቻ ነው። ይህ ነገር እጅግ ተምኔታዊ ነው። ባዕዳን ቢሰጡንም፣ ቢረዱንም፣ ቢያበድሩንም የኋላ ኋላ መጥፊያችን ለመሆኑ ግሩም ማሳያ ይሆናል። ከሌለህ የለህም! ዓለም እኛን ለማበልጸግ ቅንጣት ጊዜና ሀብት አያጠፋም። ከኋላ ያለነውን ጎትተው ከጎናቸው አያቆሙንም። ወዳጅነቱና ዲፕሎማሲውም ቢሆን የራሳቸውን ጸጥታና ሰላም ለመጠበቅ፣ ቁሊጥ እርዳታቸውም ቢሆን ምራሳቸውን ለመገንባት ልዕለ ኃያልነታቸውን ለማስረጽ ብቻ እንጂ ለእኛ ከልብ በማዘን አይደለም።

በሐሳብ መብተክተኬን ትቼ ጥንታዊቷን ከተማ ለመቃኘት ሞከርኩ። የስርኤል ከተማ በቅርብ የተሠሩ የሚመስሉ ከድንጋይ ግድግዳና የቆርቆሮ ክዳን ያላቸው በአስራዎች የሚቆጠሩ ቤቶች አሏት። የኗሪዎቿን ፍላጐት ባያረካም የቧንቧ ውኃ አላት። ብልጭ ድርግም የሚል የኤሌክትሪክ መሥመርም ገብቶላታል። ት/ቤት፣ ክሊኒክ፣ አነስተኛ ሱቆች፣ ወፍጮ ቤት እና የጤኔ ማስታገሻ የዕርዳታ እህል መጋዘኖች አሏት።

አንደ አብዛኛው የዋግ ሕዝብ ችግር የማያደበዝዘው ውበት፣ ድህነት የሚያጠወልገው ፈገግታ፣ ፊቱና የማይጋርደው ተስፋ በነዋሪዎቿ ፊት ይነበባል። ታሪክ ምንም ይበል፣ ኑሮ ምንም ያክል ይክበድ፣ እራፊ ጨርቅ የለበሰው ገላ፣ ያልጠገበው አንጀት የደስታ ፊት ከማሳየት እንግዳን በፍቅር ከመቀበል የማያግድ መሆኑ ሁልጊዜ ይገርመኛል።

መኪናችንን ያዩ ሕፃናት መጥተው መከበብ ጀምረዋል። ነቢል ስማቸውንና ዕድሜያቸው እየጠየቀ ዘና ሲያደርጋቸው ሲጀምር ሹልክ አልኩና ራቅ ብለው የቤታቸውን ግቢ በድንጋይ የሚከቡ ጐልማሳ ሰው አይቼ ወደርሳቸው አመራሁ። ሲያዩኝ ሥራቸውን አቁመው ፈገግ ብለው ላቀረብኩላቸው ሰላምታ አፀፋውን አገውኛ ቃና ባለው አማርኛ መለሱልኝ።

"ዳጎነመ?" አልኳቸው ደግሜ በለቃቀምኩት አገውኛ የበለጠ ዘና እንዲሉ ብዬ።

"እምዜ ናና!" አሉ

"ግሬድ ቀሰውመ?" አልኩ መልሼ

"የይ ቀሰው የን" ብለው የበለጠ ፈገግ አሉ።

የለቃቀምኳቸው የአገውኛ (ኽምጥኛ) ቃላቶቼ አለቁና፡-

"ይህች ከተማ ማን ትባላለች?" አልኳቸው በአማርኛ።

"ስርኤል ሊባኖስ" አሉኝ። ‹ስርኤል› ከሚለው ስም በላይ ‹ሊባኖስ› የሚለው አስደነቀኝ።

"እንዳው አንድ ነገር ልጠይቅዎት ነበር የማላስቸግር ከሆነ?" አልኩኝ





ምን ችግር?" አሉ አሁንም አሁንም ፈገግ እያሉ።

‹ቀጥታ ልጠይቃቸው አልኩና ያልሆነ ጥርጣሬ ቢገባቸውስ› እያልኩ ከራሴ ጋር ስታገል በሐሳብ መንገዴን አይተው፡-

"እምወድህ ሰላም ነህ?" አሉኝ።

አገዎች ስምህን ካላወቁ ‹እምወድህ› ብለው ይጠሩሃል።

"ሹሪ ደኅና ነኝ" አልኩና "እ…እዚህ አካባቢ ቤተ እስራኤላውያን ይኖሩ ነበር ይባላል?" አልኳቸው

"አዎን እንጂ" አሉና "ድሮ ለአባቶቻችን ምጣድ፣ ድስት የሚሠሩ፤ ማረሻ የሚሠሩ፤ ሸማዕቃም እንደዚሁ እነርሱ ነበሩ" አሉ። ትንሽ ቆይተው፡-

"በዚያን ጊዜ ‹ካይላ› ነበር የሚባሉት። ግና እነሱ ‹ካይላ› ሲባሉ አይወዱም" አሉ።

"ዛሬም አሉ እንዴ?" አልኩ።

"እምወድህ የት አሉ! እኛ እጣን ሁነን በርሀቡ ጊዜ በኮረም አድርገው ወዳገራቸው ሂደዋል ሲባል እንሰማለን" አሉ።

"የትኛው ርሃብ የ1977ቱ ወይስ የ1966ቱ" አልኳቸው።

"የበፊቱ ነው፤ እኛ ዕጣን እያለን ነው" አሉ። ወደ ምፈልገው ጥያቄ ለመሄድ ሳቅማማ፤

"አሁን አሁን እየመጡ መቃብራቸውን ያያሉ። እንደ ግንብም ይሠራሉ" ሲሉ ያስታዩን መቆጣጠር አቃተኝና

"የመቃብር ሥፍራቸውን ያውቁታል?" አልኳቸው።

"ሕምወድህ ተገዘየ ታች እኮ ነው!" አሉና በእጃቸው ወደ ደቡብ አመለከቱኝ።

ዙሪያ ጥምጥም ስንዘ የነበረው የመቃብር ሥፍራቸውን ለመጠየቅ ነበር።

"ተለይቶ ይታወቃል?" አልኳቸው።

"አዎን! ታፋፉ ስትደርስ የተካበ እንደ እርከን ያለ አለ፤ ግንቡም ይታይሃል እሱ ነው" አሉ።

ወዲያው ወደ አፋፉ ሩጥ ሩጥ የሚለኝ መጣ። ‹እንዴት ያለ በሽታ ነው?› አልኩ ለራሴ ችኮላዬ ታውቆኝ። በአግባቡ አመሰገንኳቸውና በዚች ውኃ ጠጡ ብዬ ትንሽ ብሮች እጃቸው ላይ አድርጌ ወደ ነቢል እየተጣደፍኩ ስሄድ እስራኤል ኒታንያ ከተማ ከኢትዮጵያውያን አይሁድ መንፈሳዊ መሪ ከአባ ዮናታን ጋር ያደረኩት ውይይትና ምሪት በአዕምሮዬ እየተመላለሰ ነበር።





# ምዕራፍ - ፲፩

አባ ዮናታን በልዩ የንባብ ክፍላቸው እንደተቀመጥን በትዝታ እየተናጡ "ያተረጓጎም ችግር አለ" አሉ።

"እንዴት?" አልኳቸው።

"‹ነበ እስራኤል ውሉደ ኢትዮጵያ› የሚለው ‹ውሉደ ኢትዮጵያ› የተባለው ትክክል ነው፤ ከኢትዮጵያ መወለድን ያመለክታል። ነገር ግን ‹እስራኤል› የሚለው እኛን የሚመለከት ቢሆንም እዚህ የምንኖርበትን ‹እስራኤል› ሳይሆን እዛው ኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸውን ጥንታዊቷን የአባቶቻችን መኖሪያ የነበረችውን ‹እስራኤልን› ነው" አሉ።

ግራ ተጋብሁና "ኢትዮጵያ ውስጥ ቤተ እስራኤላውያን መኖራቸው እውነት ነው ‹እስራኤል › የሚባል ስፍራ ግን ስለመኖሩ አላውቅም" አልኳቸው።

"አየህ የኔ ልጅ! አባቶቻችን በኢትዮጵያ በኖሩበት ዘመን መንደር መሥርተው፣ ከተማ ቆርቁረው፣ ጥበብና ዕምነት ሲያስፋፉ አልፎ አልፎ ከተስፋ ሀገራቸው እስራኤል ስም እየወሰዱ ይሰይሙ ነበር። እናም ‹እስራኤል›፣ ‹ሰይዳ›፣ ‹ቃና› የመሣሠሉት ስሞች ተወስደዋል። ክርስትያኖቹም ቢሆኑ ‹ደብረ ታቦር›፣ ‹ገሊላ›፣ ‹ናዝሬት›፣ ‹ደብረ ዘይት› የሚባሉ ስሞችን ወስደው ሰይመዋል።" አሉ።

"እና ኢትዮጵያ ውስጥ ‹እስራኤል › የምትባል ከተማ ወይም መንደር አለች ማለት ነው?" አልኩ።

"አዎን ዋግ ውስጥ ከቀደሙት የአባቶቻችን የጥበብ የፍልስፍና ማዕከል ከነበሩት ግንባር ቀደም ነበረች። በአባታችን በያዕቆብ ስም ‹እስራኤል› ብለው ሰይመዋት ነበር። በዘመን ሂደት ‹እስራኤል› የሚለው ስም ‹ስርኤል› እየተባለ እንደሚጠራ ሰምቻለሁ። ዋናው ስሟ ግን ‹እስራኤል› ነው" አሉኝ።

"በጣም ይገርማል!" አልኩና "ታዲያ ከዚያ ለመኖሩ ምን ፍንጭ አለው?" አልኳቸው።

"እንዳልኩህ ቤተ-እስራኤላውያን ከጣና በስተሰሜን በደንቢያ፣ በወገራ፣ በበለሳ፣ በወልቃይት፣ በጠለምት፣ በአድዋ፣ በዋግ ከሌላው ህዝብ ጋር ተሠባጥረን ለሺ ዘመናት ኖረናል። የዋን ‹እስራኤል› ከሁሉ ልቃ የጥበብና የፍልስፍና ማዕከል ነበረች። ከአባቶቻችን እንደተነገረን የተከዜ ወንዝ ዳርቻን ዐለትና አፈር በመጠቀም አፈር ማንጠር፣ ብረት





ማቅለጥ፣ ማዕድናትን ማዳቀልና በእሳት መጥበስ የተካኑ ነበሩ። ከዚያ ሌላ በረድ እንዳይመጣ መከላከል፣ ዝናብ ሲጠሩ ደመና መሳብ ሁሉ ችለው ነበር። እርግጥ ይህ ሁሉ ጥበብ ከሰሎሞን ይዘውት ከመጡት በተጨማሪ ከጥንት ኢትዮጵያውያን ጥበበኞች ጋር በማስተባበር ያደገ እንደነበር ግልጥ ነው።"

"እሺ" አልኩ በመገረም።

"እናም ይህ ‹ዕብነ ኩሕል› የተባለው ከሌሎች የጥበብ ማዕድናት አንዱ ነበር። ስለ ብዙ አስደናቂ ነገሮች ልጅ ሁነን ብንሰማም ካደኩ በኋላ በደንብ የማውቀው ነገር ቢኖር ስለ ‹ዕብነ ኩሕል› ጉዳይ ነበር። በአንድ አዛውንት እጅ ተቀምጦ የነበረ ቢሆንም ‹ለምንና እንዴት መጠቀም እንደሚቻል› የሚያመለክተው ዕውቀት በእኛ ዘንድ በአግባቡ አልተፃፈም ነበር። ነገር ግን በገዳማት የነበሩ ሊቃውንት ለመዛግብት ጠባቂዎች ስለነበሩ ሳይጽፉት አልቀረም።" አሉና ራሳቸውን በትዝታ ሲያወዛውዙ ቆይተው፦

"ለማንኛውም በሰሜን ኢትዮጵያ ረኃብ ሲከፋ፣ አዛውንቶችም በሞት ሲያልቁ፣ የእርስ በርስ ጦርነት እየሰፋ ሲመጣ ሁላችንም ወደ አባቶቻችን ሀገር ወደ ተስፋ ምድራችን ወደዚህ ለመምጣት ትኩረታችን ሆነ። እናም ቀድመው የወጡት ከዚያች ከእስራኤል አካባቢ የሚኖሩት ወገኖቻችን ናቸው" አሉ።

ይህን ሲናገሩ የሆነ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት እንደገና ተሰማኝና፦

"እንደዚያማ ከሆነ ‹ዕብነ ኩሑሉን› ወደዚህ ይዘውት መጥተዋል ማለት እኮ ነው?" አልኳቸው።

"አይ አላመጡትም" አሉ ፊርጠም ብለው።

"እንዴት እርግጠኛ መሆን ይቻላል?" አልኩ።

"አየህ የኔ ልጅ! መጀመሪያ አካባቢ ከኢትዮጵያ የወጡትም ሆኑ ኋላ ላይ የወጣነው እኛም የተሰሩ ምድራችን ተዚህ ስለመድረሳችን እርግጠኞች አልነበርንም። ተዚህ ሲቀበሉንም የለበስነውን ልብስ ሳይቀር አስወልቀውና አቃጥለው አዲስ ልብስ ይሰጡን ነበር። እና በዚያ ሁኔታ ጥንታዊ የሆኑ፣ የምሥጢር ዕቃዎች፣ ልዩ ማዕድናትን በኖርንበት አካባቢ ቀብሮ መውጣት ስልት ነበር" አሉ። ቆይተው

"ከኢትዮጵያ ይዘነው የወጣነው ነገር ቢኖር ናፍቆትና ትዝታ ነው ያልኩህን ልብ በል። አካላችን ተዚህ ቢሆንም የልቦናችን ግማሽ አሁንም ኢትዮጵያ ውስጥ እኮ ነው" አሉ።

የሆነ ተስፋ እንደገና ተሰማኝና፦

"እና እንዴትና የት የማገኘው ይመስለዎታል? ያው የተፈለገው አንዲት ምስኪን ሴትን ከስቃይ ለመገላገል ነው። ስቃይና መከራዋ ደግሞ በዛ!" አልኩ፤ የበለጠ እንዲራሩ ብዬ።

"አውቃለሁ፤ ሁሉንም ተረድተነዋል። ለበጎ ነውና መሬት ውስጥ ተቀብሮ ከሚኖር አጠቃቀሙን የሚያውቁ አባቶች ተተገኙ ማለፊያ ሐሳብ ነው እኮ! የእኛም ፈቃድ ሆኗል" አሉ።

"እንግዲህ እኔም በዝርዝር አላውቀውም። ግን አንድ ትልቅ የብራና መጽሐፍ ገልጠው እያነበቡ እንደነገሩኝ አስታውሳለሁ" አልኩ፤ የበለጠ ምኞት እንዲሰማቸው ብዬ።





"ማለፊያ ነው! የኢትዮጵያ ገዳማት እኮ መዛግብት ላይ ጠንካሮች መሆናቸውን አውቃለሁ።" አሉ ደግመው ረጅም ጺማቸውን እየላጉ።

"እና ዋግ ‹እስራኤል › ከተማ ሄድኩ እንበል ከዚያስ?" አልኳቸው።

"አንድ ትልቅ አባት ነበሩን ተዚያ አካባቢ መጥተው ተዚህ ደርሰው ዕድሜ የጠገቡ እና ..." አሉና በትዝታ ነጎዱ።

በትዕግስት መጠበቅ ነበረብኝ። አሁን ወደ ዋናው ነጥብ እየተጠጋሁ ስለሆነ ስሜታቸውን የሚያደፈርስ ጠባይ ላለማሳየት አደብ ገዝቼ መጠበቅ ያዝኩ።

ከሐሳባቸው እንደመባነን አሉና፦

"ሁልጊዜ ሳገኛቸው አገር ይዳንበት፣ ትውልድ ይጠቀምበት፤ የኢትዮጵያ አንጡራ ሀብቷ ንብረቷ ነውና ለእኛም ማስታዎሻ ይሆን ዘንድ ለጥበበኛ እንድትነግር ይሉኝ ነበር" አሉ።

"እኔ እንኳን ጥበበኛ አይደለሁም መልእክተኛ ነኝ። ብቻ የሴትዮዋ ስቃይ ያሳዝናል" አልኩ።

ዝም ብለው ፈገግ ብለው ሲያዩኝ ጊዜ ‹ዱሮስ አንተን ማን ጥበበኛ አደረገህ?› ያሉኝ መስሎኝ ተሳቀቅኩ።

"ግዴለም አንተም ትጋትህ ማለፊያ ነው! የላኩህም የሚሠሩትን የሚያውቁ ናቸው" አሉና ዝም ሲሉ፤

"እና አድራሻ አልነገሩዎትም" አልኳቸውና ‹ዋናው ጉዳይ እሱ አይደል› አልኩ ለራሴ።

"መቃብራቸው ከአፈር ገደል ሥር ነው፡፡ ተዚያ በነሐስ ሳጥን ታገኘዋለህ" አሉ፡፡

"ያው የመቃብር ስፍራ መቼም ሰፊ ነው፡፡ ያን ሁሉ መቆፈር አይቻልም እንዲያው የተለየ ምልክት ይኖር ይሆን" አልኩ፡፡

"የተለየ የምነግርህ ምልክት የለም የኔ ልጅ ድካም ይኖርብሃል!" አሉ፡፡

‹እንዴት ያለ ነገር ነው? እንደ ፍልፈልና አውጪ ያገር መቃብር ልቆፍር ነው እንዴ?› ብዬ ለራሴ አጉረመረምኩ፡፡

"አንድ የማውቀው ነገር ቢኖር..." አሉና ትንሽ ሲያቅማሙ ቆይተው "የእኛ አባቶች የሆነ ነገር በምሥጢር ሲቀብሩ ለምልክት ይሆን ዘንድ ለየት ያሉ ዕፅዋትን በላዩ ላይ ወይም ከጉኑ ይተክላሉ" አሉ፡፡

"ምን አይነት ዕፅዋት?" አልኩ ፈጠን ብዬ፡፡ ‹ዕፅዋት እማ ዕጣ ክፍሌ ናቸው› ብዬ ሰፍ እያልኩ፤

"እርሱን ለይቼ አላውቅም፡፡ እንግዲህ ተዚያው ሂደህ ማስተዋል ነው" አሉና ፈገግታቸውን ለገሱኝ፡፡

ፈገግታቸው የውይይታችን ማብቂያ መድረሱን ወዲህ ደግሞ ‹እስቲ የዕፅዋት ተመራማሪ ነኝ ትላለህ እናያለን› እንደማለት አድርጌ ተረጐምኩት፡፡

"ሁለት ነገር ልብ በል፤ በቀን በፀሐይ እንዳትቆፍር፣ ስታገኝ ደሞ የተጠየከውን ብቻ ለይተህ ውሰድ፡፡" አሉ፡፡





ይሆን ተናግረው ሲጨርሱ ነበር መስህለ-ማርያም ውይይታችን እንድንቋጭ በር ላይ ሆኖ ያሳሰበችን ፡፡

በዚህ የአባ ዮናታን ምሪት መሠረት ነው ከነቢል ጋር ወደዚች ከተማ የመጣነው፡፡ እስራኤል የአሁኗ ‹ስርኤል› የቤተ አይሁዶችን ስም ይዛ ከመኖሯም በላይ ክርስትና በአካባቢው ሲስፋፋ ቤተ ክርስትያን ሊተከል የድንግል ማርያም እናት ሀገር የሆነውን ‹ሊባኖስ› የሚለው ስም ዕላት ተቀርፆለት ‹ስራኤል ሊባኖስ› መባሉ የታሪኩን የማይናወጥ መሠረት አመላካች ነው ማለት ይቻላል፡፡

ነቢልን በሙያው ካደነቅኩበት አንዱ ‹ዕብነ ኵሕል› በተከዜ ተፋሰስ ሊኖር ይችላል ብሎ የገመተውን አባ ዮናታን በዚሁ በተከዜ ተፋሰስ ተነጥሮ ተዘጋጅቶ መኖሩን ስላረጋገጡልኝ ነበር፡፡

ከዚህ በኋላ የነቢል ዋናው ርዳታው በያዘው መሣሪያ ፍንጭ መፈለግና ስናገኘው ደግሞ ራሱ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ የእኔ ሥራ ደግሞ የማላውቀውን ልዩ ዕፅዋት በአንክሮ ከመቃብሩ አካባቢ መፈለግ ይሆናል፡፡

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)



Scanned with CamScanner



# ምዕራፍ - ፲፫

በሕፃናት ተከቦ የደራ ጨዋታ ይዞ የነበረውን ነቢልን ጠቀስ አደረኩና ወደ መኪና እንዲገባ አመለከትኩት። ልጆቹን እየጨበጠ ‹ቻው ቻው› አለና መኪናውን ከፍቶ ገባ።

ወደ ደቡብ እያመለከትኩ፡-

"የመቃብሩ ሥፍራ በዚያ አቅጣጫ ነው" አልኩና መኪናውን አስነስቼ ወደ ደቡብ ትንሽ እንደነዳሁ በአካባቢው ከሚገኘው ትምህርት ቤት አጥር አካባቢ የዛፍ ጥላ ፈልጌ አቆምኩ። በል መሣሪያህን አውርድና አዘጋጅ አልኩት።





ነቢል በባትሪ የሚሠራውን ልዩ ልዩ ማዕድናትን የሚያነፈንፈውን መሣሪያውን አወጣና መኪናውን ቆላልፈን ወደ አፋፉ ስንጠጋ ከአፋፉ ደረት እስከ ግርጌ የድንጋይ እርከን የተሠራበት እልፍ አልፎ ዕፅዋት የበቀሉበት የመቃብር ስፍራ ዝምታውን ይዞ ለዘመናት ከታቀፈው ምሥጢሩ ጋር ቁልቁል ታየን። የመቃብር ስፍራ ነው ለማለት ያስቸግራል። የተለመደው የመቃብር ድንጋዮች አይነት የሉም። ብቻ ከወደ ታች ሦስት በስሚንቶ ግንብ የተሠሩ የመቃብር ላይ ሃውልት መሣይ ነገሮች አሉ። አንደኛው ሃውልት በመቃብሩ አንፃር ከመሬት ከፍ ብሎ በድንጋይ ተሠርቶ የተለሠነ ነው። ሁለተኛውና ሦስተኛው ደግሞ በመቃብሩ ልክ የተገነባ ከአራት ማዕዘን ላይ ሌላ ቁመቱ ረዘም ያለ ግንብ ተገንብቶ ጫፉ ላይ ግዝረትን የሚያሳይ ቅርፅ ተሠርቶለታል። ሁሉም በድንጋይ የተገነቡ ሲሆን በሲሚንቶ ተለስነው ነጭ ኖራ ተቀብተዋል። እነዚህ ግንቦች አካባቢው መቃብር ለመሆኑ ያመለክቱ እንደሆን እንጂ ከዚያ ውጭ ዝም ብሎ ጋራ ሊመስል ይችላል።

ትንሽ ወረድ እንዳልን አካባቢውን እያመላከትኩ፡-

"ይሄ እንግዲህ ለዘመናት የቤተ-እስራኤላውያን ትውልዶች ሲቀበሩበት የነበር ስፍራ ነው። ብዙ ምሥጢር የያዘ የአይሁዶች መካነ መቃብር ነው" ብዬ ሳልጠየቅ እንደማነብነብ ስል፤

ነቢል ቀጠል አድርጎ፡-

"በሕይወቱ እምጠላውና የምፈራው ስፍራ ቢኖር መካነ መቃብር ነው። እንዲያው ምን አይነት ሰው ነህ ግን እዚህ ይዘኸኝ የመጣህ?" አለ። መሬቱን ሲረግጥ ከሥር የተቀበሩት ሰዎች የሚያማቸው ይመስል ተጠንቅቆ ነው። ሁኔታውን አየሁና፡-



Scanned with CamScanner

"ረግጠህ እንዳታሳምማቸው እያየህ ተራመድ" አልኩት።

"ቀልደህ ሞተኻል! ምንድን ነው አሁን በዚህ ሰዓት መቃብር ስፍራ መምጣት" አለ።

ሁኔታውን ሁሉ ሳየው ምቾት የተሰማው አይመስልም። ዘና እንዲል ብዬ፦

"ስማ ነቢል! ታዋቂው የካሪቢያን ፕሮቴስታንት ሰባኪ ዶ/ር ማይልስ በአንድ የቀብር ሥነ-ስርዓት ላይ፦ ‹የዓለም ሀብት ያለው የዐረቦች የነዳጅ ጉድጓድ ውስጥ አይደለም ወይም የኮንጎ ማዕድን ማውጫ ወይም የደቡብ አፍሪካ የአልማዝ ጉድጓድ ውስጥ አይደለም። የዓለም ሀብት ያለው በመካነ መቃብር ውስጥ ነው ብሏል።›

አየህ! እዚህ ያልተፈታ ህልም፣ ያልተኖረ ራዕይ፣ ያልተቀነቀነ ዜማ፣ ያልተጻፈ ድርሰት፣ ያላለቀ የኪነ ሕንፃ ንድፍ ተቀብሯል። እርግጥ ይህን ብንቆፍር የፈረሰ አፅም እናገኝ ይሆናል። አሳዛኙ ጉዳይ ግን ህልሞቻቸውንና ትልሞቻቸውን አናገኝም። ሲሞቱ ተናዘው ይሆናል። ቢሆንም የሠሩትን ኃጢያት ለስርዬት ወይም ያፈሩትን ሀብት ለውርስ ይነግሩን ይሆናል። ህልሞቻቸውንና ራዕዮቻቸውን ግን አይነግሩንም። እናም እየተራመድን ያለነው ባልተኖረ ህልም፣ ባልተነገረ ዕውቀት ላይ ነው።" አልኩና

"ያም ሆነ ይህ ነቢል! አንተ ሙስሊም ነህ፣ እኔ ክርስቲያን ነኝ፣ እነርሱ ደግሞ" በእጣቴ ወደ መሬት እያመለከትኩ "የአይሁድ ዕምነት ተከታይ ነበሩ። ብዙ ልዩነቶች ቢኖሩንም የሥጋችን መዳረሻ የሁላችንም የመጨረሻ ማረፊያ (Common Destiny) የሆነውን የመቃብር ስፍራ





ለምን ትፈራለህ?" አልኩት።

"ወንድም ሲሳይ! ስለ አላህ ብለህ መፈላሰፍክን ተውና የምንሠራውን ሠርተን ከዚህ እንውጣ" አለኝ።

ከትከት ብዬ ሳቅኩና፦

"እሺ ይሁን ወደታች ዝቅ እንበልና መሣሪያህን ሥራ አስጀምር፣ እኔም ምልክቶችን ልፈልግ" አልኩ።

ነቢል የያዘው መሣሪያ አሠራሩ እንደሚከተለው ነው። መጽሐፍ የምታክል ኮምፒውተር ጫፉ ላይ ስፌ ቀለበት ያለው ዘንግ ጋር በኬብል የተያያዘ ነው። መጀመሪያ ከተፈለገው አካባቢ ቀለበቱን መሬት ላይ ጠጋ አድርጎ በማንሳፈፍ ኮምፒውተሩ ላይ ኖርማላይዝ በማድረግ ወይም ፕሮግራም ማድረግ ያስፈልጋል። ትንሽ ቆፍሮም እንደዚሁ ፕሮግራም (Train) ይደረጋል። ከዚህ በኋላ ይህ መሣሪያ መጀመሪያ ከሚያውቀው የድንጋዩና የአፈር ማዕድን ውጭ ባዕድ ነገር ተቀብሮ ከሆነ ይጮኻል። ከሌለ ግን መጀመሪያ የሚያውቀው የአፈርና የዐለት ዓይነት ከሆነ ዝም ይላል ማለት ነው። ነቢል በተደጋጋሚ መሣሪውን አፈርና ድንጋይ አካባቢ እያቀረበ ፕሮግራም አደረገ።

አስተካክሎ እንደጨረሰ፦

"የት አካባቢ ልጀምር?" አለኝ።

"ቆይ እስኪ ትንሽ አካባቢውን ላጥናው" አልኩትና ከላይ ወደ ታች፣ ከጐን ወደ ጐን እርከን እንደ ሹርባ የተሠራበትን ዳገታማ ስፍራ ላብ እየዘፈቀኝ ጉልበቴ እየተብረከረከ ፈተሽኩት።

ምንም ስሜት የሚሠጥ ፍንጭ አጣሁ። እንደገና ወደ አፋፉ ጫፍ ወጣሁና ቁልቁል ስመለከት ብቸኛ የሆኑት ሦስቱ የድንጋይ ሃውልቶች ሦስት ማዕዘን ያለው ቅርስ ይዘው እንደተገነቡ አስተዋልኩ። ምሥጢሩ ከነዚህ ሃውልቶች እንደማይርቅ ልቤ ነግሮኝ እየተንደረደርኩ ቁልቁል ወረድኩና የሃውልቶቹን ዙሪያና በመካከል ያለውን ሥፍራ በደንብ ፈተሽኩት። ሃውልቶችን ይገኙ በመካከላቸው ያለውን ርቀት ስለካ ሁለቱ ጐኖች እኩል ሆኑ፤ ‹አይሶስለስ ትሪአንግል› የሚባለውን አይነት ቅርፅ እንደሚሠሩ ተረዳሁ። ሦስተኛው ጎን በታች በኩል ሁለቱን ሃውልቶች የሚያገናኝ ሲሆን መካከሉ ላይ ትኩረቱን የሚስብ ዕፅ አየሁ። በመጀመሪያ ትኩረቱን የሳበው ከሁለቱ ሃውልቶች እኩል ዕርቀት ላይ ያለ መሆኑን ስለካው ስላረጋገጠልኝ ነበር። ዕፁን ጠጋ ብዬ ሳየው በቅርብ የለመለመ ግንድና ቅጠል ያለው ነው። ምንነቱን ለመለየት የቅጠሉን ዓይነትና መዋቅር በማስተዋል ላይ ሳለሁ የሆነ ነገር አዕምሮዬ ውስጥ ይተራመስ ጀመር። የዚህን ዕፅ ቅጠል የሆነ ቦታ በእርግጠኝነት አይቸዋለሁ።

ፀሐይዋ ወደ መኻል አናቱ ላይ ደርሳለች። ዋግ እንኳን በቀትር ረፋድ ላይም የፀሐዩ ንዳድ አይቻልም። በዚያ ላይ ዳገት ስወጣና ስወርድ ስለቆየሁ ሰውነቱ ዝሏል። አዕምሮዬ ዕፅዋን ያየሁበትን ሥፍራ ፍለጋ ይባዝናል። ልክ የሆነ የዕቃ መጋዝን ላይ የተደረደረውን ኮተት እያተራመሰ እንደሚፈልግ የሽቀጥ ነጋዴ ውስጤ ተተራማመሰ። ከአንደኛው ሃውልት ላይ ቁጭ ብዬ ራሴን እየፎከትኩ እታገላለሁ።

ነቢል በመነፀር /አቅርቦ የሚያሳይ መሣሪያ/ አካባቢውን አሻግሮ እያየ ያስሣል። የሆነ ነገር ውልብ አለብኝ። አእምሮዬ ውስጥ ድንገት ከግራ ወደ ቀኝ፣ ከቀኝ ወደ ግራ ውልብ ውልብ የሚል አረንጓዴ ምስል ታየኝ። ዐይኔን ጨፍኜ ወደ ውስጤ ሳይ ብልጭ አለልኝ።





"ብጣም ይገርማል!" ብዬ አፌን ከፍቼ ፈዝገፔ ቀረሁ።

በለሳ ከተራራው ሥር በታላቁ ገዳም ለዚህ ተልዕኮ ከመላኬ በፊት ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ተጠግቼ የዕለቱ ስንክሳር ሲነበብ አባ አካለ ወልድ ከወንበሩ ላይ ቁጭ ብለው ባንድ እጃቸው እንደ ጭራ እያወዛወዙ ዝንብ ሲከለከሉበት እንደነበር አስታወስኩት። እስከ ማታ ድረስ ከእጃቸው እንዳልተለየ በደንብ ትዝ አለኝ። ‹በእርግጠኝነት ዝንብ ለመከልከል አልነበረም የያዙት፤ ለእኔ ለሚገጥመኝ ለአሁን ሥራዬ ፍንጭ እየሰጡ ነበር ማለት ነው› ብዬ አመንኩ።

የዕፅዋን ምንነት ዙሪያዋን እየዞርኩ ለማየት ሞከርኩ። ወደ መሬት በእጀ ቆፈር ቆፈር ሳደርግ ድንች የመሠለ ጠንካራ ሥር መሠረት እንደላት ተገነዘብኩ። ባለኝ ዕውቀት ሳይንሳዊ መጠሪያዋንና ምድቧን ለመለየት ሞከርኩ በፍፁም አልቻልኩም። አባ አካለ ወልድ ቅርንጫፏን ይዘው ከማየቴ በፊት ከዚህ ቀደም የትም ቦታ አይቻት አላውቅም። ይሁን እንጅ አጠቃላይ ውጫዊ መዋቅሩን (Morphology) በማየት እንዲህ ዓይነት ዕፅዋት ቋሚነታቸውን ለመጠበቅ ድርቅ በሚሆንበት ሰዓት በቅጠላቸውና በግንዳቸው ያከማቹትን ካርቦሃይድሬት ወደ ሥራቸው ወስደው በማከማቸት (Translocation) ከመሬት በላይ ያለውን አካላቸውን አድርቀው መጥፎ ወራትን ሥረ መሠረታቸውን ጠብቀው ያሳልፉና እርጥበት ሲመጣ እንደገና ያቆጠቁጣሉ። በዚህ ችሎታቸው ቋሚ ተክልነታቸውን ለረጅም ዘመን ያስጠብቃሉ። የቅጠሉ ሽታ ደስ አይልም። ቅርንጫፉንና ከሥሩ አንድ ድንች የሚያክል አወጣሁና ፎቶ አንስቼ የዕፅዋትን ዝርያ በመለየት እጅግ ለተካነው ጓደኛዬ ቶሎ ለይቶ እንዲነግረኝ ከሚያሳስብ መልዕክት ጋር በቴሌግራም ላኩለት።

ድንገት ብድግ አልኩና፦

"ነቢል ቶሎ ናማ ወደዚህ" አልኩ በእጄ ጭምር እያጣደፍኩ።

"ይህን ዕፅና ዙሪያውን በደንብ ፈትሽልኝ" አልኩት።

ሁሉን ነገር ገጣጥሞ መሣሪያውን አስተካክለና መሬቱን እየነካካ ዙሪያውን ሲዞር ትንሽ ድምፅ ያሰማና ይጠፋል። እስኪ ድንጋዮችን በደንብ ልቀማቸው አለኝ። ዙሪያውን የተጐነፉትን ኮረቶች ሙልጭ አድርጌ ለቀምኳቸው። ነቢል እንደገና ሲሞክር ባዕድ ነገር ስመኖሩ ፍንጭ የሚሰጥ ምልክት ለማን።

"እንዴት ነው?" አልኩት።

"ለየት ያለ ነገር ተቀብሯል። ነገር ግን ከአንድ ሜትር በታች መሆን አለበት" አለኝ።

"ለምን?" አልኩት።

"ይህ መሣሪያ ውጤታማ ማነፍነፍ የሚሠራው እስከ አንድ ሜትር ጥልቀት ነው። ከዚያ በላይ ከሆነ ምልክቱ ደካማ ይሆናል። ሆኖም አሁን ያየነው ምልክቱ ግልፅ ነው የበለጠ እርግጠኛ ለመሆን መቆፈር አለብን" አለ።

እኔ ግን ዕፅዋን እንደ ምልክት ስለወሰድኩ አባ ዮናታንም የነገሩኝ ይህንኑ ስለነበር ጥርጣሬ አልነበረኝም።

"ለማንኛውም አሁን መቆፈር አንችልም" አልኩት።

"ለምን?" አለኝ።





ገመጀመሪያ የመቃብር ስፍራ ነው። ስንቆፍር ብንታይ ለአካባቢው ሰው ጥሩ ስሜት አይሰጥም። ሲቀጥል አባ ዮናታን ቀን በሁለይ እንዳልቆፍር ነግረውኛል" አልኩ።

"ታዲያ ምን አሰብክ?" አለኝ።

"አሁን እንሂድና አረፍ ብለን ውለን ሰው ከተኛ በኋላ ማታ እንመጣለን" አልኩ።

"እግዚኦ! በጨለማ ወደዚህ የመቃብር ስፍራ እንምጣ እያልክ ነው?" አለ በመገረም።

"ምን ችግር አለው! ለሁሉም የሚመች ማታ ነው" አልኩት።

"እኔ አልመጣም! ራስህ ብቻህን ትመጣለህ። ለአሁኑም እየቀፈፈኝ ነው እንኳን በጨለማ ልመጣ" አለና መሣሪያውን መሸካከፍ ጀመረ።

መምጣቱን ባይወደውም ብቻዬን ስመጣ ጨክኖ መቅረት እንደማይሆንለት አውቃለሁ።

"እና እኔስ ብቻዬን የመምጣት ግዴታ አለብኝ?" አልኩት የእውነት የተቆጣሁ መስዬ።

"እኔ እኮ አይደለሁም በየገዳማቱ እየዞርኩ ተዘግቶ የኖረ ምሥጢር ለማወቅ ስዳክር የተያዝኩት" አለኝ እየሳቀ።

እንዲህ እየተቀላለድን የመቃብሩን ስፍራ ለቀን ዳገቱን ወጥተን ይልዳላው ስፍራ ስንደርስ አንድ አርሶ አደር ከወጣቶች ጋር ድንጋይ ሲፈልጡ አየሁና ወደ እነርሱ ሄጄ ዕፅዋን እያሳየሁ 'ምንድናት?' ብዬ ጠየኳቸው። ተቀብለው አይተው የአካባቢ መጠሪያ ስሟን ሲነግሩኝ

‹ለምን ጥቅም ይውላል?› አልኳቸው፡፡

"አይ! ደሞ እሱ ለምን ጥቅም ይውላል?" አሉ፡፡

"እንዴት ምንም ጥቅም የለውም? " አልኩ

"መርዝ እኮ ነው! ሰውም ኸብቶችም ተሳሳተው ከበሉት ደም እስተፍቶ ወዲያው ነው ፍግም የሚያደርግ እና ኸብቶችም አሽትተው ነው የሚተውት" አሉኝ፡፡

ይኸን ሲነግሩኝ በአዕምሮዬ የሆነ ነገር እየተመላለሰ ነበር፡፡ "ልክ ነው!" አልኩ ለራሴ ሳይታወቀኝ፡፡

"ምኑ ነው ልክ?" አለኝ ነቢል ሳላስበው የተናገርኩትን ሰምቶኝ ኖሮ፡፡

"እየውልህ ነቢል! ይህ ዕፅ ድርቅ እንዳያጠፋው የራሱ ተፈጥሮአዊ ስልት አለው፡፡ በሥሩ ራሱን ደብቆ የመቆየት ሰውና እንስሳት እንዳያጠፉት ደግሞ እጅግ መርዛማ ስለሆነ ራሱን አስከብሮ ይኖራል፡፡ እናም ዘመናትን የሚሻገር ዕቃ ለመቅበርና እንዳይጠፋህ ምልክት ለማድረግ ይህን ዕፅ መጠቀም ትልቅ ስልት ነው" አልኩት በእጄ የያዝኩትን ድንች መሰል ሥረ-መሠረት (Root stock) እያሳየሁ፡፡

"ይገርማል!" አለ ነቢል፡፡

መኪናችን ደርሰን ዕቃችንን አስቀምጠን ትንሽ አረፍ እንዳልን የዕሁን ፎቶ የላኩለት ጓደኛዬ ሳይንሳዊ መጠሪያውን እስከ ማብራሪያው ድረስ በቱለይ ከላይ እኔ እንደገመትኩት ጠባይ ያለው ቋሚ ተክል መሆኑን ገልጾ ላከልኝ፡፡ መጨረሻ ላይ ግን በወፍራም ቀለም (Bold) የተጻፈው መልዕክት እንዲህ ይላል፡-





'That is a very toxic plant, take care of it'

'እጅግ መርዛማ ዕፅ ስለሆነ ጥንቃቄ አደርግ' የሚል ነበር፡፡

አሁን የምፈልገው ነገር በእርግጠኛነት ከዚህ ዕፅ ሥር እንደተቀበረ አመንኩና በትልቅ ተስፋ ምሽቱን መጠባበቅ ያዝኩ፡፡

ወደ 12 ሰዓት አካባቢ ከዋናው መንገድ ዳር ካለች አነስተኛ ምግብ ቤት እራታችን በሽሮ ወጥ በላዩ ላይ ስኳር የበዛበት ወፍራም ሻይ ጠጥተን አደላደልን፡፡ እርግጥ ብስኩቶችና ውኃ ይዘን መጥተን ነበር፡፡ ከተገኘ በሚል ነው ምግብ ቤት የፈለግነው፡፡ የራታችን ነገር ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ ገደሉ አፋፉ ጠጋ ብሎ ከሚገኝ የአርሶ አደር ቤት መኪናችንን አስጠግተን ‹የውኃ ጥናት ለማካሄድ የመጣን› መሆናችንን ተናግረን እንዲፈቀድልን ጠየቅን፡፡

ሳያንገራግሩ ፈቀዱልን፡፡ ቤት እንድንገባ ሲያነጣጥሩ ሲገቡ ሲሉ፡-

"አይ እኛ የምናድረው መኪና ላይ ነው" አልኩኝ፡፡

"እንዴ! ቤት እያለ?" አሉ፡፡

"ግዴለም መኪና ላይ ዕቃ ስላለ ለመጠበቅ ብለን ነው" አልን፡፡

"እንደዚያም ተሆነ እናንተ ቤት እረፉ፡፡ እኔ ውጭ መኪናውን እጠብቃለሁ" አሉ ደጉ አባዎራ፡፡

ነገር ተበላሸ አልኩና፡-

"አይ ግዴለም! የመኪናው ወንበር ለጉናችን ስለሚመች ነው" አልኩኝ፡፡

"እርሱማ ከእኛ ደረቅ መደብ ይሻላል፤ እንዲያው ብርዱ.." ሲሉ

"ችግር የለም በቂ ልብስ ይዘናል አያስቡ" ብለን አሠናበትናቸው።

ትንሽ ቆይተው ስንዴ አስቆልተው ‹እስኪ ይችን ቆርጥሙ› ብለው አመጡልን።

ነቢልም እኔም በሁኔታቸው ልባችን ተነካ።

"ምናለ ለሰጪ ቢሰጠው!" አልኩ በጥልቅ ስሜት።

የመኪናችን የኋላ ወንበር ተዘርግቶ እንዳልጋ የሚሆን የመስክ መኪና ስለሆነ አልተቸገርንም። የስንዴ ቆሏችንን እየቆረጠምን የባጥ የቆጡን ስናወራ አመሸን።

ጀንበሯ ስትጠልቅ ጭልምልም ብሎ የነበረው አካባቢ ወደ ሦስት ሰዓት ላይ በጨረቃ ብርሃን ወገግ ማለት ጀመረ። የቤቱ ባለቤቶች መተኛታቸውን ስናረጋግጥ ቀስ ብለን እኔ መቆፈሪያና አካፋ ነቢል መሣሪያውን እና የእጅ ባትሪ ይዘን ሹልክ ብለን ወደ አፋፉ አመራን።ከአፋፉ ወርደን ወደ መቃብሩ ስፍራ እስክንጠጋ ድረስ ድምፃችን እንዳይሰማ አልተነጋገርንም፤ ባትሪም አላበራንም ነበር።

ከመቃብሩ ክልል ገብተን አንድ ሁለት እርከኖችን እንደወረድን ከፍተኛ ንፋስ ይነፍስ ጀመር። ንፋሱ ከእጽዋቱና ከዲንጋዩ ጋር ሲጋጭ የሚፈጥረው ድምጽ የሚያስፈራ ግርማ አለው።

‹ሽ...ሽ.. ሲ....ሲ.... ሩ....ሩ› ይላል።

"ነቢል" አልኩት እንደማንሾካሾክ ቀስ ብዬ ።





"ምንድን ነው?" አለኝ። ሁሉን ነገር አልወደደውም። ጸሎት ነገር የሚያየርግም መሰለኝ።

"የሙታን መንፈስ እኮ በየጊዜው መቃብራቸውን ማታ ላይ ይጎበኛሉ ይባላል" አልኩት።

"እንዴት? ለምን?" አለ ግራ እየተጋባ።

"በአይሁድ አፈ-ታሪክ በተለይ በሰው እጅ የተገደሉ ግፉዓን፣ ገንዘብ አበድረው ወይም ተቀምተው ያልተመለሰላቸው እና ደግሞ ታጭተው ወይም አፍቅረው ሳያገቡ የሞቱ የሙት መንፈሳቸው ከመቃብራቸው እየተመላለሰ ይጠይቃል ይባላል" አልኩት ከዚህ በፊት ሰምቼው የማላውቀውን አፈ-ታሪክ ፈጥሬ።

"ምንድን ነው እሚጠይቀው?" አለ ድምሁን ዝቅ አድርጎ።

አሁንም እርከኖችን እየዘለልን ወደ ድንጋይ ሃውልቶቹ እየወረድን ነው።

"ያው የገደላቸው ሰው ፍርድ ተሠጠው ወይ? ገንዘቤ ተመለሰ ወይ? እጮኛዬ ምን ሆነ/ሆነች እያሉ ይሆናል" አልኩት።

"ምን አይነት ቅዠት ነው?" አለ።

"የሚታመነውን እኮ ነው የምነግርህ። በተለይ እጮኛ ኑሯቸው የሞቱት በዚህ ሰዓት መቃብር ያገኙትን ሰው ሁሉ ከኋላው ይሠፍሩበትና ተቆራኝተውት ይኖራሉ ይባላል" አልኩት።

"እንዴት ነው መቆራኘት ማለት?" አለ።

ዝቃ ሚስት ወይም ባል ይሆናሉ" ማለት ነው አልኩ።

"አብዙሉላሂ ምሽጣ! አንተ ምንድን ነው የምታወራው?" አለ።

ይህን እየተነጋገርን ወደ ሃውልቱ ስንጠጋ የሆነ ድምፅ ሰማንና ሁለታችንም ባለንበት ደርቀን ቀረን።

"ኩ.. ኩር.. ኳ.." ይላል። ነቢል ድንገት ባትሪውን ወደፊት አድርጉ ሲያበራ ዐይኖቹ በባትሪው ብርሃን ቦገግ አሉ።

ነቢል ደንግጦ ባትሪውን ዘወር ሲያደርገው ‹አመድረፍ› ብሎ እሮጠ።

ዐይኖቹን ሳይ ነበር ወዲያው የለየሁት። አውጪ የሚባል አውሬ ነው። ያው መቃብር አካባቢ የማይጠፋ ሥጋ በል የዱር እንሠሣ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ እኔም በድምፁ ደንግጬ ነበር። አይኖቹን ሳይ ግን የድመት ቤተሠብ እንደሆነ ስላወኩ ከድንጋጤዬ ወዲያው ነበር የተመለስኩት። የነቢል ድንጋጤ ግን አልበረደም ነበር።

"ምንድን ነው ሲሳይ?" አለኝ።

"አፍቃሪ የምትፈልገው የሙት መንፈስ ናት" አልኩት ቀስ ብዬ።

"አንተ አትቀልድ" አለኝ።

‹አውጪ› መሆኑን ነግሬው ከዕዕዋ ሥር ደርሰን ነቢል አልፎ አልፎ እያበራልኝ ቁፋሮ ጀመርኩ።

አንድ ክንድ ያክል እንደቆፈርኩ በመሣሪያው ነቢል ማዳመጥ ጀመረ። ጥርት ያለ ድምፅ ሠጠን።





"ነቢል ና እስኪ ትንሽ ቆፍር አልኩት" ለቀልድ።

"እኔ መቃብር አልቆፍርም" አለኝ ቁርጥ አድርጎ።

"ቆይ አንተ ሙያህ ዐለት መፈልፈል፣ አፈር መቆፈር አይደል እንዴ?" አልኩት እያለከለኩ።

"እኔ እኮ የደረቀ ዐለት፣ ምድረ በዳ እንጂ መቃብር እምቆፍር መሰለህ?" አለኝ።

"ይሁንልህ ብቻ እንደቆምክ መጥታ ከኋላህ እንዳትይዝህ ብዬ ነው" አልኩት።

"ማን?" አለ።

"አፍቃሪዋ የሙት መንፈስ" አልኩት።

"ወንድም ሲሳይ ምናለ ዝም ብለህ ሥራህን ብትሠራ!" አለኝ።

እየሳቅኩ የቆፈርኩትን አፈር ዝቂ አውጥቼ መቆፈሪያውን ሳክ ሳደርግ ‹..ኳ..› የሚል የብረት ድምፅ ተሰማ። እጄን ሰድጄ ስዳብስ የብረት ሣጥን መሆኑን አወኩ።

"ነቢል አገኘሁት!" አልኩና ከወገቤ በላይ ወደ ጉድጓዱ ሁለመናዬን አስገብቼ ስቤ አወጣሁትና አፈሩን ጠረግ ጠረግ አድርጌ አፀዳሁት።

ነቢል ባትሪውን እያበራልኝ በጉን የተቆለፈበትን ቁልፍ ጠምዝዤ ሰበርኩና ከፈትኩት።

"ኩም!" አልኩ።

ሣጥኑን የሞላው አሸንክታብ ብቻ ነበር። ‹ወገቤ እስኪቆረጥ የቆፈርኩት ለዚህ ኖሯል› አልኩና አፈሩ ላይ በተስፋ መቁረጥ ዝርፍጥ አልኩ። ነቢልም ሐዘኔ ተጋብቶበት ቁርጥጥ አለ። ትንሽ ቆይቶ፡-

"ወንድም ሲሳይ እስኪ ዘወር በል" አለና የመሣሪያውን ዘንግ ወደ ጉድጓዱ ከተተው። ከዕሁ በተቃራኒ አቅጣጫ ድምፁ ተሰማ።

"ሌላም ሳይኖር አይቀርም" አለ።

"በየት በኩል?" አልኩት። ከቆፈርኩበት በተቃራኒው አቅጣጫ አመለከተና ከዕሁ በላይ በኩል መሆኑ ነው። የቆፈርኩት በታች ነበር።

በእልህ መቆፈር ጀመርኩ። ላቤ በጀርባዬ ይንቆረቆራል። መጨረሻ በተመሣሣይ ጥልቀት ብረቱ ‹ን› አለ።

እንደ ቅድሙ አድርጌ ሣጥኑን አውጥቼ አፈሩን ጠረኩና፡-

"አሁንስ የዚያች መከረኛ ሴት አምላክ እርዳኝ" አልኩኝ።

እጆቼ እየተንቀጠቀጡ ቁልፉን ሰብሬ ከፈትኩት። በሆነ ቆዳ መሰል ከረጢት የተከተተ ረዘም ያለ ነገር አየሁ።

"ነቢል!" አልኩት በስሜት።

ባትሪውን ጠጋ አድርጎ ካዩ በኋላ ባትሪውን ለእኔ ሠጥቶ ከቆዳ መሰል ከረጢቱ ውስጥ መዝዞ አወጣው። ቁመቱ 25 ሳ/ሜ ውርዱቱ 10 ሳ/ሜ የሚሆን እርሳስ የመሰለ አብረቅራቂ ብዙ ጠርዝ ያለው ነው።

"ዋው!" አለ ነቢል።





"ራሱ ነው?" አልኩት ጉጉት ብዬ።

"ራሱ ብቻ ሳይሆን በአግባቡ ፒዩሪፋይድ የሆነ ነው" አለኝ።

"የስ" አልኩና ተጠመጠምኩበት።

ፅሁኩሑሉን ከነቢል እጅ ተቀብዬ ከፍ አድርጌ ደገፍ :-

"አብነ ኩሕል ነበ እስራኤል ውሉደ ኢትዮጵያ

አንች ምስኪን ሴት ተስፋ አድርጊ!"

አልኩ ጮክ ብዬ።

"ትንሽ አልበዛም?" አለኝ ነቢል።

"ከውነትክን ነው በደረቅ ሌሊት መካነ መቃብር ላይ ቆሞ መፈንጠዝ" አልኩና ‹ምን ማድረግ አለብኝ ብዬ› ሳስብ አባ ዮናታን ያሉኝ ትዝ አለኝ።

‹ከታዘዝከው ውጭ ያለን ነገር እዛው መልስ›።

ስለዚህ አሸንክታቡን የያዘውን ሳጥን በነበረበት መለስኩ እና አፈሩን ወደ ቦታው ስመልስ ድካሜ ከፊቱ ላይ በሚንጠባጠበው ላብ የተረዳው ነቢል፡-

"አካፋውን አምጣው" አለኝ።

"መቃብር አልቆፍርም አላልክም" አልኩት።

"አሁንም አፈሩን ልመልስ እንጂ ልቆፍር አይደለም" ሲለኝ ተሳሳቅን።



Scanned with CamScanner

ነቢል አፈሩን ሲመልስ ቅድም ስቆፍር ያላስተዋልኩት ‹ቅሪተ አጽም› ከአፈሩ መካከል ታዬ። ‹ቆይ ቆይ› አልኩትና በእጄ አነሣሁት።

"ምንድን ነው?" አለኝ

"የሰው አጥንት" አልኩት። በጣም ሰቀጠጠው።

"እንዲያውም በዚህ አካባቢ ‹የካይላዎች› ቅሪተ አጽም መድኃኒት ነው ይባላል፤ ትፈልጋለህ?" አልኩት እያሳየሁት።

"አንተ እብድ የሆንክ ልጅ" አለኝና "እንዲያውም ራስህ አፈሩን መልሰው" ብሎ አካፋውን ሰጠኝ።

እየሳቅኩ ሁሉንም እንደነበር አድርገን ጓጉንቻችንን ይዘን ዳገቱን ተያያዝነው። በእውነቱ በድካም ሙትት ብያለው። የምራመደው እንደ ምንም እየተጎተትኩ ነበር። ማንም ሳያየን መኪናችን ስንደርስ መኪናው ወንበር ላይ ዘፍ አልኩ። ልብሴ፣ ፊቴ አፈር ባፈር ሆኗል። ጉዳዩ አልነበረም። አሁን የምፈልገው እንቅልፍ ብቻ ነው።

ጥዋት ሲነጋ ነቢል ከእንቅልፌ እስኪቀሰቅሰኝ ድረስ ያለሁበትንም አላወኩም ነበር።

"አንተ ግን እንዴት ያለኸው ነህ?" አለኝ አፈር የሞላውን ፊቴን እንድታጠብ ውኃ እየጨመረልኝ።

"ምነው?" አልኩት።

"መቃብርን ያክል ነገር ስትቆፍር ቆይተህ እንቅልፍ እንዲህ አድርጎ የሚወስድህ" አለኝ።





"አንተ አልተኛህም እንዴ?" አልኩት።

"እንቅልፍ በዐይኔ ሳይዞር 11 ሰዓት ሆነ። በቃ ለሶላት ተነሣሁ" አለኝ።

"እየህ! እኔ የምፈልገውን ካገኘሁ ለጥ ነው። ባይሆን የምፈልገውን ካላገኘሁ ግን ፍጥጥ ብሎ ማደር ነው። እንቅልፍ ከነበርንበት ገቢር ወደ ሚቀጥለው መሸጋገሪያ መጋረጃ ነው። ቲያትር ቤት ገብተህ ከአንድ ገቢር ወደ ሌላ ገቢር ለመሄድ መጋረጃ ሲዘጋ አይተሃል አይደል? እንደዚያ ነው እንቅልፍ። ካልተኛሁ ትናንትናና ዛሬ ምን ልዩነት ይኖረዋል። የሰው ልጅ ካምናና ከትናንት ቁራኛ የሚላቀቀው በመርሣት እና በማንቀላፋት ነው። ማስታወስ ጥሩ የሆነውን ያህል መርሣትም ጥቅም አለው። መንቃት መልካም የሆነውን ያህል ማንቀላፋትም ጥሩ ነው። ወሣኙ መጠኑ ነው። እናም ዛሬ ከነገ የሚለየው በመኻል ባለው እንቅልፍ ነው። ማለዳን አዲስና በተስፋ የተሞላ የሚያደርገው እንቅልፍ ነው" አልኩ እየተንጠራራሁ።

"እንቅልፋም" አለኝ ደግሞ።

"እርግጥ እንቅልፍ ሲበዛ የተራዘመ ሽግግር ይሆንና የበለጠ ወደ ትናንት ይመልስሃል። እኔ ግን በጠዋት ተነሥቻለሁ። አንተ ግን ትናንት ላይ ነህ፤ እኔ ደግሞ ዛሬ ላይ ነኝ" አልኩት።

"አቤት አቤት! ይልቅስ ቁርስ ፈልግና ቀማምሰን በጠዋት እንንገዝ" አለኝ።



# ምዕራፍ - ፲፮

በከተማዋ ካሉ አነስተኛ ምግብ ቤቶች በአንዱ እንቁላል አስጠብሰን ቁርሳችንን ቀማምሰን መኪናችንን አስነስተን በሌኢ ሹፌርነት ጉዞ ወደ ገዟላ ጀመርን።

የገዟላ ወረዳ ዋና ከተማ የሆነችውን ፅፅቃን አልፈን ተከዜን ተሻግረን ሳሀላ ሰየንት ወረዳ መሸሃ ከተማንና መሸሃ ወንዝን አቋርጠን ረጅሙን የበረኃ ጉዞ ስንጥቀን የተከዜ ወንዝ ገባር የሆነውን የመናን ወንዝ አልፈን ሽቅብ ተጉዘን በለሳ መግባት ደኖርብናል። የዕለቱ ጉዟችን በጠቅላላ 200 ኪ./ሜ. የሚሸፍን ፈታኝ የበረኃ ጠጠር መንገድ ነው።





ጠዋት በፈነጠቀችው የሀሐይ ብርሃን ጨረር መልክዓ ምድሩ ግልፅ ሆኖ መታየት ሲጀምር ነቢል ካሜራውን አውጥቶ ያየውን ሁሉ ለማንሣት ሲሞክር እንደ አልሞ ተኳሽ ‹ቀጭ ቀጭ› ያደርገዋል።

"ህማም ያምራል" ይላል እየደጋገመ።

እንደ ኒዮወርክ ፎቆች ሰማይን የሚታከኩ የሚመስሉ የተደረደሩ ሀለታማ ተራሮች በዕውቅ ባለሙያ የተጠረቡ ይመስላሉ። የተራሮቹን ውበት አይተህ ሳትጠግብ ግራ ቀኝ በዐለቶች የተገደገደ ስምጥሽለቆ ታያለህ። በሰርጡና ስምጡ እንዲሁም በተራሮቹ መካከል ደግሞ የተለያዩ ቀለማት ያላቸው አብረትራቂ ኮረቶች የሞሉት ማለቂያ የሌለው የሚመስል ሜዳዎች ለንዕዕር በሚመስል ተዘርግተው ይታያሉ። ዕዕዋት የሚባል የለም ማለት ይቻላል። ብዙ ነዋሪዎች የሌሉበት ይመስላል። አልፎ አልፎ ወንዞችንና ሸለቆዎችን ተከትሉ የፍየል መንጋዎች ፍጥረት ለመኖሩ ምልክት ይሆኑ ዘንድ ይገኛሉ። በተረፈ ተፈጥሮ ሀጥ ረጭ ያለችበት ስፍራ ነው። የገዟላ መልክዓ ምድር የያዘውን ይዞ ለዘመናት ዛሬም በእርምጥ እንዳለ አለ።

ውበት እንደተመልካቹ ነው ቢባልም አንዳንዴ ውበትን ለመረዳት ዕውቀት ይጠይቃል። ነቢል መደነቁን አላቆመም። እየደጋገመ ካሜራውን ያንቀጫቅጫል።

"ፊልሙ እንዳያልቅብህ" አልኩት ለተረብ ዲጂታል ካሜራውን እየመለከትኩ።

"Can't you see the extra ordinary beauty"

"ልዩ ውበት አይታይህም?" አለኝ ለተረቤ መልስ መሆኑ ነው።

እርግጥ የገዘፋ መልክዓ ምድር ውበት በዓለም ላይ አልፎ አልፎ የሚገኝ ብርቅዬ ነው። ሙያ የተፈጥሮ ውበትን ለማድነቅ ተጨማሪ ጉልበት መሆኑ እውነት ነው። እንዲያውም ለማበላለጥ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል። እንደ እኔ በደንና ብዝሃ ሕይወት ጥናት የሳይንሱን ዓለም የተቀላቀለ ሰው የተፈጥሮ ውበት የሚጎላለት ዕፅዋትንና እንስሳትን ሲያይ ሊሆን ይችላል። እንደ ነቢል ላለ ሰው ደግሞ ደረቅ መልክዓ ምድር ከዐለቶችና ቋጥኞች ጋር የውበት መገለጫ ሊሆኑለት ይችላል።

ለእኔ ትልቅ የመሬትና የመልክዓ ምድር ውበት ከዕፅዋት ይገኛል ባይ ነኝ። ዛፍ ነፍሴን ያሳርፋታል። ዕፅዋት በሌሉበት አካባቢ መኖር ያስፈራኛል። በቤቱና በቢሮዬ አቅራቢያ አንድም ይሁን ከዚያ በላይ በመስኮትም ይሁን በበር አሻግሬ የማየው ዕፄያትና አረንጓዴ ተክሎች ያስፈልጉኛል። በቤቱና በቢሮዬ ውስጥ በገበታ የተተከሉ ዕፅዋት ከሌሉ ትንፋሽ ያጠረኝ ይመስለኛል። ዕፄያትና አረንጓዴ ተክሎች ስል ከፕላስቲክ የተሠራ በድን ማለቴ አይደለም። እርሱ የበለጠ ጭንቀቱን ያባብሰዋል። በተፈጥሮ ላይ ምሁት ይመስለኛል። አስከሬን አቅፎ ሙቀትና ፍቅር እንደመጠበቅ ቀፋፊ ይሆንብኛል። ያው ሰው የአመለካከቱ ባሪያ አይደል? አመለካከት ደግሞ ከትምህርትና ከሙያ መቀረሁ አይቀርምና!

ወደ ዝቋላ ሚዳና ተራሮች እየዘለቅን በመጣን ቁጥር አስገራሚ መልክዓ ምድር የክቱን ይዞ የተሰለፈ ይመስላል። ወደ ታላቁ ወንዝ ተከዜ ስንቃረብ የዓሳው ሽታ ከወንዙ ለመጠጋታችን ምልክት ሰጪ ነበር። ነቢል አድናቆቱን መቆጣጠር አልቻለም።

"አቁም አቁም" አለና ከመኪናው ወርዶ ሁለት እጆቹን እንደ አሞራ ክንፍ ዘርግቶ ወደ መስኩ ትንሽ ሮጥ አለና ልዩ ልዩ ቀለማት ያላቸውን ኮረቶች እየለቀመ ይታቀፍ ጀመር።





የበለጠ ስሜቱን ልቆስቁሰው አልኩና፡-

"አሁን ይሄ የደረቀ መልክዓ ምድር ምኑ ነው እንዲህ የሚያስፈነጥዝህ?" አልኩት።

"ወንድም ሲሳይ አንተ ያልተደሰትክበት ምክንያት ብዙ ዕፅዋት ስላላየህ ይሆናል" አለኝና "እኔ ግን አሁን የማየው ልዩ ውበት ብቻ እንዳይመስልህ፤ የወደፊት ሀብት ጭምር ነው" ሲል

"የሚታየው ሁሉ ቋጥኝና ዐለት ነው፤ የቱ ላይ ነው ሀብቱ?" አልኩት።

ቶሎ ስለሆነ ካልጠየቁት አያወራም። ሲጠይቁት ግን ከውስጡ የታመቀው ዕውቀት እንደ እሳተ ገሞራ ይፈነዳል። እንደ ዶ/ር ከብረ በዓል ነው።

"አየህ ወንድም ሲሳይ! ከ1940ዎቹ በፊት በዐረቡ ዓለም የፔትሮሊየም ድፍድፍ ወደ ገጸ ምድር ፈሶ ሲገኝ ለአረቦች ጆሰቢያቸውን የሚያቆሽሽ፣ ለግመሎቻቸው የሚከረፋ ቆሻሻ ነበር። የኋላ ኋላ ዕውቀት ሲገልፀው የዓለም የኢኮኖሚ ጉልበት፣ የዐረቡ ዓለም የብልፅግና መሠረት፣ የህልውናቸው ዋስትና ለመሆን በቃ!" አለ አንገቱን እየነቀነቀ።

በረጅሙ ተንፍሶ፡-

"እና እኔ እዚህ የማየው የአገር መገንቢያ ብረት ነው፣ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ ወርቅ ነው፣ የፋብሪካ ግብዓት ነው፣ አንተ አሁን የምትነከራተትለት ስታቢናይት ነው፣ የትንግርታዊ ክዋኔ በተለይ የመኪናና የሞተር ውድድር ማካሄጃ፣ የተራራ መውጣት ስፖርት

ስፍራ ነው!" አለኝ ከመሬት የለቀማቸውን ኮረቶች ወደ መኪናው እየጫነ፡፡

ይዟቸው ከመጣው መሣሪያዎች የተወሰኑትን አውርዶ አልፎ አልፎ ከሀለቱና ካፈሩ ላይ ኬሚካል እየረጨ በውጤቱ ራሱን በአድናቆት እየወዛወዘ በዚያው ሰጥሞ መቅረቱን ሳይ፡-

"ኸረ አባክህ በረኃ አታስበላኝ ወዲህም ይመሻል እንሂድ" አልኩት፡፡

"ቢመሽስ፣ በረኃስ ቢሆን፣ በዚህ መገኘት እኮ በስንት አንድ ጊዜ የሚገኝ ዕድል ነው" አለኝ እንደገና እነዚያን ውብ ኅብረ ቀለማት ያላቸውን ኮረቶች መሰብሰብ ቀጠለ፡፡

"አየህ! አላህ ምድርን ወዷታል፡፡ ለመውደዱም በዕፀዋትና በአበቦች አሳመራት፡፡ ግን ልብ በል እንደ ሙሽራ የበለጠ ያከበራት ግን በከበሩ ዐለቶች፣ ድንጋዮችና በማዕድናት ነው" አለኝ የሚያምሩትን ኮረቶች እያሳየ፡፡

ዕፀዋትን ስላነሳልኝ ደስ አለኝና "እሱስ እውነትክን ነው፡፡ ብቻ ደኑ ስለተራቆተ አካባቢው እርቃኗን የቆመች ሙሽራ እንደማሳየት ይሆናል እንጅ" ስል

"እውነት ነው! ግን ለሁሉም ቦታ አለው፤ ይህ አካባቢ ውበቱ ይህ የምታየው ነው፡፡ ሌላ ቦታ ግን እርቃን ሊሆን ይችላል" አለ፡፡

"እርግጥ ሁሉም ቦታ አረንጓዴ ይልበስ ማለት አይገባም፡፡ ከሰውነት ክፍል እንኳን የምንሸፍነውና የምንገልጠው አለና፡፡ መገለጥ ያለበትን ብንሸፍነው፤ መሸፈን ያለበትን ብንገልጠው ሁለቱም ችግር አለው፡፡





በሀገራችን ያለው ችግር ግን መሸፈን ያለበትን እርቃኑን ማስቀረታችን ነው" ስለው

"Right" አለኝ፡፡

"ብቻ...." ብዬ ሳቅማማ እያዳመጠኝ ለመሆኑ በዐይኑና በእጁ ምልክት ሰጠኝ፡፡

"ብቻ አሁን አሁን መራቆታችንን አውቀን እርቃናችንን ለመሸፈን የምናደርገው ጥረት የሚመሰገን ቢሆንም ቆም ብለን ማሰብ ያለብን ነገር አለ" አልኩኝ፡፡

"ምንድን ነው እርሱ?" አለ፡፡

"የት ቦታ ምን አይነት ዝርያ ያስፈልጋል? የሚለው ቅድመ ዕቅድና ዝግጅት ይጠይቃል፡፡ ለጣውላና ለቁሳቁስ፣ ለግንባታና ለማገዶ፣ ለጌጥና ለውበት፣ ለምግብና ለመድኃኒት፣ ለጥላና ለንፋስ መከላከያ እንዲሁም ለሥርዓተ ምህዳር ጥበቃ ተብለው የሚተከሉ የችግኝ ዓይነቶች በእጅጉ ይለያያሉ፡፡ በገጠጠ መሬት ላይ የሚተከል ችግኝ በደለበ መሬት ከሚተከል፣ ከምንጭ አናት ላይ የሚከተል ከወንዝ ዳርቻና ግርጌ ከሚተከል፣ በማሳ ዙሪያ የሚተከል ከከተማ መንገድ አካፋይ ከሚተከል ይለያል፡፡ የደን ልማትና የአረንጓዴ ማልበስ ተግባር ጥልቅ እሳቤ፣ ሰፊ ቅደመ ዝግጅት የሚጠይቅ ቴክኒካዊ ጉዳዮች አሉት፡፡ ስለሆነም ምድርን ማልበስ ሲባል ተገቢውን ልብስ ለተገቢው ቦታ መርጦ በማዘጋጀት ነው፡፡ ለእግር ካልሲ እንጅ ኮፍያ አይሆንም፣ ለእራስም ኮፍያ እንጅ ካልሲ ማልበስ አይሆንም፡፡ ሸሚዝን ሱሪ አድርጐ ማልበስ እንደማይሆን ሁሉ ሱሪንም ኮት ማድረግ አይቻልም፡፡ ሁሉም ተገቢውን ስፍራ ሲይዝ ውጤትን፣ ውበትንና ዘላቂነትን ያሳብሳል፡፡

ችግኝ ተክሎ ዛፍ ለማድረግ በሀገራችን ቢያንስ አራት ዓመት የሚጠይቅ በመሆኑ ከግብታዊነት ይልቅ አርቆ ማሰብንና ተገቢውን አደረጃጀት መፍጠር ይጠይቃል። የማያድግ ችግኝ መትከል የሀገርን ሀብት ጭቃ ላይ እንደመጣል ይቆጠራል። መልካም ሐሳብ መልካም ሆኖ የሚዘልቀው መልካም ሆኖ ሲፈጸም ነው።" አልኩት።

"እውነት ነው! በሀገራችን ብዙ መልካም ነገሮች ይጀመሩና የባለሙያ ምክርና ድጋፍ አጥተው ሲመክኑ አይተናል" አለኝ የውስጤን ስሜት ስለተረዳው።

ከለምለሙ ምዕራብ ኢትዮጵያ ጅማ ተወልዶ ያደገው ነቢል ከአረንጓዴው መልክዓ ምድር ይህ ቢበልጥበት አይገርምም ሙያ ነውና። ለእኔ ደግሞ በመልክዓ ምድር ውበት ምዕራብና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ይበልጥብኛል። ከፋ፣ ቦንጋ፣ ሚዛን ቴፒ ረዣዥም ዛፎች የተሞላው ጥቅጥቅ ደን፣ ቀረሮ የሞላበት፣ ስንበት አክባሪው ጉሬዛ እንደሰው ከዛፍ ዛፍ የሚዘልበት፣ ጉም ባዘቶ ጥጥ መስሎ በመሬቱ ላይ የተኛበት፣ ሌላ ዓለም፣ ሌላ ስፍራ፣ ልዩ ውበት ይሆንብኛል። ደቡብ ምዕራብ እና ምዕራብ ኢትዮጵያን የጎበኘ ሰው ደን የአገር ልብስ፣ የአገር ጸጋ መሆኑን ይረዳል። ይህንን የጠበቁ ሰዎች የተባረኩና የተመሰገኑ ናቸው። ‹እንደ ደን ባለሙያነቱ መኖር ያለብኝ እኮ ከፋ አለዚያም ቦንጋ ነበር› ብዬ አውቃለሁ። ብቻ አጠቃላይ ኢትዮጵያን አይቶ ሰሜንና ምሥራቁን ከምዕራቡና ከደቡብ ምዕራቡ ጋር ያነጻጸረ ሰው ግማሹን ተላጭታ ግማሹን አጎፍራ የቆመች አንጉል ጉብል ትመስለዋለች። ደቡብ ምዕራብ እና ምዕራብ የልብ ምቷን የደም ዝውውሯን ሳያስታጉል የሚያዘዋውርላት ንጹሕ አየር የሚያስተነፍሳት የኢትዮጵያ ሳንባ ነው።





ተክሌ ወንዙ ዳር ከበቀሉት ዛፎች ጥላ ስር ተኝተው የሚያመስኩትን ፍየሎቻቸውን እየጠበቁ እነርሱም ከአንዱ ዛፍ ጥላ ሥር ቁጭ ያሉ እረኞችን ጠጋ አልና ሰላምታ ከሰጣቸው በኋላ፡-

"ልጆች! ዝቋላ ቆንጆ አገር ናት አይደል?" አላቸው ወደኔ እያየ ንገሩት እንደማለት።

"አዎን እንጂ" አሉት በአገውኛ ቃና።

"ከዚህ ከናንተ ጋር ብኖር ትፈቅዱልኛላችሁ?" አላቸው።

"ምን ችግር?" አሉት ፍልቅልቅ ብለው። ‹ችግር የለም› ለማለት ይመስላል። ቀጠለና ወዲያ ወዲህ ሲራመድ ቆየና፡-

"በዚህ መኖር ደስ ይላል አይደል?" አላቸው።

"ደስ ይላል እንጂ" አለ ተለቅ ያለው ልጅ።

የነቢል መጠን ያለፈ ደስታ፣ የልጆቹ በራስ መተማመን የሆነ ነገር አስታወሰኝ። አንድ ወዳጄ ሰሜን ተራራ በረዶ ከሚፈላበት ስፍራ እራፊ ጨርቅ የለበሱ እረኞችን አይቶ እሱ ራሱ ደራርቦ ለብሶ ብርዱን አልቻለውም ነበርና ሁኔታቸው ገርሞት፡-

"ልጆች አይበርዳችሁም?" ሲላቸው

"ጋሼ! አገር ይበርዳል እንዴ?" ብለው አሉኝ ብሎ አጫውቶኝ ነበር።

እውነትነት አለው። ሀገር ቀዝቃዛ ሊሆን ይችላል ግን አይበርድም፤ ሀገር በረኃ ሊሆን ይችላል ግን አያቃጥልም፤ ሀገር ጋራ ሸንተረር ሊሆን ይችላል ግን አያታክትህም። በተለይ እኛ ኢትዮጵያዊያን ሀገራችን

ምንም ትባል ምንም ለእኛ ምቹ ናት እንወዳታለን። በ1950ዎቹ አንድ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ከነጠራማው ደቡብ ጎንደር ስማዳ ወጥተው ግሪክ ሀገር ለሥነ መለኮት ትምህርት ይላካሉ። ሃያ ፎቅ ባለው ምቹ አፓርትመንት እየኖሩ ትምህርታቸውን ይከታተላሉ። በዚያው ሳሉ አንድ ደብዳቤ ለዘመዶቻቸው ይልካሉ።

ደብዳቤው ከሞላ ጎደል እንዲህ ይላል፡-

> "የምኖርበት ቤት ሙቅና ቀዝቃዛ ውኃ በቧንቧ ይመጣለታል። መቀመጫዬ ፎቁ ወንበር፣ መኝታዬም ምቹ ነው። ከቤቱ ሆኜ ውቡ የሜዲትራኒያን ባሕር ተንጣሎ ይታየኛል። ምግቤን በኮረንቲ ኃይል ጭስ ሳይነካኝ አበስላለሁ። አካባቢው ለጤና የተመቸ ጽዱ ነው። ያም ሆኖ ግን ጠዋት ማታ እናንተና ያደኩበት ቀዬ ይናፍቀኛል። ናፍቆቱ ውስጤን ይቧጭረዋል ይልና" መጨረሻ ላይ "ለተወለድንበት ሀገርና ለገዛ መልካችን ፍቅር የሰጠ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን" ይላል።

ሰው የገዛ መልኩን እንደማይጠላው ሁሉ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ሀገራችንን የመውደድ ጸጋ ከፈጣሪ የተቸረን ይመስላል።

ከሐሳቤ ስመለስ ረጅም ጊዜ ያጠፋን መሰለኝና ነቢልን፡-

"በል በሌላ ጊዜ ከፍለህ ትጉበኛለህ ለአሁኑ በነጻ ስለሆነ ይበቃናል።" አልኩና እየቀላለድኩ ወደ መኪና አስገብቼ የበረኃ ጉዟችንን ቀጠልን።





የቆሞን መልክዓ ምድር ጨርሰን የሰሜን ተራሮች ሠንሠለት አካል ወደሆነው ተራራማው በለሣ ስመድረስ የመናን ወንዝ አቋርጠን ሽቅብ መውጣት ስንጀምር፡-

"ነቢል" አልኩት ሲከነክነኝ የቆየውን ጉዳይ ለማወቅ።

"ወዬ" አለኝ ከመልክዓ ምድሩ ጋር የሚታገለውን አዕምሮውን ሰብስብ አድርጎ ወደ እኔ እየዞረ።

"እእእ...ስለዚህ ስለ ‹ዕብነ ኩሕል› ባለፈው ስምን ሲፈለግ እንደቻለ ግምትክን ጠይቂህ መጀመሪያ የታዘዝከውን ፈፅም ብለኸኝ ሳትገልፅልኝ እኮ ነው የቀረህ" አልኩት።

"ምናለበት የታዘዘከውን ብቻ ብትፈጽም" አለኝ ፈገግ እያለ። ጉጉት የሚነጠኝ ሰው መሆኔን ስለሚያውቅ የበለጠ እንድቃትት ነው።

"የታዘዝኩትንማ ፈፀምኩ እኮ" አልኩና "መብት ባይሆንም አሁን ላይ መቼም ፍንጭ ይገባኛል ብዬ ነው" አልኩ።

"ታድያ ለምን እነሱኑ አትጠይቃቸውም?" አለኝ።

"መጠየቁማ አይቀርም። እንዲያው በአንተ በኩል ያለውን ደግሞ ልወቅ ብዬ ነው እንጂ" አልኩ እንደመለማመጥ ብዬ።

"እሽ ይሁንልህ! ብቻ እኔ የምነግርህ የነሱን ሐሳብ ላይተካ ይችላል ወይም ላይገጥም ይችላል። ለምን ከምናውቀው ይልቅ የማናውቀው ይበልጣልና" አለና ዝም ብሎ ቆይቶ

"ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ገዳማውያን ዕውቀትና ጥበብ በተለይ ኪብሩን እስከተዋወኩበት ጊዜ ድረስ ምንም ዓይነት ግንዛቤ አልነበረኝም።

ኪብሩን ካወቅሁ ወዲህ ግን በሩቅም ቢሆን በእርሱ ሕይወትና አስተሳሰብ ውስጥ ለመረዳት ችያለሁ እና ትልቅ አክብሮት ይገባሁ ማለት እችላለሁ፡፡" አለና ትንሽ ሲያስብ ቆይቶ "ስለዚህ ጉዳይ ከነገርከኝ በኋላ ሊትሬቸሮችን ሳገላብጥ የበለጠ መደነቅ ፈጥሮብኛል" አለኝ፡፡

"እንዴት አልኩት" የኔም ጉጉት እየናረ መጥቷል፡፡

"አንተ የነገርከኝ እንዴት የታመመች ሴትን ለማዳን እንደተፈለገ ነበር አይደል?" አለኝ፡፡

"አዎን! እንዴት እንደሆነ ግን ለእኔም አልገባኝም" አልኩት፡፡

"እየውልህ መቼም ሀገራችን ጥንታዊት ብትሆንም፣ ስልጣኔዋም ቀደም ያለ ቢሆንም የነበረንን ጥበብና ዕውቀት በአግባቡ ስላልተመዘገበ ተረትም ይሁን ትንግርት ወይም ቲዮሪ ሁሉንም ከግሪክ ወይም ከሮማውያን ጋር አስተሳስሮ መናገር መራራ ዕጣ ፈንታችን ሆኗል፡፡ እናም የምነግርህ ከዚያ አንፃር ተጽፎ ያየሁትን ነው" አለና ዝም ሲል

"እኮ ምን ተባለ?" አልኩት፡፡

"ያው ባለፈው እንደነገርኩህ ኮሕል ለዐይን ሕክምናና ውበት በአጠቃላይ ለሕክምና በተያዩ አገሮች ውሏል ነገር ግን ከዚያም በላይ ጥቅም አለው ተብሎ ይታመናል" አለኝ፡፡

"ነቢል እባክህ በፈጠረህ ዘርዘር አድርገህ ንገረኝ" አልኩት፡፡

ዝርዝር እወዳለሁ፡፡ አመንዝራው አሳቢዬ የሁሉን ዕርቃን ማወቅ ይፈልጋል፡፡ በቃ እንደዚህ ነኝ! ፕሮቶኮል፣ ዲፕሎማሲያዊ ጨዋነት ምናምን ያስጨንቀኛል፡፡ ማንም ምሥጢር ነው እንዲለኝ አልሻም፡፡ ነገሮችን በይደር መተው አይሆንልኝ፡፡ ብችል ዛሬ ዘርቼና አብቅዬ፣





ዛሬ አጭጄና ወቅቼ፣ ዛሬ አበክቼና ጋግሬ ባየው ደስ ይለኛል፡፡ ቶሎ ቶሎ! በቃ ሁሉን ዝርግፍግፍ አድርጎ ቶሎ መስማት፡፡ ሁሉን ቶሎ አውቆ ከዚያ ቶሎ ደግሞ ሁሉን ረስቶ ደግሞ ሌላ ሁሉን ለማወቅ ቶሎ መቅረቅረብ ነው፡፡ እንደዚህ ነኝ እኔ!

"ወይ ወንድም ሲሳይ! እንዲያው ትዕግስት የሚባል እኮ አልፈጠረብህም፡፡ ና ዘቡ መንገድ አስን አይደል የት እሄድብሃለሁ?" አለኝ እየተገረመ፡፡

አይ....ይ አፈጠንኩ ብዬ የበለጠ አስረዘምኩት፣ ብዬ ለራሱ እያተተመተምኩ ሳለ ሀሐይ ያጋለው የሾለ ድንጋይ ሲሸረክተው የቆለው በነቢል በኩል ያለው የኋላ ጐማ ድምፅ አሰምቶ ተተረተረ፡፡

ብሽት አልኩ፡፡ የጎማው መተርተር ብቻ ሣይሆን ነቢል ወደ ዋናው ነጥብ እየተጠጋ እያለ የማቋረጫ ሰበብ በመገኘቱ ነበር፡፡ እየተነጫነጭኩ መኪናውን ዳር አቁሜ ወረድኩ፡፡

"አዲያ!" አልኩና የተተረተረውን ጎማ በካልቾ ጠለዝኩት፡፡ ውጤቱ የእግሬን አውራ ጣት ጥፍር ቀርድዶ ማሳመም ሆነ፡፡

እግሬን በእጄ ይዤ በአንድ እግሬ እንክሽ እንክሽ እያልኩ ኡ... ኡ ብዬ ጮኩ፡፡ ነቢል በድርጊቱ ተገርሞ

"ወይ አንተ! እንዴት ያለኸው እብድ ነህ" አለና ከት ብሎ በመሳቅ፡፡

"አሁን እኮ የተናደድከው ጎማው ስለተነፈሰ ሳይሆን ምሥጢሩን ስላልነገርኩህ ነው አይደል፡፡ በዚህ ሁኔታህ የምነግርህ አይመስለኝም" አለና የኋላ በሩን ከፍቶ ክሪክና ጐማ ለማውረድ ይታገል ጀመረ፡፡

እንዳከረፍኩ ጎማውን ቀይረን ጉዞችንን ቀጠልን፡፡

"በቃ አታኩርፍ ልነግርህ ነው" አለኝ፡፡

"እንዲያውም አልፈልግም" አልኩ ሳላስበው፡፡

"ካልፈለክማ ምን ይደረግ! መቼስ በግድ ስማኝ አልልህ" አለና ግደ ማደ ያይ ጀመር፡፡ ሰረቅ አድርጌ ሳየው ሳቁን ለመቆጣጠር ሲታገል አየሁትና የእኔም ሳቅ መጣ፡፡

"እሽ ንገረኝ" አልኩ፡፡

"አይ ወንድም ሲሳይ! ለካ ኪብሩ እንስቶ የማይጠግብህ ለዚህ ነው" አለ፡፡

"አንተ ሰውዬ ምን ሆነሃል? ለምን ዝም ብለህ ወደ ጉዳዩ አትገባም" አልኩ ኮስተር ብዬ፡፡

"እሽ እሽ አትቆጣ" አለና

"እንግዲህ መጀመሪያ የግሪኩን ሚቲዮሎጅ እንዲሁም አውሮፓውያን በጉዳዩ ላይ ያላቸውን ትርክት ልንገርህ፡፡ የእኔን መላምት ደግሞ አስከትላለሁ" አለ የመኪናው ወንበር ላይ ፊቱን ወደ እኔ አዙሮ ጀርባውን ለመኪናው በር ሰጥቶ ተመቻችቶ እየተቀመጠ፡፡

ስሜቴንና አዕምሮዬን ጆሮ አድርጌ ዐይኔን ከመኪና መንገዱ ሳልነቅል ለማዳመጥ ተዘጋጀሁ፡፡

"‹ዕብነ ፈላስፋ› ወይም ‹philosophical stone› የሚባል ሁሉን ማድረግ የሚያስችል ድንጋይ ለመፍጠር ወይም ለመፈለግ በዘመኑ የነበሩ ፈላስፎች ብዙ ደክመዋል፡፡ ይህም ተግባር ‹ታላቅ ተግባር (Magnum





Opus) ይባል ነበር፡፡ ይህን ድንጋይ የፈጠረ ወይም ያገኘ ሰው በምድር ላይ ያለ ማንኛውንም ነገር ማትለጥ ወይም ማሟሟት ይችላል፡፡ የነበሩ ማዕድናትንም ከአንዱ ወደ በለጠው መቀየር ይችላል ተብሎ ይታመናል፡፡ ለምሳሌ ከመዳብ ወደ ብር፣ ብርን ደግሞ ወደ ወርቅ መቀየር ይቻላል፡፡ እንዲሁም ልዩ ዕዕዋትን ከዚሁ ጋር በመቀየጥ ሙሉ ጤናን መጎናፀፍ እንዲሁም ያረጁ ሕዋሳትን በማደስ የማቱላላን ዕድሜ መጎናፀፍ ይቻላል ተብሎ ይታመን ነበር፡፡" ሲል

"እሽ እና ያገኘው ሰው ነበር?" አልኩ በጉጉት፡፡

"የማግኘቱ ወይም የመፍጠሩ ሂደት ደረጃ በደረጃ የሚከናወን ነበር፡፡"

"እንዴት ማለት?" አልኩ፡፡

"‹ዕብነ-ፈላስፋን› ለማግኘት በቅድሚያ ‹የፈላስፎች ሜርኩሪ› የሚባል የብረት መሠረት የሆነውን ማዕድን ማግኘት ያስፈልጋል፡፡ ይህን አግኝተህ በአግባቡ በማንጠር ወደ ‹ዕብነ ፈላስፋ› ግኝት ትደርሳለህ ማለት ነው" ሲል

"ታድያ ከዕብነ-ኩሕል ፍለጋ ጋር ምን ያገናኘዋል ይኼ?" አልኩ፡፡

"ቀናው አስገራሚው ፍንጭ ያለው እሱ ላይ ነው" አለና አቀማመጡን አስተካክሎ በበሩ መስኮት ማደ ማደ ያይ ጀመር፡፡

"የምን አስገራሚ ፍንጭ?" አልኩት አሁን መለስ እያልኩ እያየሁ፡፡

"‹የፈላስፎች ሜርኩሪን› ማግኘት ‹ዕብነ-ፈላስፋን› ወደ ማግኘት ያደርሳል ያልኩህን ይዘሃል አይደል?" አለኝ

"አዎን" አልኩ በፍጥነት

"‹የፈላስፎች ሜርኩሪ› ለማግኘት ደግሞ አንድ ነገር በቅድሚያ ማግኘት ይኖርብሃል" አለ

"ምን አልኩት?" እየተጣደፍኩ፡፡

"እርሱን ስታገኝ የጠቢባኑን የትመጣና ሽግግር ሂደት ‹አልኪሚ› ትጀምራለህ፡፡ የጥበቡ መግቢያ በር ነው! " አለኝ፡፡

"እኮ ምኑን ስታገኝ?" አልኩ፡፡

ትንሽ ዝም ብሎ ቆይቶ "አሁን አንተ እንድታመጣ የተጠየቅኸውን ነገር" አለኝ ፈገግ ብሎ፡፡

"ዕብነ ኩሕሉን ነው?" አልኩት በአግራሞት፡፡

"ታድያ ሌላ ምን ፍለጋ መጣን?" አለኝ፡፡

"እውነትክን ነው ነቢል?" አልኩት በአድናቆት፡፡

"እውነት ወይም ውሸት ልልህ አልችልም፡፡ ያነበብኩትና የተረዳሁት የምርምር ጫፍ ይህ ነው" አለኝ ፈርጠም ብሎ፡፡

‹ምን ውስጥ ነው እነዚህ አባቶች እየከተቱኝ ያለው!› አልኩ በልቤ፡፡ ትንሽ ቆይቼ፡-

"የእኔን መላምት እነግርሃለው ያልከኝ ደግሞ ምንድን ነበር?" አልኩት፡፡

"አይ አጅሬ! ሁሉን ካላዘረገፍክ አይሆንልህም አይደል?" አለኝ፡፡





ሆው የተሟላ ግንዛቤ እንዲሆንልኝ ብዬ ነው" አልኩ
እየተለማመጥኩ፡፡

ዝኔ ግምት አ...ቀደምት ኢትዮጵያውያን ‹ዕብነ-ፈላስፋ› ወይም
የተቀራረበ ጥበብ እንደነበራቸው ይህን ጉዳይ ካነበብኩ በኋላ
ተገንዝቤአለሁ፡፡" አለኝና

ቴእሉጅስት እንደ መሆኔ መጠን የአክሱም ሃውልት የተሠራበትን
ዐለት በማየት ‹ተጠርቦ ነው ወይስ በማቅለጫ ቀልጦ ቅርፅ እንዲይዝ
ተደርጐ ነው› የሚለውን ለመወሰን ግራ ገብቶኝ ቆይቷል፡፡ ጠርቦ
ለማንንዝ ለማሰብም ይከብዳል፡፡ ነገር ግን ዐለቱን አቅልጦ ቅርፅ
አስይዞ ማቆሙ ሲመስል ይችላል፡፡ ዋናው ነገር በምን ያቀልጡታል
የሚለው ነው፡፡ ነገር ግን ‹ዕብነ-ፈላስፋ› የተባለው ነገር አንድ ጠባዩ
ሁሉን አሟሚ (Universal solvent) ነው ተብሎ መታመኑን ስታስብ
ኢትዮጵያ ውስጥ ዕብነ-ፈላስፋ አልነበረም ወይም ተመሳሳይ ጥበብ
አልነበረም ለማለት የሚቻል አይመስለኝም፡፡" አለ

ዋው!" አልኩ ሳላስበው፡፡

ዝሪያ በላይ..." አለና ትንሽ ሲያስብ ቆይቶ "የተለያዩ ዕፆችን
እንድታመጣ ከዚህ በፊት እንደተጠየክ ነግረኸኛል፡፡ ይህን ሁሉ ሳስብ
እነዚህ የገዳም አባቶች ሀሳባቸው ሩቅ ፍላጎታቸው ጥልቅ ይመስለኛል፡፡
ኪብሩን ያህል ምሁር ላፍ አድርገው የወሰዱት በዚህ ብልጫቸው
መሆን አለበት፡፡" አለኝ፡፡

ግን እንዲያው ከሳይንስ አንፃር መዳብን ወደ ብር፤ ብርን ወደ ወርቅ
መቀየር የሚቻል ሀሳብ ነው?" አልኩት፡፡

"እየሀ ወርቅን ወርቅ፣ ብርንም ብር የሚያደርገው የሞሎሙኪላር ይዘቱና መዋቅሩ ነው። መዋቅሩን መቀያየር ከቻልክ፣ ይዘቱን መቀነስና መጨመር ከቻልክ ለምን አይቻልም! ቲማቲም በባሕሪው ሙቀት ይፈልጋል አይደል? በእናንተ በባዮሎጅ ሙያ ከዓሣ አንድ ጅን አውጥቶ ቲማቲሙ ላይ በመጨመር ውርጭ ተቋቁሞ ብዙ ምርት የሚሠጥ ቲማቲም አልተፈጠረም? ዓሣ በቀዝቃዛ ውኃ ውስጥ መኖር የሚስችለውን አንድ ጅን ለይቶ አውጥቶ ወስዶ ቲማቲም ውስጥ ማስገባትና ቲማቲም እንደ ዓሣ ቅዝቃዜን ተቋቁሞ እንዲያድግ ማድረግ ከተቻለ ከብር ላይ የሆነ ነገር ጨምረህ ወርቅ ማድረግ የማይቻልበት ምክንያት የለም። ያው በጅኦሎጅ ዓለም ደግሞ ነፋስ ውኃና ፀሐይ የሚሠሩትን መተካት እኮ ነው" አለ።

ትንሽ ሲያስብ ቆየናː-

"ለማንኛውም ወንድም ሲሳይ! የምመክርህ ነገር ቢኖር የሚያዘህን ሳታንገራግር ፈፅም፣ እስካቀረቡህ ድረስ አትራቅ፣ ከጀርባቸው ሂደህ ግን ምሥጢር ለማወቅ አትሞክር። በአጠቃላይ ‹Do not mess with them›!" አለኝ።

የፍርሀት ይሁን የአድናቆት የተደበላለቀ ስሜት ተሠማኝ። ላቤ ከቀኑ ሙቀት ጋር ተደምሮ በጀርባዬ ሲንቆረቆር ይታወቀኛል። "ወይ ጉድ! " አልኩ በአድናቆት።

የበረኃውን አቀበት ጨርሰን ደልዳላው ሜዳ ጉሣላ ከተማ ስንደርስ ጀንበሯ በስተምዕራብ እያዘቀዘቀች ነበር።





# ምዕራፍ - ፲፪

ቀጥ ያለውን ተራራ ወጥቼ በቀጥታ የሄድኩት ባለፈው ጊዜ ሚተራሊዮን ኩርምት ብላ ተቀምጣ ለመጀመሪያ ጊዜ ወዳየሁበት ዋርካ ነበር። ነገር ግን ዛሬ የለችም። ፈጠን ብዬ ወደ አባ አካለ ወልድ ቤት ዘው ብዬ ገባሁ፤ ከመደቡ ላይም የለችም። ግራ ገብቶኝ ሳለ ባለፈው አባ እዚህ እንደማትቆይ የተናገሩት ትዝ አለኝና ‹እንዴት ሆና ይሆን!› እያልኩ እንደገና ልብ የሚያጠፋውን ዳገት ይገፍ ወደ ቤተ ክርስትያኑ አመራሁ።

ሣጥኔን በጉኔ አድርጌ ዳገቱን ስወጣ የሆነ ኩራት ቢጤ ተሰማኝ። ሚተራሊዮንን አግኝቻት ድካሜንና ልፋቴን ብነግራት

ጥሩ ነበር እያልኩ ስገበዝ ከዋሻው በስተውጭ ከታጠረው ዕድጥ ደረስኩ፡፡ የቆርቆሮ በሩን ገፋ አድርጌ ስዘልቅ አባ ጀርባቸውን ለጠዋት ፀሐይ ሰጥተው ፊታቸውን ወደ ቤተ ክርስትያኑ አዙረው የጸሎት መፅሐፋቸውን ዘርግተው ጸሎት ሲያደርጉ ተመለከትኩ፡፡ ቤተ ክርስትያኑ መግቢያው ከዋናው ቋጥኝ በጥበብ ተጠርቦ የተሠራና አሁንም ድረስ የተያያዘ ሲሆን መቅደሱ ወደ ውስጥ ተፈልፍሎ የተሠራ ነው፡፡

በቀስታ ወደ መቅደሱ ዞሬ እጅ ከነሳሁ በኋላ ጸሎት ቢጤ አድርጌ ሳበቃ "እህህ...ህህህ" ብዬ ድምፅ አሰማሁ፡፡ ዘወር ብለው እኔ መሆኔን ሲያዩ ፈገግታ ለግሰውኝ እንድቀመጥ በእጃቸው አመላከቱኝ፡፡ ሣጥኔን ከፊቴ አድርጌ ከተደረደሩት ለስላሳ ድንጋዮች በአንዱ ላይ ተቀመጥኩ፡፡

በዚህ መኻል ቀደም ብሎ ሲከነክነኝ የነበረ አንድ ጉዳይ የበለጠ ያብሰለስለኝ ጀመር፡፡ ‹ዕብነ ኩሉሉን› ያገኘሁበት ቦታ ላይ የበቀለችው ዕፀ ቅርንጫፍ መጀመሪያ መጥቼ የነበረ ጊዜ አባ ይዘው ማየቴ የት እንደተቀበረ ቦታውን በትክክል እንደሚያውቁ በቂ ማሳያ ነው፡፡ ‹ታዲያ ለምን እዚሁ ዋግ 150 ኪ/ሜ ርቀት ላይ ሂድ እንደማለት እስራኤል ኒታንያ ድረስ ማስለፋት ለምን ፈለጉ?› ‹ድካሜ፣ ጊዜዬ፣ ገንዘቤ አያሳዝናቸውም ማለት ነው?› እያልኩ ስብሰከሰክ አባ ጸሎታቸውን ጨርሰው ከመቀመጫቸው ተነሡ፡፡ በፍጥነት ሂጄ እግራቸው ሥር ለመደፋት ጉንበስ ስል አፈፍ አድርገው አንሥተው ትከሻዬን ሳሙኝና መስቀል አሳለሙኝ፡፡

"እንኳን በደኅና ተመለስክ የኔ ልጅ" አሉኝ፡፡

"በአምላክም" አልኩ





"ቀናህ ልጄ?" አሉኝ፡፡

"አዎን! ጸሎታችሁ አግዞኝ ዕብነ-ኩሕሉን አመጣሁ" አልኩና ሣጥኑን አምጥቼ ከፍቼ አሳየሁ፡፡

ፊታቸው ወገግ ሲል ይታይ ነበር፡፡ ሣጥኑ ውስጥ በቆዳ ከረጢት የተቀመጠውን ዕብነ-ኩሕል አነሱና ወደ ቤተ መቅደሱ ይዘውት ገቡ፡፡ ትንሽ ቆይተው ተመለሱና፡-

"ልጄ ሠልፍህ ግሩም ነው!" አሉኝ፡፡

"ያመጣሁት የተፈለገው ነገር ራሱን ይሆን?" አልኳቸው ለማረጋገጥ፡፡

"ነው እንጅ የኔ ልጅ አበጀህ!" ሲሉኝ እፎይታ ተሰማኝ፡፡

"አባ! ሚተራሊዮን የት ሄደች" አልኳቸው፡፡

"እዚህ የለችም" አሉኝ፡፡

"ደኅና ናት? ትንሽ አልተሻላትም?" ብዬ ሳልጨርስ

"የኔ ልጅ ስለ ተስፋዋ እንጅ ስለ ደኅንነቷ አሁን የምልህ የለም፡፡ ይልቅ ተከተለኝ" አሉና የዋሻውን ቅጥር አልፈው ወደ ቤተ ክርስትያኑ ተፈልፍሎ ወደተሠራበት ቋጥኝ አናት የሚያወጣ ቀጭን ስርጥ ይዘዉ ሲወጡ ተከተልኳቸው፡፡

የቋጥኙ አናት ጠበብ ያለች ደልዳላ ገላጣ ስፋራ ያለው ሲሆን የቀረው በከፍታ የተሞላ ነው፡፡ ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ አዞሩና በእጃቸው በቆዳ የተሸፈነውን ‹ዕብነ-ኩሕል› ከፍ አድርገው ይዘው በለሆሳስ የሆነ ነገረ ሲሉ ቆዩና ይህንን ነገር በልብህ ጻፈው አሉ፡፡



Scanned with CamScanner

"ምኑን?" አልኳቸው፡፡

ትንሽዬ የተጠቀለለች ብራና ሰጡኝና ገልጬ ሳየው፡-

> "ወዳጅ ሆይ ተነሺ፣ ውበቱ ሆይ ነይ፣ እነሆ ክረምት አለፈ፣ ዝናቡም አልፎ ሄደ፣ አበቦች በምድር ላይ ተገለጡ፡፡ የዜማም ጊዜ ደረሰ፤ የወፎችም ቃል በምድራችን ተሰማ፤ በለሱ ጐመራ፤ ወይኖችም አበቡ መዐዛቸውንም ሰጡ፡፡ ወዳጄ ሆይ ተነሺ፣ ውበቱ ሆይ ነይ፣ በዐለት ንቃቃትና በገደል መሸሸጊያ ያለሽ ርግብ ሆይ! ቃልሽ መልካም፤ ፊትሽም ያማረ ነውና መልክሽን አሳይኝ ድምፅሽንም አሰሚኝ!" ይላል፡፡

አንብቤ ስጨርስ እንባዬ እንደጐርፍ ይወርድ ጀመር፡፡ ሚተራሊዮን ደጋግማ በዐይነ ሕሊናዬ ትመጣለች፡፡ ጉስቁልናዋ ደግሞ ድብቅ ውበቷ፣ ድምጿ፡፡

በእንባ መታጠቤን ያዩት አባ "ሠልፍ ላይ ያለ አያለቅስም" አሉኝና እንባዬን በወይባቸው ጠረጉልኝ፡፡ "ሠልፍህ ግሩም ነው! ሠልፍ ላይ ያለ ሰው ያለ ድል አይመለስም፡፡ ወንድምህ አባ መዐዛ ቅዱሳን ይጠብቅሃል፡፡ ይህ ለሚቀጥለው ተግባራችሁ ያስፈልጋልና በጥንቃቄ ያዘው፡፡ የቀረውንም እንዲሁ ጨርስ" አሉና ዕበነ-ኩሕሉን መልሰው ሰጡኝ፡፡

"በል እንውረድ፤ አፍህን ሻረውና ወደ ወንድምህ በቶሎ ሂድ፡፡ ሲያገዝህ የሠነበተውም ማለፊያ ሰው ነውና አታስጠብቀው" አሉኝ፡፡

ነቢል ከእኔ ጋር ለመሆኑ እንዴት እንዳወቁ እየተደነኩ ወደ ታች ቁልቁለቱን እየመሩኝ ወረድን፡፡ ቤታቸው ገባንና ሰዎች ለበረከት





የመጡላቸውን ዳቦ ባርከው ቆርሰው ሰጡኝ፡፡

እርሱን እየበላሁ ቀደም ሲል የረበሸኝን ጥያቄ መጠየቅ ፈለኩ፡፡ ‹ለምን በቀላሉ ማምጣት እየቻልኩ ያደክሙኛል?› የሚለው በጣም ረብሾኛል፡፡

እርግጥ እዚህ ላይ ትልቁ ጉዳይ የሚተራሊዮን ጉዳይ ሆኖ ሳለ የእኔን ድካም ትኩረት ማድረግ ይገባል ወይ? የሚለው በአንድ በኩል ቢፈትነኝም ‹ግን ለምን?› እላለሁ፡፡ በቃ ለመጠየቅ ቆረጥኩ፡፡

"አባ" አልኳቸው፡፡

"አቤት" አሉኝ ፊት ለፊቴ እንደተቀመጡ፡፡

"ዕበነ-ኩሕሉን እኮ ያገኘሁት ዋግ ውስጥ ከቤተ እሥራኤላውያኑ መቃብር ከአንደ ዕፅ ሥር ተቀብሮ ነው" አልኳቸው፡፡

"ይሆናል እንጃ" አሉኝ፡፡ ይህ መልስ አውቃለሁ ወይም አላውቅም ሊሆን ይችላል፡፡

"ዕፁን ደግሞ ባለፈው እዚህ መጥቼ ሳለ ግንጣይዋን እርስዎ እንደ ጭራ ሲጠቀሙበት አይቼ ነበር" አልኩ፡፡

ፈገግ ብለው መልስ ሳይሰጡ ቆዩ፡፡

"የእኔ ግምት የነበረበትንና የተቀበረበትን ትክክለኛ ስፍራ ያወቁ እንደነበር ነው" አልኩ፡፡

ዝም! ጭጭ! ፈገግታ ብቻ፡፡

"እኔ እኮ በብዙ ወጭና ድካም ነው እስራኤል ሀገር የሄድኩት" አልኩኝ፡፡



Scanned with CamScanner

"የኔ ልጅ ታዲያ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም መሄድህ ምን ይጎዳል?" አሉ።

"እርግጥ ቅዱሳት መካናትን እኔም ባለቤቴም መሳለማችን ትልቅ ዕድል ነው። ለዚህ ጉዳይ ሲባል ግን መሄድ አልነበረብኝም" አልኩኝ ፈርጠም ብዬ።

ዝም ብለው የእጅ መስቀላቸውን እያገላበጡ ሲያዩ ቆዩና፡-

"የኔ ልጅ ሌላ ሰው በምሥጢር ቀብሮ ያስቀመጠውን ውድ ዕቃ ያስፈቃዱ መንካት እኮ ተገቢ አይሆንም!" አሉና

"ከሰዎች ዘንድ ያለን ነገር ያስፈቃዳቸው ስናገኝ ከፈጣሪ ዘንድ ያለውን እናጣለን። ከሰዎች ዘንድ አግኝተን ከፈጣሪ ያለውን ማጣት ደግሞ አንሻምና!" አሉኝ ፈገግ ብለው።

"የፈጣሪ ያለህ!" አልኩ። ለካ ወደዚያ የሄድኩት ፈቃዳቸውን ለማግኘት እንጅ አድራሻ ለማወቅ አልነበረም። ወዲያው ከአባ ዮናታን ጋር ያደረኩት ውይይት መጨረሻው በተለይ ግልፅ ሆኖ መጣልኝ።

"የሚያውቅ ሰው ከተገኘ ፈቃዳችን ነው!"

ያሉት ቁልፍ ጉዳይ ነበር።

ሰው ያልደከመበትንና ያልለፋበትን ንብረትም ሆነ ማንኛውንም ሀብት ማንቁርቱን ይዞ መሣሪያ ደግኖ በሚዘርፍበት ዓለም ለዘመናት መሬት ውስጥ የተቀበረን ማዕድን ለመጠቀም ፈቃድ ለማግኘት ብዙ ሺ ኪሎ ሜትሮችን አቋርጦ መልእክተኛ መላክ ከፍ ያለ የሞራል ልዕልና





ይጠይቃል። የሰው ሀቅ የሰው ነው፣ የሰው ሳብ የሰው ነው። ‹የሰው የአዕምሮ ውጤት የሰው ነው› የሚለውን ለማክበር የሄዱበት ርቀት እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን ለማንፃት ምን ያህል እንደሚተጉ ማወቅ ያስደምማል።

የሰው የአዕምሮ ውጤት የሆነን ድርሰት ያለ ፈቃድ ኮፒ እያደረገ የሚበትን፣ በስንት ጭንቅ ሴሲ.ቶች የተወለደን ፊልምና ሙዚቃ በአንድ ቀን እያራቡ በማከፋፈል ደራሲንና አሳታሚን ባዶ እጅ የሚያስቀሩ የቀን ዘራፊዎች በሞሉባት ሀገር፤ እንዲጠብቁና እንዲያስተዳድሩ የተሰጣቸውን የመንግሥትና የሕዝብ ሀብት ዘርፈው በጠራራ ፀሐይ መሀል ከተማ ሕንፃ ገንብተው ወዳጅ ዘመዶቻቸው እያጨበጨቡላቸው በኩራት ሲንጎማለሉ በሚታይባት ሀገር መሬት ውስጥ ተቀብሮ ለዘመናት የቆየን ነገር ያውም ባለቤቶቹ ትተውት ሀገር ቀይረው መሄዳቸው እየታወቀ ፈቃድ መጠየቅ ‹ምን ዓይነት የሞራል ልዕልና ነው?› ያስብላል።

በአሁኑ ወቅት እንኳን መሬት ውስጥ ሜዳ ላይ የተቀበረን ሀብት ይቅርና ለዐይን ጥቅሻ ዘወር ስትል ኪስህ ዘው ብሎ የሚገባ፣ አጥር ቅጥርህን ዘሎ ካልሰማህ ሰርቆ፣ ከሰማህ አስፈራርቶ የሚቀማ በሞላበት ሀገር ሜዳ ላይ የተቀበረን ሀብት ሳላስፈቅድ ብሎ ባሕር አቋርጦ መልእክተኛ የሚያስልክ እንዴት ያለ የሞራል ከፍታ ነው?

ሰዎች ለፈጣሪ ፍቅርና ክብር ሲሉ ስማቸው እንዳይጠቀስ ማንነታቸው እንዳይታወቅ ብለው በምሥጢር የለገሱትን መባና አሥራት ያለ ኃፍረት ሙዳዬ ምፅዋት ገልብጦ የሚወስድ የሃይማኖት ሰው ነኝ ባይ በሞላባት ሀገር የእነዚህ አባቶች ንጽሕህና እንደምን ያለ ነው?

በሕግና በሞራል ትርጉም ስርቆት ማለት የሌላ ሰው የሆነን ነገር ያለ ባለቤቱ ፈቃድና ዕውቅና እንዲሁም የሕግ ፈቃድ ውጭ በጉልበት ወይም ሳይታወቅ መውሰድ ማለት ነው። የሌላ ሰው የሆነን ነገር ሲባል ዕቃ፣ ዕውቀት፣ ንብረት፣ ሐሳብ ሊሆን ይችላል። ወይም ሕንዶች እንደሚሉት ጉዳዩ የዱባ ፍሬ ወይም አልማዝ ፍልቃቂ ሊሆን ይችላል።

ስለ ስርቆት ስናወራ ኪስ የሚያወልቀውን፣ ቤት የሚሰረስረውን፣ በረት የሚገለብጠውን መናጢ ድሃና ተራ ዱርዬ ብቻ የሚመለከት ይመስለናል። በአሁኑ ሰዓት ሌቦች ባለ ኮትና ከራቫት፣ ባለቆብና ቀሚስ፣ ባለ ኒሻንና ማዕረግ ሆነዋል። ሌብነት ቢዝነስ ሆኗል። የሚያሳፍር ሳይሆን በወዳጅ ዘመዶችህ እንደ ብልጥና ቀልጣፋ የሚያስቆጥር ሆኗል። ዘርፈህ ቤት ብትሠራ ይጨበጨብልሃል። ሰርቀህ ብትመፀውት ትመረቃለህ፣ 100 ሚሊዮን የሀገር ሀብት ዘርፈህ አንድ ሚሊዮን ለቤተ ክርስቲያን ወይም ለቤተ መስጊድ ብትሰጥ ‹ምዕመናን እልል በሉላቸው› ይባልልሃል። ቢሊዮን አጭበርብረህ መልሰህ ሚሊዮን ለመንግሥት ፕሮጀክት ስትለግስ ከሀገሪቱ ባለስልጣን ጎን ተቀምጠህ ‹የቁርጥ ቀን ልጅ› ትባላለህ። ገንዘብ መያዝክን እንጅ ከየት አመጣኸው የሚልህ የለምና ትከበራለህ።

ሌቦች ዘርፈው ቀጥፈው የሠሩትን ቤት፣ የገዙትን መኪና፣ የከፈቱትን ድርጅት መጸየፍ ሲገባን እያጨበጨብን እንመርቅላቸዋለን። ‹ባለጌን ከወለደ ይልቅ ያሳደገ ይከፋል!› እንዲሉ ሌብነትንና ቅሚያን እየኮተኮትን አሳድገን ዛሬ ላይ ቢዝነስ የሚል ካባ አለበስነው። በአሁኑ ዘመን በኢትዮጵያ ስርቆትና ዝርፊያ ከሀገሪቱ ዕድገት ጋር መሣ ለመሣ መሆኑ ወይም ስርቆትና ሌብነት እየጨመረ መምጣቱ አይደለም አሳሳቢው ነገር፤ ይልቁንም ስርቆት የማያሳፍር ቢዝነስ መሆኑ እንጂ!





ባንድ ወቅት ዶ/ር ክብረበዓል እንዲህ ብሎኝ ነበር፦

"በስርቆት በጎ ነገር መሥራት አይቻልም፤ የተዘረፈን ሀብት መመፅወት አይቻልም፤ በተዘረፈ ሀብት ቤተ መቅደስ ወይም ቤተ መስጊድ ሠርቶ መጽደቅ አይቻልም። ‹አትስረቅ› ያለን አምላክ ሰርቀን መስዋዕት አድርገን ብናቀርብለት የስርቆታችን ተባባሪ እንዳደረግነው ይቆጠራል። ሰርቆና ዘርፎ ጽድቅ ያማረው ወይም የፀፀተው ቢኖር ለባለቤቱ መመለስና ንስሐ መግባት እንጂ ለቤተ እግዚአብሔር ወይም ለድሆች በመስጠት ሕሊናን ማንፃት አይችልም። አፍሪካ ውስጥ ‹ሮቢንሁዲዝም› አይሠራም። ሲጀመር የምትዘርፈው ከድሆች ላይ ነውና። ክርስቶስ በወንጌል ፍፁም እንድትሆን ከፈለክ ያለህን ሁሉ ለድሆች ስጥ ብሏል። ‹ያለህን› ሲል ለፍተህ ደክመህ ያፈራኸውን ማለቱ ነው። የዘረፍከውን ግን መስጠት ያለብህ ለባለቤቱ ነው።"

‹በዚህ ሁሉ ዝቅጠት የሰው ሀቅ የሰው ነው፣ የሰው ጥበብ የሰው ነው፣ ለበጎ ዓላማ እንኳን ቢሆን ባለቤቱ ያስቀመጠውን የሚያነሣ ባለቤቱ ብቻ ነው። ወይም እርሱ የፈቀደለት ብቻ ነው› ብለው የሚያስቡ ጥቂት ሰዎች መኖራቸው ሞራላችን ተንጠፍጥፎ አለማለቁን እንረዳለን። ‹እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኑሮ እንደ ሰዶምና ገሞራ ጠፍተን ነበር› እንዲል መፅሐፉ ጥቂትም ቢሆኑ የሞራል ዘር፣ የንጽሕና ዘር፣ የታማኝነት ዘር ፈጣሪ በዚች ሀገር ዘርተን እናበቅለው ዘንድ አልነሳንም።

ይህን ሁሉ የንጽሕና ተግባራቸውን ከነባራዊው ዓለም ጋር ሳወዳድር ቆይቼ ‹ለምን አደከሙኝ› ብዬ ማኩረፌን አስታውሼ፦

‹እኔ አፈር ለሚበላው ጉልበቱ ስሳሳ እነርሱ ለዘላለማዊ ጸአዳ ነፍሳቸው ይጨነቁ ኖሯል። እኔ እኮ ገ/ም ብዬ ነው በጅብደኝነት እንደ ፈንጣ ከዚህም ከዚያ የምዘል። ነቢል እውነቱን ‹Do not mess with them› ያለኝ› እያልኩ እንደገና የራሴን ግልብነት ታዘብኩ።

"በል ኃይለ ጊዮርጊስ (የክርስትና ስሜ ነው) ፀሐይ ሳይበረታ መንገድህን ጀምር" አሉና ቆመው ጸሎት አድርገው ግንባሬን ስመው መስቀል አሳልመው ሸኙኝ።

ከቤታቸው ወጥቼ በትልቁ ዋርካ ሳልፍ እንደገና ሚተራሊዮን በዐይነ ሕሊናዬ ሞላች። ‹ብቃ! ቶሎ… ቶሎ…› አልኩ ለራሴ።

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)
Telegram Channel





# ምዕራፍ - ፲፪

ካደርንበት ሆቴል በረንዳ ላይ ሲንቆራጠጥ የቆየውን ነቢልን አሳፍሬ አቧራማውን መንገድ እያስጨስን ወደ ባሕር ዳር መንዝ ጀመርን። እኔና ነቢል አንድ ሙሉ የጉዞ ክብ ልንደፍን ትንሽ ይቀረናል።

ከተወሰኑ ሰዓታት በኋላ መንገድ ላይ አባ መዐዛ ቅዱሳንን በእርሱ አጠራር ‹ኪብሩን› እንደምናገኘው ለነቢል ስነግረው ደስታው መጠን አጣ።

"እውነትክን ነው ወንድም ሲሳይ?" አለኝ።



Scanned with CamScanner

"እውነቱን ነው እናገኘዋለን" አልኩና "ደስታህን ስታገኘው ታጣጥማለህ ይልቅ ባለችኝ ትንሽ ጊዜ ባለፈው ታስረዳኛለህ ያልኩትን ርዕሰ ጉዳይ ላነሣ ነው" አልኩት።

"ደግሞ ምን ቀረህ?" አለኝ ደስታ ባልተለየው ፊት።

"ስለ ውኃ ጠባይ በጥልቅ እንድታስረዳኝ ያልኩህን" አልኩት።

"እ .... " አለና "እስኪ አንተ መጀመሪያ ከኢኮሎጅ አንፃር ስለ ውኃ ያለህን ግንዛቤ ንገረኝ" አለ።

"ከኢኮሎጂ አንጻር እስካሁን ያለ ኦክስጅን፣ ያለ ፀሐይ ብርሃን የሚኖሩ ፍጥረታት እንዳሉ ቢታወቅም ያለ ውኃ ግን ሕይወት ያለው ነገር በሳይንስ አይታወቅም፡ ውኃ የሕይወት ጠባቂዋና የደህንነት ዋስትናዋ ነው።" ስለው

"ያለ ኦክስጅን ስትል አልገባኝም። ምክንያቱም ውኃ ራሱ ከሃይድሮጅን እና ከኦክስጅን ሞሎኪውል የተሠራ ስለሆነ ብዬ ነው።" አለ።

"በእርግጥ ልክ ነህ። እኔ ማለት የፈለኩት ግን ያለምንም ተጻምሮ በጋዝ መልክ የሚገኘውን ኦክስጅንን ነው። አየህ በርካታ የምድር ፍጥረታት ምግብ ለማዘጋጀትም ይሁን ምግብ አቃጥሎ ኃይል ለማግኘት ኦክስጅን ላይ ጥገኛ ቢሆኑም አንዳንድ ፍጥረታት ግን ኦክስጅንን የማይጠቀሙ አሉ ለማለት ነው" ስለው

"ገባኝ" አለ።





ትንሽ አሰብ አድርጌ ደግሞ፡-

"ውኃ ምንም ዓይነት ካሎሪም ሆነ የምግብ ንጥረ ነገር ባይኖረውም የምግብ ሁሉ ምንጭ በመሆኑ ተኣምራዊ ፍጥረት ያደርገዋል። ውኃ ቀለም አልባ፣ ሽታ አልባ፣ ጣዕም አልባ ቢሆንም የቀለም መበጥበጫ፣ የሽታ መቀመሚያ፣ የጣዕም ማምጫ የሆኖ ወሳኝ ነገር ነው። በኢኮሎጂ ውኃ ሲፈለግ በጠጣር (በረዶ) ወይም በፈሳሽ /ውኃ/ አለዚም በተን (ደመና) መልክ ሆነ የሥርዓተ ምህዳር ሚዛንን ጠባቂ ወሳኝ ቁስ አካል ነው። ይኸው ነው" አልኩት።

"መሠረታዊውን ነገር ተናገርኸዋል። ከሃደሮሎጅና ጅኦሎጂ አንጻር ደግሞ ውኃ ተቃራኒ የሚመስሉ ጠባያት ያሉት ፍጥረት ነው" አለና

"ውኃ ድልዳል ሆኖ ግዙፍ መርከብን ያንሳፍፋል፤ አንዲት ትንሽ ጠጠርን ግን ያሰጥማል። ውኃ መስኖ ሆኖ በቦይ ተመርቶ ከድርቅ፣ ከረሃብ ይታደግሃል፤ እርሱ ምን ችግሮት ውኃ ጎርፍ ማዕበል ሆኖ ሊጠራርግህም ይችላል። ጥጥር በረዶ ሆኖ ሊኮረኩምህ ይችላል፤ ፈሳሽ ሆነ ቆዳህን ሊያረሰርሰው ይችላል። ከአካባቢው ጋር ባለው ፈጣን ተራክቦ ቀዝቃዛ ሆኖ ሊያኮማተረህ ይችላል፤ ፍል ሆኖ ሊገሽልጠህ ይችላል። ውኃ ያቀዘቅዛኻል፤ ውኃ ያሞቅኻል። ውኃ ያነጻኻል፤ ውኃ ተበክሎ ቆሻሻ ሆኖ ይበክልኻል።" ብሎ ዝም አለ። ሲናገር በእርጋታ ቃላቱን እረገጥ እያደረገ ነው። ቀጠለ፡-

"ውኃ በተቃርኖ የሚገለጽ ብቻ ሳይሆን ከምትገምተው በላይ ልዩ ጉልበት የተጎናጸፈ፣ በግዙፍ አካለት ከመስረግ ጀምሮ በማንኛውም ቅርጽ ባለው ቀዳዳ መሹለክ የሚችል ተፈጥሮ ያለው ነው። ውኃን ከአሸዋ ጋር ቀላቅለህ በኃይል ብታፈሰው የመጋዝ ያህል ሊቆርጥ ይችላል" አለ።



Scanned with CamScanner

ማዶ ማዶ ሲያይ ቆይቶ፡-

“ውኃ ብዙ ሰው የማያስተውለው የተለየ ባሕሪም አለው፡፡ በዘመናዊው ሳይንስ ውኃ ድርጊቶችን በበጎም ይሁን በክፉ የመመዝገብ ትውስታን የመያዝ (memory) አቅም እንዳለው ተደርሶበታል፡፡ ውኃ በብርጭቆ አድርገህ ስትረግመውና ስትሰድበው ቆይተህ ወደ በረዶነት እንዲቀየር አድርገህ ብታየው የበረዶው ግግር አስፈሪ ቅርፅና ጉድፍ የበዛበት መልክ ይዞ ብቅ ይላል፡፡ በአንፃሩ ውኃውን እያመሰገንክና እየመረቅክ በጎ ቃላትን እያስተማርከው ቆይተህ ወደ በረዶ ብትቀይረው ቀለሙ ጸዐዳና አስደሳች ቅርፅ ይዞ ታገኘዋለህ፡፡ በዚህ ጠባዩ ውኃ የአካል ብቻ ሳይሆን የመንፈስ ንጽሕናን ያጎናጽፋል፡፡ ከሶላት በፊት በውኃ ታጥቦ ንጽሕናን መጠበቅ በኢስላም ግማሽ ኢማና ነው፡፡ የክርስትናውን ጠበል አስተምህሮ አንተ የበለጠ ታውቀዋለህ!” አለና

“ይህንን ልዩ የውኃ ባሕርይ መረዳትና መግራት ከተቻለ ውኃ የስልጣኔ፣ የልማት፣ የብልጽግና የመንፈሳዊነት ምንጭ ይሆናል፡፡ ምሥጢሩን ባግባቡ የተረዱ ሀገሮች በልጽገዋል፡፡ የአውሮፓ፣ የአሜሪካ፣ የመካከለኛው ምሥራቅና፣ የሩቅ ምሥራቅ ስልጣኔ ከውኃ የተቀዳ ነው፡፡ ከተሞቻቸው ያጌጡት፣ ህልውናቸው የተመሠረተው በሐይቅና በወንዝ ነው፡፡”

“እኛ ኢትዮጵያውያን ግን” አለና ዝም ብሎ ቆይቶ “ካሰፋፈራችን ጀምሮ ከውኃ ርቆ በተራራዎች ላይ ነው፡፡ ለዚህ አሰፋፈራችን ራሱን የቻለ የጦርነት ስጋት ምክንያትነት ቢኖረውም በሰላም ዘመንም ከወንዝና ከሐይቅ ቀርበን መኖር አልደፈርንም፡፡ እንዲያውም ሐይቅ ወንዙን የአጋንንት መኖሪያ አድርገን ውኃ ዝናብ ሆኖ ሲወርድ እንጅ ከሐይቅና ጅረት ጉልበት፣ መስኖ ሆኖ ሲያለማን ብዙ አልታየም፡፡”





ግእርግጥ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ‹ብዓለ ጥምቀትን› በውኃ አካባቢ ውኃውን በመባረክና በመቀደስ ሕዝቡ በውኃ እየተረጨ ከውኃ የሚገኝን ጸጋ የምትዘክር ቢሆንም እንዲሁም በኦሮሞ ባህል በየዓመቱ ‹እሬቻን› በውኃ ዳር በማክበር ለውኃ ክብር ማሳዬት ያለ ቢሆንም በዕለት ተዕለት ኑሯችንና ተግባራችን ግን ለውኃ ክብር ስንሰጥ አይታይም፡፡ በሌሎች ሀገራት ውኃ የስልጣኔና የሞራል ልዕልና ምንጭ በመሆኑ ትልቅ ክብርና እንክብካቤ ይሰጠዋል፡፡ አንዳንዴ እንዲያውም ሞኝነት የሚመስል ክብርና ከለላ ይሰጠዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ አክብሮቱ በማኅበረሰብ እሴትና ወግ ብቻ ሳይሆን በፖለቲካውም የተደገፈ ይሆናል፡፡ ለዚህ አንድ ምሳሌ ልስጥህ” አለና ፈገግ ብሎ ዝም ሲል የእኔም ጉጉት ጨመረና፡-

“ንገረኝ እንጂ” አልኩት፡፡

“እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2018 ዓ.ም ሸራይን አብደል ዋሂድ የተባለች የግብፅ ታዋቂና ተወዳጅ ዘፋኝ የተባበሩት ዐርብ ኢሚሬትስ ውስጥ ታላቅ ኮንሰርት ተዘጋጅቶላት ታዋቂ የሆነውንና ስለ ዐባይ ወንዝ ግርማና ፍቅር የሚያወሳውን ዘፈኗን ለአድናቂዎቿ ታቀነቅናለች፡፡ የዘፈኑ መጠሪያ “Haven’t You Ever Drunk from the Nile?” የሚል ሲሆን የዘፈኑ ይዘት ከሞላ ጎደል ከዐባይ ውኃ የጠጣ ሰው የትም ቢሆን ተመልሶ መምጣቱ አይቀርም የሚል ነው፡፡ ዘፈኑን በስሜት ዘፍና ስትጨርስ አድናቂዎቿ እንድትደግምላቸው በጩኸትና ፉጨት ይጠይቃሉ፡፡ ጥያቄውን ተቀብላ ደግማ ዘፈነች አሁንም ስትጨርስ እንደገና እንድትዘፍን ለሦስተኛ ጊዜ ተጠየቀች፡፡ በዚህ ጊዜ ከመደጋገም ይልቅ ወደ ሌሎች ዘፈኖቿ መሄድ ስለፈለገች ጉዳዩን በቀልድ መልክ ለታዳሚዎቿ፡-

‹ወዳጆቼ! የዐባይን ውኃ ደጋግሞ መጠጣት ብልሃርዚያ ያሲይዛል፤ ስለዚህ ይቅርባችሁ። ይልቅ ሌላ የምንጭ ውኃ ጠጡ።› አለች በቀልድ መልክ።

ይህንን እንደተናገረች ከኢሚሬትስ እስከ ግብፅ ካይሮ፣ ከተራ ሙዚቃ አድናቂ እስከ ሀገሪቱ ፖለቲከኞች ጆሮ ወሬው በብርሃን ፍጥነት ተዳረሰ።

ሽራይን ታላቁን ወንዝ ዐባይን በመድፈሯና ክብሩን ዝቅ በማድረጓ ተከሰሰች። ኮንሰርቷ እንዲቋረጥ ተደረገ። የግብፅ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የእስር ብይን አስተላለፈባት። አየህ የዐባይን ክብር በግብፅ!" አለና

"እኛ ሀገር የራሳችንን ድክመት ወደ ወንዙ አስተላልፈን፡-

‹ዐባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል!›

በማለት እንሳለቃለን። እውነታው ግን ለዐባይ ማደሪያ ያልሰጠነው እኛ ነን። እናም የችጋር ግንድ ይዘን የምንዞር እኛ እንጅ እርሱማ አስዋን ላይ ማደሪያ ከተበጀለት ቆየ እኮ!" አለ በምፀት ምርር ብሎ።

"እናም" አለ ትንሽ ቆይቶ፡-

"እናም ስለውኃ ባለን ደካማ የሥነ ልቡና ውቅር ምክንያት ኢትዮጵያ ሀገራችን የዚህ ተኣምራዊ ፍጥረት መፍለቂና መከማቻ ብትሆንም አሁንም ድረስ ውኃ ታቅፈን በድርቅ እንሰቃያለን፣ ኃይል ቀብረን በጨለማ እንኖራለን።" አለ። ወደኔ አተኩሮ እየተመለከተ ደግሞ





'ልብ በል ወንድም ሲሳይ!" አለ አነጋገሩ ከወትሮው በተለየ እየጋለ።

"ከኢትዮጵያ ወደ ሌላ የሚፈስ እንጅ ከሌላ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣ ወንዝ አንድም የለም። የምትሰጠው እንጅ የምትቀበለው የለም። ኢትዮጵያ ወንዞቿ ከተቀደሰው ማሕፀኗ ፈልቀው ከእርሷ ወጥተው የሚሄዱ እንጅ ከሌላ ቦታ መንጭተው የሚመጡ አይደሉም። የኢትዮጵያ ወንዞች ደግሞ አፈር ማዕድን የታደሉ የእናት ጡት ማለት ናቸው። የኢትዮጵያ ወንዞችና ጅረቶች ከአካል ከገላዋ የሚመነጩ ከውስጥ ከሕዋሷ የሚቀዱ ለእኛ እንዲሆኑን፣ እንዲያሳድጉን፣ እንዲያጎለምሱን ከፈጣሪ የተሰጡን ስጦታዎች ነበሩ።" ሲል አቋረጥኩትና

"ከእኛ መንጭተው ወደ ውጭ የሚፈሱ መሆናቸው ነው እኮ ችግር የሆነው" አልኩት።

"እንዴት?" አለኝ ኮስተር ብሎ።

"ያው የጋራ ሀብት ስለሆነ እኛን ሳታስፈቅዱ መጠቀም አትችሉም ስለሚሉ" አልኩት።

"ይህ እንኳን ስንፍናችንን ለመሸፈን የምናደርገው ጥረት ነው። አንድ በእስልምና አስተምህሮ ውስጥ ያለ ትልቅ ነገር ልንገርህ" አለ መከሳተሩ ጠፍቶ ፈገግ እያለ። እኔም ለመስማት ጓጓሁ። መቼም አዲስ ነገር መስማት ነፍሴ አይደል?

"በአንድ ወቅት ሁለት ሰዎች በውኃ አጠቃቀም ተጣልተው ብዙ ሲነታረኩ ከቆዩ በኋላ ከውኃው መፍለቂያ በስተግርጌ ያለው ሰው ወደ ነብዩ ሞሐመድ ለአቤቱታ ይመጣል። ሰላማቸው ይብዛና ነብዩም ጉዳዩን በደንብ እንዲያስረዳቸው ይጠይቁታል። ውኃው ከተቀናቃኙ መሬት መንጭቶ ቁልቁል እንደሚወርድና ከላይ በመሆኑ

ውኃውን ቅድሚያ እየተጠቀመ በመሆኑ እርሱ ግን ከታች ስለሆነ መጠበቁ አግባብ አለመሆኑን ጠቅሶ እኩል መጠቀም እንዳለበት ያመለክታቸዋል። ነብያችንም ውኃውን በወንድማማችነት እየተመካከሩ መጠቀም እንዳለባቸውና ከላይ ያለው ባለመሬት አጠጥቶ እስኪጨርስ እንዲታገሰው ይመክሩታል። ያ ሰው ግን እጅግ ሞገደኛ ነበርና ነብዩን ሳይፈራ፡-

‹ይህን ያሉት የአክስትዎ ልጅ ስለሆነ ነው› ይላቸዋል በቅሬታ።

በአጋጣሚ ምንጩ የሚፈልቅበት መሬት ባለቤት እውነትም የነብያችን የአክስት ልጅ ነበር። ይሁን እንጅ ሰላማቸው ይብዛና ነብዩ ሞሐመድ ከላይ የሰጡትን ምክር ያቀረቡት በፍፁም ቅንነትና ያለማዳላት ነበር። እናም እንዲህ አሉት፡-

‹ስለ ፍቅርና ስለ ወንድማማችነት ነው ተመካከራችሁ ተጠቀሙ ያልኩት እንጅ በሕግ ይታይ ከተባለ የምንጩ መገኛ የውኃው መነሻ እርሱ ስለሆነ እርሱ የሚበቃውን ያህል ወስዶ መደቡ እስኪሞላ አጠጥቶ እስኪጨርስ ድረስ አንተ መጠበቅ ግዴታህ ነው› አሉት።

እናም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ይህ ሕግ ከቅዱስ ቁራን ጋር አብሮ እንዲወርድ ሆኗል። ቁም ነገሩ ከሀገራችን የሚመነጩትን ወንዞች የመጠቀም የሕግ፣ የሞራልና የሃይማኖት ፈቃድ አለን ለማለት ነው። ነገር ግን ይህን ስልህ የመጠቀም ፈቃድን ምንጊዜም ቢሆን ማንም ሲሰጠን ወይም ሲነሳን አይችልም" አለና ኮስተር ብሎ…

"ይልቁንም ባልተረዳነውና በኮረጅነው የፖለቲካ ድሪቶና የዲሞክራሲ ዲቃላ እርስ በርሳችን ስንባላ፣ አንድ ቀን ስለ ሀብታችን ባግባቡ ሳንነጋገር፣ ከእናት ጡት የሚመነጨውን ጸጋ እኛ ሳንጠባው ሌሎች እንደ ሸለምጥማጥ ላምን በጭራ ገመድ ወድሮ ከጥጃዋ ቀምቶ እንደሚጠባው አግሯን ወድረው ይመጠምጧታል። እኛ ግን ዳር ሆነን የእናት ጡት ሳይነጥፍ ከልማት ተገልለን፣ በጨለማ ተውጠን፣ በጠኔ ቀንጭረናል! ውኃ ጎርፍ ሆኖ ሲሄድ የህልውናችን አፈር ብቻ ሳይሆን የነጻነት መንፈሳችንንና ሞራላችንን ጭምር ጠርጎት የሚሄድ በመሆኑ ራቁትነት ይሰማናል፤ ቀልብ የሌለን የማንደማመጥ እርጉማን ሆነናል!" አለና

"አንተ ግን ለምን ስለ ውኃ ትጠይቀኛለህ? ለምን ሕመሜን ትቀሰቅሳለህ?" አለ ስሜቱ ልውጥውጥ እያለ።

በውስጡ የሚያብሰለስለውን ቁጭቱን እንደቆሰቆስኩበት ገብቶኛልና ተጨማሪ ጥያቄ ማቅረብ አልደፈርኩም። ከዚያ በኋላ የቀረው ጉዟችን በዝምታና በሐሳብ ንውዘት የተሞላ ነበር።

ባሕር ዳር ለመድረስ አንድ ሃያ ኪሎ ሜትር ሲቀር ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ጣና ሐይቅ ውኃ እንደ መስታዎት እየፈለቀ ከሚታይበት ስደርስ መኪናውን ከመንገድ አውጥቼ አቆምኩ።

ይህ ስፍራ እስካሁን ድረስ በግልፅ የማውቀው ነገር ባይኖርም ምሥጢራዊና መንፈሳዊ ጉዳዮች የሚከናወንበት አካባቢ ለመሆኑ ብዙ ፍንጮች አሉኝ። ዶ/ር ክብረ በዓል ከመመንኮሱ በፊት ከከተማ ድንገት ጥፍት ይልብኝና ቆይቶ መኪና ይገፍ መጥቼ እንድወስደው የሚጠይቀኝ እዚህ ስፍራ ላይ ነበር። "የት ሂደህ ኖሮ ነው?" ስለው "የማርያምን ብቅል ልፈጭ ሂጄ ነው?" ይለኛል እንደቀልድ። ዛሬም በጠዋት እንድጠብቀው የቀጠረኝ ከዚሁ ቦታ ላይ ነበር። ቋሚ መኖሪያ ገዳሙ እዚህ አካባቢ ለመሆኑም ምንም መረጃ የለኝም።

ለነቢል "በማንኛውም ሰዓት አባ መዐዛ ሲመጣ ይችላል። እዚህ ነው እንድጠብቀው የቀጠረኝ" አልኩት።

ነቢል ከመኪናው ወርዶ እግሩን እያፍታታ ወዲያ ወዲህ እያለ በአቅርቦ ማሳያ መነፅር ጣናን እና አካባቢውን እየቃኘ እያለ አባ መዐዛ ቅዱሳን አንድ አመክሮ ቆብ ካደረጉ ወጣት ጋር ከድፋው ብቅ ሲሉ አየኋቸው።

"ነቢል መጡ" አልኩት።

ወደነርሱ አቅጣጫ ፊቱን አዙሮ ሲያይ ጥቁር ረጅም ቀሚስ ከጥቁር የመነኩሴ ቆብ ጋር ከላዩ ላይ ወደ ቢጫ የሚጠጋ ወይባ የደረበ መነኩሴ ወደ እርሱ እጁን ዘርግቶ እየተጠጋ ነው።

ነቢል ዐይኖቹ በእንባ ከመቅፅበት ተሞልተው ባለበት ደርቆ ቀረ።

አባ መዐዛ ቅዱሳን ፈጠን ፈጠን እያለ ተራመደና ‹ነቢል ወንድሜ!› ብሎ ጭምቅ አድርጎ አቀፈው። ከዚያ በኋላ የሆነው ሳግ የተሞላበት የናፍቆት ልቅሶ ነበር። ሁኔታቸውን ሳይ እንባዬን መቆጣጠር አቃተኝ።

ብዙዎች በሃይማኖት፣ በጎሳና በቋንቋ ልዩነት ሽፋን እንደ ውሻ በሚናከሱባት ሀገር እነዚህን በዕውቀት የበለፀጉ፣ በሞራል ከፍ ያሉ ጋራና ሸንተረሩን አቆራርጠው በፍቅር ሲጠማጠሙ ማየት ብርቅ ሆነብኝና አነባሁ።

የጥላቻ አቧራ የሚያስነሱት ብዙዎች ናቸው፤ የሚያሰክኑት ግን እንደነዚህ ያሉ ጥቂት ንጹሓን ናቸው። መርገም የሚዘሩ ብዙ ናቸው፤ በረከት የሚያሳጭዱ ግን ጥቂት ናቸው። ይሁን እንጅ የብዙዎች ክፋት ሳይሆን የጥቂቶች ደግነት የፈጣሪን ትኩረት ይስባል፤ ከብዙ





ዙዎች ሁከት ይልቅ የእነዚህ ጥቂቶች ስክነት ምድሪቱን አረጋግቶ ይይዛታል። እና እነዚህ ንጹሓን እስካሉ ድረስ በምድሪቱ ዝናብ ይዘንባል፣ ልጆች ተወልደው ያድጋሉ፣ ሀገር ትኖራለች።

የለድናቆት እንባዬን አጉርፌ ሳበቃ የኔም ናፍቆት ተቀሰቀሰና፡-

ኝሬ እዚጋም ወንድም አለ" አልኩ።

አባ መዐዛ ደርባባ ፈገግታውን እያሳየ እጆቹን ዘርግቶ

ኘኔ ታዛዥ" ብሎ አቅፎ ሲስመኝ ነቢል "የኔ እብድ ብትለው" ይሻላል አለ። ሁላችንም ተያይዘን ሳቅን።

ፀቃ ፍቅር ባለበት ሰላም አለ፤ ሰላም ባለበት ዕውቀት አለ፣ ዕውቀት ባለበት መፍትሄ አለ። ዶ/ር ክብረ በዓል መካነ ጎርመት ሥርዓተ ምንኩስና መፈፀሙን ሳይ መጀመሪያ ላይ እርር ድብን ብዬ እንደወቀስኩት ሁሉ ነቢልም የፍቅር ወቀሳ አቀረበ።

'እንዴት ዝም ብለህ ሳትነግረኝ ትሰወርብኛለህ?" አለ።

'ይኸው ጊዜው ሲደርስ ወንድም ሲሳይ ጎትቶ እንዲያመጣህ ያደረኩት እኮ እኔ ነኝ" አለ አባ መዐዛ ቅዱሳን።

'ምን ዋጋ አለው ቢመጣ ሥራ አላገዘኝ" አልኩ ጣልቃ ገብቼ።

'ምን ዓይነት ሥራ ነው ያላገዘህ?" አለ አባ መዐዛ።

'መቃብር ቁፋሮ" ስል ሁሉም ተያይዘው ሳቁና

'ነቢል የማይወደው ስፍራ ቢኖር የመቃብር ቦታ ነው" አለ አባ መዐዛ።

"በቀንም በሆነ በውድቅት ሌሊት በጨለማ እኮ ነው የወሰደኝ፣ ያንተ እብድ" አለ ነቢል እየሳቀ።

ለብቻቸውም እኔንም እየጨመሩ ከሁለት ሰዓታት በላይ ዛፍ ሥር ቁጭ ብለን ስናወራ ቆይተን

አባ መዐዛ ቅዱሳን ወደ እኔ ዘወር አለና፡-

"ወንድም ሲሳይ በሉ ሂዱ። ነቢልን ዛሬ ይረፍና ነገ ወደ አዲስ አበባ ሸኝተኸው ከነገ ወዲያ ከጠዋቱ 12 ሰዓት እዚህ እጠብቅሃለሁ፣ በተቆረጠልን ቀን ቀሪ ሥራችንን መጨረስ አለብን" አለና የታጠፈ ወረቀት አቀበለኝ።

"እዚህ የሚያስፈልገን ዕቃ ዝርዝር አለልህ" አለ ወረቀቱን እያመለከተ።

አባ መዐዛ ቅዱሳንና ነቢል ሲገናኙ እንደነበረው ሌላ ዙር ሳግ የተናነቀው ለቅሶ ሆኖ ተሰነባበቱ።





# ምዕራፍ- ፲፱

አባ መዐዛ ቅዱሳን ያዘዘኝን ዕቃዎች በሙሉ አዘጋጅቼ እስከ ሾፌሩ የተከራየሁትን መኪና ይገፔ ልክ ባለኝ ሰዓት ከጠዋቱ 12 ሰዓት ከአስፓልቱ ዳር ሄደን ቆምን።

ከድሩው ጥግ ቀደም ብሎ መጥቶ ሲጠብቀኝ ስለነበረ መምጣታችን ሲያይ ቀልጠፍ ብሎ ወደ እኛ መጣ። ሦስት ትላልቅ ከመዳብ የተሠሩ ኮዳዎችን ይዟል።

የጠዋቱን ሰላምታ አቅፎ ስሞኝ ከተለዋወጥን በኋላ፡-

"እባክህ ወንድሜ አዙርና ወደመጣኸሁበት

ንዳ" አለው ሾፌሩን በትህትና ከኋላ ወንበር እንደተቀመጠ።

"ወደየት ነው የምንሄደው?" አልኩት ከጠበኩት በተቃራኒ አቅጣጫ ቢሆንብኝ።

"ወደ ሰከላ ግሺ ዐባይ" አለኝ።

"አ ወደ ዐባይ ምንጭ፤ ደስ ይላል" አልኩና "እንደዚያማ ከሆነ ዛሬውኑ መመለስ እንችላለን ማለት ነው?" ስል ጥየቄ አቀረብኩለት።

"አይ አይመስለኝም" አለ።

"ጸበልተኞች ሁሉ የሚጠመቁባቸውንና የዐባይ መነሻ የሚባሉትን ምንጮች እኮ አውቃቸዋለሁ፤ ቀድቶ መመለስ አይደል? " አልኩ እያቃለልኩ።

"ወንድም ሲሳይ እንደምታስበው ቀላል አይለም፤ ውስብስብ ጉዳይ አለው" አለኝ።

"ደግሞ ምን እንቆቅልሽ ውስጥ ልገባ ይሆን?" አልኩና በልቤ

"ግዴለም ዛሬም ባንመለስ በዐባይ ምንጭ አካባቢ መቆየት አስደሳች ይሆናል" አልኩት ዞር ብዬ።

"በጎ መመኘት መልካም ነው" አለ።

በጉዟችን ላይ የመጀመሪያውን አንድ ሰዓት አካባቢ የጸሎት መጽሐፉን አውጥቶ ጸሎት ሲያደርግ ቆዬ። ጸሎቱን ሲጨርስ እንደገና በሌላ ተመስጥኦ ውስጥ ገባ። ብዙ የሚያንሰላስለው ጉዳይ ያለው ይመስላል። አልፎ አልፎ ላናግረው ስሞክርም ጥያቄ ከሆነ አጭር





መልስ አለበለዚያ ብዙውን ዘወር ብዬ ሳዬው በፈገግታ ከማየት በቀር መነጋገር እንዳልፈለገ ገባኝና እኔም ተውኩት።

አልፎ አልፎ ከሹፌሩ ጋር አወራለሁ። ‹ድሮም ብዙ አያወራም ነበር፤ አሁን የበለጠ ጨምሯል ወይም የሚያሣሥበው ጉዳይ አለ ማለት ነው?› እያልኩ እኔም በሐሳብ ተወሰድኩ።

ቲሊሊ ከተማ ስንደርስ አስፓልቱን ለቀን ወደ ግራ ታጠፍንና የጠጠር መንገድ ይዘን ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ መንገዝ ቀጠልን።

አንድ ሃያ ኪሎ ሜትር እንደተጓዝን ከመንገዱ በስተቀኝ በኩል ለየት ያሉ ሁለት ስፍራዎች ስንደርስ መኪናውን እንዲያቆም ሹፌሩን በትኅትና ጠየቀውና ቀልጠፍ ብሎ ዳር ይዞ ቆመ።

እጅግ የሚያምር አረንጓዴ ስጋጃ ምንጣፍ የተነጠፈበት የሚመስል ለጥ ያለ መስክ ነው። በርከት ያሉ ‹ኩንበል ወይም ቆባ› የሚባሉ ዛፎች በተፈጥሮ የበቀሉ በማይመስል ሥርዓት በግምት ከሁለት ሜትር በማይበልጥ መራራቅ ይታያሉ። የዛፎቹ ቁመት፣ የቅርንጫፋቸው ግዘፈት፣ የግንዶቻቸው ውፍረት ሌላው ቀርቶ ግንዶቹ መንታ የሚሆኑበት ከፍታ ሁሉ በእጅጉ ተመሣሣይ ነው። በቃ አረንጓዴ ምንጣፍ ላይ ለጌጥ የተተከሉ አርቴፊሻል እንጂ እንዲህ በተፈጥሮ የበቀሉ ናቸው ብሎ ለማመን ይቸግራል። የቅርንጫፎቻቸው ጠፈጠፍ ሳሩን አላጠፋውም። በግንዳቸው ዙሪያ የበቀሉት ‹ፈርንና ሞስስ› የተባሉ ዕፅዋት የአዛውንት ፅህም ይመስላሉ። ሰዐይን ከመማረኩም በላይ በዛፎቹ መካከል ሲራመዱ ከታች የውኃ ጋን ያለ ይመስላል።

አባ መዐዛ በዛፎቹ ዙሪያ በአድናቆት ሲዘዋወር ቆዬና ከኋላም ስለነበርኩ ዘወር አለና፦

"ወንድም ሲሳይ ስለ ኢነርጅ ዲስፔሽን (Energy dissipation) ታውቃለህ አይደል?" አለኝ፡፡

"ይመስለኛል፤ ኃይል መቀነስ ወይም ማራገፍ ይመስለኛል" አልኩት፡፡

"ልክ ነው፤ ይህ ቦታ እንደዚያ ነው" አለኝ፡፡

"የምን ኢነርጅ" አልኩት፡፡

"እርሱን የምናገኛቸው አባቶች ይነግሩን ይሆናል" አለኝና ወደ መኪናው ሲያመራ ተከተልኩት፡፡

በምዕራብ ጎጃም የሰከላ ወረዳ ዋና ከተማ የሆነችው የግሺ ዐባይ ከተማ ስንገባ ባለ ግርማው የቅዱስ ሚካኤል ወአቡነ ዘርዐ-ቡሩክ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ተቀበለን፡፡ መኪናችንን ከአጥሩ ጥግ አቁመን ወደ ግቢ ገባንና ተሳለምን፡፡

"እዚህ ማግኘት የሚገባን አባት አሉ፡፡ እርሳቸውን እስካፈላልግ አንተ ዘወር ዘወር ማለት ትችላለህ" አለኝ፡፡

"እሺ ይሁን፤ ግን የት ነው የማገኝህ?" ስለው

"እዚሁ አካባቢ አልጠፋም" አለኝ፡፡

ከቤተ ክርስቲያኑ ቅዕር ወጥቼ በውጭ ካሉት የንዋዬ ቅድሳት መሸጫ ሱቅ ውስጥ ገድለ አቡነ ዘርዐ-ብሩክ የተባለውን መጽሐፍ







ገዝቼ የደቡብን አቅጣጫ ይዤ በዝግታ እየተራመድኩ ወረድኩ፡፡ ቤተ ክርስቲያኑ ከፍታ ቦታ ላይ ያለ ሲሆን ወደ ደቡብ አቅጣጫ ያለው መሬት መጀመሪያ አካባቢ ተዳፋት ይሆንና ወደታች ደግሞ ወደ ሜዳነት ይቀየራል፡፡ ተዳፋቱን ትንሽ ወረድ እንዳሉ በስተቀኝ በደን የተሸፈነ ስፍራ ውስጥ አንድ የቆርቆሮ ክዳን ያላት አነስተኛ ቤት ትታያለች፡፡ እርሷ የዐባይ መነሻ የሆኑትን ምንጮች የምትከልል ቤት ናት፡፡ ከእነዚሁ ምንጮች የሚወጣው ውኃ ለሕሙማን ፈውስ ይሆን ዘንድ መጠመቂያዎች ወረድ ብለው ተሠርተዋል፡፡

ከመጠመቂያዎቹ በታች ግልገል ዐባይ ዘንዶ መስሎ ብዙ ወንዞችንና አፍላጋትን እያስገበረ የሺ ኪሎ ሜትሮች ጉዞውን ሲገሰግስ እንደ ቀዛ የሚጀምርበት ስፍራ ነው፡፡ ግራና ቀኝ ደስ የሚል ለምለም ሜዳ አለው፡፡ ዓመት እስከ ዓመት ሜዳው ፈውስን በሚፈልጉ ሕሙማን እንደተሞላ ነው፡፡ ግልገል ዐባይ መጀመሪያ ወደ ምሥራቅ ቀጥሎ ወደ ሰሜን፣ ከዚያም ወደ ምዕራብ እየታጠፈ ግማሽ ክብ ሠርቶ ከተማዋን እየከበበ በአጭር ርቀት የወንዝ ቅርፅ ይይዝና የመጀመሪያውን የጉዞ ምዕራፉን ወደ ጣና ሐይቅ ያደርጋል፡፡

በዝግታ ቁልቁለቱን እየወረድኩ ወደ ምንጮቹ ሳመራ አሁን በተራመድኩበት አንፃር እየተራመዱ ራሳቸውን እንደ ትልቅ ጀግና የቆጠሩ ዓለማቀፍ አሳሾች የጻፏቸው የጉዞ ማስታዎሻዎች በዐይነ ሕሊናዬ ይመላለሱ ጀመር፡፡

በ1610 ዓ/ም አካባቢ ፖርቱጋላዊ የካቶሊክ ሚሲዮናዊ ቄስ ፔድሮ ፔየዝ ከሥራ ባልደረባው ጋር በመሆን በዚሁ መስመር ተጉዞ ከምንጮቹ ደርሶ የዐባይን መነሻ በማየቱ ልዩ ስሜት እንደተሰማው የሚከተለውን ጽፏል፡፡

‹አጅግ ታላቅ ክብርና ደስታ እንደተሰማኝ መናገር ይኖርብኛል። የጥንቱ ንጉሥ ቂረስና ልጁ ካቢስስ፣ ታላቁ አሌክሳንደር፣ ዝነኛው ዮሊዮስ ቄሳር ከጥንት ጀምሮ ሲያዩት ይመኙት የነበረውን እኔ በአካል በማየቴ ደስታዬ ወደር የለውም።›

ሎቦ የተባለ የዚሁ የፖርቱጋል ሚሲዮን አባል ወደ ምንጮቹ ተጠግቶ ሲመረምር እያንዳንዳቸው ሁለት ጫማ ስፋት ያላቸው መሆናቸውንና አንደኛው ምንጭ አምስት ጫማ ጥልቀት ያለው ሲሆን የታተመ ሆኖ ውኃው ግን እየሰረገ የሚመጣ እንደሆነና ጥልቀቱንም ማግኘት መቻሉን ገልጿል። ሁለተኛው ምንጭ ግን መዳረሻውን ማግኘት እንዳልቻለና በአካባቢው ያገኛቸው ነዋሪዎችም ማንም ጥልቀቱን እንዳላገኘው እንደነገሩት ጽፏል። ሲያጠቃልልም ‹እነዚህ ምንጮች ከመሬት በታች ለተቀበረ ታላቅ ሐይቅ ማስተንፈሻ ናቸው› ብሏል።

ፖርቱጋላዊው ሚስዮናዊ ፔድሮዝ ይህን የውኃ ጋን የዐባይን ምንጭ በአካል ለመጀመሪያ ጊዜ ያየ የውጭ ተጉዥ በመሆኑ ልዩ ስሜት ቢሰማው አይፈረድበትም። ከእርሱ ከ150 ዓመት በኋላ 1762 ዓ/ም አካባቢ ወደዚህ ስፍራ የመጣው የስኮትላንድ ተወላጅና ተጓዥ ዝነኛው ጀምስ ብሩዝ እዚሁ ስፍራ ሲደርስ እራሱን እንደ መጀመሪያ አሳሽ ቆጥሮ ፈንድቋል። የምዕራባዊያን ራስ ወዳድነት፣ ከመጠን ያለፈ የዝና፣ የሀብት ፍቅርና ስግብግብነት መገለጫ የሆነው ጀምስ ብሩዝ ከእርሱ በፊት እነ ፔድሮ ቦታውን እንደረገጡ ቢያውቅም ጉብኝታቸውን በማጣጣል የራሱን ዝና ለመካብ ሞክሯል። ቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ ሲደርስ ቁልቁል በረግረግ የተከበበውን አካባቢ ሲያይና አስጐብኞቹ የዐባይ መነሻ ምንጮች መሆናቸውን ሲነግሩት በሙሉ ስሜት አካባቢው የተቀደሰ ነው ብሎ በማመኑ ጫማውን አውልቆ በባዶ እግሩ ወደ ምንጮቹ እንደሮጠ ጽፏል።





ብሩዝ ከምንጮቹ ሲደርስ ራሱን መቆጣጠር አቅቶት አብረውት የተጓዙት አሽከሮቹ እስኪታዘቡት ድረስ እንደ ድል አድራጊ ጀግና የድል መዝሙር ዘምሯል።› ይለናል ‹ዘ ብሉ ናይል› የተባለው መጽሐፍ ጸሐፊ አለን ሙርሄድ።

ብሩዝ በዚሁ የድል አድራጊነት ስሜት ውስጥ ሆኖ፡-

‹እናንተ የዓለም ኃያላን፣ ፈላስፎች፣ ጀግኖችና ልዑላን ኑ ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ፤ የታላቁን ወንዝ መገኛ አገኘቼዋለሁና› ብሏል።

አሁንም በጥልቅ ስሜት ሆኖ ለውኃ መጠጫ የሚጠቀምበትን ከኮኮናት ፍሬ የተዘጋጀውን ፋጋ አውጥቶ ከምንጩ ውኃ ቀድቶ ወደ ላይ እንደ ጽዋዕ ከፍ አድርጎ፡-

‹የተከበርከው የታላቋ ብሪታንያ ንጉሥ ግርማዊ ጆርጅ 3ኛ ሆይ፣ የታላቁ የሩሲያ ልዕልት ካትሪና ሆይ ለጤናችሁ!› ብሎ ከውኃው ተጐንጭቷል። እንደገናም ለጓደኞቹና ለሚወዳት እጮኛው ‹ለማርያ!› ብሎ ድጋሜ ተጐንጭቷል።

‹ይህ ሁሉ በስሜት መነካት የዐባይን ምንጭ በማግኘትና በማየት ከሆነ የዐባይ ምንጭ መገኛ ባለቤቶች እኛ ምን ይሰማናል?› ብዬ ሳስብ ‹በእጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ ቁጥር ነው› የሚለው ምሳሌ ታወሰኝ።

‹የግሪኮች የፍልስፍና ምንጭ ዐባይ፣ የሮማውያን የኃይል ምሳሌ ዐባይ፣ የግብፅ ፒራሚዶች የሥልጣኔ ምሥጢር ዐባይ፣ የእስራኤልን የተስፋ መሪ ሙሴን የታደገው ዐባይ፣ የኑቢያ የዕለት እንጀራ የዓመት ቀለብ ዐባይ፤ ምን ያክል ኢትዮጵያውያን ምንጩን ለማየት አስበው

ያውቁ ይሆን?‹ለመሆኑ ምን ያህል ኢትዮጵያውያን የዐባይን ምንጭ ለማየት እንጓጓ ይሆን?› ለመሆኑ ዐባይ ለኢትዮጵያውያን ምንድን ነው?, እያልኩ ሳስብ ‹ምን እዚም የተደረገብንና የተጋረደብን ዜጎች ነን› አልኩ።

አውሮፓውያን የዝናና የሀብት ልክፍታቸውን ገሀድ ያወጡበት፣ መጀመሪያ ያገኘሁት እኔ ነኝ እያሉ ያለ ይሉኝታ ሲወራረፉበት እኛ ባለቤቶቹ ግን ባይተዋር ነበርን። እንዴት ከእኛ ዘንድ ያለን ዕንቁ ሌላው በማየቱ ብቻ በግብዝነት ሲፎክር የዕንቁው ባለቤቶች እኛ ግን ለማየት እንኳን እንደነገዛለን! ከዐባይ ወንዝ መዳራሻ ላይ የተገነቡትን የካርቱምንና የካይሮን ከተሞች ግዝፈትና ዝማኔ አስቤ ከዐባይ ምንጩ ላይ የምትወተረተረውንና እንደነገሩ የሆነ ማረፊያ እንኳን የሌላትን እንደ ድሃ ኩራዝ ጭልጭል የምትለውን የግሺ ዐባይ ከተማን ሳይ ‹ቁመን እንደንቀር ማነው ያሰደገመብን?› አልኩ።

ነገሩ እየቆየ ሲሄድ መነሻውን በማየት የፈነጠዙት አውሮፓውያንና አሽከሮቻቸው ከማየት ‹የኔ ነው› ወደ ማለት ተሸጋገሩ። ‹አካሄዱን አይተህ ጭብጦውን ቀማው› መሆኑ ነው። ቆይተው ደግሞ እኛ ሳንፈቅድ ከላይም ከታችም፣ ከምንጩም ከጅረቱም አትንኩብን ሲሉን ትንሽ እንኳ ኃፍረት የላቸውም።

ለብዙ ዘመናት የግሪክ አማልክት ከዳሚዎች፣ ፈላስፎች፣ የሮማ ገዥዎች፣ የፋርስና የግብጽ ልዑላንና የጦር አዛገሮች የዚህን ታላቅ ወንዝ መገኛ ለማወቅ እጅግ ከመጓጓታቸውም በላይ ብዙ መላምቶችን አስቀምጠዋል። ብዙዎች የአሰሳ ሙከራ አድርገው በግብጽና ኑቢያ በረኃ ቀልጠው ቀርተዋል። የጅኦግራፊ ዕውቀት በደንብ ባላደገበት ዘመን የዐባይ ወንዝ መነሻን ብዙዎች ሲያምታቱት ኖረዋል። በነጭ ዐባይና በጥቁር ዐባይ መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት አቅቷቸው አንዳንዶች ቪክቶሪያ ሐይቅን እንደ መነሻ አድርገው ወስደዋል።





ይሁን እንጅ ከሰማንያ በመቶው በላይ የሚሆነውን የናይል ውኃ የሚያበረክተው ጥቁር ዐባይ ከኢትዮጵያ ደጋማ ስፍራዎች እንደሚመነጭ አንዳንዶቹ አላጡትም ነበር። እንዲያውም በግሪክ ሚቲዎሎጅ የዐባይ /ናይል/ ውኃ አማልክት ተቆጥተው የሜድትራኒያንን ባሕር ሲያናውጡት ውስጥ ለውስጥ ተገፍቶ ከኢትየጵያ ተራሮች ምንጭ ሆኖ ከፈነዳ በኂላ እንደገና ቁልቁል ወንዝ ሆኖ ይመጣል ብለው ያምኑ ነበር።

ይህን እስተሳሰብ ላስተዋለ ሰው ውኃው ከሜዲትራኒያን ተነሥቶ ተመልሶ ወደ ሜዲትራኒያን የሚመለስ በማስመሰል የታችኛውን ሀገሮች የባለቤትነት መንፈስ ለማጎልበት ይመስላል። ዐባይ ከኢትዮጵያ ተራሮች ላይ ከሚዘንበው ውኃ ወደ ከርሰ ምድር ተጠራቅሞ ምንጭ ሆኖ ይፈሳል የሚለውን የዘመናዊ ሃይድሮሎጅ ትንታኔ ገሸሽ አድርጎ በግሪኩ ሚቲዎሎጅ የአካባቢውን የውኃ ትርክት ለመቀየር ይመስላል። ምክንያቱም የዘመናዊ ሃይድሮሎጅ ባለሙያዎች ሳይንሳዊ ትንታኔ ዐባይ ከኢትዮጵያ ተራሮች የሚዘንበው ዝናብ የሚፈጥረው የውኃ ክምችት ነው። ይህ ማለት የዐባይ ውኃ መነሻ የኢትዮጵያ ተራሮች እንጅ ከሜዲትራኒያን የሚገፋ ውኃ ነው ብሎ ለማመን የመልክዓ ምድርና የሃይድሮሎጂ አመክንዮ የሌለው ነው ብለው ይሞግታሉ። እናም የዐባይ ምንጭ ኢትየጵያ ናት የሚለውን ነጥብ ያስረግጣሉ።

በዚሁ የግሪክ አፈታሪክ መሠረት የግሺ ዐባይ አካባቢ በመሬት ውስጥ የተቀበረ ታላቅ ሐይቅ (Great Subtranian Lake) አለው ተብሎ ይታመናል። እርግጥ ዘመናዊ ሃይድሮሎጅስቶችና ሃይድሮ-ጅኦሎጅስቶች ጭምር የግሺ ዐባይ አካባቢ የውኃ ጋን መሆኑን ይስማማሉ።

ግሺ ዐባይ የውኃ ጋን ለመሆኑ የሚያስማማ ቢሆንም የውኃውን ምንጭ አንደኛው በአማልክት ቁጣ ከሜዲትራኒያን የሚገፋው ውኃ ነው ሲሉ ዘመናዊው ሳይንስ ደግሞ ‹በደጋማዋ ኢትዮጵያ ከህንድ ውቅያኖስ በነፋስ እየተገፋ የመጣው ደመና የሚያዘንበው ዝናብ ነው› ይላሉ።

የዐባይ ምንጭ በዘመነ ኦሪት በየዓመቱ በኅዳር ወር የጊደር ደም መስዋዕት ይቀርብለት ነበር። አንዳች መለኮታዊ ኃይል አለው ተብሎ ስለሚታመን በየዓመቱ ይኸው መስዋዕት ሳይታጐል ይሰዋለት ነበር። ይህ የዐባይ አምልኮ አሁንም ድረስ በተለያዩ ስፍራዎች ሲከወን ይታያል። ከጣና መውጫ ወረድ ብሎ እስከ ጉባ ድረስ በተለያዩ ቦታዎች ዛሬም ድረስ የበግ፣ የዶሮ፣ የቂጣና አረቄ ግብር ይገባለታል። ሰዎች ስለት ይሰማል፣ ጤና ሀብት ይሰጣል ብለው በዐባይ አምላክ ያምኑበታል። ብዙ የተጫጫነው ትርክት ከአጋንንት ጋር የተያያዘውን ጨምሮ ስለ ዐባይ ቢነገርለትም አንዱ ትልቁ ቁም ነገር ከግሪክ እስከ ግብጽ፣ ከኑቢያ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ ዐባይ ልዩ ኃይል የተሰጠው የሥልጣኔ፣ የብልፅግና የሕይወት ምንጭ መሆኑን ነው።

የክርስትና ዕምነት በደጋማው ኢትዮጵያ ሲስፋፋ የዐባይ ምንጭ የጊደር ደም መስዋዕት መቀበሉ ተሸሮ የሐዲስ ኪዳን ጸሎትና ቡራኬ እየተቀበለ ብዙዎችን ከደዌያቸው እየፈወሰ ቀጥሏል። ይሁን እንጅ በኢትየጵያውያን ፖለቲካና ኢኮኖሚ ዕድገት ግን እዚህ ግባ የሚባል አስተዋፅኦ ነበረው ለማለት ያስቸግራል።

ከጸበል መጠመቂያው አልፎ ‹ግልገል ዐባይ› ተብሎ ጉዞውን ከሚጀምርበት ስፈራ ላይ በርከክ አልኩ። የመጣው ሄዶ የሚመጣው ሲሄድ ዐባይ ላይመለስ ረጅሙን ጉዞ የሚጀምርበት ሆድ የሚያባባ ስፍራ ነው። ከእኛ ወጥቶ ለእኛ ላይሆን ዝም ብሎ ጉዞ የሚጀምርበት





ስፍራ ነው። ትንሽ መስሎ ዳር ሲደርስ ሲገዝፍ አባብሎን ከእኛ የሚወጣበት ስፍራ ነው። ከእኛ ተወልዶ ባዕድ ሲሆንብን ‹ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ› እያለ ትቶን ሲሄድ እንዳለፈው ሦስት ሺ ዘመን ሁሉ ጉዞ የሚጀምርበት ስፍራ ነው። መዘዝ ሲልክብን እንደዋዛ አዘናግቶን ምዝዝ ብሎ የሚወጣበት ስፍራ ነው።

ሳላስበው ውኃውን በእጄ እየቀዳሁ መልሼ እየደፋሁ ከውኃው ጋር መነጋገር ጀመርኩ፦

"ምነው ዐባይ! ከታች ሆነው ወደላይ ሲፈሩን ሲገባ ሲያንኳጥጡን ዝም አልክሳ? ከላይ ሆነን ወደታች የምንልክላቸውን አንተን ሲቀሙን ሲታትሩ ምን አልክ? ውኃችን፣ አፈራችንን፣ ታሪካችንን፣ ቅስማችንን፣ ፈውሳችንን ሁለነገራችንን እየወሰድክ አንድ ቀን አንድ ዘመን እንኳን በበጎ የማያዩን ሲሆኑ እንዴት ፍትህ ተረሣህ? ከእኛ ጋር ትንሽ ቆይ ስላለንህ ዓለም ሁሉ ሲያብርብን ምን ተሰማህ? እንዲያውም እምቢ አልመጣም አትልም! ከደጋ በረኃን፣ ከላይ ይልቅ ከታች መሆንን፣ ከምትጀምርበት ይልቅ የምትጨርስበትን፣ ከተወለድክበት ይልቅ የምትሞትበትን እንዴት መረጥክ? እኔ የምልህ በቃ አትሄድም ብንልህ፣ ወንዝ መሆንህ ቀርቶ ሐይቅ ብናደርግህ፣ ፈሳሽ መሆንህ ቀርቶ ተን ደመና አድርገን በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ ብናንልልህ ምን ታመጣለህ? ምን ያመጣሉ?!" አልኩና ስለማመጠው የነበረውን ትቼ አፈጠጥኩበት ወንዙን፤ ግልገል ዐባይን!

‹ሆ..ሆ..! አሁን እንደ ዕብድ ብቻዬን ስነጋገር ሰው ቢያየኝ ምን ይላል? እዚሁ ግዮን ጸበል ሰባት ይጠመቅ ብባልስ!› አልኩ ለራሴ።



# ምዕራፍ - ፳

ስለ ዐባይ ምንጭ ሲነሳ አቡነ ዘርዐ ብሩክ የተባሉት ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ስም አብሮ ይነሳል። በስምንተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ የተነሡት እኒህ ቅዱስ በዐባይ ምንጭ አካባቢ ለ30 ዓመታት ያክል በጸሎትና በቅድስና የኖሩ ናቸው።

በወቅቱ ከነበረው ገዥ ጋር ደህ ተበደለ፣ ፍርድ ተጓደለ፣ የእግዚአብሔር ሕግ ተሻረ ብለው በድፍረት በማስተማራቸው ገዥው ተቆጥቶ ለግዞት እንደሚልካቸው ሲያውቁ ብዙ ምሥጢራትን የያዙትን የትምህርትና





የጸሎት የብራና መጽሐፍቶቻቸውን ወደ ዐባይ ምንጭ በመጣል ቅዱሱ ውኃ በአደራ እንዲጠብቅላቸው ሰጥተው ወደ እስር ቤታቸው ሄደዋል።

የአምላክ ፈቃድ ሆኖ የግዞትና የእስር ጊዜያቸውን ጨርሰው ከአምስት ዓመታት በኋላ ወደ ዐባይ ምንጭ ተመለሱ። እንደደረሱ ወደ ምንጩ ጠጋ ብለው አቡነ ዘበሰማያት፣ ውዳሴ ማርያም ደግመው 400 እግዚኦታ፣ 41 ኪራላይሶን አድርሰው፦

"በእግዚአብሔር ፊት በአደራ የሰጠሁሽን መጽሐፎቼን ግሺ / ትፊ/" አሏት።

ያን ጊዜ ሰባቱን መጽሐፎቻቸውን ተፋች። ብራናቸው ሳይርስ ቀለማቸው ሳይደመሰስ አገኟቸው። ወዲው ደቀ-መዝሙራቸውን ዘሩፋኤልን ጠርተው፦

"አባ እይ!" ስላሉ ከዚህ በኋላ ‹ግዮን ግሺ ዐባይ ተባለች።›

አባ ዘርዐ ቡሩክም "ዮናስን በከርሠ አንበሪ እንደጠበቀ ሁሉን በሚያርስና በሚያረጥብ በግዮን ውኃ ውስጥ ሳይረጥቡ በደረቅ መጽሐፎቼን የጠበቀ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን" አሉ። ይላል ገድለ ዘርዐ ብሩክ የተባለው መጽሐፍ።

አስደናቂው ነገር ዘርዐ ብሩክ 482 ዓመታታን በምድር ኖረው ያረፉ መሆናቸው ነው። ዛሬ ከምንጩ በስተራስጌ ተራራው ላይ የተሠራው ቤተ ክርስቲያን ከቅዱስ ሚካኤል በተጨማሪ በስማቸው ዕላት ተቀርጾ ለምዕመን መማፀኛ ሆኗል።

በዚሁ የገድል መጽሐፍ ላይ አዕምሮዬን አስፍቼ እንዳስብ የሚያደርግ አንድ አስገራሚ ታሪክ አነበብኩ። እንዲህ ይላል፡-

"ዳግመኛ እግዚአብሔር ብፁዕና ቅዱስ ለሚሆን አባታችን ዘርዐ ቡሩክ... ልዩ ልዩ ሀብታትን ሁሉ ሰጠው። ለሥላሴ ከሚገባ ከስግደትና በቃልና በሥልጣን ፍጥረታትን ከመፍጠር በቀር ምንም ያልሰጠሁህ የለም" አለው ይልና

"ዳግመኛም ጽንፍ እስከ ጽንፍ ደርሶ በቀን ያበራ ዘንድ በውስጡ የፀሐይ ብርሃን ወደሌለበት በሌሊትም ያበራ ዘንድ የጨረቃና የከዋክብት ብርሃን ወደ ሌለበት ሀገር ይሄድ ዘንድ አዘዘው።

በዚያም ሀገር መዓልትና ሌሊት በጋና ክረምት የለም። በዚያም ሀገር ከላይ እስከ ታች የሚደርስ ውኃ ሞልቷል። ለዚህም ውኃ በታች የሚደርስበት እና የሚከማችበት የለውም ደግሞ የሚወሰንበት ድንበር የለውም። ከላይ እስከ ታች ሁልጊዜ ምሉዕ ነው እንጂ።

ይህን ሀገር የሚያውቁ የሉም። ያም ውኃ በአሸዋ በድንበር እንደሚወስኑት ውኃዎችና ባሕሮች ድንበርና ወሰን የለውም። ጥበበኞች እንዳያውቁት በሰማይና በምድር ያሉ ቅዱሳንም እንዳያዩት ሙሉ አድርጎ ፈጥሮ እግዚአብሔር ሰወረው።

ያም አባታችን በሁሉ ላይ ሥልጣን ካለውና ኃያል ከሚሆን ከፈጣሪው ሥልጣንን ተቀብሎ እስከ አድማስ ድረስ ሄደ በውስጡ ጨለማና ውኃን ወደተሞላ ሀገር ደረሰ። በየቀኑና





በየሰዓቱ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ወደዚያ እየሄደ ይህን ሀገር ከላይ እስከ ታች የመላውን ወሰን ድንበር የሌለውን ይህን ውኃ ባሳየውና ከክፉ ነገር ሁሉ በሰወረው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ታስርባት ወደ ነበረበት ሀገሩ በቅጽበት ይመለስ ነበር።

ጻድቅ አባታችን ከዚያ ተመልሶ ከወዳጆቹ የሰወረው ይህን የመላ ውኃ የሰወረውን እግዚአብሔር እንደገለጠለት ነገረን። እኛም ይህን ነገር ከአንደበቱ ሰምተን እግዚአብሔር የሰወረውን ሁሉ ገልጦ እንዳሳዬው አወቅን አመንን። ይህም ሁሉ ነገር ከአንደበቱ የሰማነው ነው" ይላል ገድሉ ሲጨርስ።

‹ይህ የተሰወረ ውኃ የተሞላ ጨለማ ሀገር ምንድን ነው? የትስ ነው?› ብዬ ባሰብኩ ቁጥር የግሪክ አፈታሪክ በመሬት ውስጥ የተቀበረ ታላቅ ሐይቅ (Great Subtranian Lake) የሚለውን አስታወሰኝና የግሺ ዐባይ ክርስ ድብቅ ምሥጢር ሦስተኛ ነገር እንዳለው ተረዳሁ።

በአዕምሮዬ ደጋጋሜ ባሰላሰልኩት ቁጥር ‹የግሺ ዐባይ እና አካባቢያዊ ውስጠ ክርስ፤ አንድም የግሪክ አፈታሪክ እንደሚለው አማልክት ሊቆጡ የሜዲትራኒያን ባሕር ውኃ በነፋስ ተገፍቶ የሚጠራቀምበት የተቀበረ ታላቅ ሐይቅ፤ ሁለትም ዘመናዊ የውኃ ሳይንስ ባለሙያዎች ከሕንድ ውቅያኖስ በንፋስ ተጭኖ የሚመጣው ደመና የሚጥለው ዝናብ እየሠረገ የሚጠራቀምበት ኮንተጋራሪ የውኃ ጋን አለ የሚለው ሲሆን፤ ሦስትም ከአባ ዘርዐ ቡሩክ ገድል ላይ ያነበብኩት እግዚአብሔር ባወቀ በመለኮታዊ ጥበቡ በውኃ ሞልቶ ሰውሮ ያስቀመጠው ጨለማ ስፍራ አለ ማለት ነው።› አልኩኝ።

‹አባ መዐዛ ቅዱሳን ጠዋት ከምታስበው በላይ ውስብስብ ነው ያለኝ ያለ ነገር አይደለም› አልኩ።

አሁን ወደ አባ መዐዛ ቅዱሳን ተመልሼ ድብቋንና ሦስተኛውን ረድፍ መላምት ወይም በውኃ የተሞላውን ጨለማ ሀገር ምሥጢር ማወቅ አለብኝ አልኩ።

ውስጤ አንድ ትልቅ ምሥጢር እዚህ አካባቢ እንዳለ እየነገረኝ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ዳገቱን እየተጣደፍኩ አመራሁ።



ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)
የቴሌግራም ቻናል



# ምዕራፍ - ፳፮

እየተጣደፍኩ ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ግቢ ገብቼ አባ መዐዛን መፈለግ ጀመርኩ። ሦስት ህንፃ ቤተ ክርስቲያኖች በግቢው ውስጥ ይታያሉ። አንዱ በግቢው በር በስተግራ በኩል መቃኞ የሚመስል አነስተኛ ቤተ መቅደስ፣ ከግቢው በር ፊት ለፊት ደግሞ ባለግርማ ሞገሱ በአዲስ የተሠራው ህንፃ ቤተ ክርስቲያን ይገኛል። ከሁለቱ ሕንፃዎች መካከል ወደ ሰሜን ፈንጠር ብሎ ሌላ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን አለ። አዲሱ ከመሠራቱ በፊት አገልግሎት ይሰጥ የነበረው ነው።



Scanned with CamScanner

ከተድሞው ቤተ ክርስቲያን በስተሰሜን ጥቅጥቅ ያለ የደጋ ቀርቀሃ ደን አለ። የቀርቀሃው ደን እና የቤተ ክርስቲያኑ ግቢ በጥንታዊ የፈራረሰ ግንብ ተለይቷል። ግቢውን ስቃኝ ቆይቼ ከዚሁ ካብ አጠገብ አባ መዐዛ ካንድ ጠቆር ያለ ፎጣ የለበሰ ሰው ጋር ቆሞ ሲነጋገር ተመለከትኩት። ወደ እርሱ ስራመድ ቀድሞ ተመልክቶኝ ኖሮ፡-

"ወንድም ሲሳይ መጣህ፤ ና በል አባት ላስተዋውቅህ" አለኝ።

"ጠጋ ብዬ በትህትና ጤና ይስጥልኝ" አልኩ።

"ባሕታዊ ኤስድሮስ ይባላሉ" አለኝ አባ መዐዛ።

"ሰብሕትውና አልበቃሁም ወንድም ኤስድሮስ ይበሉኝ" አሉ።

ቁዳቸው ከአጥንታቸው ጋር የተጣበቀ መንፈስ እንጅ ሥጋ የለበሱ የማይመስሉ ናቸው። ጸጉራቸው ከራስ ቆባቸው አፈትልኮ በትከሻቸው ላይ ተደፍቷል። ቀጫጫ እጃቸው ላይ ብዙ ዙር ያለው ከእንጨት የተሠራ መቁጠሪያ አላቸው።

እጃቸውን ለሰላምታ ሲዘረጉልኝ ጣቶቻቸው የሚሰበሩ ስለመሰለኝ ለመጨበጥ ተሣቀቅኩ። እርሳቸው ግን በአንድ እጃቸው ብቻ ሳይሆን በሁለቱም ጨበጥ አድርገው፡-

"እንኳን ወደ ፈለገ ግዮን ግሺ ዐባይ በሰላም መጡ" አሉኝ።

"እባክዎትን አንተ ይበሉኝ" አልኩ በአንቱታው እየተሳቀቅኩ።

እጃቸው እንደገመትኩት የሚሰበር ሳይሆን ጥንካሬው የብረት ፌሮ የመጨበጥ ያክል ነበር። ትኩረቱ ሁሉ ከአካላቸውና ከሁኔታቸው ላይ ስለነበር ዝም ብዬ አትኩሬ ከማዬት በስተቀር መልስ እንኳን





አልሰጠኋቸውም ነበር። ከመጠን በላይ ማፍጠጤ ታወቀኝና አንገቴን ቀለስ አድርጌ ወደ አባ መዐዛ መመልከት ጀመርኩ።

ወደ ቀርቀሃው ደን ውስጥ ተጠቃቅሰው ሲሄዱ ተከትዬ ሄድኩና ትንሽዬ ክፍተት ባለበት ስፍራ ላይ ከተቀመጡ ድንጋዮች ላይ አረፍ ሲሉ እኔም ተከታታዬ ቁጭ አልኩ።

አባ መዐዛ ወደ እኔ እየተመለከተ፡-

"ወንድም ሲሳይ ባሕታዊ ኤስድሮስ የአቡነ ዘርዐ ቡሩክ ቃል ኪዳንና የግዮን ምሥጢር ጠባቂ ማህበር መናንያን አንዱ ናቸው። ስንመጣ እንደነገርኩህ እንድናመጣ የተጠየቅነው ‹ማዬ ገቦ› በታላቁ መጽሐፍ እንደተረዳሁት እዚህ ነው። በቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ካርታ ላይ ሰሜንን እንደ ራስጌ ደቡብን እንደ ግርጌ አድርገን ብንወስደው ወይም ደቡብን እንደ ራስጌ ሰሜንን እንደ ግርጌ አድርገን ብንመለከተው ይህ ስፍራ በእካል ክፍል ጎን አካባቢ ያርፋል። ስለሆነም ‹ማዬ ገቦ› ወይም ከጐን የሚፈስ ውኃ ሊባል ይችላል" ብሎ ሊተጥል ሲል።

"ታድያ እንዲያ ከሆነ ለምን ከምንጮቹ ቀድተን አንሄድም? ሚተራሊዮን እኮ በየቀኑ ሥቃይ ላይ ትመስለኛለች" አልኩት። ለእርሷ በእውነት አስቤ ይሁን ወይም ቶሎ የታዘዝኩትን ተገላግዬ ወደ ቤቴ ለመመለስ በመፈለግ ይሁን ለራሴም ግልፅ አይደለም።

"በየቀኑ ሥቃይ ላይ መሆኗ እውነት ነው። ይሁን እንጅ መጽሐፉ ባዘዘው መሠረት ካልሆነ ዞሮ ዞሮ ድካም ነው " አለኝ።

"ታድያ ማዬ ገቦውን ከዐባይ ምንጭ ካልሆነ ከየት ነው የምናገኘው?" አልኩ።

ችኩልነቱንና ስልቹነቱን የሚያውቀው አባ መዐዛ በባሕታዊ ኢሰድርስ ፊት ሊያሳጣኝ አልፈለገምና፡-

"ይኸውልህ ወንድም ሲሳይ በእርግጥ የምናገኘው ከዐባይ ምንጭ ነው። በዚህ ቦታ ዐባይና ግዮን የሚባሉ ስሞች በጥንቃቄ የሚታዩ ናቸው። ታላቁ መጽሐፍ ያዘዘን ግዮን ዐባይን ከሚወልድበት ሥፍራ ላይ ነው" አለ።

"አልገባኝም ዐባይን ግዮን እያልን እየቀያየርን አይደል የምንጠራው? ሁለቱ ያው አንድ መስለውኝ?" አልኩና በዚሁ አጋጣሚ ጥያቄዬን ላንሳ ብዬ፡-

"እንዲያውም አሁን ወደ እናንተ ከመምጣቴ በፊት ገድለ አቡነ ዘርዐ ቡሩክን ሳነብ በውኃ ስለተሞላ ጨለማ ዓለም የሚናገር አይቼ ለመጠየቅ ነበር የመጣሁ" አልኩ ወደ ባሕታዊ ዘወር ብዬ።

ስከዚህ ሰዓት ባሕታዊ በፈገግታ እያዳመጡ ነበርና ጥያቄዬ ለእርሳቸው መሆኑ ስለገባቸው፡-

"ማለፊያ ንባብ አድርገሃል!" አሉ ድምጻቸው በከፊል የተዘጋ ይመስል ጉልበት የለውም።

"እኛ በዚህ ቦታ ያለን ቃል ኪዳኑን ተስፋ የምንጠባበቅ መናንያን ዋናው ሥራችን አባታችን ያዩትን ምሥጢር መጠበቅና የመንፈስ ልዕልና ያለው ትውልድ ሲመጣ ማሳወቅ ነው። ግሺ ዐባይ የምንለው ይህ ሥፍራ ከዔድን ገነት ጋር በምሥጢራዊው ግዮን እትብትነት የተሳሰሩ የቃልኪዳን እናትና ልጅ ናቸው።" አሉ።





ቃል ኪዳን፣ ምሥጢር የሚሉት ነገሮች የበለጠ እያምታቱኝ መጡ። ምንም የምጨብጠው አልነበረም። ብቻ ቀደም ሲል ከነበረኝ ሦስት መላምቶች ሦስተኛው የኢትዮጵያ ሊቃውንትና መናንያን የራሳቸው መረዳትና ምሥጢር ያላቸው መሆኑን ነው።

"የዐባይ ውኃ ምንድን ነው? የምናያቸው ምንጮችስ እውነተኞቹ ምንጮች አይደሉምን? ዐባይና ግዮን ለአንድ ወንዝ የተሰጡ ስሞች አይደሉምን?" እያልኩ በሐሳብ ጭልጥ አልኩ።

በሐሳብ መንጉዶዬን ያየው አባ መዐዛ፡-

"ለማንኛውም ወንድም ሲሳይ በገሃድና በስውር በዚህ ስፍራ የመነኑ የአቡነ ዘርዐ ቡሩክ የቃል ኪዳን ልጆች ባይገባንም በቅንነት ስለመታዘዛችንና የዚያች ምስኪን ሴት የመከራ ዘመን ማብቂያ ጊዜ ስለደረሰ ምሥጢሩን በከፊል ሊያሳዩን ከተገቢው ስፍራ ላይ ‹ማዩ ገቦውን› እንድንቀዳ አብረውን እንደሚሠለፉ መልካም ፈቃዳቸው ሆኗል" አለ።

ምን እንደተፈቀደ፣ ምን እንደምናይ ባይገባኝም "እግዚአብሔር ያከብርልን" አልኩ በደፈናው።

"በመጀመሪያ ዋሻውን በቀን ማየቱ ጥሩ ነው። ማረፊያችንም በዚያው አካባቢ ስለሚሆን እንውረድ" ብለው ከመቀመጫቸው ተነሡ።

"የምን ዋሻ?" አልኩ።

"ልናየው አይደል!" አለ አባ መዐዛ። እባክህ ተረጋጋ ነው ነገሩ።

የቤተ ክርስቲያኑን ግቢ አቋርጠን ቅድም ወርጀበት የነበረውን መንገድ ተከትለን ወደ ምንጮቹ አመራን፡፡ ከምንጮቹ አቅራቢያ ስንደርስ የምንጮቹን መገኛ በስተቀኝ ትተን ቁልቁል ወረድንና ገና የተወለደውን ጨቅላውን ግልገል ዐባይን በእንጨት ርብራብ አቋርጠን በጸበልተኛ የተሞላውን ሰምለም መስከ አቋርጠን ወደ ደቡብ አመራን፡፡ መስኩን ጨርሰን የገበሬዎችን መኖሪያና የባሕር ዛፍ ተክል ግራና ቀኝ አልፈን ደልዳላው መሬት አልቆ ከ15 ደቂቃ ጉዞ በኋላ የገደል አፋፍ ላይ ደረስን፡፡ እዚህ ስፍራ ላይ በግምት 100 ሜትር ከፍታ ልዩነት ዝቅ ብሎ እንደገና ሌላ ሜዳማ አገር ለዓይን እስኪ.ታክት ይታያል፡፡

ባሕታዊ የገደሉ አፋፍ ሲደርሱ ወደ ቀኝ ታጠፉና የገደሉን ጠርዝ ተከትለው ተጓዙ፡፡ በግራ በኩል ጭው ያለውን ገደል ስበት እየተጠነቀኩ አባ መዐዛን ተከትዬ ሄድኩ፡፡

አንድ ሁለት መቶ ሜትር እንደተጓዙ አንድ ጫማ በላይ በአንድ ጊዜ የማታስረግጥ የበሬ ምላስ የምታክል  የሥርጥ መንገድ ተከትለው መውረድ ጀመሩ፡፡ በግራ በኩል ጭው ያለ ገደል በቀኝ በኩል ደግሞ የሚያገ፣ የሚጨብጥ የሌለው ዐለት ከመንገዱ ጥበትና ተዳፋትነቱ ተጨማምሮ "‹ወደ ጽድቅ የሚወስደው መንገድ ጠባብ ነው› የተባለው ይሄ ይሆን?" አልኩ፡፡ ትንሽ እንደተራመድን ለመውረድ ሰውነቴ ሲንቀጠቀጥ፡-

"እነዚህ ሰዎች እስከ ኃጢያቴ ገደል ሲጨምሩኝ ይፈልጋሉ ማለት ነው" አልኩ በምሬት፡፡

ለባሕታዊ መንገዱ ችግር አልነበረም፡ ‹እርሳቸው መንፈስ እንጅ ሥጋ አይደሉም› አላልኩም? አባ መዐዛም ብዙ አልተቸገረም፡፡ ነፍስና ሥጋዬ እየተላቀቀ እነርሱ ከቆሙበት ሲደርሱ መንገዱ አልቆ ፍፁም





ገደል ላይ ደርሰናል፡፡ ‹በገመድ ይዘውኝ ሊወርዱ ይሆን?› ብዬ ስፈራ ባሕታዊና አባ መዐዛ የእኔን መድረስ ሲያዩ ወደቀኝ እጥፍ ብለው ከዐይኔ እልም አሉ፡፡

አንድ ሁለት ሜትሮችን ራመድ ስል ከላይ ያላየሁት ትልቅ ዋሻ በስተቀኝ ኖሯል፡፡ ወደዋሻው መግቢያ ስጠጋ ጫማቸውን እያወለቁ አየሁ፡፡ ‹ጫማ ተደርጐ አይገባም ማለት ነው› አልኩና እኔም አወለቅኩ፡፡ የዋሻው መግቢያ ሰፊ ሊባል የሚችል ነው፡፡ ወደ አራት ሜትር ይጠጋል፡፡ ወደ ውስጥ ሲዘለቅ ከፍታው በአብዛኛው ከአንድ ሜትር አይበልጥም፡፡ አልፎ አልፎ ቀና ለማለት የሚያስችል እስከ አንድ ሜትር ከግማሽ  የሚደርስ ከፍታ አለው፡፡ የዋሻው ወለልም ይሁን ጣሪያ ጽድት ያለ ነው፡፡ በየጊዜው እንደሚጠረግ ማሣያ ነው፡፡ እነርሱ ወደ ውስጥ ሲዘልቁ ተከትዬ ለመራመድ ስሞክር ለመቆም የማያስችል በመሆኑ በጉንብስ መሄድ ግዴታዬ ሆነ፡፡ ትንሽ እንደተራመድኩ ወገቤ መንቋቋት ጀመረ፡፡ ተንበርክኬ ለመሄድ ሞከርኩ! ዐለታማው ወለል ጉልበቴን የሚልጠው ሆነ፡፡ ባሕታዊ ተጐንብሰው ለመሄድ ችግር ያለባቸው አይመስሉም፡፡ መሰስ ብለው መቆም ወደሚያስችለው ስፍራ ደርሰው ቆሙ፡፡ እንደ ምንም እየተንቋቋሁ አጠገባቸው ደርሸ ቆምኩ፡፡

ተጐንብሼም ሆነ ቆሜ የምረግጠው የዐለት ወለል ‹ድም.. ድም..› የሚል ድምፅ የሚያሰማ መሆኑን ተገነዘብኩ፡፡ ከስሩ ክድፍን ቋጥኝ ወይም ከዐለት ጋር የተያያዘ ሳይሆን ከሥር ውስጡ ሙሉ ለሙሉ ክፍት ወይም ቤዝመንት ያለው ለመሆኑ ምንም ጥርጥር አልነበረብኝም፡፡ እንደ ቆምኩ ዋሻውን ሳይ አልፎ አልፎ ወለሉን ከጣሪያው ቋጥኝ ጋር የሚያገናኙ ተሽካሚ አምዶች አሉ፡፡ ‹የዐለት አምዶቹ አልፎ አልፎ ጣሪያውን ደግፈው መቆማቸው ይህ ዋሻ የተፈጥሮ ይምሰል እንጅ በከፊል ሰው ሰራሽ ለመሆኑ ማስረጃ ነው› አልኩ ለራሴ፡፡

ደ.ጋግሜ እየተንቀሳቀስኩ የዐለት ወለሉን በእግሬ መታ መታ አደረኩት ‹ድም ድም› የሚል ከሥር ክፍት የመሆን ድምፅ አሰማኝ፡፡

"ለመሆኑ ይህ ስፍራ ምንድ ነው?" አልኳቸው፡፡

"ይህ ዋሻ ታላቁ አባት አቡነ ዘርዐ ቡሩክ ይጸልዩበት የነበረ ዋሻ ነው፡፡ ዛሬም ድረስ ብዙ ስውራን፣ ቅዱሳን፣ ባህታውያን ሰጸሎት ይተጉበታል" አሉ ባሕታዊ፡፡

" ከታች ምን እንዳለ ይታወቃል? መቼም ክፍት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡' አልኳቸው፡፡

ባሕታዊ የእኔን ጥያቄ ችል ብለው፡-

"እንግዲህ ወንድሞቼ በዚህ ስፍራ ቸርነቱ የማያልቅ በመለኮቱ ሁሉ የሚቻለው ፈጣሪ ለአባታችን ብዙ ቃል ኪዳን የሰጠበት፣ ለሌሎች ክቡራን ተሠውሮ ለእርሳቸው የተገለጠላቸው፤ ጨለማው ሀገር ውኃ የሞላበት ስፍራ ከዚህ ዋሻ በታች ጀምሮ አባታችንና ፈጣሪ ብቻ የሚያውቁት ዳርቻው የማይታወቅ ነው፡፡" አሉ፡፡

"ጨለማው ውስጥ ገብቶ ውኃውን ያየ ሰው ይኖራል?" አልኩ፡፡

"ሁሉም ምሥጢር ባይታወቅም አባቶቻችን የተረዱት ዐብይ ጉዳይ አለ፡፡ ከዔድን ተነስተው ገነትን የሚያጠጡ አራት ወንዞች አሉ። እነርሱም ኤፌሶን፣ ግዮን፣ ጤግሮስና ኤፍራጥስ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ግዮን ‹ኢትዮጵያን ሁሉ ይከባል› ተብሎ በታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ሁለት የተጻፈው ነው፡፡ ይህ ማለት ግዮን ገነትን ከጠጣ በኋላ መለኮታዊ ጉዞውን ወደ ምድር አድርጎ







እዚህ ስፍራ ሲደርስ ወደ ገጸ ምድር ይወጣል፡፡" አሉና ወደ ጨለማው ዋሻ ሲያዩ ቆይተው፡-

"ነገር ግን ታላቁ የፈውስና የበረከት፣ የኃይልና የክብር ወንዝ ከገነት በመጣበት ኃይሉ ወደ ምንጮቹ ከመውጣቱ በፊት ከዚህ ዋሻ በታች ምሥጢራዊ ስፍራ ላይ ይደርሳል፡፡ ከዚያም ከላይ ባሉት ምንጮች መጠኑን ቀንሶ ‹ዐባይ› ተብሎ እንደገና ምድራዊ ጉዞውን ይጀምራል" አሉ፡፡

አባ መዐዛ መንገድ ላይ ስንመጣ ስለ ኢነርጂ ዲስፔሽን የጠየቀኝ ትዝ አለኝና ‹ይሄ ሰው ስለዚህ ስፍራ ቀደም ብሎ መረጃ ነበረው ማለት ነው? እነዚያ ቦታዎችም ማስተንፈሻ ናቸው ማለት ነው?› አልኩ ለራሴ፡፡

የእኛን ጥያቄም አስተያየትም ሳይጠብቁ በስተግራ አቅጣጫ አሁንም አጎንብሰው መራመድ ጀመሩ፡፡ አሁን ሙሉ ለሙሉ ዋሻው በጽልመት ተውጧል፡፡ ባሕታዊ በያዙት የእጅ ባትሪ እየተመራን ተጓዝን፡፡ ድቅድቅ ጨለማና ቀዝቃዛ ቢሆንም የሆነ ደስ የሚል ስሜት አለው፡፡ ግርማው የሚከብድ እንጅ የሚያስፈራ አይደለም፡፡

ትንሽ እንደተጓዝን፤ "ይህን ይዞን ብንጓዝ ወደ ልዩ ልዩ መካናት ሊያደርሰን ይችላል፡፡ ዋናው ለእናንተ ተልዕኮ የሚፈለገው ግን ወደ መጀመሪያውና አሁን ባለን መረዳት እንድንገባበት ወደ ተፈቀደው ሥውር ዋሻ ወደ ‹በኩረ ግዮን› ነው" አሉ፡፡

የማየው ሁሉ በህልሜ ስለመሰለኝ መጠየቅ ሁሉ ትቻለሁ፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ ስለ ግሺ ዐባይ ሲወራ፣ ስለ ዐባይ ምንጭ ሲነገር፣ እነ ጀምስ ብሩገዝም ሆነ እነ ፔድሮ በታሪክ ማስታወሻቸው ስለዚህ ዋሻና ባለ ውኃ

ጋን ምድርቤት ምንም አለማለታቸው ደነቀኝ። 'የኢትዮጵያውያን ምሥጢራዊነት ያስደምማል' አልኩ ለራሴ።

ባሕታዊ ወደ ኋላ ተመለሱና እንደገና በቀኝ በኩል አሁንም ተንንብለን ተጓዝን። የወገቤ ነገር ቆይቶ ምን እንደሚያደርገኝ እያሰብኩ ተከተልኩ።

"ወደዚህ ጠጋ በሉ" አሉን።

እየተንፏቀቅን ተከተልናቸው። ከዋሻው ግድግዳ ላይ የተበየዱ የሚመስሉና ካርታ የሚመስሉ ነገሮችን አሳዩን። አንደኛው ከጥላ ጎደል የኢትዮጵያ ካርታን ይመስላል፣ ሌላኛው የአፍሪካ ብቻ በሥርዓት የተቆረቆሩ ወይም ተፈልፍለው መልሰው የተገጠሙ ይመስላል።

"እንግዲህ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነልን ዛሬ ማታ በሦስተኛው ሌሊት ክፍል መጥተን በእነዚህ ምሥጢራዊ የዋሻው በሮች መከፈቻ ከፍተን ወደ 'ብኩረ ግዮን' እንወርዳለን። የቀረውን እዛው እንነጋገራለን" አሉ። የዋሻው በሮች መከፈቻ ብለው እያሳዩን ያሉት ራሳቸው የቋጥኙ አካል የሆኑ ድፍን ናቸው። እንዴት ሁነው የበር መከፈቻ ቁልፍ እንደሚሆኑ ባይገባኝም በጣም ብዙ ያልገባኝ ነገር ስላለ መተውን መረጥኩ።

የማየውም የምሰማውም ሁሉ ድብልቅልቅ ያለ ስሜት ፈጠረብኝ። የተለመደው ጉጉቴና የማየት ፍላጎቴ ተቀሰቀሰ። በሌላ በኩል በድቅድቅ ዋሻ ውስጥ ተዳፍኖ የተቀመጠን የዐለት በር ከፍቶ እንደገና ከመሬት በታች የሚገኝ ሌላ የጨለማ ዋሻ ውስጥ መግባት አጉል ጀብደኝነት መሰለኝ። በሁለት ነገሮች ግን ተፅናናሁ። አንደኛ እጅግ ቀዝቃዛና እርጥበታማ በመሆኑ አስፈሪ እንስሳት አይኖሩም። እባብም ዘንዶም ቢኖሩ በዚህ ቅዝቃዜ ማሸለብ (Hibernate) ማድረግ ግዴታቸው





ነው። ሌላ አውሬም ሊኖር አይችልም። ምናልባት አጋንንትም ቢሆኑ በዚህ በሀባይ ጸበል ስንቱ እየተፈወሰ ጭራሽ ዋናው ጋን ላይ ሊኖሩ አይችሉም። ይልቁንስ ያሳሰበኝ ወይም ያስፈራኝ እጅግ የተቀደሰ ምሥጢራዊ ስፍራ ስለሚሆን 'እኔ ለዚያ የተገባሁ ባለመሆኔ መቅሰፍት ቢመጣብኝስ የሚለው ነው?' ግን ባሕታዊም አባም አሉ፤ ቢያንስ ስለነሱ ሲባል መቅሰፍት አይመጣም ብዬ ተፅናናሁ።

እናም ጉጉቴ ጨመረና፦

"ታድያ ለምን አሁን አንሞክርም?" አልኩ።

"አይ ቀን አይሆንም! እንዳልኩት በሌሊቱ ሦስተኛ ክፍል ላይ ብቻ ነው። አሁን እንሂድና አረፍ ብላችሁ ሌሊት እንመለሳለን" አሉ።

በቀን እየተንቀጠቀጥኩ የወረድኩት ገደል በሌሊት እንዴት ነው የምወርደው ብዬ ፈራሁና፦

"በሌሊት መውረጃው አይከብድም?" አልኩ።

"እንዲያውም ሌሊት አስፈሪነቱ ይቀንሳል" አሉ።

"ለምን?" አልኩ።

"በጨለማ ገደሉ ስለማይታይህ፤ መንገዷን ብቻ በመብራት እያየህ ስለሆነ ይቀላል" አሉ።

አመንኳቸውና ጭንቀቴ ቀለል አለኝ።

ከዋሻው ወጥተን ያችኑ ሠርጥ ደግሜ ነፍስና ሥጋዬ እየተላቀቀ ወጥተን ወደ መኪናችን አመራን። ጓዛችንን ይዘን ሹፌሩን ከተማ ሆቴል ፈልጎ እንዲያርፍ ነግረን እንደገና ተመልሰን ከዋሻው አናት አካባቢ የአርሶ አደር ግቢ ከሚመስል ቤት ገብተን እቃችንን አስቀመጥን። ቤቱ ግን ኋላ ላይ እንደተረዳሁት የባሕታውያኑ ዕቃ ማስቀመጫ፣ የእንግዳ ማረፊያ መሆኑን ነው። አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በዋሻው ውስጥና ከግሺ ዐባይ ከተማ በደቡብ ምዕራብ ከሚገኝ ተራራ መሆኑን ተረድቻለሁ። ባሕታዊ ከቤቱ አስገብተውን ሄደዋል።

‹ሕንግዲህ እዚሁ አረፍ ብለን የሌሊቱን ሦስተኛ ክፍል እንጠብቃለን ማለት ነው› አልኩ። ምንም ይሁን ምን ወደ ዋሻው ለመውረድ ጉጉቴ መጠን አልነበረውም።

ሰዓቱን ለመግፋት ጋደም ካልኩበት መደብ ቀና ብዬ ወደ አባ መዐዛ እየተመለከትኩ፦

"ነቢልን ስለውኃ ጠይቂው አስተውየው የማላውቀውን እስገራሚ የተቃርኖ ጠባዮቹን ነገረኝ አልኩት።

"አይ አበሳጭተ'ኸዋል ማለት ነው?" አለኝ።

"አዎን! እንዴት አወክ?" አልኩት።

"ስለውኃ ሲነሳ በጣም ስለሚቆጭ ተናግሮ ሲጨርስ ስሜቱ ይጎዳል። ነቢልን ሳውቀው የሚበሳጨው ስለ ውኃና ስለ ኢትዮጵያ ወንዞች ሲነሣ ነው" አለኝ።

"ይገርማል!" አልኩና በተለይ ስለ ውኃ ትውስታና መንፈሳዊ ቁርኝት






የነገረኝ አሁን ድረስ እየተደነኩ ነው።" አልኩና ለመሆኑ "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሲቃውንትስ ምን ይላሉ?" አልኩት።

ዝም ብሎ ሲያስብ ቆየና፦

"ጥንታዊት ኢትዮጵያ ሲቃውንት ዘንድ ውኃ፣ ዕፅና ዕብን ትልቅ ትኩረት አግኝተው ጥልቅ ምርምር ይደረገባቸው ነበር። ውኃ የመጀመሪያው መጀመሪያ ነው። ‹የእግዚአብሔር መንፈስ በውኃው ላይ ሰፎ ነበር› ይላል ኦሪት ዘፍጥረት። እግዚአብሔርን ለማነጋገር የበቃው፣ የእስራኤል የነጻነት መሪ ሆኖ ከግፍ ባርነት ነፃ ያወጣቻውና የኤርትራን ባሕር የከፈለው ሙሴ የተገኘው በግብጽ ከተማ ረግቶ ከተንጣለለው የዐባይ ውኃ ተጥሎ እንደነበር በጥልቅ ያስተውሉታል። የሰውን ልጅ የመከራ ቀንበር የገፈፈው ክርስቶስ ራሱን የገለጠው በማዕከለ ዮርዳኖስ ወንዝ መሆኑን ልብ ይሉታል። ክርስቶስ በትምህርቱ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ አይድንም ያለው የቤተ ክርስቲያኗ ማዕከላዊ ትምህርት ነው። ክርስቶስ በመለኮት እሳት ባሕርይው ዮርዳኖስ መሀል ቆሞ በውኃ ተጠመቀ እያሉ ሊቃውንቱ መለኮታዊ እሳትነቱን እያሰቡ ሕዝቡን በውኃ ይረጩታል። በትላልቅ አዛውንትና መኳንንት ዘንድም የውኃን ክብር ከጨዋታ ጋር አዋዝተው ያቀርቡታል። ‹ቀዳማዊ ምኒሊክ ከንጉሥ ስሎሞንና ከንግሥት ማክዳ ለመወለድ የበቃው በውኃ ጥም ምክንያት አይደለም ወይ?› ይላሉ" አለና ትኩር ብሎ ወደኔ ተመለከተ። እያደመጥኩት እንደሆነ ለማረጋገጥ ይመስላል።

"ቀደምት ኢትዮጵያውያን ውኃ የሰብል ማሣደጊያ፣ የጥም መቁረጫ፣ የንጽሕና መጠበቂያ ከመሆን በላይ ትልቅ ምሥጢር እንዳለው ጠንቅቀው ያውቁ ነበር። ውኃ ኃይል ሆኖ መብራትና ጉልበት እንደሚሆን በተግባር ባይገልጡትም ምሥጢሩን እንደተረዱት

አፍነውት ቀርተዋል። የውኃን መንፈሳዊ ምሥጢር ግን በጠጉ ተጠቅመውበታል። ውኃ ፈውስ እንደሆነ ውኃ መርገምንም በረከትንም ተቀብሎ እንደሚያስተላልፍ ያውቁ ነበር። በብዙዎቹ የኢትዮጵያ አድባራትና ገዳማት የሚገኙ የጸበል ቦታዎች የሚነበብላቸውን የጸሎት መጽሐፍት ስመ እግዚአብሔርና ስመ ቅዱሳን በጉ የመድኀን ቃላት ተቀብሎ በሕሙማን ላይ ፈውስና ድኅነት ማሣደሩ የውኃን መንፈሳዊ ምሥጢርነት ያሳያል። ኢትዮጵያውያን ሲቃውንት ርኩስ መንፈስን፤ የአካል ደዌን በተቀደሰ ውኃ ሲፈውሱ ኖረዋል። መስኖ ጠልፈው ዝናብ ጠብቀው በውኃ እያመረቱ ኢትዮጵያውያን አርሶ አደሮች ቀዳሚ የሰብል አምራች ሊሆኑ ችለዋል" አለ።

ትንሽ ቆይቶ ከመቀመጫው ተነሣና ቤቱ ውስጥ በቀስታ እየተራመደ፡-

"ወንድሜ ነቢል እንዳለው ውኃ ተቃርኖ የሚመስሉ ጠባያት እንዳሉት ሁሉ ኢትዮጵያም ብዙ ተቃርኖዎችን ታቅፋ የምትኖር ሀገር ናት። ውኃ ሕይወት ሆኖ ያሳደገውን ሰብል በረዶ ሆኖ መቅሰፍት ሆኖ ያጠፋዋል። እርሷም እንደ ውኃ በተቃርኖ የተሞላች ናት፤ ደግ ስትሆን ክፉት፣ ጥንታዊ ስትሆን ጀማሪ፣ ሥልጣኔ ፋና ወጊ ስትሆን ኋላቀር፣ ባለጸጋ ስትሆን ደሀ፣ ውብ ስትሆን ጉስቁላ፣ ለብዙዎች መሆን ስትችል ለልጆቿ ያልሆነች፣ ሰፊ ሆና የጠበበችን ውኃ ናት ኢትዮጵያ!!! ኢትዮጵያ ውኃ ላይ ተኝታ ድርቅ የሚያሰቃያት፤ የውኃ ማማ ሆና ኃይል የሚያጥራት ናት። ተበተነች ስትባል አንድ የምትሆን፣ ደከመች ስትባል የምትበረታ፣ ብቻዋን ቀረች ስትባል ከብዙዎች መካከል የምትገኝ ናት ኢትዮጵያ። ውኃስ ፈሳሽ ሲሆን የሚጠጥር፣ ጠጣር ሲሆን ተን የሚሆን እንደምንድን ነው?" አለ።





ነቢል ቀደም ሲል ያስረዳኝን የውኃ የተቃርኖ ጠባያት አባ መዐዛ ቅዱሳን ከኢትዮጵያ የተቃርኖ ግብር ጋር አሰናስሎ ሲያቀርበው ስሰማ "ምሥጢራዊው ውኃ- ምሥጢራዊቷ ኢትዮጵያ!!!" አልኩኝ በለሆሳስ።

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)



Scanned with CamScanner

በመካከላችን ለረጅም ጊዜ ዝምታ ሰፍኖ ቆዩ። ልንገረው ወይስ አልንገረው እያልኩ ከራሴ ጋር ስታገል ቆሁና፦

"ኀቢል እኮ ስለ ‹ዕብነ ኩሕሉ› ምሥጢርም ነግሮኛል" አልኩት።

"ምን ነገረህ?" አለ ብዙም ባለመደነቅ።

"ለሕመም ፈውስ ከመፈለጉም በላይ ለትልቅ ምሥጢራዊ ዓለማ እንደሚፈለግ ነገረኝ" አልኩት።

"ምን ዓይነት ምሥጢር?" አለ አሁንም በላመገረም። ምሥጢር ያለ ሲመስለኝ መቃተት፣ የደረስኩት ሲመስለኝ የበለጠ ማነፍነፍ እንደምፈልግ ያውቃል።

"‹ዕብነ ኩሕሉ› ከተገኘ Philosophical Mercury (የፊላስፎች ሜርኩሪ)ን ማግኘት እንደሚቻል በመጨረሻም Philosophical Stone (ዕብነ-ፊላስፎች) የተባለው እንደሚገኝና ያ ከተሳካ ደግሞ የጥበብ ቁንጮ ተገኘ ማለት ነው" አልኩት። ምሥጢሩን ደርሸበታለሁ እንደማለት ኮራ ብዬ።

ዝም ብሎ አዳምጦኝ ሲበቃ ቆየና በተመሰጥኦ ሆኖ ትኩር ብሎ ይመለከተኝ ጀመር። እየተበሳጨብኝ ይሁን እያዘነብኝ ስላልገባኝ ውስጤ ተረበሸ።

"ባይሆን…" አለ በምንኩስና ቆቡ ሥር እጁን ሰዶ ራሱን እያሻሸ "ባይሆን ከቃረምክ አይቀር ነገሩን ከውጭ የተኮረጀ አታስመስለው። ከጅረቱ ሳይሆን ከምንጩ ከሆነ Philosophical Mercury ሳይሆን ‹ባዜቃ›፣ Philosophical Stone ሳይሆን ‹እልመቂልጦስ› ብለህ ያዘው። " አለና ተጨማሪ ውይይት አለመፈለጉን ለማሳየት መጽሐፍ አውጥቶ ማንበብ ጀመረ።







# ምዕራፍ - ፳፪

ዶብን አድርጎ ከወሰደኝ እንቅልፍ የቀሰቀሰኝ አባ መዐዛ ነበር። እየተደናበርኩ ተነሣሁ። ጫማዬን ብቻ እንጂ ልብሴን አላወለኩም ነበርና ቀልጠፍ ብዬ ፊቴን እያሻሸሁ ተነሳሁና ጫማዬን አደረኩ። የምንዘውን ይዘን ከቤት ተከታትለን እንደወጣን፦

"ከገደሉ አፋፍ እስከንደርስ ድረስ መብራት አናበራም፣ ድምጽም አናሰማም። በቅርብ እኔን ተከተሉ" አሉ ባሕታዊ።

በዚሁ ተስማምተን መጀመሪያ እርሳቸው ቀጥሎ አባ ከዚያም እኔ ተከተልኩ፡፡ እውር ድንብሬን ትንሽ እንደሄድኩ እንቅፋት አነገደኝ፡፡ ነፍሴ በጣቴ ሾልካ የሄደች መሰለኝ፡፡ ‹ኡ..ኡ..› ብዬ መጮኸ ፈለኩ፡፡ እንደምንም አፍኜ ‹እ..ሁ..ሁ› አልኩ፡፡

እነርሱ ግን ኢንፍራሬድ የተገጠመላቸው ይመስል ቀጥ ብለው ሲሄዱ እኔ እየተደናበርኩ እንዳይደረስ የለም ከገደሉ አፋፍ ደረስን፡፡

"አሁን ባትሪ ማብራት ትችላላችሁ" አሉ ባሕታዊ፡፡

ከራሴ ላይ ያሰርኩትን ባትሪ አበራሁ እነርሱም እንዲሁ፡፡ እውነትም ገደሉ እንደቀኑ አላስፈራኝም፡፡

ጫማችንን አውልቀን ወደ ዋሻው ውስጥ ባሕታዊን ተከትለን ተጎንብሰን ተራመድን፡፡ በስተግራ በኩል አንድ ሃምሳ ሜትር እንደተጓዝን ሸለቆ የመሰለ ነገር አገኘን፡፡ እርሱን ዘለን አለፍንና ቀጥ ብሉ የሚሄደውን ትተን ወደ ቀኝ ትንሽ መስኮት የሚመስል ግን የተደፈነ ስፍራ ስንደርስ ባሕታዊ፡-

"እዚሁ ጠብቁኝ የምንገባው በዚህ በኩል ነው፡፡ ግን ለመክፈት እኔ እንደገና ወጥቼ ቀን ባሳየኋችሁ በኩል መሄድ ይኖርብኛል" አሉና መልስ ሳይጠብቁ እንደ እንሽላሊት ሽር ብለው ሄዱ፡፡

እኔና አባ መዐዛ በየራሳችን ዓለም ነጎድን፡፡ መብራቱን ሳጠፋው የጨለማው ክብደት የሚዳሰስ ግድግዳ ይመስላል፡፡ በተረፈ ጸጥ ረጭ ያለ ነው፡፡






ትንሽ ቆይቶ ‹ጉ…ጉ› የሚል ድምጽ ሰማንና ባትሪያችን ስናበራ ባሕታዊ ካሳዩን ስፍራ ላይ በግምት አንድ ሜትር በአንድ ሜትር ስፋትና ቁመት ያለው መስኮት ተከፍቶ ታየን፡፡

"በፈቃድህ ለቅዱሳን በሰወርከው በዚህ ስፍራ እንድንገኝ የፈቀድክ አምላክ-ዘርዐ ቡሩክ ስምህ የተመሰገነ ይሁን" አሉና ወደ መሬት ሰገዱ አባ መዐዛ፡፡

እኔም ተከትዬ ይህንኑ አደረኩና ‹ብምን ጥበብ ይሆን ከዚያ ሁነው መክፈት የቻሉ?› እያልኩ ሳንሰላስል፡፡

አባ መዐዛ "የጅኦሜትሪ ጥበብ ነው" አሉኝ ጥያቄዬን እንዴት እንደተረዳ ባላውቅም፡፡

ወዲያው ባሕታዊ መጡና "መግባት እንችላለን" ብለው እያማተቡ ቀድመው ገቡ፡፡ ተከተልን፡፡

የጨለማው ክፍል ወደ ታች የሚያስወርዱ ደረጃዎች አሉት፡፡ ባትሪያችንን እንዳበራን ደረጃውን መውረድ ጀመርን፡፡ ቀዝቃዛ እርጥበት በተሞላው ዋሻ ቁልቁል በወረድን ቁጥር እጅግ የሚከብድ ግርማ አለው፡፡ ለጊዜው ያላወኩት ግን ደስ የሚል ሽታ አለው፡፡

"የአየሩ ሽታ ደስ ይላል" አልኩ ቀስ ብዬ፡፡

"መዐዛው ከመሐሊብ ዘዕጎልት ነው" አሉ ባሕታዊ ወደኔ ዘወር ብለው፡፡ ‹እንደ ጊደር ወተት ነው› ማለታቸው ነው፡፡ ወዲያው ቅድም




Scanned with CamScanner

ያላወኩትን ሽታ እኔም ተረዳሁት። በቃ ወዲያው ታልቦ የመጣ ትኩስ ወተት፣ ትኩስ ወተት ነው የሚሸት።

ደረጃውን ወርደን ስንጨርስ ረግረግ ይገኛል። ከረግረጉ መካከል አካላቸው በከፊል ረግረጉ ውስጥ የሠመጠ የተወሰነው ከፍላቸው ደግሞ ከረግረጉ በላይ በግልፅ የሚታዩ ሦስት ጥቋቁር ድንጋዮች አሉ። ከሦስቱ ድንጋዮች ባሻገር ሽቅብ የሚፈላ ውኃ ይታያል። ወደላይ ይወጣና በተቃራኒው በኩል እንደገና ወደ ዋሻው ውስጥ ተወርውሮ ይገባል። እጅግ ብዙ ውኃ ነው!

ባሕታዊ በተዘጋ በሚመስለው ድምጻቸው ወደ እኛ ዘወር ብለው፡-

"አባቶቻችን እንዳስረዱን ይህ ግዮን በቀጥታ ከዔደን ገነት ተነሥቶ ጉዞውን ጨርሶ የመሬት ገጽ ላይ የሚወጣበት ስፍራ ነው። አንዳንድ አባቶች ከዚህ ከመውጣቱ በፊት ምድርን ሰባት ጊዜ ይዞራል ይላሉ።ከገነት ተነሥቶ እንዴት ወደ ምድር ይመጣል የሚለው መለኮታዊ ጉዞ ስለሆነ ማንም አያውቅም። ያም ሆነ ይህ ለዘመናት በምሥጢር ሲጠበቅ የኖረው ይህ ዋሻ ግዮን ከሰማይ ዝቅ ከምድር ከፍ ብላ በስተምሥራቅ ከምትገኘው ከዔደን ገነት ተነሥቶ መለኮታዊ ጉዞውን ጨርሶ እንደገና ‹ዐባይ› ተብሎ ኢትዮጵያን ለመከበብ ጉዞ የሚጀምርበት ስፍራ ነው" አሉ።

"ታዲያ በላይ በኩል ያሉት የዐባይ መነሻ የሚባሉት ሁለት ምንጮች ምንድን ናቸው?" አልኩ።

"አየህ! በቀጥታ ከገነት እንደመጣ ወደ ወንዝነት ከመቀየሩ በፊት በዚህ ስፍራ መብረድ ነበረበት። እዚህ ውስጥ የምታየው ውኃ ፍፁምነት አለው። ፍጹም ኃይል፣ ፍጹም ፈውስ፣ ፍጹም በረከት





ከላይ ከምንጮቹ የሚወጣው መለኮታዊ ኃይሉን ለምድራዊ ፍጥረታት እንደግንዛቤያቸውና አቅማቸው እንደሚመች ሆኖ ለጊዜው ተስተካክሎ ነው። እናም በጣም ጥቂቱ በምንጮቹ በኩል የሚወጣ ሲሆን አብዛኛው ግን ዘመኑ እስኪደርስ አሁን ከምናየው ጀርባ በትልቅና ጥልቅ ዓለም እግዚአብሔር ባወቀ ለጊዜው በዚያ ይኖራል" አሉ።

"ለጊዜው ማለት እንዴት ነው?" አልኩ እየተገረምኩ።

"የግዮን ውኃ ከነሙሉ ኃይሉ ወደ ምንጮቹ የሚለቀቅበት የተስፋ ዘመን ስላለ" አሉ።

"መቼ ነው ይሄ ዘመን?" አልኩ።

"‹የግዮን ወንዝ ኢትዮጵያን ሁሉ ይከባል› የተባለው ቃል-ኪዳን ሲፈፀም" አሉ።

"እንዴት?" አልኩኝ።

"ግዮን ከዚህ ወጥቶ ዐባይ ተብሎ፣ የኢትዮጵያን መሬት ሠንጥቆ፣ አፈር ማዕድናቱን ተሸክሞ፣ ቃል-ኪዳናችንን ይዞ ነው ወደ ሱዳንና ግብጽ የሚሄድ። እንደ ታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ ቢሆን ኖሮ ግን ከዚህ ወጥቶ ኢትዮጵያን ሁሉ መከበብ ነበረበት" አሉ ባሕታዊ።

"ያማ እንዴት ይሆናል የመሬት አቀማመጡ አይመች?" አልኩ።

"አየህ ትልቁ ችግራችን ያ ነው!" አሉና

"እስራኤላውያን ማርና ወተት የምታፈስ ሀገር ትወርሳላችሁ ተብለው ከነዓን ሲደርሱ የጠበቃቸው ግን ደረቅ ምድር ነበር። ነገር ግን አሉ ‹እግዚአብሔር አይዋሽም!› ‹ማርና ወተት ምድሪቱ ካላፈሰሰች የእኛ

ስንፍና እንጅ የእርሱ እብለት አይደለም› ብለው አመኑ:: እናም ከናጌብ በረሃ እስከ ጃፋ፣ ከሰማሪያ እስከ ይሁዳ ምድር በደረቅ መሬት ላይ ማርና ወተት ፈለቀ::" አሉና ትክዝ ብለው

"‹ኢትዮጵያን ሁሉ ይከብባል› የተባለው ግዮን ግን መከበብ ሳይሆን አቋርጦ አፈርና ጥሪት አሟጦ የሚሄድ ሆነ:: እግዚአብሔር ዋሸ? ታላቁ መጽሐፍ አበለ? የለም የለም እኛ በተስፋው ቃል አለማመናችን ነው! ‹ከገነት ወጥቶ ኢትዮጵያን ሁሉ ይከባል› የተባለውን ዘንግተን እንቀላፍተን ውኃውን ቁልቁል እንዲሄድ መፍቀዳችን የመንፈሳዊ ዕሴት ዝለት የወለደው የሥጋ ስንፍና ያመጣው ነው:: የቃል ኪዳናችን ምሥጢር አለመረዳታችንና አለማመናችን ነው!" አሉ ባሕታዊ በድቅድቁ የጨለማ ምሥጢራዊ ዋሻ ደረጃ ላይ እንደቆሙ:: ድምጻቸው በጉልህ ባይሰማም መንፈሳቸው ግን ልብ ድረስ ዘልቆ እንዲገባ ያደርጋል::

"ኢትዮጵያ ሕመሟንም መድኃኒቷንም፣ ድህነቷንም ብልፅግናዋንም፣ ጉስቁልናዋንም ውበቷንም በጉያዋ የያዘች ምሥጢር ሀገር ነች:: እንዴት ነው መድኃኒት ይዘህ መታመም፣ እንደምን ያለ ነው ብልፅግና ቁልፉ እያለህ ድሀ መሆን፣ ኃይል ታቅፎ ደካማ መሆን፣ እንደምን ያለ ይሆን ውብ የሚያደርገን ብርሃን ይዘን በጨለማ መኖር፣ ፀጋ ይዘህ መጉሳቆል፣ እንደምን ያለ ይሆን በደምና በሥጋ ተሳስረህ ቃል ኪዳን መጠበቅ ሲገባ እርስ በርስ መባላት?" አሉና

"እና የዐባይ ውኃ በዕማሪያዊ ፍቹ ከወሰድነው ኢትዮጵያን አይከብም:: በፍካሬያዊ ፍች ግን የዐባይ ውኃ ኃይል፣ ፈውስና በረከት ነው:: ልብ በል የዐባይ ግድብ ሲያልቅ ኃይል ያመነጫል:: ይህ ኃይል ኢትዮጵያን ሁሉ ይከባል:: ከራስ ካሣ እስከ ሞያሌ፣ ከካራማራ እስከ አሶሳ ድረስ ኢትዮጵያን በብርሃን ይከባል:: በዚያ ፋብሪካዎች ያሽካኩበታል፣







ቡሮች ይወነጨፉበታል፣ መንደሮችና ከተሞች ይደምቁበታል:: እናም በተራራማ ሀገራቸው በየሸንተረሩ እየተንደረደሩ የሚፈሱትን ወንዞቻቸውን የጨለማ ብርሃን፣ የድካም ጉልበት፣ የርኩስ መንፈስ መቀደሻ፣ የሕሙማን መፈወሻ፣ የጥም መቁረጫ፣ ከኃጢያት መንጽያ ፀጋቸው ያሆን ዘንድ ፈጣሪ በታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈ ቃልኪዳን ሰጥቶናል:: ኢትዮጵያውያን ለዚህ ቃል ኪዳን ፍካሬያዊው ፍች ይተጉ ዘንድ ይገባቸዋል::" አሉ::

የመጽሐፍ ቅዱሱ ‹ግዮን ኢትዮጵያን ሁሉ ይከባል› የተባለውና ከዐባይ ጋር ያለው እጅና ጓንትነት ለመጀመሪያ ጊዜ በመጠኑ ግልጽ ሆነልኝ:: የባሕታዊ ነገሩን በዚህ ደረጃ መረዳታቸው ለምን በዚህ ጨለማ ዋሻ የተሰፋ ቃል ኪዳን ለመጠበቅ ሲሉ ከወንድሞቻቸውና ከአባቶቻቸው ጋር እንደመነኑ አሳማኝ ሆኖ ታየኝ:: ከዚህ በላይ የሚጠበቅና የሚናፈቅ ቃል ኪዳን ይኖራል?!

አባ መዐዛ ቅዱሳን ቀበል አድርጎ፦

"ኢትዮጵያውያን ስለቃል ኪዳናቸው ሲቃትቱ አልኖሩም ማለት አይቻልም:: በ1950ቹ በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ጥያቄ በዐባይ ሸለቆ ጥናት ያደረገው የአሜሪካው የቅየሳ ድርጅት ከዐባይ ወንዝ አቅራቢያ በመቶ ኪሎሜትር የሚለካ ርዝመት ያለው ፈርስ ጋልቦ የማይዘለው የተቆፈረ ቦይ በአየር ፎቶግራፍ ማንሳታቸውን በአድናቆት መዝግበዋል:: ዘመኑ ያልታወቀለት አንድ ትውልድ ዐባይን ከዋናው ጉዞ አስቀይሶ ለመውሰድ መሞከሩን ይህ ትውልድ ልብ ሊል ይገባል:: በ14ኛው ክ/ዘመን የነገሡት አጤ ዳዊት ዐባይን ለመገደብ ሲነሡ ግብጻዊያን በብዙ አማላጅና ተማጽኖ ጉዳዩ እንዲቀር አድርገዋል:: ግብጾች ግን አሁን አሁን በገጸ-በረከት መማፀኑን ትተው በጦር ኃይል ያስፈራሩን፣ በተንኮልና በመሰሪነት ያንገላቱን ይዘዋል:: ‹ሞት በእንቅልፍ ይሰልላል›

እንደተባለ ሰልለውን ሰላላ ናቸው ብለው በእንቅልፋችን ናቁን::" አለና

"ልብ በል! ምዕራባውያን፣ ግብጾች፣ ሱዳኖችና ዓለም ሁሉ በግድቡ መገንባት የሚንጫጫው ውኃው ይቀራል ብለው አይደለም:: ለኃይል ማመንጫ የተሠራ ግድብ ውኃ ዘግቶ እንደማይዝ ያውቁታል:: የግድቡ ትርፍ ያለው ኃይል ከማመንጨቱ ላይ እንደሆነ ኃይል ለማመንጨት ደግሞ ውኃው መፍሰሱ ግድ እንደሆነ አጥተውት አይምሰልህ::" አለ::

"ታዲያ ምንድን ነው?" አልኩ::

"ግዮን ኢትዮጵያን ሁሉ ይከባል የሚለው ፍካሬያዊ ትርጉም ቀድሞ ስለገባቸው ነው:: ይህች ተራራማ ሀገር በኃይል ከተከበበች ካላት የነፃነት ታሪክ ጋር ተዳምሮ ‹ይህች ባቂላ ካደረች አትቆረጠምም› የሚለው ብሂል ስለሚታያቸው ነው:: የዐባይ ግድብ የተጋረደብንን የብልፅግና ዐይን ጥላ የሚገፍልን እሳያችን ላይ የሰፈረውን የድንቁርና መንፈስ የሚያስለቅቅልን ጸበል መሆኑን ስለሚያውቁ ነው:: የእምዬ ኢትዮጵያ ማሕፀን ያፈለቀው ቃል ኪዳናችን፣ ጽድቃችንና የትንሣኤያችን ምልክት እንደሆነ ስለገባቸው ነው:: የዐባይ ግድብ ግዙፍ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨቱ፣ ሰው ሠራሽ ሐይቁ ዓሳ ማርቢያ መሆኑ፣ ውበቱና ድምቀቱ ከተማ የሚያስመሠርት መሆኑ ብቻ አይደለም:: ይልቁንም በራስ የመተማመን በራስ አቋም የመቆም ተምሳሌት ነው:: ባሕታዊ እንዳሉት የታላቁ መጽሐፍ ቃል ኪዳን ፍጻሜ ለመድረሱ ምልክት ነው:: ዐባይ ኃይል ነው ውስጣዊ ኃይል፣ ዐባይ መንፈስ ነው መለኮታዊ መንፈስ፣ ዐባይ ዜማ ነው የሚያሸልል የሚያስፎክር፣ ዐባይ ቅኔ ነው አዕምሮን የሚያጎለምስ፣ ዐባይ የግዮን በኩር የገነት ጸጋ ነው!"





"ለዚህ ነው ዓለሙ ሁሉ በአንድ ተሰልፎ ሀገራችንን ብቻዋን እንደ ክርስቶስ በየመድረኩ አቁመው ለመስቀል የሚጣደፉት:: በዲፕሎማሲና እርዳታ ሽፋን ተርቦ እንደሚያገሳ የዱር አንበሣ ዙሪያችንን እየዞሩ የሚያሥፈራሩን:: ዓለም ከነጭ እስከ ጥቁር፣ ከሀብታም እስከ ደሃ፣ ከሩቅም ከቅርብም አብሮ ቢነሣብን ይሆን ዘንድ ግድ ነው:: ለእኛ ከእኛ ውጭ ማንም ያለመኖሩ ትምህርት ነበር:: ከዐረብ እስከ ፈረንጅ ቢጮህብንም እንደ አፋር ግመል ቀጥ ብለን ፈጣሪ ወደ ገባልን ቃልኪዳናችን መንገዘ ይገባናል:: በተስፋ ምድራቸው ጉዞና ልማት እስራኤላውያን ብቻቸውን እንደቆሙ ሁሉ እስራኤል ዘነፍስ የምንባል እኛ ከነርሱ ልንማር ይገባናል::" አለ ንግግሩ እየጋለ

"እስኪ ተመልከት የዐባይን ግድብ! የዐባይ ወንዝ ዱሮም ነበር፣ የጉባ መልክዓ ምድር ጥንትም ነበር:: አሁን የፈጠርነው የቃል ኪዳናችን ግድብ ድሮ ልንፈጥረው የሚገባ በህልም ዓለም ኢትዮጵያ የነበረ የገዘፈ ጸጋዋ ነው:: አዲስ ነገር የለም:: አዲሱ ነገር በከፊል ከእንቅልፋችን መንቃታችን ነው:: ግን ልብ በል! ብዙ ያልተሠሩ ግድቦች፣ ያልወጡ ማዕድኖች፣ ያላለማነው መሬት፣ ያልገነባናቸው ውብ ከተሞች፣ ያልተጠቀምንባቸው ጭንቅላቶች አሉ::"

"ውብ ሃውልቶች፣ ግሩም ሕንፃዎች፣ አስደናቂ ድልድዮች አልተገነቡም:: ቱባው ባህላችን መች ተመነዘረ፣ ሙዚቃችን መች ተቀነቀነ፣ ከውብ መልክዓ ምድራችን የተቀዳ ሥነ-ቃል፣ ተውኔት ፊልምና ድራማችን የት አለ? እንስሳት አዕዋፋቱን መች ደመቅንባቸው፣ የገረዓልታ ተራሮችን መች ተጠበብንባቸው፣ የሰሜን ጃናሞራ መልክዓ ምድርን መቼ ናኘንበት፣ ስምጥ ሸለቆን፣ ኦሞን፣ የዋግ ሽንተረሮችን መቼ ትንግርታዊ የጉዞ መስመር አደረግናቸው" አለ::

በንግግሩ ባሕታዊ ሐሤት ሲደርጉ እኔ ግን ፈገግ እየው ነበር። በመካከላችን ለሴኮንዶች ጸጥታ ሰፈነ።

“እና...” አሉ ባሕታዊ ድንገት ሰፍኖ የነበረውን ጸጥታ ሰብረው።

“እና ቅድም ያልኩህን ልድገምልህና ግድቡ ሲያልቅ፣ ሥነ ልቦናችን ከፍ ሲል፣ መንፈሳዊ ዕሳቤያችን ሲመለስ፣ ውኃው የእኛ መሆኑ ሲታወቅ ኃይሉ እንዲበርድ የተደረገው ግዮን እስከ ሙሉ መለኮታዊ ክብሩ ወደ ዐባይ ምንጮች ይለቀቃል።” አሉ ባሕታዊ።

ይህን ሲሉ የሆነ በራስ መተማመን ተሰማኝና፡ “ምነው የማልሞት በሆነ!” አልኩኝ በለሆሳስ።

“እምነት ተስፋ የምናደርገውን ነገር የሚያስረግጥ ነው። እንደገና የመነሣታችንና እርግጠኝነት በእምነታችን ውስጥ አለ” ብሎ ሲቀጥል ሲል አባ መዐዛ ቀበል አደረኩና፡-

“እኔ ይሄ የኢትዮጵያ ትንሣኤ፣ ህዳሴ የሚባል ነገር አይገባኝም አልኩት። በጥብቅ ምሥጢር ታትሞ በሚኖር አጅግ ግርማው በሚከብድ ዋሻ ውስጥ ሳይሆን የትምህርት ቤት ክፍል ውስጥ እንደገባ ሞልቃቃ ተማሪ አከባቢዬን ረስቼ።

ፈገግ አለና፡-

“በዘመነ አክሱም ድንጋይ አቅልጠን ቅርዕ አስይዘን ወደላይ ብዙ ፎቆች ያሉት ሕንፃ መሥራት እንደምንችል ከብዙ ሺ ዓመታት በፊት ለዓለም ያበረከትን ነበርን። ከብዙ ዓመታት በኋላ ላሊበላን ስናነፅ ዐለቱንና ቋጥኙን ፈልፍለንና ጠርበን ዲዛይኑን በእዕምሯችን ጨርሰን





ከታች ወደላይ ሳይሆን ከላይ ወደታችም፣ ጨርሶ የመጀመርንም ስልትና ጥበብን አበርክተናል። ዲንጋይ በዲንጋይ ላይ በታላቅ ብልሃት ደርደረን አጥር ቅጥር ገንብተን በሐረር ጀጎል ከተማን ከጠላት መከለል ችለናል። ከአምስት መቶ ዓመታት በኋላ ኖራ አቡክተን፣ በእንቁላል አብላልተን፣ ድንጋዮችን ሰብስበን፣ ቅርዕ አስይዘን ቤተ-መንግስት፣ ድልድይ፣ ውኃ ማቆረያ የመሥራትን ጥበብ አበርክተን ነበር። ከዚያ በኋላ ጭቃ አቡክተን ሣር አጭደን ጐጆ ቤት ወደ መቀለስ ወደማይመጥነን ሕይወት ተፈጠፈጥን እንጂ። የእህል ዘር አላማጅ የብዙ አገርዕት አብቃይ ሀገር ባዶ አቁማዳ ይዘን ለልመና ወደ አደባባይ ወጣን። በዚሁ ሁሉ የዘመናት ጉዞ ወደላይ ሳይሆን ወደታች፣ ወደ መበልፀግ ሳይሆን ወደ መኮሰስ ተጓዝን። ልብ በል! የአክሱምን ሃውልት ድንጋይ ጠርበን የሠራነው አይደለም። እውነታው ድንጋይ አቅልጠን የሠራነው ጥበብ ነው። እናም ከኋላ የመጣው የላሊበላ ኪነ ህንጻ በራሱ እጹብ ድንቅ ቢሆንም የአክሱምን ሃውልት የሠራንበትን ጥበብ አልበለጠም። ከዚያ ኋላ የመጣው የፋሲል ቤተ-መንግሥት ጥበብ ከላሊበላ አልተወዳደረም። ከዚያ ወዲህም በኮረጅነው ጥበብም ቢሆን እንደ ቀድሞው አልሆነም። ይህ ሁሉ የሚያመለክተው ከፊት ወደ ኋላ፣ ከላይ ወደታች መጓዛችንን ነው። ግን ይህን ጉዞ በጥልቀት ካየነው ትንሣኤ ወይም ህዳሴ (Renaissance) እንዳለን ያመለክታል። በዓለም ያሉ ሁሉም ሀገሮች ትንሣኤ ወይም ህዳሴ አይኖራቸውም። የዕድገት፣ የመሻሻል፣ የመበልፀግ መንገድ ይኖራቸዋል እንጂ። ትንሣኤ እንዲኖርህ ግን ከከፍታ የወረድክበት መልስህ የምትጓዝበት ጥንታዊ የታሪክ መስመር (Trajectory) ሊኖርህ ግድ ነው። እናም ኢትዮጵያ ትንሣኤ አላት ሲባል ዝም ብሎ አፈታሪክ እንዳይመስልህ። ድንጋይ አቅልጠን ወደ ላይ ወደ ተንጠራራንበት ዘመን፣ ሥራን ጨርሰን ወደ

ጀመርንበት ዘመን ብቻ ሳይሆን ዓለም ሲፈጠር ቃል ወደ ተገባለን ወደ ግዮን ቃል ኪዳን ‹ግዮን ኢትዮጵያን ይከባል› ወደተባለው ነው ጉዟችን" ሲል

ነሸጥ አደረገኝና "እዎን! እብነ ኩሕልን አግኝተን የፈላስፎች ባዜቃን ፈልገን፣ ወደ ዋናው የፈላስፎች ዕብን ‹እልመቂልጦስ› ፈጠራ የምንገባ ማግኘም ኦገስ ነው አይደል?" አልኩት። ነቢል የነገረኝንና ከእርሱም በከፊል የሰማሁትን ምሥጢር የገባኝና የተረዳሁት መሆኑን ለመንገር።

አባ መዐዛ ቅዱሳንና ባሕታዊ ኤስድሮስ በድንጋጤ ሲተያዩ አየኋቸው። ያለጊዜው እና በቅንጭቡ የተገለጠ ምሥጢር ነው ብለው ይሆናል። እኔ ግን ግድ የለኝም። ዋናው ምሥጢር ማወቄን መግለፁ ላይ ነው። ፖለቲካዊም ይሁን ወታደራዊ፣ ሳይንሳዊም ይሁን ሃይማኖታዊ ምሥጢር ያለጊዜው ብናገረው ምን ጉዳት ያመጣል የሚል ዕሳቤ በእኔ ዘንድ የለም። በእኔ ዘንድ ያለው ምሥጢር የማውቅ፣ ከፊት መስመር ከጠባቡ ክበብ ውስጥ ያለሁ መሆኑን ማሳወቅ ብቻ ነው። እንደዚያ ነን እኔና እኛ! ‹አይጥ ያየችው ብቅል ...› ትል ነበር አክስቴ።

አባ መዐዛ ቅዱሳን ከነበረበት ጥልቅ ስሜትና ድንጋጤ ወጥቶ ወደ ባሕታዊ ዞር አለና፡-

"ሥራችንን እንጀምር" አለ። እንደምን አድርጉ ሰከን ያልኩ ሰው ማድረግ እንደሚቻል ጠፍቶበትም ይሆናል።

"ለማንኛውም አሁን ወደ ተግባራችን እንመለስ" ብሎ ባሕታዊን አሳሰባቸው።

"እዎን ብዙ ጊዜ ወሰድን" አሉና





"ዋናው ተግባራችን ‹ማዬ ገቦ› መቅዳት ነው። የምንቀዳው ሽቅብ ከሚፈላው በኩሬ ግዮን ላይ ነው" አሉ በእጃቸው ሽቅብ የሚፈላውን ውኃ እያመለከቱ።

"ታዲያ ምን እንጠብቃለን?" አልኩ።

"ረግረጉ ጥልቅና አደገኛ ነው መረማመድ የሚቻለው በድንጋዮቹ ላይ ብቻ ነው" አሉ።

"ታዲያ ምን ችግር አለው፤ ድንጋዮቹ ላይ ለማረፍ ስፋታቸው ያስችላል ለመዝለልም እሩቅ አይደሉም" አልኩ።

ባሕታዊ እና አባ መዐዛ ቅዱሳን ተያይተው ፈገግ ሲሉ አየኋቸውና፡-

"ምነው ቀላል አይደለም?" አልኳቸው።

"አንተ እንደምታስበው ቀላል አይደለም" አለ አባ መዐዛ።

"ለምን?" አልኩ።

"አየህ ከሦስቱ ድንጋዮች መርገጥ የምንችለው ሁለቱን ብቻ ነው" አሉ ባህታዊ።

አትኩሬ ስመለከት ሁለቱን ብቻ በመርገጥም ቢሆን ወደ ውኃ መጠጋት እንደሚቻል አመንኩና

"ሁለቱን ብቻ በመርገጥም ቢሆን አይከብድም" አልኩ።

ሁለቱ እንደገና ተያዩና ፈገግታ ሲለዋወጡ አየኋቸው፡፡ ‹ምን ቀኘር ቃገ ነው› ሳይሉ አይቀሩም ባሕታዊ፡፡

"ከብደቱ ስላልታዩኝ እኮ ነው?" አልኩ ግራ በመጋባት፡፡

"ከሦስቱ መርገጥ የሚቻለው ሁለቱ የትኞቹ እንደሆኑ ስለማይታወቅ ነው" አሉ ባሕታዊ፡፡

"አልገባኝም?" አልኩ ግራ ግብት ብሎኝ፡፡

"ከነዚህ ሦስት ድንጋዮች አንደኛው ልዩ ኃይል ያለው ስለሆነ መርገጥ ከባድ አደጋ ያስከትላል፡፡ ችግር የማያስከትሉትን ሁለቱን ለማወቅ ሦስተኛውን መለየት ግድ ስለሆነ ነው፡፡ በዚያ ላይ ውኃውን ቀጥታ መቅዳትም አይቻልም" ሲሉ

"ምን አይነት አደጋ?" አልኩ፡፡

አባ መዐዛ በጉያው የያዘውን ማስታዎሻ አውጥቶ እያየ "ወንድም ሲሳይ ከባድ አደጋ!" አለ፡፡

"ወይ ጣጣ! ታዲያ እንዴት ነው የምንለየው" አልኩ፡፡

"በተመስጦ ነው" አሉ ባሕታዊ

"እንዴት?" አልኩ፡፡

"ሦስታችንም በታላቅ ጥሞና ድንጋዮችን እንመለከታለን፡፡ በዐይነ ህሊና ወይም በዐይነ ሥጋ ሲሆን ይችላል" ሲሉ

"ከዚያስ?" አልኩ ነገሩን ባለማመን፡፡







"ከዚያማ ከተፈቀደልን የተለየችው ድንጋይ ላይ ምልክት እናያለን" አሉ፡፡

"የማይሆን ነገር ነው" አልኩ በልቤ፡፡

"በሉ እንደ መመሰጥ አቅማችን ወደ ሕሊናችን ውስጥ እንግባ ወይም በፍፁም አትኩሮት ወደ ድንጋዮች እንመልከት" አሉና ባሕታዊ በርከክ አሉ፡፡

ነገሩን ፈፅሞ ልቤ አለመቀበሉ ይታወቀኛል፡፡ ሁለቱ ግን ደረጃው ላይ ፊታቸውን ወደ ውኃና ድንጋዮቹ አቅጣጫ አዙረው ተንበርክከዋል፡፡ ሳያቸው ዐይናቸውን ጨፍነዋል፡፡





Scanned with CamScanner



# ምዕራፍ - ፳፫

በጨለማው ምሥጢራዊ ዋሻ ሁለቱ በጸጥታ ተንበርክከው እኔ እንደቆምኩ ደቂቃዎች አለፉ:: የአካባቢው ዝምታ ሕሊናዬ ውስጥ ጭራሽ ይንጫጫ ጀመር:: ‹ምንድን ነው መመሰጥ? ምንድን ነው ወደ ውስጥ መመልከት?› እላለሁ::

ጩኸት ከውጭ ብቻ አይደለም:: ጩኸት ከውስጣችንም አለ:: አንዳንዴ ምንም እንኳን አካባቢያችን ፀጥ ቢልም ውስጣችን በጩኸት የተሞላ ከሆነ ሰላምና ጸጥታ አይሰማንም:: እንዲያውም ዝም ባልን ቁጥር፣ አካባቢው ጭር ባለ





ቁጥር የውስጣችን ጩኸት ጎልቶ ይሰማናል:: የውስጥ ጩኸታችንን ላለማዳመጥ የውጭ ጩኸት እንሻለን:: እናም የሚጮህ ሙዚቃ፣ ጫጫታና ሁካታ የበዛበት ስፍራ መገኘት እንፈልጋለን:: እኔ ዘመኔን በጩኸትና ሁካታ ነው የኖርኩት:: ‹ጭር ሲል አልወድም› የሚለው ትውልድ አባል ነኝ:: ሁሉ ነገር እንዲጮህ እንሻለን:: ሚዲያው፣ ቴሌቪዥኑ፣ ሬዲዮኑ፣ ታምቡሩ ሌላው ቀርቶ ስብከቱ ሁሉ ጩኸት ሆኗል:: በአካባቢያችን የሚጮህ ብናጣ እንኳን የሚጮህ ታኮ ያለው ጫማ እናደርጋለን:: ‹ቋ…ቋ…ኳ….ኳ መጥቻለሁ፣ ደርሻለሁ፣ ሄጃለሁ፣ ወጥቻለሁ› ይላል ጫማችን እኛን ተክቶ እየጮኸ!

እኔ ሁሌ ውስጤ ይጮሃል:: ያልረካ ፍላጎት፣ የማያልቅ ምኞት፣ የመጥፎ ሥራ ፀፀት፣ ተበደልኩ ባይ ቁርሾ ተደማምረው እሳተ ገሞራ፣ የውቅያኖስ ማዕበል ነው ውስጤ:: ይህን የውስጤን ማዕበል ጸጥ የሚያደረግ ሰላም የለኝም:: ወይም የገሊላን ባሕር ሞገድ ጸጥ እንዲል የገሰጸው የክርስቶስን መንፈስ በውስጤ አልታደልኩም:: አሻግሮ ማየት እንጅ ወደ ውስጥ ማዬትን አለመድኩም::

ይህን ሳንሰላስል ጭራሽ ሕሊናዬ ይጮህ ጀመረ:: አካባቢው ጸጥ ብሎ እነ ባሕታዊ ወደ መመሰጥ ሲገቡ የእኔ አእምሮ ግን ውስጡ ይንጫጫ ጀመር:: ሁለቱን ሳያቸው አካላቸው እንጅ መንፈሳቸው ዋሻው ውስጥ እንደሌለ ተሰማኝ::

በያዝኩት ዘንግ ሁሉንም ድንጋዮች ነካ ነካ ሳደርግ መሠረት ያላቸው መሆኑን ተረዳሁ:: እዚህ ዋሻ ውስጥ በቅዝቃዜና በጨለማ ጊዜዬን ከማጠፋ ዕድሌን ልሞክር አልኩና የእጅ ጓንቴን አውጥቼ አደረኩና አንደኛው ድንጋይ ላይ እመር ብዬ በግራ እግሬ ቆምኩ:: ሰላም ነው:: ‹ከቀሩት ሁለት ድንጋዮች ባንዱ ላይ ብቆም ከውኃው እደርሳለሁ›

እልኩና እንዲሁ እመር ብዬ በቀኝ እግሬ አንዱ ላይ አረፍኩ፡፡ አሁንም ሰላም ነው፡፡

በአንድ እግሬ እንደቆምኩ ሚዛኔን ጠብቄ የያዝኩትን የመዳብ ኮዳ ጠጋ አደረኩና ወደ ላይ ከሚነሣው ውኃ ጥግ ቀድቼ ሞላሁ፡፡ ወዲያው ውኃ የሞላው ኮዳ ሲግል ታወቀኝ፡፡ መፋጀቱ ከአቅም በላይ ሆኖ ከመወርወሬ በፊት ቅድም የረገጥኩትን ድንጋይ በፍጥነት ረግጬ ደረጃው ላይ ስደርስ የለበስኩትን ጓንት አልፎ እጄ በእሳት የተቃጠለ መሰለኝ፡፡

‹ ዋ..ይ.. › አልኩና ኮዳውን በፍጥነት ደረጃው ላይ አስቀመጥኩ፡፡

እነርሱ በታላቅ ተመስጦ ውስጥ ስለነበሩ ያደረኩትን አላዩም፡፡

ድንገት ‹ዋይ› ብዬ ስጮህ በድንጋጤ ከሄዱበት ዓለም ተመለሱና፡-

“ምነው ምን ሆንክ?" አሉኝ ባንድ ድመፅ፡፡

“እጄን ፈጅቶኝ ነው" አልኩ እጄን በትንፋሼ እያበረድኩ፡፡

“ምኑ ነው የፈጀህ?" አሉኝ፡፡

“አላያችሁኝም እንዴ ቀዳሁ እኮ" አልኳቸው እንፋሎቱ የሚትጐለጐለውን የሞላ ኮዳ እያሳየሁ በጅብደኝነት፡፡

“የተለየችው ድንጋይ ታየችህ እንዴ?" አሉ ግራ እየተጋቡ፡፡

“እረ አልታየችኝም" አልኩ

“ታዲያ እንዴት ረገጥክ?" አሉ እየተሸበሩ

“ሳዬው ብዙ የሚከብድ አልመሰለኝም፡፡ እዚህ ጊዜ ከምናጠፋ ብዬ





ሁለቱን በግምት ረገጥኩና ቀዳሁ" አልኳቸውና "አሁን መሄድ እንችላለን" አልኩ ዘና ብዬ፡፡

ሁለቱም በመደሻ የተመቱ ያክል ራሳቸውን በድንጋጤ ይዘው ቁጭ አሉ፡፡ ድንጋጤያቸው አስደነገጠኝና

“ዋናው የምንፈልገውን ነገር ማግኘታችን አይደል?" አልኩ፡፡

“ወንድም ሲሳይ በመንፈሳዊ ዓለም ተልዕኮ አንድን ነገር ማግኘት ብቻ ሳይሆን እንዴት እንዳገኘኸው ትልቅ ፋይዳ አለው፤ ለምን በራስህ ላይ መዓት ታመጣለህ?" አለኝ አባ መዐዛ በታላቅ ተግሳጽ፡፡

“ምን መዓት አመጣሁ? እንድናመጣ የተጠየቅነውን መስዋዕትም ቢሆን ከፍዬ አመጣሁ አይደል" አልኩ፡፡

“ወንድሜ! ከመስዋዕት መታዘዝ ይበልጥ ነበር" አሉና "አሁን በፍጥነት ከዚህ እንውጣ ምን ሊፈጠር እንደሚችል አናውቅም አሉና አጣደፉን ባሕታዊ፡፡

“የቀዳሁት ውኃ እኮ ያቃጥላል ትንሽ ይብረድ እንጂ" አልኩ፡፡ አሁንም ጭንቀታቸውና ስጋታቸው አልተጋባብኝም ነበርና፡፡

“ሥርዓት ተጥሷል! ‹ዕፀ በለስ› ማለት ነው፤ ልንወስደው አንችልም" አሉ ባሕታዊ ፈርጠም ብለው፡፡

አባ መዐዛ ቅዱሳን የሚይዘውን የሚጨብጠውን አጥቶ ይቅበዘበዛል፡፡ በጣም እንደተበሳጨብኝ ይታወቅበታል፡፡

እኔም በበኩሌ መበሳጨት ጀምሬያለሁ፡፡

"ምንድን ነው ሕግ፣ ሥርዓት ዋናው ውጤቱ አይደል እንዴ?" አልኩና ‹ልንወስደው አንችልም› ያሉትን ቸላ ብዬ ኮዳውን ብድግ ሳደርገው ከወገቡ በታች ብስክስክ ብሎ ተቦተረፈና ውኃው ከመቅዐበት ፈሰሰ።

የመዳቡ ኮዳ በዚህ ፍጥነት በዚህ ደረጃ መበሳሳቱን ሳይ የቀዳሁት ተራ ውኃ አለመሆኑ ገባኝና ድንጋጤ ለመጀመሪያ ጊዜ ከላይ እስከ ታች ወረረኝ።

"ምን ጉድ ነው?" አልኩ ሳላስበው።

"ጉዱን ቆይተህ ታየዋለህ፤ አሁን ቶሎ እንውጣ" አለኝ አባ መዐዛ።

እየተርበተበትኩ ሽቅብ ደረጃውን ወጥተን መግቢያውን አልፈን ወደ ዋናው ዋሻ እንደገባን ባሕታዊ በከፈቱበት በኩል በፍጥነት ሄደው ሲነካኩ የገባንበት ጠባብ በር የሆነ ዐለት ተንከባሎ መጥቶ ዘጋው።

ዋናውን ዋሻ ለቀን ስንወጣ ገና ድቅድቅ ጨለማ ነበር። በእኔ ችኩልነትና ሥርዓት አልበኝነት የተነሳ ‹ማዩ ገቦውን› ሳንቀዳ ምሥጢራዊው የግዮን በር ተዘጋ። በአሪት ዘፍጥረት፡-

> ‹እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ከዔደን ገነት አስወጣው፤ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን ከዔደን ገነት ምሥራቅ አስቀመጠ›

የሚለው ቃል ደጋግሞ ራሴን ይወቅረኝ ጀመር። ጥልቅ የሕሊና ሀፀት ይሁን የማላውቀው መጥፎ ስሜት ብቻ ድካም ተሰማኝና ማረፍ ፈለኩ። እየደገፉኝ ማረፊያችን አደረሱኝ። በቃ መተኛት ፈለኩ ያደረኩትን ሁሉ ሳስብ ራሴን ጠላሁት።





ዘልጅነት እስከ ጉልምስና የኔ ዕድገትና የኔ የአንድ ትውልድ ዘመን ልክ አልነበረም። በትምህርት ቤት አድርጉ የተባልነውን አለማድረግ፣ አታድርጉ የተባልነውን ማድረግ እንደ ጀብድ የደስታ ምንጭ አድርገን አየቆጠርን አሳለፍን። በሥራ ዘመን የመሥሪያ ቤትንና የተቋምን መመሪያ መጣስ፣ ሕግ ማፍረስ በራስ የመተማመን ምልክት አድርገን የምንቆጥር ሆንን። በሥራ ዘመኔ የታዘብኩት ነገር ቢኖር የመሥሪያ ቤትን ሕግና መመሪያ የምንጠብቀው ሌሎችን ለመጉዳት ወይም ተገቢውን አገልግሎት ላለመስጠት ስንል ነው። ‹መመሪያ አይፈቅድም› እንባለን ለማጉላላት፤ እኛ ግን ሺ ጊዜ እንጥሰዋለን። ሕግና ሕገ መንግሥት ትዝ የሚለን ሌሎችን ለማሠር ስንፈልግ ብቻ ነው። በማኅበራዊ መገልገያ ስፍራዎች በሆስፒታል፣ ባንክ፣ ትራንስፖርት ፎርማታ ወዘተ ወረፋና ሥርዓት መጠበቅ አይሆንልንም። ሁልጊዜ ትርምስ ሁልጊዜ ግፊያ ነው። ቤተ እምነቶች ሄድን በረከት ድህነት ለመቀበል ትዕግስት የለንም። ለጸበል፣ ለእምነት፣ ለመሳለም አንዱ ባንዱ ላይ መተራመስ ነው።

ሌላው ቀርቶ ለራሳችን ደኅንነት ሲባል የወጣውን የትራፊክ ሕግ እንጥሳለን። የትራፊክ ፖሊስ ዘወር ሲል የታጠቅነውን የደኅንነት ቀበቶ አውልቀን እንጥላለን። በዚህ ሁኔታ ነው ያደኩት። የሞራል ሕግ፣ የሃይማኖት ሕግ፣ የሀገር ሕግ አይገዛኝም። መረን የመልቀቅ ፍላጎቴ መደዴ አደረገኝ። ስለነፃነት ያለኝ መረዳት አጉራ ዘለል ከመሆን የተለየ አይደለም። ሁሌ አመፅ ላይ ነኝ። ለጤናዬ እንደሚጎዳ ባውቅም ዘፈቀደ ባውቅም መጠን የለኝም። ነፍሴን እንደሚያጎድፋት ባውቅም ዘፈቀደ ኗሪ ሆኛለሁ። እኔ ብቻ አይደለሁም የምጋራው ትውልድም እንዲሁ ነው። የምናከብረው ሰው፣ የምንከተለው ሥርዓት ያለን አይመስልም። የመሪና ተመሪ፣ የአለቃና ምንዝር፣ የአስተማሪና ተማሪ ግንኙነት መከባበር የሌለው መረን ሆኗል። በሆነ ዝግጅት ላይ ማን ከማን

ይቀድማል ምን ከምን በፊት ይደረጋል፣ በአነጋገር በአቀማመጥ ሁሉ ነገር ጠፍቶብን ዝብርቅርቅ ብሎብናል፡፡ መንግሥታዊ፣ ፖሊሳዊ፣ ወታደራዊ ማዕረግ፣ ሥነ-ሥርዓት፣ ኘሮቶኮል አጥተን ሁሉ ነገር ሻሞ ነው፡፡ የቀረን ጥቂት ሥነ-ሥርዓት በሃይማኖት አካባቢ ቢሆንም እርሱንም ወግ አጥባቢ፣ ኋላ ቀር እያልን ማኅበረሰባዊ መደዴነት እየነገሰብን ነው፡፡ ሁሉን እንሽራለን በሁሉ እናምፃለን ራዕይ ስለሌለን መረን ሆነናል፡፡

መጽሐፍ ‹ራዕይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆናል› እንዲል የምንጋራው ትልቅ ራዕይ ስለሌለን፣ የምንጋረው የጋራ ግብ ስላጣን መረን ሆነናል፣ አመፀኞች ነን፡፡ በሁሉ ነገር እናምፃለን፡፡ እርግጥ ግፍ ሲበዛ በግፈኞች ላይ ማመፅ ተገቢ ነው፡፡ ግን ያም ቢሆን ከማመፅ በፊት የግፉን አይነት በተገቢው መረዳትና መግለፅ፣ በመግለፅ ሂደት ውስጥ መወያየትና መመካከር ይቀድማል፡፡ ተንደርድሮ ማመፅ ሰላም እያመጣም፣ ሀገር አይገነባም፡፡ ስለማመጽ ብቻ ስለምናምጽ በትልቁ አመጻችን ውስጥ ሌሎች ትናንሽ አመጾች የፈጠሩና መደማመጥ ይጠፋል፡፡ ስለሆነም አመጻችን የሰው ሕይወት ከመገበር ያለፈ ብዙ ፋይዳ አላመጣልንም፡፡ ፖለቲካችን ራሱ በዓመፅ ተወልዶ፣ በዓመፅ አድጎ፣ በዓመፅ ይሞታል፡፡ በልዩ ሐሳብ ተጠንስሶ በሐሳብ ብልጫ ሲያድግ አላየንም፡፡ እናም አመጻዊ ግብሬ የማይሽፈን ሆነና የተነገረኝን በጎ ነገር መከተል አቅቶኝ ቅኖቹንም ጨምሬ አሰናከልኩ፣ በመንፈስ ጀምሬ በሥጋ ጨረስኩ፡፡

እነ አባ መዐዛ ቅዱሳን እኔን ማረፊያችን ትተው ነግሀ ኪዳን እናድርስ በሚል ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደዋል፡፡ ትንሽ እንቅልፍ ጨንፈር አደረገኝ፡፡ ብዙ አልቆየሁም የግራ እግሬ ትንሽ እጣቱ ላይ እሳት ያቃጠለኝ ያክል ተሠማኝ፡፡ ወዲያው ወደ ሌሎች እጣቶቼ ማቃጠሉ ሲሰራጭ ታወቀኝ፡፡ ተነሥቼ ቁጭ አልኩና ጣቶቼን በእጄ ጭብጥ





አያረኩት፡፡ የማቃጠሉ ሕመም እየጨመረ ወደ ቁርጭምጭምቴ ወደ
ባቴ ብሎ ወደጭኔ ተዳረሰ፡፡

የእሳት ረመጥ የተደፋብኝ ያክል ነበር ሕመሙ፡፡ ትንሽ ቆይቶ ማበጥ
ጀመረ፡፡ እነ አባ መዐዛ ሲመለሱ በከፍተኛ ስቃይ እየራገፍሁ ደረሱ፡፡

"እባክህ አባ ቶሎ ብለህ ወደ ሆስፒታል ይዘኸኝ ብረር" አልኩ በስቃይ
ውስጥ ሆኜ፡፡

እነርሱም የእኔ ስቃይ የተጋባባቸው ይመስል ከጐኔ ኩርምት ብለው
በጭንቀት ይተያዩ ጀመር፡፡

"አባ ምን ትጠብቃለህ?" አልኩት አሁንም እግሬን ከላይ ታች እየዳበስኩ፡፡

"ወንድም ሲሳይ ይሄ ስቃይ እኮ በተዋህሲያን ወይም በሆነ ተራ ቁሳዊ አደጋ የመጣብህ አይደለም" ሲል

"ምን ማለት ነው?" አልኩት እየተንሰፈሰፍኩ፡፡

"ወንድም ሲሳይ! ይህ እኮ ባለመታዘዝህ፣ ምሥጢራዊውን ሕግ በመተላለፍህ የመጣብህ ቅጣት ነው" ሲል ባሕታዊ ተቀብለው፡-

"እውነት ነው ይህን ሕመምክን ሐኪም አያድነውም እርሱ ራሱ የዚህ በሽታ ተጠቂ ስለሚሆን" ሲሉ ቀበል አድርጌ

"ታዲያ እንዴት ነው የምሆነው፡፡ እኔ እኮ የሚተራሲዮን ስቃይ አስጨንቆኝ ጊዜ መውሰዱ አሳስቦኝ ነው" አልኩኝ፡፡

"ሊሆን ይችላል፡፡ ግን ፈውስ በዓመፃ፣ መዳንም በሕግ ጥሰት አይሆንም፤ የጽድቅና ፈውስ መንገድ ከትንትናና ከመታዘዝ ትሠራለች" አሉ ባሕታዊ፡፡

"እሺ አጠፋሁ፡፡ ትዕቢት ሳይሆን ችኩልነት ጐዳኝ፤ ዕቡይ ነኝ ብዬ አላስብም ግን ትዕግስት የለኝም፡፡ ያም ሆኖ ይቅርታ አይደረግልኝምን?"

"ይቅርታማ ታገኛለህ እንጅ! ይቅር የማይባል ጥፋት የለም፡፡ የጥፋትህን መጠን ታውቀው ዘንድ ስህተቶችህን እያስታወስክ ሕመምክን ለጥቂት ጊዜ መቻል ቀኖናህ ነው፡፡" ሲሉ

አባ መዐዛ ቀበል አድርጎ "ሰዎች ተነግሯቸው ካላመኑ በተግባር ሲማሩ ግድ ነው፡፡‹The Law of Effect› የሚባለውን ጽንሰ ሐሳብ የምታውቀው ነው፡፡ ሕፃናት እሳት እንደሚያቃጥል ሺ ግዜ ብትነግራቸው ለመንካት ከመጣር አይመለሱም፡፡ ቀላሉ መንገድ በጥቂቱ እንዲፈጃቸው በማድረግ በውጤቱ ማስተማር ብቻ ነው" አለ፡፡

"ለማንኛውም የምትፈወሰው ‹ደብረ አንሕዬ› ስንሄድ ነው፡፡" አሉ ባሕታዊ፡፡

"የት ነው? መቼ ነው የምንሄደው?" አልኩ ጥድፍ ብዬ፡፡ እግሬ በዚህ ሰዓት ዝሆኔ በሽታ የያዘው ሰው ይመስል ከላይ እስከታች ቅትት ብሎ አብጧል፡፡

"ዛሬ ማታ እንደገና ወደ በኩረ ግዮን ዋሻ እንመለሳለን፡፡ ፈጣሪ ረድቶን የሕግ መጠበቂያዋ ድንጋይ ከተከሠተችልን ‹ማዬ ገቦውን› ቀድተን በጠዋት እንሄዳለን" አሉ፡፡







ቀትን ሙሉ በስቃይ ውዬ እንደገና አድሬ ከዚያ ጉዞ ሆኖ ‹ደብረ አንሕዮ› ደርሼ እስክፈወስ በስቃዩ የምሞት መሠለኝ፡፡ ከሥቃዩ ጋር እየታገልኩ ጊዜው የሚያጥርበትን ሳንሰላስል አንድ ነገር ትዝ አለኝ፡፡

"የሚያግዝ ከሆነ አንድ ሐሳብ መጣልኝ" አልኳቸው፡፡

"ምንን?" አሉ ባንድ ላይ እንደተማከሩ ሁሉ፡፡

"እኔ የረገጥኩት ከሦስቱ ሁለቱን ብቻ ነው የመጀመሪያውን በግራ፤ ሁለተኛውን ደግሞ በቀኝ እግሬ ነው የረገጥኩት፡፡ እንደምታዩት ያመመኝ ግራ እግሬን ነው፡፡ ስለዚህ ምሥጢራዊዋ ድንጋይ በግራ እግሬ የረገጥኳት ነች ማለት ነው" አልኩ እየተቅመደመድኩ፡፡

"እና?" አለ አባ መዐዛ፡፡

"እናማ ወደ ዋሻው እንደገባችሁ ምንም መጠበቅ ሳያስፈልጋችሁ ሁለቱን ድንጋዮች ረግጣችሁ ቶሎ ቀድታችሁ መመለስ ይቻላል ብዬ ነው" አልኩ፡፡

በአግራሞት ራሳቸውን እየወዘወዙ ሲተያዩ አየሁና፡-

"ምነው?" አልኩ፡፡

"አሁንም አልገባህም ማለት ነው?" አሉ በመደነቅ፡፡

"ምኑ?" አልኩ፡፡

"ስልትና ብልጠት በዚያ ቦታ አይሠራም፡፡ የሚሠራው እንደታዘዝነው መፈፀም ብቻ ነው" አሉ ባሕታዊ፡፡

ኩምሽሽ ብዬ ሥቃዬን ማዳመጡን ቀጠልኩ። እልፍ እልፍ የሚተራሊዮን ስቃይ ይመጣብኛል። ‹ይህን ሁሉ ዘመን እንዴት ቻለችው?› እላለሁ። አሁን በእርሷ ሰበብ እኔም እየተሰቃየሁ ነው። የሆነ አዝማሪ ግጥም ትዝ አለኝ፡-

'ደምሽ ተፈናጥሮ ልብሴን አበላሸው

መከራሽ አይለቀኝ ብሸሸው ብሸሸው'

ቀኑን ሙሉ ስነሣ ስወድቅ ውዬ መሸ። እንቅልፍ የሚታሠብ አልሆነም። የሌሊቱ አጋማሽ እንደተጠናቀቀ ለመሄድ ሲነሡ እየተንኳተትኩም ቢሆን መሄድ አለብኝ ብዬ ተነሣሁ። ብዙም አልተከላከሉኝም።

እስከ ዋሻው ድረስ በበትር እየተደገፍኩ ሄድኩና እየተንኳተትኩ ወደ ምሥጢራዊው የዋሻው ክፍል እነ አባን ተከትዬ አመራሁ። ባሕታዊ በትናንትናው ስልት ድብቁን ቁልፍ ሲነኩ ሸርተት ብሎ ተከፈተ። ትናንትም ዛሬም እንዴት እንደከፈቱት ማሳዬት የፈለጉ አይመስልም። ደረጃውን በእንኩትቴ ወረድኩ።

የተለመደው የጸሎትና የተመስጥኦ ጊዜ ደረሰ። አሁን እኔም ወደውስጥ ለመመልከት ሞከርኩ። ብዙ ሐሳብ እየተመላለሰ አስቸገረኝ። ራሴን ታገልኩ። መጀመሪያ ሕመሜን ብቻ ለማዳመጥ ሞከርኩ። ሐሳቤን ሙሉ ለሙሉ ሕመሜ ላይ ሳደረግ የበለጠ አካባቢው ሀጥ ያለ መሰለኝ። ውኃው ሽቅብ ፈልቶ እንደገና ተመልሶ በዋሻው ውስጥ ሲሄድ የሚሠማው ድምፅ በጉልህ ይሰማኝ ጀመር። ዐይኔን ሙሉ ለሙሉ ጨፍኜ ሕመሜን እየረሳሁ የሆነ የተለየ አስደሳች ድምፅ እየሰማሁ መሰለኝ። የሚገርመው ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በእግሬ ላይ ያለውን ስቃይ ረስቼው የውኃውን ልዩ ድምጽ ብቻ እንደ ጽጌ ማኅሌት እሰማ ጀመር።





ምንያክል ጊዜ እንደሆነ አላስታውስም ብቻ ቆይተን፡-

"የአባቶቻችን አምላክ ቸር ነው፤ ስሙ ይባረክ!" አሉ ባሕታዊ።

ድንገት ከእንቅልፍ እንደሚባንን ሰው ዐይኔን ስገልጥ ባለፈው ማታ ያልረገጥኳት ከረገጥኳቸው ሁለቱ ድንጋዮች በስተጉን የነበረችው ድንጋይ ወደ ሙሉ ብርሃን የምትሠጥ እንቁነት ተቀይራለች። ዋሻው በብርሃን ተሞልቷል። የእንቁው ብርሃን ወደላይ ከሚፈላው ውኃ ላይ ሲያርፍ የተፈጠረው የቀስተ ደመና ሕበረ ቀለማት ነጸብራቅ አካባቢውን ሌላ ውብ ዓለም አድርጎታል። የብርሃኑ ሕብረ ቀለማት ከአካባቢው ውብ መዐዛ ጋር ተዳምሮ የዔደን ገነት ሽራፊን ያየሁ መሰለኝ። ነፍሴ ለመለመች፤ መንፈሴ ሐሤት አደረገች፤ ሕመሜም የጠፋ መሰለኝ። ‹ምነው በዚህ ብቆይ?› አልኩ ብለቤ።

ባሕታዊ ኤስድሮስ አባ መዐዛን ወደ ‹ማዬ ገቦው› እንዲሄድ በእጃቸው አመለከቱትና "አባ ሰላም ለኪ መድኀኔን አይርሱ" አሉ ።

"እሺ" አለና ‹ዕብነ-ኩሕሉን› ከቆዳው ከረጢት አወጣና በዝርግ ሳህን ላይ አደረገው። የመዳብ ኮዳውን በአንገቱ አንተለጠለና እኔ እንዳደረኩት በአንድ እግሩ የመጀመሪያውን ረግጦ ሁለተኛው ላይ በሁለት እግሩ አረፈ።

ከዚያም ዕብነ-ኩሕሉ ያለበትን ዝርግ ሳህን ሽቅብ ወደሚጉነው ውኃ ጠጋ አድርጎ ሞላ። ትንሽ ቆይቶ ወደ ኮዳው በጥንቃቄ ገለበጠ። ዝርግ ሳህኑንና ዕብነ-ኩሕሉ እዛው ትቶ ወደ መጀመሪያው ድንጋይ ተመለሰና የሞላውን ኮዳ ለባሕታዊ አቀበሎ ሁለተኛውን ባዶ ኮዳ ተቀብሎ ተመልሶ ሄደ። እንደ መጀመሪያው አድርጎ አሁንም በሳህኑ ቀድቶ ወደ ኮዳው ገለበጠ። ከዚያም ድንጋይዋን ረግጦ ደረጃው ላይ አረፈ።

እኔ እንደቀዳሁት እንደባለፈው የሚፋጅ አልነበረም::

‹‹ዕብነ-ኩሕሉ› አብርዶታል ማለት ነው› አልኩ ለራሴ:: አሁን በሁለት የመዳብ ኮዳዎች ማዬ ገቦው ተቀድቶ አለቀ ማለት ነው:: ሦስተኛው ኮዳ ትናንት እኔ አስበልቸዋለሁ!

በጣም የገረመኝና የዘገነነኝ የምታበራውን ድንጋይ ትናንት አለመርገጤ ነበር:: ምናልባት ረግጫት ቢሆን ኑሮ የሕይወቴ ማብቂያ ሊሆን ይችል ነበር:: የተደረገልኝን ምሕረት አስቤ የእግሬን ሕመም እስከዚያው ድረስ በጸጋ ለመቀበል ተጋሁ::

ዕብነ ኩሕሉ በከረጢት ተከተተ:: ሁሉም በሰላም ተከናወነ:: ከዚያም ባሕታዊ ሁለቱን ኮዳዎች ይዘው እኔን አባ መዐዛ የመሸከም ያክል ደግፎኝ ወደ ላይ ደረጃውን ወጥተን ወደ ውጭ ልንወጣ ስንል የዕንቁው መብራት ድንገት ጠፋና ዋሻው በፅልመት ተዋጠ::

“ትጉሃን፣ ትሁታንና ቅኑዓን የኢትዮጵያ ልጆች መጥተው የታመቀውን ሙሉ ኃይል በኢትዮጵያ ምድር እስኪያከቡት ድረስ በዚህ ጨለማ ምሥጢር ሆኖ ይቆይ!” አሉና ባሕታዊ የምሥጢራዊውን ዋሻ በር ለመዝጋት ሄዱ:: ቆይቶ እስከ መቼ እንደሆነ ባላውቅም ጥርቅም ብሎ ሲዘጋ ተሰማኝ::

ሲነጋ ባሕታዊ ኤስድሮስን ጨምረን ጉዞ ወደ ‹ደብረ አንሕዮ› ሆነ:: ሕመሜ ከዋሻው ከወጣን ጀምሮ እንደገና አገርሽቶብኛል:: ይሁን እንጅ የሥራዬ ውጤት ስለሆነ ቻልኩት:: ለማዬት የሚያስፈራውን እግሬን ይገፎ ወደ ቤት ማምራትም አልፈለኩም:: ባሕር ዳርን አልፈን አባ መዐዛ ቅዱሳንን ካገኘሁበት ስፍራ ስንደርስ መኪናውን ሹፌሩ ይዞት





እንዲመለስ አድርገን እኛ ከመንገድ ወጣ ብላ ወደምትገኝ የደቅማ ዛፍ ጥላ ሥር አረፍ አልን::

“እስኪመሽ እዚሁ መቆየት አለብን” አሉ አባ መዐዛ:: እኔ ግን ‹የምፈወስባትን፣ ምሕረት የማገኝባትን ደብረ አንሕዮን› የማየት ጉጉቱ ንሮ ነበር::

ወደ 12 ሰዓት አካባቢ ሁለት መነኮሳት ቃሬዛ ይዘው ወደ እኛ መጡ:: ለዐይን ያዝ ሲያደርግ በቃሬዛ ተሸከመውኝ የምዕራብ አቅጣጫን ይዘን አመራን:: ከጨለማ የበለጠ ግርማ ያለበት ደን ውስጥ ስንገባ ይታወቀኛል:: ትልልቅ ዛፎች አካባቢውን የበለጠ አጨልመውታል:: በደኑ ውስጥ ከፍታ ያለው መንገድ ወጥተን ደልዳላ ስፍራ ስንደርስ አወረዱኝ:: በመቋሚያ ተደግፌ ቆም አልኩና ከሕመሜ ጋር እየታገልኩ በጨረቃዋ ወጋገን ሳስተውል ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑን በስተምሥራቅ በኩል አልፈነው መጥተናል:: ትንሽዬ የቆርቆሮ ቤት በራፍ ላይ አረፍ አልኩ::

ተሸከመውኝ የመጡት መነኮሳት ወዲያው ውኃ በገበታ አመጡና አጠቡኝ:: እንደ እሳት የሚፋጀኝ እግሬን ቀዝቀዝ አደረገው:: እግሬን ታጥቤ ሳበቃ በሶ ተበጥብጦ ተሠጠኝ:: እሱን በደንብ ጠጣሁና ማረፍ እንደምፈልግ ስነግራቸው ቤቷን ከፍተው መደብ ላይ አነጠፉልኝ:: ውስጧ ዕድት ያለች ቤት ነች::

አባ መዐዛ መጣና “አይዞህ ታግሠህ አረፍ ለማለት ሞክር፤ ነገ በጠዋት እመጣለሁ የፈውስ ቀንህ ነገ ይሆናል” አለኝ::

“እንደቃልህ ይሁንልኝ” አልኩና ጋደም አልኩ::



Scanned with CamScanner

ሌሊቱ ግማሽ ስቃይ፣ ግማሽ እንቅልፍ ሆኖ አለፈ። ወፎች ሲንጫጩ መንጋቱ ነው አልኩና ተነሥቼ ቁጭ አልኩ። የወፎቹ ድምፅ አይነትና ብዛት ሳስተውል በጣም አትራቢያ እንዳለሁ ገመትኩ፡፡ ‹የት ይሆን ያለሁት?› አልኩ። ቆይቶ በሩን ከፍቶ አባ መሀዛ ገባና ‹ተነሥ ታጠብ› ብሎ ውኃ አቀረበልኝ። ፊቴን እንደነገሩ ታጠብኩና ‹ጨርሻለሁ› አልኩት።

ደግፎኝ ወደ ውጭ አወጣኝና በቤቷና በቤተ ክርስቲያኑ መካከል ባለች ቀጭን መንገድ ደግፎኝ ይዞኝ ሄደ። ትንሽ እንደሄድን በትላልቅ ዛፎች የተከበበ መኻሉ ላይ አውድማ የመሰለ ሰፊ ስፍራ ላይ መነኮሳት ከበ ሠርተው ቆመው ጸሎት ያደርጋሉ።

በስተደቡብ በኩል ካለ አንድ የድንጋ ዛፍ ሥር ወስዶ አቆመኝ። ዐይኔን በደንብ ገልፌ ሳይ ‹መካነ ኀርመት› የአባ መሀዛ ቅዱሳን ምንኩስና ሲፈፀም ያየኋቸው አባቶች ናቸው። ሌሎች የማላውቃቸውም አሉ። በስተምሥራቅ ከትልቁ የሎል ዛፍ ሥር ኩርምትምት ብላ የተቀመጠች ጉስቋላ ሴት አየሁ። ትኩር ብዬ ሳይ ድንገት ቀና ስትል ፊቷን አየኋትና፡-

"ሚቲራሲዮን" አልኩ

ሕመሟ፣ ስቃይዋ፣ ጉስቁልናዋ ታወሰኝና አንጀቴ ስፍስፍ አለ። ብዙ ግን አልቆየም የኔ የራሴ እሳት ረመጥ የተሸከመው እግሬ ሥቃይ አገረሸብኝና "ተቃጠልኩ!" አልኩ ሳላስበው።





# ምዕራፍ - ፳፬

‹ደብረ እንሕዮ› በታላቁ ደን ውስጥ ነጫጭ የለበሱ አበው መነኮሳት ትልቅ ከብ ሠርተው ቆመዋል። ረጅም ጸሎት ከተደረገ በኋላ በሁለቱ ኮዳዎች የነበረው ‹ማየ ገቦ› ወደ ትልቅ የመዳብ ገበቴ/ጎላ ላይ ተገለበጠ። በሀር ጨርቅ ተጠቅልሎ የነበረውን ‹ዕብነ-ከሕል› ጥቅልሉ ተፈትቶ ወጣና ከላዩ ላይ ‹ዕፀ-ሲና እና ዕፀ-ኀርመት› የተባሉት ዕፆች እየተሰባበሩ ዙሪያውን ተጠመጠመበትና ‹ከማየ ገቦው› ውስጥ ተጨመረ።



Scanned with CamScanner

ትንሽ ቆይቶ ‹ማዬ ገቦው› እንደፏፏቴ አረፋ ደፍቆ ሽቅብ ተነሣና በገቡቴው ትይዩ አየር ላይ ደመና ነገር ሠርቶ አረገረገ። ከሴኮንዶች በኋላ እንደገና ተመልሶ እንደ ዝናብ ገቡቴው ላይ መልሶ ተጠራቀመ።

‹ምን ጉድ ነው!› አልኩ ለራሴ ሕመሜን ረስቼ።

ትንሽ ቆይቶ የለመለመ ‹ዕፀ-ተክህኖ› አመጡና ከገቡቴው ነክረው ሲያማስሉት ትንሽ ቆይቶ ‹ማዬ ገቦው› እንደ ማዕበል ተናውጦ ቀለሙ ወተት መሰለ።

ኩርምት ብላ ቁጭ ብላ የነበረችው ሚተራሊዮን ትልቅ አንበር መጣና የተቀመጠችበት ተጋረደ። የተመረጡ ሦስት አባቶች ገቡቴውን ከመሬት ከፍ አድርገው ይዘው ወደ አንበሩ ከማምራታቸው በፊት ትልቁ አባት ከገቡቴው ላይ በጻሕል ጨልፈው ቀዱ።

ከዚያ መጀመሪያ ወደ ሰሜን ፊታቸውን አዙረው፡-

"ከመይኩን ቡሩክ ቅዱስ" እያሉ ረጩት። ቀጥለው ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ አዙረው እንዲሁ አረጩት።

‹ምን ሊደረግ ነው?› እያልኩ ሳንሰላሰል ሳለ እኔ ወደ ቆምኩበት ደቡብ አቅጣጫ ዞረው እንዲሁ "ከመ ይኩን ቡሩክ ቅዱስ" ብለው ሲረጩ የተለወጠው ውኃ ፍንጣሪ ፊቴ ላይ አረፈ። ትልቅ መርግ የወደቀብኝ መሰለኝ። ከመቅዕበት ትራንኩላይዘር እንደተወጋ አውሬ ሰውነቴ ፍዝዝ አለና በዐይኖቼ ቀስተ ደመና ቀለማት እየታዩኝ ከተደገፍኩበት የዶንጋ ዛፍ ሥር ሸርተት ብዬ ወደ መሬት ስወድቅ ትዝ ይለኛል።





ለስንት ደቂቃ ወይም ሰዓት ወይም ቀናት አሸልቤ እንደቆየሁ አላውቅም። ምናልባት እንደ አቤሜሌክ ስድሳ ዘመናትን እንቀላፍቼም ይሆናል። ብቻ ስነቃ ውስጤን የደስታ ስሜት ሞልቶታል። የሆነ ቅልል የሚል መንፈስ ተሰማኝና ቶሎ ብዬ ወደ ታመመው ግራ እግሬ ስመለከት እንደ ቀኝ እግሬ ሆኖ ፍፁም ድኗል። የሕመም ስሜቱ ፈጽሞ ጠፍቷል።

ለምስጋና ዘልዬ ስቆም ገና የራሴን ደስታ አጣጥሜ ሳልጨርስ በስተምሥራቅ በኩል አንበሩ ተነሥቶ ሚተራሊዮን በተኣምራዊ ግርማ ከመሬት ከፍ ከሰማይ ዝቅ ባለ መንበር ተቀምጣ አየኋት። የማየውን ማመን አቅቶኝ በአድናቆት "ሚተራሊዮን!" አልኩ።

ዳግም መወለዷ እውነት ነበር። ገፅታዋ ደመና እንደተገፈፈላት ሙሉ ጨረቃ ብሩህ ሆኗል። ዐይኖቿ ከጉድጓዳቸው ወጥተው የነጠረ የብር አለሎ መስለው ይንከባለላሉ። ዞማው የሐር ፏፏቴ ጸጉሯ ላይ አንዳች ውበት ያለው አክሊል ተደርጎላታል።

‹የለበሰችው ጸዐዳ ቀሚስ የደረበችው ካባ ምን ጥበበኛ እጅ ሠራው ያስብላል። ጉንደሬ ፈትሎ ዶርዜ ሸመነውን? አደይ አበባውን ቀሚሷ ላይ ማን ጠለፈው? አኩስማይ ነው ሀማሴን? የዐይኑ ርግቡንስ ማን ሰጣት? አፋር ነው ሱማሌ? የእጅ አንባሯን፣ የእግሯን አልቦ፣ የአንገቷንስ ድሪ ማን ሠራው? የአገው አንጥረኛ ወይስ የሸናሻ? የተቀመጠችበት ድንቅ መንበር ከየት ተገኘ? ከጅማ አባጅፋር ወይስ ከጌድዮ?› እያልኩ በሐሳቤ ሳደንቅ፡-

አፈ መምህሩ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው፦

"የምትታመም ወይም የማትታመም ሆና ዳግም አልተወለደችም እንዳትታመም እንጂ፤

የምትፈርስ ወይም የማትፈረስ ሆና ዳግም አልተወለደችም እንዳትፈርስ እንጂ፤

የምትሞት ወይም የማትሞት ሆና ዳግም አልተወለደችም እንዳትሞት እንጂ፤

ንዑዳን ክቡራን በአረቦኑ ማስሪያ መመረቅን መርቋት" ሲሉ

እልፍ አእላፍ ወትእልፊት ቅዱሳን መረቋት። እጆቿን ከፍ አድርጋ አሰንጋ ጣቶቿን ዘርግታ ምርቃቱን ትቀበላለች።

"ልጆችሽ ይሚገቱልሽ እንጂ አይሞግቱሽ፣ ተጣልተው ይታረቁልሽ፣ በውስጥ በአፍአ ይተባበሩልሽ፤

አጥተሽ ባዶ አቁማዳ ይዘሽ ከማንም ፊት አያቁምሽ፤

ለጠላቶችሽ የብረት ቆሎ፣ የድንጋይ ንፍሮ ሁኚ፤

የዋኖችሽን እርም አትብዪ፤

መከራሽ ከኋላ እንጂ ከፊትሽ አይሁን፤

እንቃዕዶ ልቦና ጥበበ ሕሊና ይስጥሽ፤

የሚረግምሽ የተረገመ፤ የሚመርቅሽ የተመረቀ ይሁን፤

የወለድሽው ይውለድሽ" አሉ።







ዐበይ ምርቃቱ ሲያልቅ ንዑሳኑ መተርጉማኑ ተከተሉ፦

"ሚተራሊዮን የሁሉ እናት ሆይ፣

የወለድሽው ይወለድሽ ተብለሻልና፦

የወለድሽው ውኃ መስኖ ሆኖ ያረስርስሽ፣ ኃይል ሆኖ ራት መብራት ይሁንሽ፣ ጸበል ጸዲቅ ሆኖ ይቀድስሽ፣

የወለድሽው አፈር ዳቦ እንጀራ ሆኖ መሶብሽን ይሙላው፣ ብረት ሆኖ ያጠንክርሽ፤

የወለድሽው ዕብን ግንብ ሆኖ ያፅናሽ፣ አፅር ቅፅር ሆኖ ይጠብቅሽ፤

የወለድሽው እሳት አብስሎ ቀቅሎ ያብላሽ፣ ጠላቶችሽን አመድ ዱቄት ያድርግልሽ፤

የወለድሽው ንፋስ መዐዛ ሆኖ ያውድሽ፣ አርአያማዊ ገውዝ ሆኖ በስማያት ያንሳፍሽ፤

የወለድሽው ዘር ዕፅዋት ሆኖ በገርሽ፣ ጽጌያት ሆኖ በደጅሽ አራዊት አእዋፋትሽን የሰጠልልሽ፣ እርቃንሽን ይሸፍንልሽ፣ ፊውስ እስተንፋስ ይሁንልሽ"

ብለው ሲያበቁ፦

"አ..ሜ..ን..!" አለች ሚተራሊዮን፤።

‹አሜን› ስትል ፍጥረት ሁሉ የሚሰማው ቀላያት የሚያስተጋቡት እንደመብረቅ ብልጭታ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ የተሰማ ነበር።

‹ምነው ደግማ በተናገርች› ስል

"ነፍሴ እግዚአብሔርን ታላቅ ታደርገዋለች፡ መንፈሴም በመድኃኒቴ በእግዚአብሔር ደስ ይላታል። የባሪያይቱን መዋረድ አይቷልና። እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ይመኩብኛል። እርሱ ብርቱ የሚሆን ታላቅ ሥራን ለእኔ አድርጓልና ስሙም ቅዱስ ነው!" አለች።

ነፍሴ ከድምጿ ቃና የተነሣ ለመለመች። ሕፃናት በረቱ፣ አራዊት ፈነደቁ፣ ዐዕዋፋት ቁጠማ ቀጥፈው ወደ ሰማያት በረሩ። ኮረብቶች ዘለሉ፣ ተራሮች አረገዱ፣ ቀላያት አሸበሸቡ፣ ወንዞች ቱልቱል ተንደርድረው ሽቅብ ፈሰሱ።

‹ይሀን የማየው በዕውኔ ነው በህልሜ› እልኩ። የለም የለም ሁሉቱም ያው ነው። ሕይወትስ ህልም አይደለች፣ ንፋስን እንደመከተል፣ ውልብ ብላ ጥፍት የምትል፣ ህልም እልም አይደለችምን? ግድ የለም በህልሜ ይሁን! ህልሜ ግን ህልመ ዮሴፍ ነው። ሲነጋ የሚሆን፣ ስነቃ የሚፈፀም፣ ቀን ቆጥሮ የሚደርስ ነው! የለም የለም ይህ ህልም እልም አይደለም፣ ህልመ ዮሴፍ ህልም ትልም ነው!!!

**‹ተፈጸመ ዘንቱ ክታብ›**



ኪነት በዩቲዩብ(@gbw_dan)
የቴሌግራም ቻናል
ኪነት በዩቲዩብ(@gbw_dan)